
ፖወር አፍሪካ መረዳት ተከታታይ ጽሁፎች (ቅጽ 1)

# የኃይል ግዢ ስምምነቶችን መረዳት

የኃይል ግዢ ስምምነቶችን መረዳት



?ገንዘብ ድጋፍ ከ

POWER AFRICA

ረቂቅ ከ

ALSF African Legal Support Facility • Facilité africaine de soutien juridique

CLDP COMMERCIAL LAW DEVELOPMENT PROGRAM

እጋር ተቋማ

ewura Energy and Water Utilities Regulatory Authority

NBET NIGERIAN BULK ELECTRICITY TRADING PLC

OPIC

THE WORLD BANK

**የሀይል ግዢ ስምምነቶችን መረዳት - ቅጽ 1.3**

በክሪኤቲቭ ኮመንስ መርህ መሰረት የታተመ
አትሪብዩሽን - ነንኮመርሻል-ሼር ኤላይክ 4.0
ዓለም አቀፍ ፈቃድ (CC BY NO SA)

የፒ ዲ ኤፍ እና ኢፒዩቢ እትሞች እዚህ ይገኛሉ፡-
http://go.usa.gov/FBzH

ይህንን ህትመት በተመለከተ ላላችሁ ጥያቄዎች Mohamed Badissyን (ሲ ኤል ዲ ፒ)
በ mbadissy@doc.gov አግኙ፡፡

# የኃይል ግዢ ስምምነቶችን መረዳት

ዩ ኤስ አሜሪካ የንግድ ሚኒስቴር

/ኤምብለም/ የንግድ ሚኒስትር

ዋሽንግተን ዲ.ሲ 20230

እ.አ.አ. በጁን 2013 ፕሬዚደንት ኦባማ ፓወር አፍሪካን መርቀው ሲከፍቱ ዓላማው ከሰሐራ በታች ያለው ሁለት ሶስተኛ ህዝብ ያለ ኤሌክትሪክ ኃይል መኖሩን ተከትሎ የኤሌክትሪክ ኃይል በእጥፍ እንዲዳረስ ለማድረግ ነው፡፡ ፓወር አፍሪካ ለአፍሪካ ኃይል ዘርፍ/ክፍል/ ኢንቨስትመንትን በማደፋፈር የወሰደው እርምጃ ከግል ባለንግዶች ጋር በመሥራት፣ እንዲሁም ከተባባሪ/ መንግሥታትና ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ጋር በመሆን የኃይል ፕሮጀክቶች በሚከናወኑበት ጊዜ የሚያጋጥሙትን እንቅፋቶች ለማስወገድ ነበር፡፡ ከዚህ ጥረት ጋር ተያይዞ የፓወር አፍሪካ አጋሮች የኃይል ግዢ ስምምነትን (ፒፒኤ) በተመለከተ ያሉ የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን መቀነስ ብዙ ዓመታት የሚፈጀውን የድርድር ጊዜ ማሳጠር እንደሚቻል ደምድመዋል፡፡

ፓወር አፍሪካ የፒፒኤን ድርድር ሂደት ለማፋጠን በተሻሻለ መግባባት ለዚሁ ውስብስብ ስምምነት የተመረጡትን ልምዶች ለዚሁ ጉዳይ ተጠቅመዋል፡፡ የአሜሪካ የንግድ ሚኒስቴር በአጠቃላይ የንግድ ሕግ ልማት ፕሮግራም ጠቅላይ አማካሪ በኩል እና የአፍሪካ ልማት ባንክ በአፍሪካ የሕግ ድጋፍ ሰጪ ክፍል አማካይነት፣ ከአሜሪካ የዓለምአቀፍ ልማት ኤጀንሲ በተገኘ ገንዘብ እንቅስቃሴውን መርተዋል፡፡

በዘጠኝ ወራት ጊዜ ውስጠ ከአፍሪካና ከዓለምአቀፍ ባለድርሻ አካላት ወሳኝ የሆኑ አስተያየቶች መሰብሰብ የቻልን ሲሆን እነዚህን ቁምነገሮች ለሁሉም በሚገባ ቋንቋ መመሪያ መጽሐፍ እንዲያዘጋጁልን ዕውቅ ባለሙያዎችን በሥራው ላይ አሰማርተናል፡፡ “የኃይል ግዢ ስምምነቶችን ለመረዳት” የሚለው መመሪያ መጽሐፍ ሊተገበር እና ፋይናንንስ ሊደረግ የሚችል ፒፒኤን አስመልክቶ የጋራ መግባባት እንዲፈጠር አስችልሏል። የጽሁፉ መታተም የፕሬዚደንት ኦባማን በአፍሪካ ውስጥ የኃይል ፕሮጀክቶች የማቋቋም ዓላማ ለማከናወን የሚረዳ ዋና እርምጃ ነው፡፡

ፓወር አፍሪካና አጋሮቹ ይህ የመመሪያ መጽሐፍ የተሻሉና የተረጋገጡ ፒፒኤዎች በማስገኘትና የኤሌክትሪክ ሃይል ባጭር ዓመታት ውስጥ ሚሊዮኖች አፍሪካውያን እንዲያገኙ የጋራ ግባችን እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡ የንግድ ሚኒስቴር ለዚህ አስገራሚ በሆነ በዓለም አቀፍና በድርጅቶች መካከል በሚካሄደው ጥረት ውስጥ መሪ ሚና መያዙ እኔን በተለይ ያኮራኛል፡፡ ይኸ የተዋጣለት ትብብራችን የዩ.ኤስና የአፍሪካ አገሮች የጋራ የንግድ ጠቀሜታዎች ምን ያህል ለምጣኔ ሀብት ልማት ጠንካራ ጎን መሆኑን እና በአፍሪካ አህጉር ውስጥ ሕይወትን ለመለወጥ የሚያስችል መሆኑን ያሳየ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው፡፡

/ፊርማ/

ፔኒ ፕሪትዝከር

ዩ.ኤስ. የንግድ ሚኒስትር

# መቅድም

በዘመናዊው ዓለም የዕድልን ሞተር የሚያሽከረክረው የኤሌክትሪክ ሃይል ነው፡፡ ልጆቻችንን በብርሃን እንዲያጠኑ ያስችላል፡፡ በፋብሪካዎቻችን ውስጥ ለሚካሄዱ ዝየዳዎች ሁሉ ኃይል ይሰጣል፡፡ ኃይል ከቴሌኮሙኒኬሽን እስከ ትራንስፖርት ድረስ በአጠቃላይ በሁሉም ረገድ እየጨመረ ለሚሄድ፣ ንቃት ላለውና ለተያያዘ ዓለም አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህም የተነሳ መዋዕለ ንዋይን የኃይል መሰረተ ልማት ላይ ማፍሰስ ለማንኛውም ምጣኔ ሃብት ልማት መሪ ዕቅድ ወሳኝ ነው፡፡ ይህም አጠቃላይ የምጣኔ ሃብት እድገት እንቅስቃሴዎች በማደግ ላይ ባሉ አገሮች እና ባደጉ አገሮች ደግሞ ለተወሰኑ የገጠር ልማት እንቅስቃሴዎች ይጠቅማል፡፡

ቢሆንም፣ እነዚህ የከፍተኛ ለውጥ የማምጣት ባህርይ ያላቸው የኃይል ፕሮጀክቶች ከስጋቶች ነፃ አይደሉም። ምንም እንኳን የኃይል ምንጭ ፕሮጀክቶች የኃይል እጥረት ባለበት ገበያ በጣም ተፈላጊ ቢሆኑም፣ እነዚህ ፕሮጀክቶች ቀዳሚ በመሆናቸው በነዚህ ገበያዎች በአብዛኛው የመዋዕለ ንዋይና የገንዘብ ሁኔታው ውስብስብ ሆኖ ይገኛል፡፡ ከዚህም የተነሳ ለረዥም ጊዜ የሚቆይ የቢዝነስ ስራ የሚያስፈልጉትን ተዓማኒነትና ዘላቂነትን ለማጠናከር ቋሚ ስምምነት መኖሩ የተለመደ አሰራር ሆኗል። ይህ ውል የኃይል ግዢ ስምምነት (ፒፒኤ) ተብሎ ሲጠራ፥ በመላው ዓለም ለሚተገበሩ ገለልተኛ የኃይል ፕሮጀክቶች ልማትና መስፋፋት አስተዋፆ አድርጓል።

ይህ መምሪያ መጽሐፍ የፒፒኤዎች አጠቃላይ ሁኔታን እንዲሁም የሚያካትቱንም ግዴታዎችን፣ ስጋቶችን እና መፍትሔዎችንም ይጠቁማል። የዚህ መምሪያ መጽሐፍ የደራሲያን ስብስብ ከመንግሥታት፣ ከልማት ባንኮች፣ ከግል ባንኮችና እንዲሁም ከታወቁ የዓለም አቀፍ የሕግ ድርጅቶች የተወጣጣ ሲሆን ሁሉም አገልግሎታቸውን በነፃ አበርክተዋል። የእኛ ምኞት በፒፒኤ ድርድር ሂደት ወቅት የሁሉንም አካላት ሃሳብ በማቅረብ ለአንባቢያን ከፒፒኤዎች ጋር በተያያዘ ሊያጋጥሙ ስለሚችሉት ተግዳሮቶች ተመጣጣኝ ግንዛቤ በማስጨበጥ እንዴት በነዚህ ውስብስብ ስምምነቶች ድርድር ወቅት ተግዳሮቶቹን መፍታት እንደሚቻል ሃሳብ መስጠት ነው። ከሁሉም በላይ ለፒፒኤ መሳካት ቁልፉ ጉዳይ የሚቃረን ሂደት ነው የሚለውን ግንዛቤ በመተው የትብብር እና የቅንጅት አሰራርን መከተል መሆኑን ለአንባቢያን ማስገንዘብ እንወዳለን። እንደዚህ ባለ ሚዛናዊ በሆነ አቀራረብ ሲከወን ብቻ ነው ስጋቱ የሚቀንሰው፣ ሁሉም አካላት ተጠቃሚ የሚሆኑት።

የመመሪያው መጽሐፍ የተዘጋጀው ቡክ ስፕሪንት (http://www.booksprints.net/) በሚለው ዘዴ ነው፡፡ ይህም ዘዴ ባምስት ቀኖች ውስጥ ማርቀቅ፣ ማርታትና ማተምን አሟልቶ የሚያቀርብ ነው፡፡ ጉዟችን ሞቅ ባለ ውይይት ተጀምሮ ወዲያው ደግሞ ወደጋለ የጽሕፈት ሂደት ተለውጦ አንዳንድ ጊዜ አስደናቂ ሃሳቦችና ወሳኝ አመለካከቶችን ለማስተናገድ ይቋረጥ ነበር። በአንዳንዱ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ መስማማት ሲታይ በሌላው ላይ ደግሞ ከፍ ያለ ክርክር ይነሣ ነበር፡፡ የመጨረሻው ውጤትም የቡድን ሥራ እንጂ የጸሐፊዎች የግል አስተያየት ወይም የሚወክሉት ድርጅት ፍላጎት አልነበረም፡፡

የቡክ ስፕሪንት አዘጋጆችን ፌይዝ ቦስወርዝንና ሊያ ሮስ ጋሽን ላላሰለሰ ትዕግስታቸውና ለማያወላውል አመራራቸው ማመስገን እንፈልጋለን። የአፍሳይት ስፕሪንት ቡድንንም ሄንሪክ ቫን ሊወን (ሰዓሊ)፣ ሬዊን ሁዋይት (አራሚ) እና ኋን ካርሎስ ጉቴሬዝ ባርኬሮ እና ጁሊየን ታኬት (የቴክኒክ ረዳቶች) ልናመሰግን እንወዳለን፡፡ በተለይም ለዚህ ፕሮግራም ስትርቅቴጂክ ዕቅድ

ሀሳብ ላቀረቡትና በሥራ ላይ ለማዋል ላስቻሉን ረኔ ፖስት (ቡክ እስፐሪንትስ)፣ ቶዪን አጆ (የአፍሪካ የሕግ አገልግሎት ሰጭ) እና ሙሐመድ ሎራዊ (የንግድ ሕግ ልማት ፕሮግራም) ምስጋና ማቅረብ እንወዳለን። እንዲሁም የዩ.ኤስ ኤጀንሲ የዓለም አቀፍ ልማትና የአፍሪቃ ሕግ ድጋፍ አገልግሎት ላደረጉልን የገንዘብ ድጋፍ ዕውቅና መስጠት እንፈልጋለን።

ይህ የመምሪያ መጽሐፍ የተዘጋጀው የቡክ ስፐሪንትን የማስተጋባት ባሕሪ በመግለጽ ለማጣቀሻ እንዲያገለግል ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱ ለመማሪያነት መንደርደሪያ እንዲሆንም ነው፡፡ የመምሪያው መጽሐፍ የወጣው በክሪየቲቭ ኮመንስ አትሪቢውሽን-ነንኮመርሺይ ነው፡፡ የሚተገበረው ጉዳይ በክሪየቲቭ ኮመንስ ላይሰንስ ስም እስከወጣ ድረስ ከደራሲዎች ፈቃድ ሳያስፈልግ ኮፒ፥ መጥቀስ፥ ማሻሻል፥ መተርጎም፥ ለማንኛውም ንግድ ነክ ላልሆነ ተግባር መጠቀም ይቻላል ማለት ነው። የመመሪያው መጽሐፍ በኤሌክትሮኒክና በሕትመት መልክ (በእንግሊዝኛና በፈረንሳይኛ) ይገኛል፡፡ እንደ ኦንላይን ኢንተር አክቲቭ ምንጭም መጠቀም ይቻላል፡፡ አስተዋጽኦ ካደረጉት ደራሲያን ብዙዎቹ ባሉበት ድርጅት የመምሪያውን መጽሐፍ የማስተማሪያ ዝግጅት መነሻ አድርገው ለኮርሶችና ለቴክኒካል ዕርዳታ ሀሳብ ማመንጫ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

በዚህ ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ልማቶች ሽሚያ በሚደረግበት ዓለም ዘንድ በበቂ ሁኔታ ግልጋሎት ለማያገኙ ማህበረሰብ የኤሌክትሪክ ሃይል ማቅረብ የመላው ዓለም ምኞት ነው፡፡ መንግሥታት፣ የግል ኩባንያዎች፣ የግል ባንኮችና የልማት ተቋሞች የኤልክትሪሲቲ ኃይል ለማቋቋም ያለእረፍት እየሠሩ ናቸው፡፡ ይህ የመምሪያ መጽሐፍ በማንኛውም መንገድ ከፍ ወዳለ የኃይል ተደራሽነት በጋራ ግብ ለመሥራት እንድንቀራረብ ካደረገን እንደተዋጣለት ክንውን እንቆጥረዋለን፡፡

ከልባዊ ምስጋና ጋር፣

*አስተዋጽኦ ያደረጉት ደራሲያን*

**Mohamed Badissy**
የሕግ አማካሪ (ዓለምአቀፍ)
ዩ.ኤስ የንግድ ሚኒስቴር
ዩናይትድ ስቴትስ

**Mahib Cisse**
ዋና የኢንቨስትመንት ባለሙያ
የአፍሪካ ልማት ባንክ
ኮት ዲቯር

**Patrick M. Dougherty**
የበላይ አማካሪ (ሲኒየር ካውንስል)
ዓለም ባንክ
ዩናይትድ ስቴትስ

**Alex Evans**
ረዳት ጠቅላላ አማካሪ
ኦቨርሲስ የግል ኢንቨስትመንት ኩባንያ
ዩናይትድ ስቴትስ

**Nnaemeka Ewelukwa**
ዋና አማካሪና የኩባንያ ጸሐፊ
የናይጀሪያ በልክ ኤልክትሪሲቲ ትሬዲንግ ፒኤልሲ
ናይጀሪያ

**Jay Govender**
ዲሬክተር - የፕሮጀክቶችና መሠረተ ልማት
ክሊፍ ዴከር ሆፍማየር አይ.ኤን.ሲ.
ደቡብ አፍሪካ

**Ryan T. Ketchum**
አጋር
ሐንተን እና ዊሊያምስ ኤል.ኤል.ፒ.
ዩናይትድ ኪንግደም

**Allen B. Leuta**
(የቀድሞ) የሕግ ኃላፊ - አፍሪካ
ስታንዳርድ ባንክ
ደቡብ አፍሪካ

**Anastas P. Mbawala**
የኤሌክትሪሲቲ ዳይሬክተር
የኃይልና የውሀ አገልግሎቶች ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን
ታንዛኒያ

**Eluma Obibuaku**
ምክትል ፐሬዚደንት - ኃይል
የአፍሪካ ፋይናንስ ኮርፖሬሽን
ናይጀሪያ

**Michael Tam**
አጋር
በርዊን ሊይተን ፔይዝነር ኤል.ኤል.ፒ.
ሆንግ ኮንግ

**Tim Scales**
አጋር
አለን እና ኦቨርሊ ኤል.ኤል.ፒ.
ዩናይትድ ኪንግደም/ፍራንስ

**Amir Shaikh**
ዋና የሕግ አማካሪ
የአፍሪካ የህግ ድጋፍ ፋሲሊቲ
ኮት ዲቯር

**Toyin Ojo**
የበላይ የሕግ አማካሪ
የአፍሪካ የህግ ድጋፍ ፋሲሊቲ
ኮት ዲቯር

# መግቢያ

ኤሌክትሪሲቲ የምጣኔ ሃብት ልማትንና የማህበራዊ ደህንነትን ለማሳደግ መሠረት ነው፡፡ ንግድ፣ ኢንዱስትሪ፣ መኖሪያ ቤት፣ ትምህርት ቤት፣ ሆስፒታል እና ሌሎች ወሳኝ የሆኑ መሠረተ ልማቶች ሁሉም ውጤታማ ሆነው ለመሥራት ኤሌክትሪሲቲ ያሻቸዋል፡፡ ብዙ ብቅ ብቅ እያሉ በመምጣት ላይ ባሉ ገበያዎች በኤሌክትሪሲቲ ፍላጎትና አቅርቦት መካከል ከፍ ያለ ክፍተት ይታያል፡፡ ይህን ክፍተት ለመሙላት እጅግ ከፍ ያለ የኃይል ማመንጨት አቅም ያስፈልጋል፡፡ ይህም በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር መዋዕለ ንዋይ ያስወጣል፡፡ ይህን የካፒታል ክፍተት ለመሙላት ከግሉ ዘርፍ አልሚዎች ጋር እየተጋሩ መሥራቱን ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን የአገር መንግሥታት እያደር እየተገነዘቡ በመምጣት ላይ ናቸው፡፡

የኃይል ግዢ ስምምነት፣ ወይም ፒፒኤ፣ ለማንኛውም ራሱን ለቻለ የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት፣ በተለይም ብቅ ብቅ ለሚሉ ገበያዎች፣ ዋና ኮንትራት ነው፡፡ ይህ የመመሪያ መጽሐፍ የፒፒኤን ዐውድ ይገልፅና ፒፒኤን በማርቀቅና በድርድር ወቅት ሊካተቱ የሚገባቸውን ቁልፍ ጉዳዮችን ያስቀምጣል። ይህም በሥራው ልምድ ያላቸውን የብዙዎችን የጋራ ዕውቀት፣ ማለትም በዓለም ዙሪያ ስለኃይል ፕሮጀክት ልማት በተግባር ለአሥርተ-ዓመታት የታወቁትን አካላት ይወክላል፡፡

ይህ የመመሪያ መጽሐፍ የሚመለከተውና የሚያገለግለው መንግሥታትን፣ አገልግሎት ሰጪዎችን፣ አልሚዎችንና ሌሎች በጉዳዩ ተጠቃሚ ተሳታፊዎችን ሆኖ የሚከተሉትን መመሪያ ይሰጣል፡-

በገበያ ላይ የሚውለው የፒፒኤ የኃይል ገበያና የኮንትራቱ ማዕቀፍ፣

የኃይል ፕሮጀክቱን ፋይናንስ ለማድረግ መካተት ያለባቸው ጉዳዮች፣

የፒፒኤ ታሪፍ አወቃቀር፣ የግዢ ግዴታዎች፣ እና ሌሎች ቁልፍ የፋይናንስ ድንጋጌዎች፣

በፒፒኤ ሥር ለሚገኙት ሻጭና ገዢ የብድር ድጋፍና የደህንነት ጉዳይ፣

አንድ ራሱን የቻለ የኃይል ፕሮጀክት ሊያጋጥሙት የሚችሉ ስጋቶች እና በምን መልኩ ፒፒኤ ለስጋቶቹ መድቧል እና ቀንሷል፣ እና

ሌሎች ዋና ዋና የፒፒኤ ድንጋጌዎች፣ በተለይም ግዴታን መፈፀም አለመቻል እና ውል ማቋረጥ ላይ ትኩረት ያደረጉ።

የዚህ ጥረት ግብ፣ ለአንባቢያን እነርሱን እጅግ ስለሚመለከታቸው ጉዳዩች ሃሳብ መስጠጥ ብቻ ሳይሆን ፣ የሌሎች ባለድርሻ አካላት አመለካከት እና ተነሳሽነት ምን እንደሚመስል የጨረፍታ ምልከታ ለማበርከት ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ራስን በሌላው ሰው እግር ተክቶ ማየት ውጤታማ ስምምነት ላይ እንዲደረስ ያደርጋል፡፡ እንደዚህ ያለው ምልከታ ስምምነት ላይ ለመድረስን ቀላል ጉዳይ ያደርገዋል፡፡

# የኃግስ ዐውድ

የኃይል ማመንጫ ገበያዎች

የኃይል ግዥ ስምምነት (ኃግስ)

ለሃይል ማመንጫዎች የሚኖር የገንዘብ አቅርቦት


አካባቢያዊና ማህበራዊ ግዴታዎች

የዋና ነጥቦች ማጠቃለያ

# የሃይል ማመንጫ ገበያዎች

ይህ ምዕራፍ ከሃይል ማመንጫ የሚገኝ የኤሌክትሪክ ሃይል እንዴት በየቤታችን እና የንግድ ቦታዎቻችን እንደሚከፋፈል አጠቃላይ መረጃ የሚሰጥ ነው፡፡ የሃይል ማመንጫ አይነቶችን ዘርዝሮ የኤሊትሪክ ሃይል ግዢ እና ሽያጭ እንዴት እንደሚከናወን ያስረዳል፡፡ እንዲሁም በሃይል ማመንጫ ገበያው ውስጥ የሚሳተፉትን ልዩ ልዩ ተዋናዮች/ባለድርሻ አካላት/ እና የሃይል ማመንጫ ፕላንት የቆይታ ጊዜ/የህይወት ዘመን/ ምን ያህል እንደሆነ ያብራራል፡፡

ከታች ያለው ስዕል በሃይል ማመንጫ ገበያዎች ውስጥ ያሉ የተለያዩ ክፍሎችን ዘርፎችን የሚያሳይ ነው፡፡ እነዚህ ዘርፎች. ኃይል ማመንጨት 2. ሃይል ማስተላለፍ 3. ሃይል ማከፋፈል ናቸው፡፡ ኃይል ማመንጨት ማለት ከተለያዩ የመጀመሪያ ደረጃ  የኃይል ምንጮች  የኤሊክትሪክ ኃይልን የማመንጨት ሂደት ነው፡፡ ማስተላለፍ  ደግሞ የመነጨው ኃይል ለረዥም ርቀት፤በከፍተኛ የቮልቴጅ መጠን ከአመንጪ ድርጅቶች ወደ አከፋፋይ ድርጅቶች የሚያደርገው ጉዞ ነው፡፡ በመቀጠል የማከፋፈያ ድርጅቶች ይህንን ሃይል በተዘረጋው የኃይል ማከፋፈያ መረብ ለቤቶች እና የንግድ ስፍራዎች ያከፋፍላሉ፡፡



የኤሌክትሪክን ሃይል ከታዳሽ ምንጮች (ለምሳሌ እንደ ነፋስ፣ ጸሃይ፣ ውሃ፣ ግዘፈ ህይወት /ባዮማስ/ እና ውስጠመሬት ግለት /ጂኦ ተርማል/ ምንጮች) ወይም ደግሞ ታዳሽ ካልሆኑ (ለምሳሌ እንደ ነዳጅ፣ የተፈጥሮ ጋዝ፣ ከሰል እና ኒውክሌር) የኃይል ማመንጫዎች ማግኘት/ማመንጨት ይቻላል፡፡ የኒውክሊየር ሃይል ማማንጫን ሳይጨምር ኤሌትሪክን የሚያመነጩ ታዳሽ ያልሆኑ ነዳጆች የግለት /ተርማል/ ሃይል ማመንጫ በመባል ይታወቃሉ፡፡

| ታዳሽ ምንጮች | ታዳሽ ያልሆኑ ምንጮች |
|---|---|
| ነፋስ | ግለት ተርማል (በካርቦን የተገነባ) |
| ጸሃይ | ዘየት/ፔትሮሊየም |
| ውሃ | ጋዝ |
| ግዘፈ ህይወት | የድንጋይ ከሰል |
| ውስጠመሬትግለት | |

በዚህ ማስረጃ መጽሃፍ ውስጥ የሚነሱት ጉዳዮች ታዳሽ ከሆኑና ካልሆኑ ምንጮች አሌክትሪክን የሚስያገኙ የሃይል ማመንጫ ፕላንቶችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ለተለያዩ የነዳጅ ምንጮች በተለየ ሁኔታ የሚያስፈልግ ነገር ካለ የማስረጃ መጽሃፉ በተቻለ መጠን ለመጥቀስ ይሞክራል፡፡ የኒውክሊየር ማመንጫ ፕላንት አንድ የሃይል ማመንጫ አማራጭ ቢሆንም፣ በውስብስብነቱ እና በሚያስፈልገው ልዩ እውቀት/ስፔሻላይዜሽን መጠን/ ምክንያት በዚህ ማስረጃ መጽኃፍ ውስጥ አልተሸፈነም፡፡

ሃይልን ለማመንጨት የሚያስፈልጉ የቴክኖሎጂ አይነቶችን እና በመካከላቸው ያለውን ልዩነት የሚዘረዝሩ ብዙ የመረጃ ምንጮች አሉ፡፡ እነዚህን ልዩነቶች ልብ ማለት አስፈላጊ ነው፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ቴክኖሎጂ ለወደፊቱ በሚኖረው የሃይል ግዢ ስምምነት መዋቅር እና የሚከፈልበት ዋጋ ላይ የሚያመጣው ተጽእኖ ስላለ ነው፡፡ አንዳንዶቹ ቴክኖሎጂዎች ላይ ያለ መረጃ በዚህ መረጃ መጽሃፍ መጨረሻ ላይ ተጨማሪ ዋቢ መረጃዎች በሚል ስር ተጠናቅሮ ቀርቧል፡፡

# የጅምላ እና የችርቻሮ ገበያዎች

በጅምላ ሃይል ግዢ ገበያ እና በችርቻሮ የሚደረግ የኤሌክትሪክ ግዢ ገበያ መካከል ልዩነት አለ፡፡ ሃይል በጅምላ ለገዢዎች /አፍቴከርስ/ የሚሸጠው የሃይል አመንጪው ከሚገኝበት ቦታ ወይም አቅራቢያው ነው፡፡ይህ የተገዛ ሃይል ኃይል በማስተላለፊያ መስመሮች እና የማከፋፈያ ሲስተሞች ለችርቻሮ ገዢዎች እና የመጨረሻ ተጠቃሚዎች ይደርሳል፡፡ በችርቻሮ ለተጠቃሚ ከመድረሱ በፊት የሃይል ባለቤትነት ብዙ እጅ ሊቀይር ይችላል፡፡

## የሃይል ማመንጫ ፕላንት ምን ያህል ኤነርጂ የማመንጨት አቅም አለው?

የሃይል ማመንጫ ፕላንቶች የሚለኩት ማመንጨት በሚችሉት ሜጋዋት መጠን ነው፡፡ ሜጋ ዋት የልኬት አሃድ ሲሆን ከ 1000000 ዋት ጋር እኩል ነው፡፡ኪሎዋት ደግሞ ከ 1000 ዋት ጋር እኩል ነው፡፡

## የሃይል ግዢ እና ሽያጭ እንዴት ይከናወናል?

አንድ ኪሎዋት አወር ማለት አንድ ሺህ ዋት ኤሌክትሪሲቲ በተከታታይ ለ1 ሰአት ጠቀሜታ ላይ ሲውል ማለት ነው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ አንድ ሜጋዋት አወር ማለት ደግሞ 1ሚሊየን ዋት የኤሌክሪክ ሃይል ለ1 ሰአት በተከታታይ ጠቀሜታ ላይ ሲውል ማለት ነው፡፡ የማመንጨት አቅም/ካፓሲቲ/ ሽያጭ እና ግዢ በሜጋዋት የሚፈጸም ሲሆን አብዛኛውን ግዜ ሁሉም አቅሙ ጥቅም ላይ ዋለም አልዋለም ሙሉ ዋጋው ይከፈልበታል፡፡ ጉልበት /ኤነርጂ/ ደግሞ በሜጋዋት አወር ወይም ኪሎዋት አወር የሚገዛና የሚሸጥ ሲሆን ጥቅም ላይ ሲውል ብቻ ነው ዋጋው የሚከፈለው፡፡

## በአጠቃላይ ሲታይ ምን ማለት ነው?

አጭር ምሳሌ እንስጣችሁ፡፡አንድ የሃይል ማመንጫ 10 ሜጋዋት የማመንጨት አቅም አለው ከተባለ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን 10ሜጋዋት ሃይል ሊያመነጭ ይችላል፡፡ አንድ 10 ሜጋዋት አቅም ያለው የሃይል ማመንጫ በሙሉ አቅሙ ሳይቆራረጥ ለ1 ሰአት ከሰራ 10000 ኪሎዋት አወር ኤሌክትሪሲቲ ያመነጫል ማለት ነው፡፡ ለ 1ኪሎዋት አወር የተመደበው ተመን .10 የአሜሪካ ዶላር ከሆነ፣ ማመንጫው በሚሰራበት እያንዳንዱ ሰአት 1000 አሜሪካ ዶላር ዋጋ ያለው ሃይል ያመነጫል ማለት ነው፡፡

## የመነጨው ኃይል ከኃይል ማመንጫው ወደ ደንበኞች እንዴት ይደርሳል?

የመነጨን ኃይል ወደ ኃይል ፍርግርጉ/ፓወር ግሪድ/ የማገናኘት እና የማስተላለፍ ኃላፊነት ከአንድ የስልጣን ክልል ወደ ሌላ የስልጣን ክልል /ጁሪስዲክሽን/ እና ከማመንጫ ወደ ማመንጫ ይለያያል፡፡ ኃላፊነቱን ማን እንደሚወስድ በአብዛኛው ጊዜ ማመንጫው የሚሰራበት ሲስተም ያልተከፋፈለ/የታጨቀ/ ወይም የተከፋፈለ ሲስተም በመሆኑ ይወሰናል፡፡


## በተከፋፈለ እና ባልተከፋፈለ የኤሌክትሪክ ኢንዱስትሪ መዋቅር መካከል ያለው ልዩነት ምንድንነው?

በህግና ቁጥጥር ማዕቀፍ እና የኤሌክትሪክ ገበያ ላይ እየተደረጉ ያሉ ማሻሻያዎች ላይ በመመርኮዝ፤ በአብዛኛው ሁለት የተለያዩ የኤሌክትሪክ ኢንዱስተሪ ማዕቀፎች አሉ፡፡ የተከፋፈለ እና ያልተከፋፈለ/የታጨቀ/፡፡


ያልተከፋፈለ/የታጨቀ/ ሲስተም ማለት  የሃይል ግዢ፤የሃይል ማስተላለፍ እና  የሃይል ማከፋፈልን የመሰሉት የገበያ ሚናዎች ሳይከፋፈሉ በአንድ አካል ማለትም በገዥው ሲጠቀለሉ ነው፡፡ባልተከፋፈለ ሲሰተም ውስጥ ገዥው ሻጭ ያመነጨውን ሃይል የማስተላለፉን ኃላፊነት ይወስዳል፡፡ በተጨማሪም የቀረበው ሃይል ተዘጋጅቶ ሲያልቅ እንዲሸጥ ገዥው የሃይል ማመንጫውን ከ ሃይል ፍርግርጉ ጋር በተወሰነ ቀን የማገናኘት ኃላፊነት አለበት፡፡

በተከፋፈለ ሲስተም ውስጥ ግን ከላይ የተጠቀሱትን ሚናዎች የመጫወት ኃላፊነት ሙሉ ለሙሉ ገዢው መወጣት አይጠበቅበትም፡፡ ሌላ አካል አንዱን ወይም ሁለቱን ሃላፊነቶች ሊይዝ ይችላል፡፡ ይህ የሚናዎች ክፍፍል እስከምን ድረስ እንደሆነ የሚወሰነው እንደየአካባቢው የኤሌክትሪክ ሲስተሙን ለማሻሻል በተወሰዱ እርምጃዎች ነው።

ያልተከፋፈለ/የታጨቀ/ ማከፋፈያ እና ማስተላለፊያ



የተከፋፈለ ማከፋፈያ እና ማስተላለፊያ



ጀነሬተር  አገልግሎት/ዩቲሊቲ/ ተጠቃሚ  ኃይል ማስተላለፍ  ኃይል ማከፋፈል  ፋብሪካ

እነዚህን የሲስተም ልዩነቶች ማወቅ አስፈላጊነቱ ምንድን ነው? በእያንዳንዱ ሲስተም ውስጥ የሚሳተፉት አካላት ቁጥር ስለሚለያይ ነው፡፡ በሲስተሙ ውስጥ የሚሳተፉ አካላት ቁጥራቸው

በበዛ መጠን፤ የእያንዳንዱ ተሳታፊ ኃላፊነት በሚገባ ተለይቶ መቀመጥ አለበት፡፡ ይሄ ደግሞ የፕሮጀክቱ መዋቅር እና ተያይዘው የሚመጡ ስጋቶች ላይ ተጽእኖ ያመጣል፡፡

በተለያዩ ሃገራት የሚገኙ የኤሌክትሪክ መዋቅሮች ከላይ በተጠቀሱት የሲስተም ምድቦች ውስጥ

ተስተካክለው ላይካተቱ እንደሚችሉ መረዳት ያስፈልጋል፡፡ እያዳንዱ የስልጣን ክልል በተከተለው የኤሌክትሪክ መዋቅር ማሻሻያ መሰረት የሃይል ገበያው የተለያዩ ደረጃዎችን ሊያልፍ ይችላል፡፡ በአብዛኛው መንግስት ብቸኛው ገዢ/አፍቴከር/ የሚሆንበት አቅጣጫ ይያዝና ቀስ በቀስ የግል ሃይል አመንጪ ድርጅቶች፣ በባለሃብቶች የተያዙ የሃይል አቅራቢዎች፤ እና ሌሎች በግሉ ዘርፍ የተሰማሩ ተሳፊዎችን ያካትታል፡፡ በመጨረሻም

ሰፖት ማርኬት የተባለው የገበያ አይነት መጎልበት ይጀምራል፡፡ በስፖት ማርኬት ምንም አይነት ቋሚ የስምምነት ውል ሳይኖር፣ ፕሮጀክቱን የያዘው ድርጅት ኃይሉን በቀጥታ በጊዜው ባለው የገበያ ዋጋ መሸጥ ሲችል ነው፡፡

በኣንዳንድ ቦታዎች ላይ የቅይጥ ገበያ አደረጃጀት ሊኖር ይችላል፡፡ ይኸውም የሃይል ግዢ ስምምነት ያላቸው አመንጪዎች  በተጨማሪ ለሰፓት ማርኬት ገበያ የመሸጥ መብት ወይም ኃላፊነት ሲኖራቸው ነው፡፡

# የተለያዩ ተሣታፊዎች/ተዋናዮች ሚና

በኃይል ግዢ ስምምነት ድርድር ላይ የሚሳተፉ የተለያዩ ተዋናዮች እነማን ናቸው? ቀዳሚ ሚናቸውስ ምንድነው?

| የመጀመሪያ ደረጃ ተሣታፊዎች/ተዋናዮች | ሁለተኛ ደረጃ ተዋናዮች/ተሳታፊዎች |
|---|---|
| • ገዢ/ኦፍቴከር/ | • መንግስት |
| • ንጪ/ሻጭ/ | • ተቆጣጣሪ |
| | • ደንበኛ/ተጠቃሚ |
| | • የማስተላለፊያ ድርጅት |
| | • የማከፋፈያ ድርጅት |
| | • አበዳሪ |
| | • የግንባታ ድርጅት |
| | • የማመንጫ ፕላንት አስተዳዳሪ |
| | • ነዳጅ አከፋፋይ |
| | • የሲስተሙ አስተዳዳሪ |

አብዛኛውን ጊዜ የመጀመሪያ ደረጃ ተሣታፊዎች ገዢው እና የኃይል አመንጪው ናቸው፡፡ እንደየ ህግ እና ቁጥጥር አውዱ ደግሞ አንዳንድ ሁለተኛ ደረጃ ተሣታፊዎችም የኃይል ግዢ ስምምነቱ አካላት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## የመጀመሪያ ደረጃ ተሣታፊዎች

### የኃይል አመንጪው/ሻጭ/

የኃይል አመንጪው ወይም አቅራቢው የሃይል ፕሮጀክቱ ባለቤት እና ሻጭ ነው፡፡ይህ አካል በአብዛኛው ራሱን የቻለ የኃይል አመንጪ ወይንም የፕሮጀክት ድርጅት በመባል ይታወቃል፡፡

### ኦፍቴከር/ገዥ/

ኦፍቴከሩ ወይም የሃይል ገዢው ሃይሉን የሚረከበው አካል ነው፡፡ ይሄ በአብዛኛው የዩቲሊቲ ድርሻ ሲሆን በአብዛኛው በመንግስት እጅ የሚተዳደር ነው፡፡

## ሁለተኛ ደረጃ ተሣታፊዎች/ተዋናዮች/

### መንግስት

የሃይል አመንጪ የሆነው አገር በሃይል ማመንጫ ስምምነቱ ድርድር የተለያዩ ደረጃዎች ላይ ተሣታፊ ነው፡፡ መንግስት የሚጫወተው ሚና እንደ ሃገሪቱ የህግ እና ቁጥጥር ማዕቀፍ ሰፋፊ ልዩነቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

በሃገሪቷ ውስጥ በኤነርጂው ዘርፍ ፖሊሲ የሚያስቀምጠውና ዋነኛ ተሣትፎ የሚያደርገው የመንግስት አካል የኤነርጂ ሚኒሰቴር ነው፡፡ ሌሎች ተሣታፊ የመንግስተ አካላት የገንዘብ ሚኒስቴር፤ የፕላኒንግ ኮሚሽን፤ የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ፤ብሄራዊ ባንክ፤ የገቢዎች ባለስልጣን፤ የአካባቢ ጥበቃአ እና የደን ሚኒሰቴር፤ የመሬት ኤጀንሲ፤ ጠቅላይ አቃቢ ህግና ህግ አውጪ አካላት ናቸው፡፡

### ተቆጣጣሪ አካል

አብዛኛውን ግዜ ማንኛውም ገዥ/ኦፍቴከር/ ስምምነት ውስጥ ከመግባቱ በፊት፤ የኤነርጂ ዘርፉን የሚቆጣጠሩ አካላት የኃይል ግዢ ስምምነቶችን ማጽደቅ አለባቸው፡፡ተቆጣጣሪው አካል የዋጋ ተመን የማውጣት እና የማጽደቅ እንዲሁም በኢንዱስትሪው ውስጥ የተቀመጡ ደረጃዎች መሟላታቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት፡፡ ቁጥጥር አብዛኛውን ጊዜ የተጠቃሚውን ደህንነት የመጠበቅ እና ራሳቸውን ችለው ኃይልን ለሚያመነጩ አቅራቢዎች በቂ ማበረታቻ ሰጥቶ ሃገሪቱ ውስጥ የሃይል ፕሮጀክቶችን እንዲያካሂዱ የማድረግ ስራዎችን በጥንቃቄ ማመጣጠንን ይጠይቃል፡፡

### ደንበኞች/ተጠቃሚዎች

በጣም ጥቂት የሆነ ቮልቴጅ ተጠቃሚ ደንበኞች የኃይል ግዥ ስምምነቶች ድርድር ውስጥ በቀጥታ አይሣተፉም፡፡ ምክንያቱም በአብዛኛው ኃይልን የሚያገኙት በአካባቢው ካለ የማከፋፈያ መረብ ነው፡፡ ነገር ግን የኃይል ግዥ ስምምነቶቸ ደንበኞንም ይመለከታሉ ምክንያም የኃይል ማመንጫ ፕላንቶችን የመገንባት እና የማስተዳደር ወጪ ዞሮ ዞሮ በዋጋ ተመን አማካኝነት ወደነሱ ስለሚተላለፍ ነው፡፡

ነገር ግን ከፍተኛ ቮልቴጅ ተጠቃሚ የሆኑ ደንበኞች ቀጥታ ከሻጩ ኃይል የሚገዙ ከሆነ የኃይል ግዥ ስምምነቱ ላይ ሊደራደሩ ይችላሉ፡፡

## ኃይል አስተላላፊ ድርጅቶች

የኃይል አስተላላፊ ድርጅቶች ሻጩ ያመነጨውን ኃይል ለሃገሪቱ የኃይል ማስተላለፊያ መረቦች የማስተላለፍ ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ባልተከፋፈለ ማዕቀፍ ውስጥ፤ አስተላላፊው አካል ከገዥው/አፍቴከር/ አካል ጋር አንድ ነው፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው በተከፋፈለ ማዕቀፍ ውሰጥ፤ ግን እንደአከፋፈሉ ሁኔታ፤ የኃይል አስተላላፊ ድርጅቱ  በቀጥታ ወይንም በተዘዋዋሪ በኃይል ግዥ ስምምነቶች ውስጥ ሊሳተፍ ይችላል፡፡

## ኃይል አከፋፋይ ድርጅቶች

ኃይል አከፋፋይ ድርጅቶች ኃይልን በቀጥታ ለተጠቀሚው የማስተላለፍ እና ተመን የመውሰድ ሃላፊነት አለባቸው፡፡እዚህም ጋር ባልተከፋፈለ ማዕቀፍ ውስጥ ገዥው/አፍቴከሩ/ ኃይሉን የማከፋፈል ሃላፊነት ይወስዳል፡፡ በተከፋፈለ ማዕቀፍ ስር ግን፤ አከፋፋዮች በቀጥታ ኃይልን ከሻጩ ሊገዙ ይችላሉ፡፡

## አበዳሪዎች

ራሳቸውን ችለው ኃይል የሚያመነጩ ድርጅቶች የፕሮጀክቱን ወጪ ሙሉ ለሙሉ ለመሸፈን የሚችሉበት አጋጣሚ በጣም ጥቂት ነው፡፡ አብዛኛውን ግዜ ኃይል አመንጪዎች ከአበዳሪዎች ገንዘብ በመውሰድ የኃይል ፕሮጀክቶችን ወጪ ይሸፍናሉ፡፡አበዳሪዎቹ በድርድር ወቅት ከጀርባ ሆነው ነው የሚሳተፉት፡፡ የኃይል ግዥ ስምምነቱ በአበዳሪዎቹ ዘንድ ተቀባይነትን ካላገኘ ገንዘብ ለማበደር ከመስማማታቸው በፊት ስምምነቱ ተመልሶ ለድርድር መቅረብ አለበት፡፡

የተለያዩ አይነት አበዳሪዎች አሉ፡፡ የንግድ ባንኮች ብድር የሚያቀርቡት ከወለድ ትርፍ ለማግኘት ሲሆን የልማት ባንኮች ደግሞ ለትርፍ እንዲሁም ልማትን ለማሳደግ ብድር ያቀርባሉ፡፡ የልማት ባንኮች የሁለትዮሽ ወይም በብዙ ሃገራት የሚመሩ (ማለትም ብዙ ሃገራትን እንደ አባል የያዙ ወይም አንድ ሃገር ብቻ በባለቤትነት የያዛቸው) ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የውጪ ንግድ አበዳሪ ኤጀንሲዎች ደግሞ በአብዛኛው የማሽነሪ ወጪ ብድር አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡

## ነዳጅ አቅራቢ

ይህ ደግሞ ለኃይል አመንጪው ነዳጅን የሚያቀርበው አከል ነው፡፡

### የግንባታ ድርጅት (የኤሌክትሪክ ኃይል ስራ ተቋራጭ)

**የግንባታ ድርጅቱ** የኃይል ማመንጫውን በኃይል ግዢ ስምምነት ውስጥ በተቀመጠው ስፔስፊኬሽን መሰረት የመገንባት ኃላፊነቱን ይወስዳል ።.

### የኃይል ማመንጫ አስተዳዳሪ

የኃይል ማመንጫ አስተዳዳሪው ማመንጫው በኃይል ግዢ ስምምነት ውስጥ የተቀመጡትን ኃላፊነቶች በሚያሟላ መልኩ የማንቀሳቀስና ስራ የማስኬድ ኃላፊነት አለበት፡፡

### የሲስተም አስተዳዳሪ


የሲስተሙ አስተዳዳሪ የኤሌክትሪክ ግሪዱን ስራ ሂደት መቆጣጠር አለበት፡፡

# የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት የቆይታ ጊዜ/የህይወት ዘመን/

ቀጥሎ የተቀመጠው ስእል የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ዝግጅት፤ግዥ/፣ድርድር፣ግንባታ እና አተገባበር ምን እንደሚመስል አጠቃላይ ግንዛቤ ይሰጣል፡፡ ፕሮጀክቱ ግዥ በሚያካሂድበት ወቅት የኃይል ግዥ ስምምነቱ በጣም አስፈላጊ አካል ነው፡፡ የኃይል ግዥ ስምምነቱ ለድርድር በጣም ሰፊ ግዜ የሚፈልግ ቢሆንም፤ ለተከታዮቹ 25-30 አመታት ፕሮጀክቱን ከማስተዳሩም በተጨማሪ የፕሮጀክቱ ወጪ ሽፋን፤ግንባታ፤ አስተዳደር እና እድሳት እንዴት እንደሚካሄድ መሰረቱን የሚጥል ነው፡፡

### የኃይል ማመንጫ ፕሮጀክቱ የህይወት ዘመን የሚያሳየው ስዕል

በስዕሉ ላይ የሚታዩ የጊዜ ሂደቶች ለማሳያ ብቻ የተቀመጡ ስለሆኑ አንዳንዴ ድግግሞሽ ሊኖር ይችላል



Preparation
12 - 36 months
Pre-feasibility
Feasibility
Procurement
12 - 24 months
PQ
RFP and Project Agreements
Bid Submission, Bidder Term Sheets
Evaluation
Negotiation
PPA Signed
If tariff fixed at bid
If tariff not fixed at bid
12 - 24 months
EPC
Transmission Agreement
Fuel Supply Agreement
Fuel Transportation Agreement
12 - 24 months
EPC
Transmission Agreement
Fuel Supply Agreement
Fuel Transportation Agreement
PPA Signed
Reaching Financial Close
12 -24 months
Financing Agreements
Direct Agreements
O&M Contract
Other Project Agreements
Financial Close
Construction
18 - 60 months
COD
Operations
20 - 30 years

# የኃይል ግዥ ስምምነት (ኃግስ)

## ኃግስ ምንድን ነው?

የኃይልን ሽያጭ እና ግዥ የሚመራው ስምምነት የኃይል ግዥ ስምምነት በመባል ይታወቃል፡፡

የኃይል ግዥ ስምምነት በሁለት ወገኖች መካከል የሚደረግ ውል ሲሆን አንደኛው ወገን ኃይሉን አመንጭቶ ለሽያጭ የሚያቀርበው (ሻጩ፤አመንጪው፤ የፕሮጀክቱ አስተዳዳሪ ድርጅት) ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ኃይሉን ለመግዛት(ገዥ/ኦፍቴከር/) የሚፈልገው ድርጅት ነው፡፡ ይህ ውል እንዳንዴ የርክክብ/ኦፍቴክ/ውል በመባል ይታወቃል፡፡

## የኃይል ግዢ ስምምነት አጀማመር (ጥንስስ)

በቀላሉ የኃይል ግዢ ስምምነት ማለት የኃይልን ግዢና ሽያጭ ለማሳለጥ የሚጠቅም መሣሪያ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ስምምነቱ እውን የሚሆነው ገዢው /ኦፍቴከር/ አስፈላጊ የሆኑ ተከታታይ ውሳኔዎች ላይ ሲደርስ ነው፡፡ እነዚህ ውሳኔዎች፤ የኃይል ፍላጎትን፣ የገዢውን ኢኮኖሚያዊ አቅም፣ተፈላጊው የኃይል ማመንጫ ቴክኖሎጂን መምረጥ እና የኃይል ማመንጫው ቦታ የት እንደሚሆን መለየትን ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡

### የኃይል ፍላጎት

ከምንም ነገር በፊት ገዥው/ተረካቢው/ ለሃይል አቅርቦት ፍላጎት እንዳለ ማጋገጥ አለበት፡፡ ወቅታዊ የኃይል ፍላጎትን ብቻ ሳይሆን፣ በጊዜ ሂደት ውስጥ ሊመጡ የሚችሉ የኃይል ፍላጎት መፈራረቆችን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ ጥናት መካሄድ አለበት፡፡

### ቴክኖሎጂ እና በጀት

የኃይል ፍላጎት እንዳለ ከተለየ በኋላ ገዥው/ተረካቢው/ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የኃይል ምንጮችን መለየት አለበት፡፡እዚህ ውሳኔ ላይ የሚደረሰው ደግሞ ኃይሉ የሚኖረውን የዋጋ ተመን የመክፈል አቅምን፣ ጥቅም ላይ የሚውለውን ነዳጅ እና ቴክኖሎጂን፣ እንዲሁም የሃይል ማመንጫው የት እንደሚሰራ ከግምት ውስጥ በማገባ ነው፡፡ የገዢው በጀት እና የሚመረጠው የኃይል ማመንጫ የቴክኖሎጂ አይነት ብዙ ጊዜ እጅ ለእጅ የሚሄዱ ነገሮች ናቸው፡፡አንዳንድ ቴክኖሎጂዎች ከሌሎቹ ይልቅ ወጪያቸው ከፍተኛ ቢሆንም፤ ፍላጎት በበዛ ጊዜ ከአንድ በላይ በሆነ የሃይል ምንጭ መጠቀም በመቻላቸው ወይም ደግሞ ለአካባቢ ጥበቃ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል ተብሎ ስለሚታሰብ ተፈላጊ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ መንግስት ለሃገሪቱ ሁኔታ ይስማማሉ ብሎ ያስቀመጣቸው የሃይል ምንጭ አይነቶችም በገዥው ውሳኔ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላሉ፡፡-

## ቦታ

በመጨረሻም ተረካቢው ገዥ/ኦፍቴከሩ/ የሃይል ምንጩ የት መሆን እንዳለበት ይወስናል፡፡ቦታው የት እንደሚሆን የሚወስነው በሃገሪቷ ውስጥ የትኞቹ ክልሎች ተጨማሪ ሀይል እንደሚያስፈልጋቸው በማየት ነው፡፡ከተቻለ ለመጨረሻ ተጠቃሚው በተቀላጠፈ መልኩ ኃይልን ለማስተላለፍ፤ ቦታው ለንኡስ ጣቢያዎች/ሰብስቴሽንስ/ እና ለማስተላለፊያ መስመሮች ቅርብ የሆነ ቦታ ነው የሚሆነው፡፡

ከሁሉም ባላይ ግን ተረካቢ ገዢዎች/ኦፍቴከርስ/ (እና አመንጪዎች) የኃይል ማመንጫውን የኃይል ፍርግርጉ ጋር ለሚገኘው የማገናኛ ቦታ በተቻለ መጠን ማቅረብ ይፈልጋሉ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ለማስተላለፊ መስመሮች እና መሰረተ ልማት ዝርጋታ የሚወጣውን ወጪ ለመቀነስ እንዲያመቻቸው ነው፡፡ ሌሎች ቦታን የሚወስኑ ዋና ነገሮች ማመንጫው ለነዳጅ ምንጭ ያለው ቅርበት፣ማመንጫው በህብረተሰቡ ሊኖረው የሚችለው ማህበረሰባዊ አካባቢያዊ ተጽእኖ፣እና በአነስተኛ ወጪ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ይህን ተጽእኖ ሊገቱ የሚችሉ ዘዴዎች መኖራቸውየመሳሰሉት ናቸው፡፡

ለምሳሌ በጋዝ የሚሰራ የኃይል ማመንጫ የጋዝ ምንጭ የሌለበት ራቅ ያለ ቦታ ቢሰራ የሚሰጠው ጥቅም ጥቂት ነው የሚሆነው፡፡ ይልቁንም እንደ ጸሃይና ነፋስ ያሉ ታዳሽ ሃይሎች ላይ ተመስርቶ የሚሰራ ማመንጫ ለእንደዚህ አይነት አካባቢዎች የተሻለ አማራጭ ከመሆኑም በላይ የካርቦን ልቀትን ለማስቀረትም ይጠቅማል፡፡

ነገር ግን እንደዚህ አይነቶቹ ታዳሽ ሃይሎች በሙቀት እንደሚሚሰሩ ምንጮች አስተማማኝነት የላቸውም፡፡ (ጸሃይና ነፋስ በተፈጥሮአቸው ለወደፊቱ የሚያስገኙት የኃይል መጠን መደበኛ እና አስተማማኝ ይሆናል ብሎ አስቀድሞ ለመተንበይ የማያመቹ ምንጮች ናቸው)፡፡ የኤሌክትሪክ ማመንጫ ቴክኖሎጂ ምርጫ ለተረካቢው ገዥ/ኦፍቴከር/ በጣም መጤን ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም የሚመነጨው ኃይል ወጪ፣ አስተማማኝነት፣ እና የሚያመጣው አካባቢያዊ እና ማህበራዊ መዘዞች ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ ስለሚኖረው ነው፡፡

# የኃይል ግዢ እና ተመን ላይ ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ነገሮች

ገዥው ከላይ የተዘረዘሩት ውሳኔዎች ላይ ለመድረስ ባለው ሂደት ውስጥ የጨበጠውን እውቀት ታጥቆ በኃይል ገበያው ውስጥ ያሉ ተሣታፊዎች የሚፈለገውን ነገር ለማቅረብ ያላቸውን ፍላጎት እና የዋጋ ጥናት ማካሄድ ይችላል፡፡ ይሄም በሁለት መንገድ ሊሰራ ይችላል፡፡

ተመራጭ የሆነው መንገድ ውድድር ያለበት የጨረታ ጥሪ ማቅረብ ነው፡፡ አብዛኛውን ግዜ ይህ የሚደረገው ተጫራቾች ፕሮፖዛላቸውን እንዲያቀርቡ ደንቡን የተከተለ የይፋ ጥሪ ሲቀርብላቸው ነው፡፡ ይህ የፕሮፖዛል ጥሪ የሚፈለገው የኃይል መጠን፤ የቴክኖሎጂ አይነት እና ሃይል ማመንጫው የተፈለገበትን ቦታ ለይቶ ያስቀምጣል፡፡ ይህንን መረጃ በመጠቀም አመንጪዎች አርስ በእርስ በመፎካከር ያላቸውን ብቃት፣ የማመንጫ ሃይሉ ግንባታን ወጪ ምን ያህል መሸፈን እንደሚችሉ እና በተቻለ መጠን የተሻለ የዋጋ ተመን በሚያስገቡት ፕሮፖዛል ውስጥ ያሳያሉ፡፡ ተረካቢው ገዥ/ኦፍቴከሩም/ የሚመረጠው ፕሮፖዛል በጊዜ ሂደት ውስጥ ሳይቆራረጥ አስተማማኝ የሆነ የሃይል አቅርቦትን እና ለተጠቃሚው የተሻለ ዋጋን የሚያረጋግጥ እንዲሆን የቀረበውን ዋጋ ያወዳድራል፤ የፋይናንስ አቅምን ይገመግማል እንዲሁም ብቃታቸውን ይመዝናል፡፡ይህ ዘዴ፤ በይፋ ጥሪ ሳይደርግላቸው በራሳቸው ፕሮፖዛል ካስገቡ ድርጅቶች ጋር ድርድር ውስጥ ከመግባ ይልቅ የተሻለ እና ተፎካካሪ ውጤት ያስገኛል ተብሎ ይገመታል፡፡

ጥሪ ሳይቀርብላቸው በራሳቸው ፕሮፖዛል ካስገቡ ድርጅቶች ጋር የሚደረግ ድርድር የኃይል እጥረት ችግር የተንሰራፋባቸው ሃገሮች ውስጥ ድንገተኛ ነገር በሚፈጠርበት ግዜ የሃይል ግዢን ለማፋጠን ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ እንዲህ አይነቱ ዘዴ የሃይል ግዢ ስምምነት ማዕቀፍ በሌለባቸው የስልጣን ክልሎች/ጁሪስዲክሽኖች/ ውስጥም ስራ ላይ ሊውል ይችላል፡፡ ጥሪ ሳይቀርብላቸው የሚመጡ ፕሮፖዛሎችን ለመጠቀም ሲታሰብ ግልጽነት እና ለሚወጣው ገንዘብ ተመጣጣኝ የሆነ አገልግሎት እንደሚሰጥ ለማረጋጥ በቂ የሆነ የቁጥጥር ሲስተም መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡

## የስምምነት ፎርማ

አንዳንዴ ተፎካካሪዎች ያሉበት ጨረታ በሚካሄድበት ግዜ፤ ሊመጡ የሚችሉ ተጫራቾች በሚያስገቡት ሰነድ ውስጥ ለወደፊቱ የሚመጣወን ስጋት የመወጣት ኃላፊነትን ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ ለማሳሰብ ረቂቅ የሃይል ግዥ ስምምነት ለጨረታ ጥሪ ከተዘጋጨው ሰነድ ጋር አብሮ ይካተታል፡፡ ጥሪ ሳይቀርብላቸው ለሚመጡ ፕሮፖዛሎች ግን ረቂቅ የማስገባት አማራጭ ያለው ተረካቢው ገዥ/ኦፍቴከር/ ነው

ህ የሚያደርገውም የፕርፖዛሉን አዋጪነት እና ውጤታማነት ላይ ተገቢውን ጥናት (due diligence) ካካሄደ በኋላ ነው፡፡

የሃይል ግዢ ስምምነቱ የመጀሪያ ረቂቅ አንዳንዴ ከኃይል አመንጪው ሊመጣ ይችላል፡፡ ነገር ግን ኃይሉን ለመግዛት ፍላጎት ስላለው እና ለመጪዎቹ አመታት የስምምነቱ ሰነድ ላይ ተመስርቶ መስራት ስለሚጠበቅበት የመጀመሪያውን የግዢ ስምምነት ረቂቅ የማዘጋጀቱን ስራ **ሙያዊ ብቃት ካለው የህግ ባለሙያ** ጋር በመነጋገር ተረካቢው ገዥ/አፍቴከሩ/ ቢያዘጋጀው ይመከራል፡፡ ብዙ ጊዜ የሁለትዮሽ እና የብዙ ሃገራት የልማት ተቋማት የመንግስት አካላት ለሆኑ ተረካቢ ገዥዎች የህግ አገልግሎት ለማግኘት የሚችሉበት የብድር አገልግሎቶች ይሰጣሉ፡፡

አንዳንዴ ደግሞ ተረካቢ ገዥ ለኢንዱስትሪ አገልግሎት የሚውል ከፍተኛ መጠን ያለው ሃይል ተጠቃሚ ስለሚሆን አመንጪው የመጀመሪያውን ረቂቅ የኃይል ግዢ ስምምነት ለተረካቢው በማቅረብ ፕሮፖዛሉ በሚገበገምበት ወቅት አብሮ እንዲመዘን የሚያደርግበት ሁኔታ አለ፡፡

አንዳንዴ ተስማሚዎቹ ወገኖች የህግ ግዴታ ውስጥ የማያስገባ የቅድመ ስምምነት ፊርማ (memorandum of Understanding) ማስፈርን እንደአማራጭ ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት በወቅቱ የደረሱባቸው ስምምነቶችን ወረቀት ላይ ማቀመጥ ሲፈልጉ ነው፡፡ ግን እንዲህ አይነት የስምምነት ሰነድ ዝርዝር ጉዳይ ውስጥ ብዙ ጊዜ ስለማይባ እና በስተመጨረሻም በኃይል ግዥ ስምምነት ስለሚተካ፤ ሁልግዜም መወሰድ ያለበት እርምጃ ላይሆን ይችላል፡፡

## ድርድር እና ስምምነቶች

የሃይል ግዥ ስምምነቱ ረቂቅ እንደ ተመን፣ቴክኖሎጂ እና ቦታን የመሳሰሉ ዋና ዋና ጉዳዮችን አካቶ ይይዛል፡፡ ተዋዋይ ወገኖች ሊስማሙባቸው የሚስፈልጉ ሌሎች ጉዮችንም ይዳስሳል፡፡ አብዛኛውን ግዜ የመጀሪያው ረቂቅ የኃይል ግዥ ስምምነት ከተዘጋጀ በኋላ፤አመንጪውና ተረካቢው ገዥ አብረው በመቀመጥየተለያዩ ነጥቦች ላይ ድርድር ያካሂዳሉ፡፡ ከተሳካም ስምምነቲን እስከዳር የሚያደርሱበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ፡፡ በድርድሩ ወቅት ሁለቱም ወገኖች የህግ ምክር አንዲሁም በቂ የገንዘብ መጠን ካለ ደግሞ መሃንዲሶች እና የገንዘብ አማካሪዎችን ማሳተፍ እንዳለባቸው ሳይጠቀስ አይታለፍም፡፡

እነዚህ አማካሪዎች የተለያዩ ሃላፊነቶች እና ስጋቶች ለተገቢው ወገን እንዲሰጡ ከማድረግ አንጻር ለተዋዋየቹ ጠቀሜታ ይኖራቸዋል፡፡ ይሄ ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች የገቡበትን ስምምነት በደንብ እንዲረዱት የሚያደርግ ድግምግሞሽ የበዛበት የድርድር ሂደት ሲሆን ግቡም በስተመጨረሻ ሁለቱም ወገኖች ሊከውኑ እና ሊገዙበት የሚችሉበት ስምምነት ላይ መድረስ ነው፡፡

በሶስተኛ ወገን አበዳሪዎች የሚሰሩ ፕሮጀክቶቸ ላይ የኃይል ግገር ስምምነቱ ተጠናቋል ተብሎ እንዲታሰብ አበዳሪዎቹ በስምምነቱ ምቾት ሊሰማቸው ይገባል፡፡ ምንም እንኳን ተዋዋይ ወገን ባይሆኑም የአመንጪውን ወጪ በብድር ስለሚሸፍኑ ይህን ብድር ለመክፈል የሚያስችለውን ለወደፊቱ የሚገኝ ገቢ የሚስተዳድረው ሰነድ (የኃይል ግዥ ስምምነት) ለነሱ ተስማሚ መሆኑን ማረጋገጥ ይፈልጋሉ፡፡

በመሆኑም አበዳሪዎቹ ገንዘብ ያበደሩት ኃይል አመንጪው ወገን ከስምምነቱ በሚያገኘው ገንዘብ እነሱን መክፈል እንዲችል በሃይል ግገር ስምምነቱ ውስጥ የተቀመጡትን ዝርዝር ጉዳዮች ማጥራት ብሎም ማሻሻል ይፈልጋሉ፡፡

የኃይል ግዥ ስምምነቱ ቢፈረምም እንኳን አበዳሪዎቹ ማብራሪዎች እና ማሻሻያዎች እንዲካተቱ ይፈልጋሉ፡፡ እንዲህ አይነት ማሻሻያዎች ከኃይል ግዥው ስምምነት ጋር አባሪ ሆነው ሊጠናቀሩ ወይም "ቀጥተኛ ስምምነት" በሚል ስያሜ በሌላ ሰነድ ሊዘጋጁ ይችላሉ፡፡ እንዲህ አይነቱ ቀጥተኛ ስምምነት በተረካቢው ገዥ፤ በአመንጪው እና በአበዳሪው መካከል የሚፈረም ሲሆን በኃይል ግዥ ስምምነቱ ላይ በአበዳሪው ፍላጎት የተደረጉ ማሻሻያዎችን፣ አመንጪው ብድሩን መክፈል በሚያቅተው ግዜ ስምምነቱን ለአበዳሪው እንዲስተላልፍ ወይም እንደ ኮላተራል እንዲያቀርብ በስምምነቱ የተቀመጡ ዝርዝር ነጥቦች ላይ የተረካቢው ገዥ/ኦፍቴከር/ ፍቃደኝነትን፤ እንዲሁም የአበዳሪውን ጣልቃ የመግበት መብት አካቶ ሊይዝ ይችላል፡፡

የኃይል ግዥ ስምምነቱ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ተዋዋዮቹ ወገኖቸ እያንዳንዳቸው ይሄ ስምምነት በከፍተኛ አስተዳደር፣ በፓርላማ ወይም ህግ አውጪ አካል፣ በተቆጣጣሪ አካል እንዲሁም በማንኛውም ሌላ የመንግስት ተቋም መጽደቅ እንዳለበት ማጣራት ይኖርባቸዋል፡፡

የውሉ መጽደቅ እና ፍቃድ ማግኘት ለወደፊቱ ለሚኖው አፈጻጸም እና ለሚፈጥረው የረዥም ግዜ ግንኙነቶች በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትን ፍሬ ነገሮች ማጠቃለያ

## ከሃይል ግዥ ስምምነቱ በፊት

- **ተመን፣ ቴክኖሎጂ እና ቦታ፡** የኃይል ግዥ ስምምነቱ ከመርቀቁ በፊት ተረካቢው ገዥ በጀታቸው ምን ያክል እንደሆነ፤ ምን አይነት የማመንጫ ቴክኖሎጂ መጠቀም እንደሚፈልጉ እና የመነጨው ሃይል የሚፈለግበትን ቦታ ማጣራት እና መወሰን አለባቸው፡፡

- **ቴክኖሎጂ:** የኃይል ማመንጫ ቴክኖሎጂ ምርጫ የሚቀርበው ሃይል አስማማኝነት እና ወጪ ላይ ቀጥተኛ ተጽእኖ ያለው በመሆኑ ለተረካቢው ገዥ(አፍቴከር) ትልቅ ውሣኔ ነው፡፡
- **ቦታ**: ተረካቢ ገዢዎች /አፍቴከርስ/ (እንዲሁም አመንጪዎች) የማስተላለፍ ወጪን ለመቀነስ እና የነዳጅ ምንጮችን ለማግኘት የሚመነጨው ኃይል በተቻለ መጠን ለተጠቃሚው ወገን እና ከኃይል ፍርግርጉ ጋር ለሚገናኝበት ቦታ አቅራቢያ እንዲሆን ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡

## የሃይል ግዥ እና የታሪፍ መጠን ላይ ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚገባቸው ነገሮች:

- **የግዥ አማራጮች፡-ይፋ የፕሮፖዛል ጥሪ -** ግልጽነትን እና ከወጪ የሚመጣጠን አገልግሎትን ለማግኘት ተረካቢው ገዥ ይፋ የሆነ የጨረታ ጥሪ አቅርቦ አመንጪዎችን በግልጽ ቢያወዳድር ተመራጭ ይሆናል፡፡ ጥሪ ሳይደረግላቸው የሚመጡ ፕሮፖዛሎች በድንገተኛ ግዜ እና የሃይል ችግር በተንሰራፋባቸው ሃገሮች ውስጥ የሃይል ግዥ ሂደቱን ለማፋጠን አንዳንዴ ጠቀሜታ ላይ ይውላሉ፡፡ ግልጽነት እና ተመጣጣኝ አገልግሎት መኖሩን ማረጋገፅ ግን ተገቢ ነው፡፡
- **ጥራት ወሳኝ ነው:** ተረካቢው ገዥ አመንጪ ሲመርጥ ዋጋን ብቻ ተመስርቶ ሳይሆን ጥራትን እና ከዚህ በፊት አመንጪው በስራው ላይ ያለውን ውጤታማነት/ስነምግባር ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

## የኃይል ግዥ ስምምነቱን ማርቀቅ

- **እስከሪብቶው ማን እጅ ነው:** ተረካቢው ገዥም ሆነ አመንጪው የመጀሪያውን ረቂቅ ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡ በአብዛኛው ግን የተረካቢው ገዥ ድርሻ ነው፡፡
- **የህግ አማካሪ ወሳኝነት:** ተረካቢው ገዥ የኃይል ግዥ ስምምነቱን በሚያረቅበት ሰአት ብቃት ያለው የህግ ባለሙያ ማማከር አለበት፡፡

## ድርድር እና አጨራረስ

- **ዝርዝር ጉዳዮች:** ተረካቢው ገዥም ሆነ አመንጪው የተጣለባቸውን ሃላፊነት እና የሚመጡ ስጋቶች አጢነው መስማማት እንዲችሉ እና ግዴታቸውን እንዲወጡ ለድርድር መቅረብ አለባቸው
- **የማይወራው እውነታ-የአበዳሪዎች ተሳትፎ፡-** ከሶስተኛ ወገን በሚመጣ ብድር የሚሰሩ ፕሮጀክች ላይ የሚደረግ የኃይል ግዥ ስምምነት ተተናቋል የሚባለው ለአበዳሪው ተስማሚ ሲሆን ነው፡፡ ስምምነቱን አመንጪው እና ተራካቢው ገዥ ቢያጠናቅቁ እንኳን አበዳሪው መልሶ ሊያስከልሰው ይችላል፡፡

በስዕሉ ላይ የሚታዩ የተለያዩ የስምምት አይነቶች ተቀምጠዋል።

# ሌሎች የፕሮጀክት ስምምነቶች

የኃይል ግዥ ስምምነቱ ግዥ እና ሽያጭን የሚያስተዳድር ቢሆንም አብረው የሚሄዱ እና ከገንዘብ ግንባታ እና አፈጻጸም ጋር የተያያዙ ሌሎች ተዛማጅ ውሎችም ይኖራሉ፡፡


የሚመጡ ስጋቶችን ከአድልኦ ነጻ በሆነ መንገድ ለመመደብ እነዚህ ውሎች ከኃይል ግዥ ስመምነቱ ጋር መስማማት እና መቀናጀት አለባቸው፡፡ ለምሳሌ የስምምነቱ ጊዜ ሳያልቅ ብድር መከፈሉ እንዲረጋጥ የሃይል ግዢ ስምምነቱ ቆይታ ከብድሩ ጊዜ ገደብ ጋር አንድ ላይ መቀናጀት አለበት፡፡

በተጨማሪም፤ የምህንድስና ግዢ እና ግንባታ ውል (ኢፒሲ ኮንትራት)፤ የአስተዳደር እና እደሳ ስምምነቶች (ኦ ኤንድ ኤም)/የረዥም ግዜ የአገልግሎ ስምምነቶች (ኤልቲኤስኤ) በአጠቃላይ በሃይል ግዥ ስምምነቱ ውስጥ ስለ ኃይል ማመንጫው ንድፍ፣ግንባታ፣ከንዋኔ፣ እና እድሳት የተቀመጡትን ዝርዝር ሁኔታዎችን ማወቅ፣ እንዲሁም ከነሱ ጋር መስማማት እና ለነሱ መገዛት ይኖርባቸዋል፡፡

የከዚህ ቀጥሎ የተቀመጡት ለሃይል ፕሮጀክት የሚያስፈልጉ ተያያዥ የፕሮጀክት ስምምነቶች ናቸው፡፡

- **የፍቃደኝነት/ከዋኔ ስምምነት:** ይሄ ለሃይል አመንጪው ማመንጫውን የመስራት፣ ፋይናንስ የማድረግ፣የመገንባት እና የማስተዳደር መብት እንዲሁም የመነጨውን ኃይል ለተረካቢ ገዥ የማቅረብ መብት ይሰጣል፡፡
- **ከሃይል ፍርግርጉ ጋር ለመገናኘት የሚደረግ ስምምነት:** ኃይል ማመንጫው ከሃይል ፍርግርጉ ጋር እንዴት እንደሚገናኝ የሚዳኝ ስምምነት ነው፡፡
- የነዳጅ አቅርቦት ስምምነት/የጅምላ አቅርቦት ስምምነት፡ የነዳጅ አቅርቦት እና ጥራት መኖሩን
  ለማግኘት የሚደረግ ስምምነት ነው፡፡
- **የነዳጅ ማጓጓዣ ስምምነት:** ነዳጅ ከአቅራቢው ወደ ሃይል ማመንጫው ለማጓጓዝ የሚደረግ ስምምነት ነው፡፡
- **የምህንድስና፣ የግዥ እና የግንባታ ስምምነት (ኢፒሲ ስምምነት):** ለሃይል ማመንጫው ንድፍ፣ ለማቴሪያሎቹ እና እቃ ግዥ፣ እንዲሁም ለግንባታ የሚያስፈልጉትን ዝርዝር ሁኔታዎች እና ግዴታዎች ያስቀምጣል። የምህንድስና ግዥ እና ግንባታ ሃላፊነቶች ተበታትነው በተለያየ ውል ሲሸፈኑ ከላይ የተጠቀሱ ሃላፊነቶችም በየውሉ ሊከፋፈሉ ይችላሉ፡፡

- **የማስተዳደሪያና የእድሳት ስምምነት (ኦ ኤንድ ኤም):** ማመንጫውን የሚያስተዳድረው እና ለእድሳቱም ሃላፊነት የሚኖርበት ተቋምን መብት የሚያስቀምጥ ስምምነት ነው፡፡
- **የረዥም ግዜ የአገልግሎት ስምምነት (ኤል.ቲ. ኤስ. ኤ):** የኃይል ግዥ ስምምነቱ ስራ ላይ በሚውለበት ግዜ ለማመንጫው የሰርቪስ አገልግሎት የሚሰጥ
- **የብድር ስምምነት፡** የኃይል ማመንጫውን ወጪ ለመሸፈን አበዳሪው ለአመንጪው አካል ገንዘብ እንዲያበድረው ኃላፊነት የሚጥልበት ስምምነት ነው፡፡
- **የካፒታል/ወረት/ መዋጮ ስምምነት፡** የኃይል ማመንጫ ባለቤቶቹ በሶስተኛ ወገን አበዳሪ የማይሸፈነውን የሚመንጫ ወጪ ካላቸው ካፒታል ወይም ሌሎች እዳዎች ከተከፈሉ በኋላ የሚከፈል እዳ ብድር እንዲሸፍኑ የሚያደርግ ስምምነት ነው፡፡.
- **የመንግስት /ሉአላዊ ተቋም/ ድጋፍ ስምምነት፡** ተረካቢው ገዥ እና ሌሎች በፕሮጀክቱ ውስጥ የሚሳተፉ የመንግስት ተቋማት ብድርን በአግባቡ ለመጠቀም ብቁ እንደሆኑ ለማመላከት መንግሰት ተያዥ የሚሆንበትን በኦዲተሮች የተጻፈ ብቁነታቸውን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ፤ አክስዮን የመሸጥ እነ የመግዛት አማራጮች፤ እና ሌሎችንም የሶስተኛ ወገን/ የመንግስት ድጋፎችን ያጠቃልላል፡፡
- **ብድር ላይ የድጋፍ ስምምነት፡** ከፊል የሆነ የእዳ ሃላፊነትን ለመወጣት የሚደረግ ድጋፍ፤ የባንክ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ወይም ኤስክሮው ስምምነቶች እና የስፖንሰር ድጋፍ ስምምነቶች ነው፡፡
- **ቀጥተኛ ስምምነት፡** በአበዳሪዎቹ እና ተበዳሪ ወገኖች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚስተዳድር ነው፡፡




# የሃይል ግዥ ስምምነት ኃላፊነቶች አጠቃላይ አይታ

በሃይል ግዥ ስምምነት ውስጥ የገዥው ዋነኛ ሃላፊነት የተስማሙበትን ታሪፍ መክፈል በሚገባው ግዜ ገደብ ውስጥ መክፈል መቻል ነው፡፡ የሻጩ ወገን ዋነኛ ሃላፊነት ደግሞ ስምምነቱ እና የሚመለከተው ህግ በሚያዘው አግባብ መሠረት የሃይል ማመንጫውን መገንባት ማስተዳደር እና ማደስ፤ከዚያም የተፈለገውን መጠን ያህል ሃይል ማቅረብ ይሆናል፡፡ነገር ግን የወገኖቹ ኃላፊነቶች እዚህ ላይ የሚያቆሙ አይደሉም፡፡

ተጨማሪ ኃላፊነቶች በቀዳሚነት (1) ግዥ እና የአፈጻጸም አስተማማኝነትን የተመለከቱ (2)የኃይል ማስተላለፍ እና ከሃይል ፍርግርጉ ጋር መገናኘትን የተመለከቱ (3) ከአበዳሪዎች ጋር የሚኖረውን አሰራር የተመለከቱ (4) የተለያዩ ፍቃዶችን የተመለከቱ (5) የሃይል

ማመንጫው/ማስተላለፊያው የሚያርፍበትን ቦታ የመጠቀም መብትን የተመለከቱ (6) የመድን ዋስትናን የተመለከቱ ይሆናሉ፡፡

TH

በአብዛኛው እነዚህ ሃላፊነቶች በአንድ ተዋዋይ ወገን ትከሻ ላይ የሚያርፉ ሳይሆኑ፤ በዙ ወገኖች የሚጋሩት እና ሃይል ማመንጫው ያለበትን ሁኔታ እና ያረፈበት ቦታ ላይ በመመርኮዝ ከአንድ ወገን ወደሌላ ወገን የሚቀያየሩ ናቸው::

| | ገዢ | ሻጭ |
|---|---|---|
| ቀዳሚ/ዋና/ ኃላፊነቶች | ክፍያን መፈጸም | የሃይል ማመንጫን መገንባት እና ማስተዳደር |
| አስተማማኝነት | የክፍያ አስተማማኝነት | የአፈጻጸም አስተማማኝነት |
| ሃይል ማስተላለፍ/ማገነኘት | ማስተላለፍ/ማገናኘት (የታጨቀ/ያልተከፋፈለ እና አንድ አንዳንድ ያልተከፋፈለ) | ማስተላለፍ/ማገናኘት (አንዳንድ ያልተከፋፈሉ) |
| ከአበዳሪዎች ጋር ያለ ስምምነት | ቀጥተኛ ስምምነት | የገንዘብ አቅርቦት |
| ፍቃዶች | ከፍቃዶች ጋር በተገናኘ እርዳታን ማቅረብ/በገዥው ወገን | ፈቃዶችን ማግኘት |
| መሬት | መጠቀሚያ ቦታን ማቅረብ/ መሬት እንዲያገኙ እርዳታ | መሬት ማግኘት |
| የመድን ዋስትና | ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ሲፈጠሩ፤ ፤የፕሮጀክት መመገታት | ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ሲፈጠሩ እና ብርን ወዘተ.... |
| ከአካባቢው የሚገኙ ነገሮች | - | ጉልበት፤ ማቴሪያል እና ማሽነሪ |
| ስራ መጨረስ/የአገልግሎት ዘመን ማብቂያ | - | ስራውን መጨረስ እና ማመንጫው የአገልግሎት |

# ጊዜን በተመለከተ ታሳቢ መደረግ ያለባቸው ነገሮች

የሃይል ግዥ ስምምነቱ በአብዛኛው ግዜን በተለመለከተ ለአመንጪውም ሆነ ለተረካቢ ገዥው ብዙ ሃላፊነቶችን ያስቀምጣል፡፡ ሁለቱም ወገኖች እነዚህን ድንጋጌዎች ልብ ሊሉ እና ከተቀመጠላቸው ሃላፊነት ጋር ምቾት ሊሰማቸው እንዲሁም በሰአቱ አለማድረስ የሚያመጣውን ሰበብ ሊያስተውሉ ይገባል፡፡

እነዚህ ከግዜ ጋር የተያያዙ ሃላፊነቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- የኃይል ማመንጫ ስምምነቱ ስራ ላይ  የሚውልበት ግዜ
- የብድር እና የፕሮጀክት ስምምነት ቅድመሁኔታዎችን የመጨረስ አና ስምምነቱ ውስጥ ያሉትን
- ድንጋጌዎች የማሟላት ቀነገደብ
- የንግድ እንቅስቃሴ ከመጀመሩ በፊት የሀይል ማመንጫውን ብቃት የመፈተሻ ቀነገደብ
- ከሃይል ፍርግርጉ ጋር ለማገናኘት የሚያስፈልጉትን እና ሌሎች ተዛማጅ ተቋማትን ሠርቶ ማጠናቀቅ
- የነዳጅ አቅርቦት መጀመሪያ ቀነቀደብ
- የፕሮፎርማ /ኢንቮይስ/ የማስገቢያ እና የመክፈያ ቀነገደብ
- አቅምን ለመፈተሸ የተቀመጠ ቀነገደብ
- ለተለያዩ ደንብ መተላለፎች ማስተካከያ ቀነገደብ
- ውል እንዲቋረጥ ማመልከቻ የማስገቢያ ቀነገደብ
- የግጭት መፍቻ ቀነገደብ

የተቀመጡት ቀነገደቦች ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ከሃይል ፍርግርጉ ጋር የማገናኘት እና የነዳጅ አቅርቦት መጀመሪያ ቀን ወደ ንግድ እንቅስቃሴ ለመግባት ከተቀመጠቀው ግዜ ገደብ በፊት መሆን አለበት፡፡

# ለሃይል ማመንጫዎች የሚኖር የገንዘብ አቅርቦት

## የገንዘብ አቅርቦት መስህብ (ባንከቢሊቲ)

**የገንዘብ አቅርቦት መስህብ** (ባንከቢሊቲ) አንድ ፕሮጀክት በአበዳሪዎች ዘንድ ያለውን ተቀባይነት እና በብድር ገበያው ውስጥ የገንዘብ አቅርቦትን እያሰሰ ያለው ፕሮጀክት የሸፋን አድማስን ያመላክታል፡፡ ነገር ግን አንድ ፕሮጀክት ከንግድ ባንኮች በተጨማሪ ከልማት ፋይናንስ ተቋማት እና የግል ፋይናንሲንግም (ፕራይቬት ኤኩዊቲ) ጭምር የገንዘብ አቅረቦት ሊያገኝ ይችላል፡፡

በመሆኑም የገንዘብ አቅርቦት መስህብ ማለት ከአንድ ምንጭ ብቻ ሳይሆን ከማንኛውም ምንጭ ብድርን የመሳብ አቅም ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል፡፡

### የሃይል ግዥ ስምምነቱ ለገንዘብ አቅርቦት መስህብነት የሚጫወተው ሚና

የሃይል ግዥ ስምምነቱ ለገንዘብ አቅርቦት መስህብነት ቁልፍ ነው፡፡ ለአንድ አይነተኛ የሃይል ፕሮጀክት አንድ የገቢ ምንጭ ብቻ ነው ያለው- በሃይል ግዥ ስምምነቱ መሰረት ከገዥው የሚመጣ ክፍያ፡፡ ገዥው መክፈል ካልቻለ ፕሮጀክቱ አበዳሪዎቹን ለመክፈል አዳጋች ነው የሚሆንበት፡፡

የሃይል ግዥ ስምምነቱ የሃይል ፕሮጀክቶችን ልዩ መልክ ለማስተናገድም እገዛ ይኖረዋል፡፡ የሃይል ማመንጨትን ልዩ የሚያደርገው በክልል ውሱን የሆና እና ቁጥጥር የበዛበት መሆኑ ነው፡፡ ከቦታ ቦታ መጓጓዝ ከሚችሉ እንደ ሃይድሮካርቦን፤ሚነራል እና ሌሎች ውድ ብረታብረቶች በተለየ፤ ከሚያገለግለው ገበያ ጋር በቅርብ መቆራኘት አለበት፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚዎች ላይ የሚጣለው የዋጋ ተመን የሚወሰነው በገበያው ሳይሆን በተቆጣጣሪ አካል ነው፡፡ በመሆኑም የሃይል ግዥ ስምምነቱ በዋጋ እና በፍላጎት ላይ ያለውን አለመረጋጋት ለመፍታት ስለሚሞክር በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በፍላጎት ደረጃ የሃይል ግዥ ስምምነቱ የረዥም ዘመን የመግዛት ሃላፊነትን ስለሚያስቀምጥ ለአመንጪው የማይቋረጥ የገቢ ምንጭ ለተረካቢው ገዥ ደግሞ የማይቋረጥ የኤሌክትሪክ አቅርቦትን ይሰጣል፡፡ ከዋጋው አንጻር ደግሞ የሃይል ግዥ ስምምነቱ ለፕሮጀክቱ የቴክኖሎጂ እና የእዳ አይነት የሚስማማ የዋጋ ተመን ቀመር ስለሚኖረው፤ እስከ ፕሮጀክቱ ማብቂያ ዘመን ድረስ ይሄንን እንደ ሞዴል መጠቀም ይቻላል፡፡ ይሄ ደግሞ የሃይል ግዥ ስምምነቱ ሃይል ለማመንጨት የሚያስፈልገውን እውነተኛ ወጪ የሚያንጸባርቅ የዋጋ ተመን እንዲያቋቁም ይረዳዋል፡፡

## የገንዘብ አቅርቦት መስህብነት ላይ ሊኖሩ የሚችሉ ስጋቶች

በሃይል ፕሮጀክት ገንዘብ አቅርቦት ላይ፤ ለአበዳሪዎች ሊኖር የሚችለው ጥቅም ያበደሩት ገንዘብ ከነወለዱ እና ሌሎች ስምምነት ላይ የተደረሱባቸውን ክፍያዎች ሲከፈሏቸው ነው፡፡ ነገር ግን የእዳ አቅራቢዎች ቋሚ ንብረት ላይ ግዙፍ ወጪ ስለሚያደርጉ እና ክፍያቸው ደግሞ ፕሮጀክቱ በሚያመጣው ገቢ ብቻ የተወሰነ ስለሆነ የፕሮጀክቱ ሰነዶች እና ስፖንሰሮች ጥንካሬ ወደ ንግድ ሊያስገባ የሚችል እንዲሆን ውትወታ ያደርጋሉ፡፡ ለክ እንደሌሎቹ ተዋዋይ ወገኖች፤ አበዳሪዎችም ፕሮጀክቱ ሙሉ ለሙሉ ሳይሳካ ቀርቶ (በተለይም ገና በግንባታው ምእራፍ ላይ እያለ) ሊፈጠር የሚችለውን አስጊ ሁኔታ መቀነስ ይፈልጋሉ፡፡ ስራ በሚጀምርበት ወቅት ደግሞ ዋነኛ የሚያሳስበቸው ነገር ገቢው እዳን ለመሸፈን በቂ ነው አይደለም የሚለው ጉዳይ ነው፡፡

ከታች የተዘረዘሩት የገንዘብ አቅርቦትን ለማግነት ታሳቢ መደረግ ያለባቸው ነገሮች ናቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች በደንብ ሽፋኑ ካላገኙ ፕሮጀክቱ የገንዘብ አቅርቦት የማግኘት እድሉ አነስተኛ ነው፡፡

**የአገልግሎት ዘመን:** የሃይል ግዥ ስምምነቱ የአገልግሎት ግዜ ርዝማኔ እዳው ተከፍሎ እስኪያልቅ የሚያቆይ መሆን አለበት፡፡ እዳው በሰአቱ ተከፍሎ የማያልቅ ከሆነ (ከወለድ ውጪ ዋናው እዳ በመከፈያው ግዜ ተሸፍኖ የማያልቅ ከሆነ የሃይል ግዥ ስምምነቱ ቀሪውን እዳ በሌላ የገንዘብ አቅርቦት መሸፈን እስከሚችልበት ግዜ ፤ ቆይታ ሊኖረው ይገባል፡፡

- **የዋጋ ተመን: አበዳሪዎች** በሃይል ግዥ ስምምነቱ ስር የሚከፈለው ተመን ላይ እርግጠኝነት መኖሩን ማየት ይፈልጋሉ፡፡

- **በህግ እና በታክስ ሊኖሩ** የሚችሉ ለውጦች: በፕሮጀክቱ የቆይታ ግዜ ውስጥ ለሚመጡ የህግም ሆነ የታክስ ለውጦችን ተከትሎ የሚመጣ ስጋት አበዳሪዎች አያስተናግዱም፡፡

- **የተረካቢ ገዥ ለብድር ብቁ መሆን፡**ተረካቢው ገዥ ከዚህ በፊት ከእዳ መክፈል ጋር ያለው ልምድ ብቁ ካልሆነ አበዳሪዎቹ ሌሎች ተጨማሪ ወጪ ያላቸው እና ውስብስብ የሆኑ ጥቅል የብድር ድጋፎች እንዲኖር ይፈልጋሉ፡፡ በአደጉ ገበያዎችም ጭምር አበዛኛውን ግዜ ተረካቢ ገዥዎች የገንዘብ አቅርቦት ማምጣት የሚችል ፕሮጀክት ለመቅረጽ በቂ እዳ የመክፈል ልምድ የላቸውም፡፡የስፖንሰሮች ጥራት: አበዳሪውም ሆነ ተረካቢው ገዥ የባለቤቶቹን ልምድ፤ ዝና (በፊት የሚኖረው ስም)፤እና ጥንካሬ ታሳቢ ያደርጋሉ፡፡

- የስፖንሰሮች ጥራት: አበዳሪውም ሆነ ተረካቢው ገዥ የባለቤቶቹን ልምድ፤ ዝና (በፊት የሚኖረው ስም)፤እና ጥንካሬ ታሳቢ ያደርጋሉ፡፡

- **ደረሰኝ እና ክፍያ:** ብዙ ያልተከፈለበት የሃይል አቅርቦት እንዳይኖር እና እዳውም በግዜው እንዲከፈል ለማስቻል፤ ተረካቢው ገዥ ለአመንጪው የሚከፍልበት ግዜ ተቀራራቢ (በየወሩ ወይም በየ ሁለት ሳምንቱ) መሆን አለበት፡፡እንዲህ ተቀራራቢ በሚሆንበት ግዜ አበዳሪዎች የክፍያ ወይም የብር አቅርቦት ችግር ሲኖር በቶሎ እንዲያውቁ ይረዳቸዋል፡፡

- **የገንዘብ ምንዛሬ/ስሌት:** የሃይል ግዥ ስምምነት ክፍያ እና ስሌት ብዙ ግዜ እዳን ለመክፈል በሚያስፈልገው የገንዘብ ምንዛሬ ነው የሚተመኑት፡፡ እንዲህ ካልሆነ የውጪ ምንዛሬ መዋዠቅ ሊያመጣው የሚችለውን ስጋት የሚያስቀር ዘዴ እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ ልዩነቶችን ከግምት ውስጥ የሚያስገባ የተመን ቀመር ስምምነቱ ውስጥ ሊኖር ይገባል፡፡ በዛ ላይ ጥቅም ላይ የሚውለው የገንዘብ ምንዛሬ አስተማማኝነት የሚያጠራጥር ከሆነ አበዳሪዎቹ በውጪ ምንዛሬ እንዲከፈላቸው ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ እንደዚህ ካልሆነ ደግሞ ተረካቢው ገዥ ወይም መንግስት ተገቢው ምንዛሬ ተለውጦ እንደሚከፈል ዋስተና መስጠት አለባቸው፡፡

- **ማብቂያ ግዜ:** አበዳሪዎች ተረካቢው ገዥ የረዥም ግዜ የግዥ ሃላፊነቶቹን ማምለጥ እንዲችል አይፈልጉም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ፕሮጀክቱ ያለገቢ ቀርቶ እዳን መክፈል ሳይችል እንዳይቀር ነው፡፡ ሻጩ እዳውን በሚዘልበት እና ከአቅም በላይ የሆኑ አደጋዎች በሚፈጠሩበት ወቅት ገዥው ፕሮጀክቱን እንዳያቋርጥ ትኩረት ማድረግ አለባቸው፡፡ ፕሮጀክቱን የሚያቋርጥበት ሁኔታ ቢኖር እንኳን ብድራቸውን እንደሚከፈል ማረጋገጥ ይፈልጋሉ፡፡

- **በገዢው በኩል ብድር መክፈል ካልተቻለ ሊኖር የሚገባው ማስተካከያ:** ተረካቢው ገዥ ገንዘብ መክፈል ካቃተው ወይም ክፍያውን እንደሚፈጽም ማስተማመኛ ካልሰጠ አበዳሪው ፕሮጀክቱን የማቋረጥ መብት ያለው መሆኑን እና ይሄንንም መብት መጠቀም መቻሉን አበዳሪዎች ማረጋገጥ ይፈልጋሉ፡፡

- **የአበዳሪ መብት:** በሚያበድሩት ገንዘብ እና ቀጥተኛ ስምምነቶች መሰረት የፕሮጀክቱን ቋሚ ንብረቶች ተያዥ ለማድረግ በፕሮጀክቱ እጃቸውን የማስገባት/የመሳተፍ/ መብታቸው በስምምነቱ እንዲደነገግ ይፈልጋሉ፡፡


- **በገዢው በኩል ብድር መክፈል ካልተቻለ ሊኖር የሚገባው ማስተካከያ:** ተረካቢው ገዥ ገንዘብ መክፈል ካቃተው ወይም ክፍያውን እንደሚፈጽም ማስተማመኛ ካልሰጠ አበዳሪው ፕሮጀክቱን የማቋረጥ መብት ያለው መሆኑን እና ይሄንንም መብት መጠቀም መቻሉን አበዳሪዎች ማረጋገጥ ይፈልጋሉ፡፡

- **የአበዳሪ መብት:** በሚያበድሩት ገንዘብ እና ቀጥተኛ ስምምነቶች መሰረት የፕሮጀክቱን ቋሚ ንብረቶች ተያዥ ለማድረግ በፕሮጀክቱ እጃቸውን የማስገባት/የመሳተፍ/ መብታቸው በስምምነቱ እንዲደነገግ ይፈልጋሉ፡፡


ከላይ የተዘረዘሩት ነገሮች ጠቃሚ መመሪያ ሊሰጡ ቢችሉም የገንዘብ አቅርቦት መስህብነት በየጊዜው የሚለዋወጥ ሃሳብ ነው፡፡ የብድር ገበያው ዛሬ የሚጠይቀው(የሚቀበለው) ነገር ነገ (ከሚጠይቀው) ከሚቀበለው ነገር ጋር ሊለያይ ይችላል፡፡፡ የሃይል ፕሮጀክቶች የሚጠቀሙበትን ቴክኖሎጂ፤ ያላቸውን መጠን፤ ስፋት፤ ይዘት እና የሚገነቡበትን ቦታ በመመልከት ገበያው የሚፈልገው ምንድነው (አብዛኛውን ግዜ የገበያ ተሳታፊዎች በተለምዶ የሚቀበሏቸው ነገሮች ስናስብ ማለት ነው)የሚለውን ነገር በእርግጠኝነት ለመናገር አስቸጋሪ ነው፡፡ ከዛም በላይ ደግሞ አንዳንድ የሃይል ፕሮጀክትላይ ልምድ ያላቸው ሰዎች የፕሮጀክት ድርጅቱን የሚጠቅሙ ድንጋጌዎች (ዝርዝር ሁኔታዎች) ያሉበትን ስምምነት አበዳሪው እንዲያጸድቅ ማግባባት ይችላሉ፡፡ በሌላ መልኩ ደግሞ አበዳሪዎች ስጋቶችን ለመሸፈን ተያዥ ወይም ሌላ የብድር ዋስትና (ከስፖንሰር ወይም ከተረካቢው ገዥ) እስካገኙ ድረስ በፕሮጀክት ደረጃ የተቀመጡ ልዩ ሁኔታዎችን እና

ስጋቶችን ለመቀበል ፍቃደኛ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በመጨረሻም አንዳንድ የሃይል ገበያዎች ፤በተለይም በበለጸጉ ሃገራት፤ በጣም የዳበሩ እና አሰራራቸውም የሚታወቅ ስለሆነ ፕሮጀክቱ የገንዘብ አቅርቦት መስህብ እንዲኖረው የሃይል ግዥ ስምምነት መኖር እራሱ አስፈላጊ ላይሆን ይችላል፡፡ በተለይም ደግሞ ያለ ቅድመ ስምምነት ሃይል ለመገበያየት በቂ ፍላጎት እንዳለ ገለልተኛ ወገን እስካረጋገጠ ድረስ አንድ ቋሚ ገዥ ሳይኖራቸው ማንኛውም ገዥ ሲመጣ እንዲገዛ ለሽቀጥ የቀረቡ ማመንጫ/መቻንት ፖወርፕላንት/ ፕሮጀክቶች ሊነደፉ ይችላሉ፡፡ አንዴ ፕሮጀክቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ማመንጫው ሃይል ለገበያው ማቅረብ ይችላል፡፡ ነገር ግን በበለጸጉ ሃገራትም ቢሆን የረዥም ግዜ የሃይል ግዥ ስምምነት አለመኖር ፕሮጀክቱን ለከፍተኛ የወለድ ተመን ሊያጋልጠው ይችላል፡፡ ስለዚህ በተለመደው መንገድ የገንዘብ አቅርቦት የሚስብ የሃይል ግዥ ስምምነት በማንኛውም ቦታ በተለይም ደግሞ በታዳጊ ሃገራት የሃይል ገበያዎች ውስጥ ተመራጭ ነው፡፡

## የገንዘብ አቅርቦት መስህብነት ሊያሳስበን የሚገባው ለምንድነው?


ለምን የሃይል ግዥ ፕሮጀክቶች ብድር ያስፈልጋቸዋል? ወጪው ለምን በትላልቅ የንግድ ስፖንሰሮች አይሸፈንም? ለምን መንግስት እነዚህን ፕሮጀክቶች በራሱ አይገነባም? ፕሮጀክት ነድፎ፣ ገንብቶ የሃይል ግዥ ስምምነት ላይ መደራደር በራሱ ከባድ ነገር ነው፡፡ ታዲያ በዚህ ላይ ደግሞ አበዳሪዎችን ለማስደሰት መጨናነቅ ለምን ያስፈልጋል? የገንዘብ አቅርቦት መስህብ ሊያሳስበን የሚገባው ለምንድነው? ከላይ የተጠቀሱት እና መሰል ጥያቄዎች ፖሊሲ ቀራጭ አካላት ላይ ሊጫሩ ይችላሉ፡፡

አንድ እርምጃ ወደኋላ ራቅ ብለን ስናስበው አንድ የሃይል ማመንጫ ሊነረው የሚችለው ግብ አስተማማኝ ሃይል በተቻለ መጠን ዝቅ ባለ ዋጋ ማቅረበ መቻሉ ነው፡፡ ብድር፤ በተለይም ደግሞ ለፕሮጀክት ተብሎ የሚሰጥ ብድር ደግሞ፤ ውድ ነው፡፡ ነገር ግን ሌሎች የገንዘብ አቅርቦት ምንጮች ደግሞ የበለጠ ውድ ወይም በተለያየ ምክንያት ስራ የማያሰሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ መንግስት የሃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን አብዛኛውን ግዜ አያደርጉትም፡፡ ምክንያቱም የሃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች በጣም ውድ እና ሌላ ቦታ ሊውል የሚችል ግዙፍ ካፒታልን ለረዥም ግዜ አስረው የሚያስቀምጡ ናቸው፡፡

መንግስት ከልማታዊ የፋናንስ ተቋማት የገንዘብ አቅርቦት ሊያገኝ ይችላል፡፡ ነገር ግን መንግስትከነዚህ ተቋማት የሚገኝን ገንዘብ በጥንቃቄ መመበደብ መቻል አለበት፡፡ በተጨማሪም ከእነዚህ ተቋማት ገንዘብ ማግኘት መቻሉ አበዳሪዎችን ምቾት እንዲሰማቸው ለማድረግ የሚኖረውን ጥረት አያስቀረውም።

ፕሮጀክቶች በሚሰሯቸው ትላልቅ ድርጅቶች ወጪም ሊሸፈኑ ይችላሉ። ነገር ግን በዚህ መልኩ ሲሰራ አብዛኛውን ግዜ የመንግስት አካላት ብዙም ወጪን እንደማይቀንስ ቶሎ ይረዳሉ። ይህ ለምን ይሆናል? ትላልቅ ድርጅቶች በትንሽ ወለድ (በተለይም ከፕሮጀክት ፋይናንሲግ ይልቅ እጅግ ባነሰ ወለድ) ከካፒታል ገበያው ብድር የማግኘት እድላቸው ሰፊ ነው። በዚህም ምክንያት ፕሮጀክቱ ላይ ወጪ መቆጠብ ይችላሉ፤ ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ አዎ አንዳንድ የፕሮጀክት ድርጅቶች ከካርታል ገበያው ወጪ ያልበዛበት ብድር ሊወስዱ ይችላሉ፤ ነገር ግን ስራ አስኪያጆቻቸው እና(ገንዘብ ያዥ ክፍላቸው) ማንኛውንም የኢንቨስትመንት ውሳኔ ሲወስኑ በእጅ ያለውን ገንዘብ ጠቅላላ እንደ ወረት/ኤክዊቲ/ ስለሚያስቡት እና ከኤክዊቲ ደግሞ ብዙ የትርፍ መጠን ስለሚጠበቅ፤ የሚያገኙት/የቆጠቡት/መጠን እንደጠበቁት ሳይሆን ይቀራል። የሚከተሉት ሁለት ስእሎች ለገንዘብ አቅርቦት ያሉትን ሁለት አይነተኛ አማራጮች ለማሳየት ይሞክራል



ከላይ እንደሚታየው ከሆነ ጥቂት ካፒታል ፕሮጀክቱ ውስጥ በኖረ መጠን ለፋይናንሲንግ የሚያስፈልገው ወጪም ይቀንሳል፡፡ የሚያመጣው ወጪ መጠን ፕሮጀክቱ የሚፈልገው የገንዘብ አቅርቦት ውስጥ በብድር ድርሻው መጠን ይለየያል፡፡ (እያንዳንዱ የብድር ድጋፍ ተጨማሪ ወጪ የሚያወጣ ነው፡፡) ወረቱ (ኤክዊቲ) በሚፈልገው የአክስዮን ትርፍ መጠን እና የብድሩ ወለድ መጠንም ወጪው ላይ ልዩነት ያመጣል፡፡

ምንም እንኳ ትላልቅ ድርጅቶች በአነስተኛ ወጪ ከካፒታላቸው ለፕሮጀክቱ ገንዘብ ማቅረብ ቢችሉ እንኳን ከሂሳብ መዝገባቸው ውጪ ያለ የገንዘብ አቅርቦት ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ይሄንንም የሚያደርጉት ብድሩ ሂሳብ መዝገባቸው ውስጥ እንዲታይ ሳይፈልጉ ሲቀሩ ነው፡፡አንዳንዴ አበዳሪዎችም ቢሆኑ ለተወሰነ ኣላማ ብቻ ከዋና ድርጅቱ ተገንጥለው የተቋቋሙ ኤስ.ፒ.ቪዎችን ማበደር ይፈልጋሉ፡፡ ምክንያቱም ደግሞ እንደዚህ አይነት ድርጅቶች ከዋና ድርጅቱ በተለየ ሃላፊነት ስላለባቸው ሌላ ብድር ላይኖርባቸው ይችላል፡፡

ቀለል ባለ መልኩ ስናየው የገንዘብ አቅርቦት መስህብ አስፈላጊ የሆነው ፕሮጀክቱ በውጪ የገንዘብ አቅርቦት ሲሰራ በአጠቃላይ ወጪ ስለሚቆጥብ ነው፡፡

# የፕሮጀክት የገንዘብ አቅርቦት እና የድርጅት የገንዘብ አቅርቦት በአጠቃላይ ሲታይ

**ፕሮጀክት የገንዘብ አቅርቦት** ማለት ለአንድ ፕሮጀክት (1) ለወደፊቱ ያመጣል ተብሎ በሚገመተው የገቢ ፍሰት እና (2) የቋሚ ንብረቶቹ ዋጋ ላይ በመመርኮዝ ብድር ሲቀርብ ማለት ነው፡፡ ለፕሮጀክት የሚቀርብ ገንዘብ ብዙ ግዜ ተበዳሪዎቹ የፕሮጀክት ባለቤቶች ላይ የመክፈል ሃላፊነት አይጥልም፡፡ አበዳሪዎቹ ፕሮጀክቱ ከሚያስገባው ገቢ፤ ወይም ደግሞ አያድርስና ብድር በሰአቱ ካልተከፈለ ፕሮጀክቱ ውስጥ ያሉ ቋሚ ንብረቶችን በመውረስ ገንዘባቸውን ያገኛሉ እንጂ ባለቤቶቹን ገንዘብ እንዲያመጡ ማስገደድ አይችልም፡፡

ብዙ ግዜ በፕሮጀክት የገንዘብ አቅርቦት ውስጥ የፕሮጀክቱን ቋሚ ንብረቶች በባለቤትነት የሚይዝ እና የሃይል ግዥ ስምምነቶችን፤ የፋይናንሲንግ እና ፕሮጀክት ስምምነቶችን የሚፈጽም ለዚሁ አላማ የተቋቋመ ልዩ ድርጅት ይመሰረታል፡፡

አበዳሪዎቹ የፕሮጀክቱ የባንክ ሂሳቦች እና እዛ ውስጥ ያለ ተቀማጭ ወይም የብድር ገንዘብ ላይም ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡

አበዳሪዎች ሁሉም የፕሮጀክት ሂሳቦች እና በእነዚህ ሂሳቦች ውስጥ ያለው የገንዘብ ፍሰት ላይ ጥብቅ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያስቀምጡ ይችላሉ፡፡ በተለይም ደግሞ የፕሮጀክት ድርጅቱ እስከተወሰነ አመት ድረስ ምንም አይነት የትርፍ ክፍፍል ወይም የገንዘብ ክፍፍል እንዳያደርግ ሊያግዱት ይችላሉ፡፡ አሁን ያለው አሰራር ሲታይ አብዛኛው የሃይል ፕሮጀክቶች ብድርን የመመለስ ሂደት ባለቤቶቹን እንዳይነካ ገደብ ተጥሎበት የገንዘብ አቅርቦት የሚያገኙ ናቸው፡፡ በመሆኑም አበዳሪዎች ገንዘብ የማስመለስ አማራጫቸው ስለተገደበ ብዙ የድጋፍ ሰነዶች በተለይም ደግሞ ሰፖንሰሮች እና ተያዦች/ጋራንተርስ) ይፈልጋሉ፡፡

አበዳሪዎች ገንዘባቸውን ለማስመለስ ባላቸው ፍላጎት ምክንያት እና ፕሮጀክቱ ውስጥ በሚደረሱ ውሳኔዎች በተለይም ደግሞ በገንዘብ ፍሰት፤ ቋሚ ንብረት ላይ መዋዕለ ነዋይ ለማፍሰስ በሚደረግ ውሳኔዎች ላይ በሚኖራቸው ከፍተኛ ተሳትፎ /ጣልቃ ገብነት/ ምክንያት የፕሮጀክት የገንዘብ ስምምነት በጣም በዝርዝር የተቀመጡ እና በተለየ መልኩ በጥንቃቄ የተዘጋጁ ውስብስብ ስምምነቶች ላይ መድረስን ይጠይቃል፡፡ ይህ ደግሞ የህግ አማካሪ

እነዚህ አይነቶቹን ስምምነቶች እንዲያረቅ እና እንዲያደራድር የሚከፈለውን ወጪ ጨምሮ ብዙ ለብዙ የግብይት ወጪ/ተራንዝአክሽን ኮስት/ ይዳርጋል፡፡

በአንጻሩ ለድርጅት የሚሰጥ የኮርፖሬት የገንዘብ አቅርቦት ገንዘብ በሚቀበለው ተቋም የሂሳብ መያዣ ሰነድ ላይ ይመረኮዛል፡፡ አበዳሪዎች ተቋሙ ውስጥ ያሉት ማንኛውም ቋሚ ንብረቶችን በመውረስ ብድር ማስመለስ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ምንም አይነት ቋሚ ንብረቶቹ ላይ ምንም አይነት security interest የላቸውም፡፡ የገንዘብ ፍሰቱ ላይ ምንም አይነት ገደብ አይጣልበትም፡፡ የስምምነት ሰነዶቹም በጣም ቀላል/ያልተወሳሰቡ ናቸው፡፡

ገንዘብን ከፕሮጀክት የገንዘብ አቅርት ከማግኘት ይልቅ ከድርጅት የገንዘብ አቅርቦት ማግኘት ወጪ ሊቀንስ ይችላል፡፡ ግን የድርጅት የገንዘብ አቅርቦት ብዙ ጊዜ የሚያገኙት ከዚህ በፊት ጥሩ ብድርን የመክፈል ልምድ ያላቸው ተበዳሪዎች ሲኖሩ እና ገንዘብ አቅራቢዎቹ ደግሞ አዎጪ የሆነ ብድሩ ተመልሶ የሚሸጥበት ድህረ ገበያ መኖሩን ሲተማመኑ ነው፡፡ በተለይም የካፒታል ገበያዎች ከግንባታ ጋር ተያይዘው ሊመጡ የሚችሉ የስጋት ሃላፊነቶችን አይቀበሉም፡፡ ከላይ እንደተጠቀሰው አንዳንድ የፕሮጀክት ድርጅቶች በዝቅተኛ ወጪ የካፒታል ማርኬት የገንዘብ አቅርቦት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን ይሄ ዝቅተኛ ወጪ የገንዘብ አቅርቦ ወደ ፕሮጀክቱ ይተላለፋል ብሎ መገመት ያዳግታል፡፡ ምክንያም የፕሮጀክቱ ድርጅት ከወረቱ/ኤክዊቲው/ከፍተኛ የትርፍ መጠን ስለሚጠብቅ ነው፡፡

# ቀጥተኛ ስምምነት

ቀጥተኛ ስምምነት ተረካቢው ገዥ የማመንጫው ፕሮጀክት ድርጅት ለአበዳሪዎቹ የሰጠውን ቋሚ ንብረት ወርሶ ብድር የማስከፈል መብት/security interest/ እንደሚያውቅ በተለይም ደግሞ የፕሮጀክት ድርጅቱን መብቶች እና አበዳሪው ብድሩን ለማስመለስ መውሰድ የሚችለውን እርምጃ በሚመለከት በሃይል ግዥ ስምምነቱ ውስጥ የተቀመጡትን መብቶች የሚያትት ሰነድ ነው፡፡ እነዚህ መብቶች ጣልቃ የመግባት መብቶች ተብለው ይጠራሉ፡፡ቀጥተኛ ስምምነቱ በተረካቢው ገዥ፤ በፕሮጀክት ድርጅቱ፤ በአበዳሪዎች የሚፈረም ሲሆን በተረከቢው ገዥ እና በአበዳሪዎቹ መካከል የተገባውን የውል ስምምነት የሚስቀምጥ ነው፡፡

የገንዘብ አቅርቦት የማግኘት ሃላፊነት የሚወድቀው በፕሮጀክት ድርጅቱ ላይ ቢሆንም፤ ተረካቢው ገዥ በአበዳሪው ጥያቄ መሰረት የሃይል ግዥ ስምምነቱን ማማሻሻል እና ግልጽ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ከተቻለ እንደዚህ አይነት ማሻሻያዎች እና ጉዳዮችን ግልጽ የማድረግ ስራዎች የሚደረጉት የሃይል ግዥ ስምምነቱ በፕሮጀክት ድርጅቱ እና በተረካቢው ገዥ ከመፈረሙ በፊት ነው፡፡ ነገር ግን የሃይል ግዥ ስምምነቱ አስቀድሞ ከተፈረመ በኋላም ተረካቢው ገዥ የሚደረጉ ማሻሻያዎች እና ግልጽ የተደረጉ ነገሮች ላይ እንዲስማማ ይጠበቅታል፡፡ ይሄ ካልተደረገ አበዳሪዎቹ የገንዘብ አቅርቦት ሊከለክሉ ይችላሉ፡፡ የሃይል ግዥ ስምምነቱ አስቀድሞ ከተፈረመ ቅያሪዎች በማሻሻያ መልኩ ወይም በቀጥታ ስምምነት አማካኝነት ወደሃይል ግዥ ስምምነቱ ሊካተቱ ይችላሉ፡፡

# አካባቢያዊና ማህበራዊ ግዴታዎች

የሃይል ማመንጫዎች ለሃይል አቅርቦት አስፈላጊ ናቸው፣ እናም ያስፈልጉናል! ግዙፍ፣ ባለከፍተኛ ድምጽ እና ውስብስብ ኢንደስትሪዎች ናቸው፡፡ በአካባቢው ነዋሪ ላይ የሚያስከትሉት ተፅዕኖ የሚከሰተው በግንባታ (ገወዙፍ መሳሪያዎች መሆናቸው፣ የመንገድ መጨናነቅ፣ ወዘተ. ጨምሮ) እና ሃይል በማመንጨት ስራ ላይ (የድምፅ፣ የአየርና የውሃ ብክለት በማስከተል) ወቅት ይሆናል፡፡ እናም እነዚህን የሚመለከተው አጠቃላይ የአገር ውስጥ ህግ የሚያካትታቸው፣ አስገዳጅም የሚያደርጋቸው በርካታ አካባቢያዊና ማህበራዊ ግዴታዎች አሉ፡፡ በተጨማሪም አበዳሪ አካላት የፕሮጀክት ግንባታው የብድር አካል አድርገውና እንዲከበሩላቸው የሚፈልጓቸው የራሳቸው የሆኑ አካባቢያዊና ማህበራዊ ግዴታዎች ይኖራሉ፡፡ በርካታ የልማት ፋይናንስ ተቋማት የIFC አካባቢያዊና ማህበራዊ የአፈፃጸም ደረጃዎች (http://goo.gl/ pNaCOv ይመልከቱ) እንዲጠበቁላቸው ሲያስገድዱ ሌሎች እንደ የአፍሪካ ልማት ባንክ ያሉት በበኩላቸው የራሳቸው የሆኑ ደረጃዎች አሏቸው (የተቀናጀ የደህንነት ስርዓት - http://goo.gl/hWTO5p ይመልከቱ)፡፡ ከእነዚህም ባሻገር በርካታ የንግድ ባንኮች የኢኳተር መርሆች (the Equator Principles (http://www.equator-principles.com/ ይመልከቱ) ያስገድዳሉ፡፡ በቀላሉ ለማመሳከር አመቺ ይሆኑ ዘንድ እነዚህን መስፈርቶች በዚህ ክፍል "የአበዳሪ መስፈርቶች" በሚል የምንጠቀምባቸው ይሆናል፡፡

# ታሳቢ አካባቢ - ነክ ግዴታዎች

የተለያዩ የሃይል ማመንጫ ኢንደስተሪዎች የተለያዩ አሳሳቢ አካባቢ-ነክ ጉዳዮችን ያስነሳሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በድንጋይ ከሰል የሚሰሩ የሃይል ማመንጫዎች የሰልፈር ዳይኦክሳይድ (sul- fur dioxide)፣ ናይትሮጅን ኦክሳይድና ብናኝ ንጥረ-ነገሮች (nitrogen oxide and dust particles)፣ ወደ አካባቢው የመልቀቅ መጠናቸው እንዲወሰን እንዲሁም የውሃ ብክለት እንዳያስከትሉ ግዴታ ይጣልባቸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫዎች ግንባታ የበርካታ የልማት ተነሺ ነዋሪዎች መፈናቀል፣ የደን ውድመት፣ የአካባቢ ስነ-ምህዳር መቃወስን የሚያስከትሉ የውሃ መጠን መቀነስ እና የውሃ አካላት አቅጣጫ የመቀየር ችግሮችን ሊያስከትሉ ይችላሉ፡፡ ማንኛውም ቴክኖሎጂ አካባቢያዊ ተፅዕኖ ከማስከተል ፈፅሞ የፀዳ አይሆንም፡፡

በአካባቢ ላይ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ ስጋቶችን በሚመለከት ተግባራዊ ምላሽ ለመስጠት ዝግጁ አለመሆን ከአካባቢው መንግሥት ዕገዳ የሚያስከትል ይሆናል፡፡ አካባቢያዊ ግዴታዎችን መወጣት አለመቻል የፋይናንስ ድጋፍ ሊያስከለክሉ ይችላል፡፡

# ታሳቢ ማህበራዊ ግዴታዎች

ከአካባቢያዊ ስጋቶች በተጨማሪ የአገር ውስጥ ህግና የአበዳሪ ተቋማት መስፈርቶች ከማህበራዊ ጉዳዮች ተያያዥ የሆኑ ግዴታዎችን ይጥላሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የአካባቢ ነዋሪዎች የሃይል ማመንጫ ግንባታን አስፈላጊነት የሚቀበሉ ስለመሆናቸው እና ከነዋሪዎች መፈናቀል ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ይገኙባቸዋል፡፡

## የሰራተኛ መብቶች

የአገር ውስጥ ህግና ከላይ የተጠቀሱት የአበዳሪ አካላት መስፈርቶች ሁሉም ከሰራተኛ መብቶች ጋር ተያያዥነት ያሏቸው ግዴታዎችን ያስቀምጣሉ፡፡ እነዚህም ከሰራተኞች አያያዝ፣ በሃይል ማመንጫው መስራት የሚፈቀድላቸው ሰራተኞች ዝቅተኛ የዕድሜ መጠን እንዲሁም የሚከፈላቸው የክፍያ መጠን ከበርካታዎቹ መካከል የሚጠቀሱት ናቸው፡፡

## የአካባቢውን ነዋሪ የሚመለከቱ ጉዳዮች

የኤሌክትሪክ ሃይል ግዢ ስምምነቱ አካል ባይሆኑ ኖሮ ነዋሪዎች በአባቢያቸው የሚተከል የሃይል ማመንጫ ከፍተኛ ስጋት የሚደቀንባቸው ይሆን ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የሁሉም አበዳሪ ተቋማት ግዴታዎች ከሚያካትቷቸው ቅድመ-ሁኔታዎች መካከል የሃይል ማመንጫዎች በአካባቢው የሚያስከትሉት ጉዳት እና የነዋሪዎች አያያዝ ምን ይመስላል፣ የሚሉት ጥያቄዎች በዋናነት ይገኙባቸዋል፡፡ የሃይል ግዢ ስምምነት አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሁለቱም ወገኖች በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ የሚያስከትሉት ስጋት ምን እንደሚመስል በመለየት አስቀድመው ነዋሪውን የማሳመን ስራን መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

## የልማት ተነሺዎች

የሃይል ማመንጫ በመገንባት ሃይል ለማቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአካባቢው ነዋሪዎች ከስፍራቸው ለመነሳት ወይም ወደ ሌላ ተለዋጭ ስፍራ የመዛወር ፍቃዳቸውን ወይም ይሁንታቸውን ማግኘት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ የልማት ተነሺነት ሲባል አካባቢን ለቆ መውጣትና በተለዋጭነት በሚዘጋጅ ስፍራ መስፈርን እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ማጣትን (የቀን ገቢንና ንብረት ማጣት ወይም የኑሮ መሰረት ከሆኑ ጉዳዮች መፈናቀል) ጨምሮ ጥሎ መሄድን ሊያመለክት ይችላል፡፡ ጉዳዩ አስገዳጅ በመሆኑ ምክንያት ነዋሪዎች ከስፍራቸው የሚፈናቀሉበት ሁኔታ ሲከሰት አበዳሪ አካላት ሊቃወሙና የገንዘብ ብድር የማይሰጡበት ሁኔታ ሊከሰት ይችላል፡፡ አስገዳጅ የልማት ተነሺነት ሲባል ነዋሪዎች ፍቃደኛ መሆን አለመሆናቸውን የሚገልፁበት አጋጣሚ ይኖርም ማለት ነው፡፡

## የሥርዓተ-ፆታ-ነክ ጉዳዮች

ለተሻሻለ የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት የሚኖር ተደራሽነት በባህርይው በአካባቢው ነዋሪዎች ላይ የሚያስከትላቸው ሥርዓተ-ፆታ-ነክ ተፅዕኖዎች ይኖራሉ፡፡ የዚህን የሃይል አቅርቦት ተጠቃሚነት ሙሉ በሙሉ ለማሳካት የሃይል ማመንጫው በሚኖርበት አካባቢ በሚኖሩ ዜጎች ውስጥ መታሰብ የሚገባቸው ሥርዓተ-ፆታ-ነክ ስልቶችን እንደ አንድ የአካባቢ ልማት መስፈርት መቀየስ ያስፈልጋል፡፡ ይህም በዘመናዊ የኤሌክትሪክ ምድጃዎች ነዋሪዎች መጠቀም የሚችሉበትን መንገድ ወይም የውሃ መስመር ዝርጋታ የመሳሰሉትን ማመቻቸት ይጨምራል፡፡

# የዋና ነጥቦች ማጠቃለያ

## የሃይል ማመንጫ መሰረተ-ልማት ገፅታ

- ***ሃይል ማመንጨት፡-*** ይህ የኤሌክትሪክ ሃይልን ከበርካታ የኤሌክትሪክ ምንጮች የማግኘት ሂደትን ይመለከታል፡፡ ይህን ሃይል የማስተላለፍ ተግባር ከምንጩ ርቆ ወደ ሚገኘው ተጠቃሚ ከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሃይልን የማጓጓዝ ስርዓት ነው፡፡ ስርጭት ሲባልም ይህን ሃይል ለተጠቃሚዎች ፍጆታ እንዲውል የማከፋፈል ዘዴ ነው፡፡

- **የኤሌክትሪክ ኢንደስተሪ የአወቃቀር ስርዓቶች፡-** ሁለት ዓይነት የኤሌክትሪክ ኢንደስትሪ አወቃቀር ስርዓቶች አሉ፣ እነሱም፡- የቀጥታ (ከምንጩ) እና የተዘዋዋሪ የአቅርቦት ስርዓቶች ናቸው፡፡ በቀጥታ የሃይል ስርጭት ግብይት ስርዓት የሃይል ቁጥጥር የሚደረገው ከምንጩና ከተጠቃሚው መዳረሻ ነው፡፡ በአንፃሩ የተዘዋዋሪ የሃይል ስርጭት ስርዓት ቁጥጥር የሚከናወነው በማስተላለፊያውና በማከፋፈያው ላይ ይሆናል፡፡

- ***ተዋዋዮች ድርሻ፡-*** የሃይል አምራቹ የዚህ አገልግሎት ሻጭና ባለቤት ነው፡፡የሃይል ገዢ አቅራቢው ክፍል ደግሞ ይህን ሃይል ገዝቶ የሚያቀርበው አካል ይሆናል፡፡

## የኤሌክተሪክ ሃይል ግዢ ስምምነት

- ***መሰረት፡-*** የሃይል ግዚ ስምምነት ውል የኮንትራት ውሉ ዋንኛ አካል በመሆኑ የሃይል ሽያጭና ግዢ የሚያስተዳድር አካል ይሆናል፡፡

- **የዕቅድና የማማከር አገልግሎት፡-** የሃይል ግዢ አቅራቢውና አምራቹ አካል የውል ስምምነት በመፈፀም ሁለቱም ወገኖች አውቀውና ፈቅደው ለውል ስምምነቱ ተገዢ የሚሆኑበትን ሁኔታ ይደራደራሉ፡፡ የሃይል ግዚ ስምምነቱ ውስብስብ ሂደት በመሆኑ ለዚሁ ተግባር የቅድመ-ዕቅድና የማማከር አገልግሎት የሚሰጥ ሌላ አካል የሚያስፈልገው ይሆናል፡፡

- *ተጫራቾች፡-* የሃይል ግዢው አቅራቢ አካል የሃይል አምራቾችን በጨረታ አወዳድሮ ቢመርጥ የተሻለ ነው፡፡ ከፍተኛ የሃይል አቅርቦት ችግራ ባለባቸው አገራት ውስጥ ያለጨረታ የሚመረጡ ሰነዶች ተቀባይነት ያገኛሉ፡፡ ይህም የሃይል ማምረትና ማቅረብ ተግባሩን ለማፍጠን ሲባል የሚፈጸም ነው፡፡

## የፋይናንስ ሽፋን

- **የከፍተኛ ሃብት ወጪዎች፡-** የሃይል ማመንጫ ፕሮጀክቶች ግዙፍና ሰፊ በመሆናቸው እጅግ ከፍተኛ ሃብት ይወጣባቸዋል፡፡ ስለሆነም በሚገባ የተረቀቀና የተዘጋጀ የሃይል ግዢ ስምምነት ሰነድ በማዘጋጀት ከፍተኛ ወጪ ላለው ፕሮጀክት የሚያስፈልግ የፋይናንስ ሽፋንን መመሳብ መቻል አለበት፡፡

- **የባንክ አገልግሎት፡-** የተሻለ የባንክ አገልግሎት ለፕሮጀክቱ ለመፍጠር (ማለትም ከፍተኛ ፋይናንስ ለመሳብ እንዲቻል) የሃይል አገልግሎት ተደራሹ መንግሥት ዋስትናዎችና የብድር ማስገኛ ተግባራትን ማመቻቸት ይኖርበታል፡፡

- **የክፍያ ዋስትና፡-** አብዛኛውን ጊዜ ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በሃይል ግዚ ስምምነት ውል መሰረት በሚፈፀሙ የክፍያ አፈፃፀም ሂደቶች የሚፈጠሩ እን ቅፋቶችን ለማስወገድ አቺ ስልቶችን ይቀይሳሉ፡፡

## አካባቢ-ነክ እና ማህበራዊ ግዴታዎች

- **የአገር ውስጥ ህግ፡-** ይህ የአገር ውስጥ ህግ አካባቢያዊና ማህበራዊ ግዴታዎችን አካቶ ይይዛል፡፡

- **የአበዳሪ አካል ግዴታዎች፡-** በርካታ አበዳሪ አካላት እንዲፈጸሙላቸው የሚፈልጓቸው የራሳቸው የሆኑ አካባቢ-ነክና ማህበራዊ የአፈፃፀም ግዴታዎችን ያስቀምጣሉ (ለምሳሌ፡- ዓለም-ዓቀፍ የፋይናንስ ኮርፖራቲነ የአካባቢ-ነክና ማህበራዊ መስፈርቶች - International Finance Corporation Environmental and Social Performance Standards፣ ኢኳተር መርሆች - Equator Principles፣ እና የአፍሪካ የልማት ባንክ የተቀናጀ የደህንነት ማስጠበቂያ ስርኣት - African Development Bank's Integrated Safeguard System ናቸው)፡፡

- **አካባቢ-ነክ ግዴታዎች፡-** የተለያዩ ሃይል ማመንጫ ዓይነቶች የተለያዩ አካባቢ-ክ ስጋቶችን ይፈጥራሉ፤ የትኛውም ዓይነት ቴክኖሎጂ ሙሉ በሙሉ ከስጋት ነፃ ሊሆን አይችልም፡፡

- **ማህበራዊ ግዴታዎች፡-** የአገር ወስጥ ህግና አበዳሪ አካላት እንዲከበሩላቸው የሚፈልጓቸው ከሰራተኛ መብቶች፣ ከአካባቢው ነዋሪ ተደራሽነትና ከልማት ተነሺነት/ተፈናቃይነትጋር ተያያዥነት ያሏቸውን ግዴታች ያስቀምጣሉ፡፡

.

# ገንዘብ ነክ ድንጋጌዎች

መግቢያ

ታሪፍ /ዋጋና ዋጋ ነክ ጉዳዮች/ አወቃቀር

የኤሌክትሪክ ኃይል ግዢ

የሽያጭ ሰነዶች ዝግጅትና ክፍያዎች

ለአገልግሎት ተጠቃሚ ግዴታዎች የብድር ድጋፍ

ለፕሮጀክቱ ኩባንያ ግዴታዎች የብድር ድጋፍ

ከግብር ነጻ

የቁልፍ ነጥቦች ማጠቃለያ

# መግቢያ

የኃግስ ፋይናንሲያዊ /ገንዘብ ነክ/ ደንቦች ከሁሉም የጎግስ ደንቦች እጅግ ጠቃሚዎቹ ለመሆናቸው የሚያከራክር አይደለም፤ ከመሠረቱ ኃግስ የግዢ ስምምነት ነውና! ሆኖም ጥያቄው በትክክል ምንድን ነው እየተገዛ ያለው እንዲሁም በምን ዋጋ? የሚለው ነው ፡፡

የእነዚህ ደንቦች መሠረት ታሪፉ (ዋጋና ዋጋ ነክ ጉዳዮች/ አወቃቀር) ሲሆን ይህም ደግሞ ከባህርዩ ውስብስብ የሆነ የአቅምንና የኤነርጂን ዋጋ ለመተመን የሚውል ፎርሙላ (ቀመር) ነው፡፡ ታሪፉ የተዘጋጀው የግዢ ሂደቱ አንዳንድ ቅጾችን አካቶ ሲሆን (የኤሌትሪክ ሃይል ግዢ)፤ ይኸውም ወይ የጨረታ ውድድር አልያም የዋጋ መግለጫ ቅጾችን በመጠቀም ነው፡፡ ከፍተኛው ችግር ያለው የሽያጭ ሰነዶች ዝግጅትና ክፍያዎች ዝርዝር ውስጥ ነው (የሽያጭ ሰነዶች ዝግጅትና ክፍያዎች)፡፡ እንደ የኃይል ገበያዎችና የኃይል ፕሮጀክቶች ተፈጥሮአዊ ባህሪ፤ ሁሌም የብድርና በቀላሉ ወደ ጥሬ ገንዘብ ሊለወጥ የሚችል ንብረት አሳሳቢነት በሁለቱም የኃግስ ጎኖች እንዳሉ ናቸው፤ ይኸው ደግሞ ለተለያዩ የብድር ድጋፍ አስፈላጊነት ለአገልግሎት ተጠቃሚና (ለተጠቃሚ ግዴታዎች የብድር ድጋፍ) ለካምፓኒው ፕሮጀክቶች (ለካምፓኒ ፕሮጀክቶች የብድር ድጋፍ) ዳርጓል፡፡ ሌላው ቁልፍ ጉዳይ ለፕሮጀክቱ ከታክስ ነጻ የመሆን ምብት መስጠት አለመስጠት ነው(ከታክስ ነጻ)፡፡

እነዚህ ሁሉ ስምምነቶች በከፍተኛ ሁኔታ ድርድር የሚካሄድባቸው በመሆናቸው በኃግስ ላይ ለየት ያለ ውስብስብነት ይፈጥራሉ፡፡

# ታሪፍ/ ዋጋና ዋጋ ነክ ጉዳዮች/ አወቃቀር

ታሪፍ እጅግ ጠቃሚ ከሆኑት የማንኛውም ኃግስ ክፍሎች አንዱ ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ታሪፍ የሚለው ቃል ሲገባ ጥቂት ክፍሎችን ያካተተ አድርጎ በመረዳት ነው ፡፡ አንደኛ ተጠቃሚው ለተደረገለት የዓቅም አቅርቦት ወይም የኃይል ምንጭ መፍለቅ ለፕሮጀክቱ ኩባንያ የሚከፍለውን ትክክለኛ ዋጋ ያጠቃልላል፡፡ በተጨማሪ ታሪፉ፤ ዋጋን ያማከሉ፤ ሰፋ ያሉ ደንቦችና ሁኔታዎችን ያካትታል' ፡፡ እነዚህ ሌሎች ደንቦች ተጠቃሚው ለፕሮጀክቱ ኩባንያ በየወሩ የሚከፍለውን ገንዘብ መጠን ይወስናሉ፤

ይህ ክፍል የሚከተሉትን ያብራራል፡-

1. የታሪፍ /ዋጋና ዋጋ ነክ/መዋቅሮች ዓይነቶች (ዓቅም ተኮርና ዓቅም ተኮር ያልሆኑ) ይኸውም በተለምዶ በኃይል ግዢ ስምምነቶች የሚገኙ
2. ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገውን ዓቅም እና/ወይም እንዲመነጭ የተደረገውን ኃይል በአንድ መለኪያ ዋጋ ለመወሰን የሚውሉ ስልቶችን
3. በነዳጅ ኮንትራቶች ስር ያሉ ውሰድ-ወይም-ክፈል ግዴታዎች እንዴት ተጽዕኖ እንደሚፈጥሩ እናም በኃይል ግዢ ስምምነት ስር ባለው የታሪፍ ክፍያ እንዴት ሊንፀባረቅ እንደሚገባ
4. የኃይል ግዢ ስምምነት ጊዜ ርዝመት በታሪፍ ላይ እንዴት ተጽዕኖ እንደሚፈጥር

ለሚሰራጩና ለማይሰራጩ ቴክኖሎጂዎች የተለያዩ የታሪፍ /ዋጋና ዋጋ ነክ/መዋቅሮች ስራ ላይ ይውላሉ፡፡

የሚሰራጩ ቴክኖሎጂዎች የሚያመለክተው በገዢው/ተጠቃሚው ሊሰራጩ የሚችሉ የቴክኖሎጂ ዓይነቶችን ነው፤ ይህም ማለት፤ገዢው/ተጠቃሚው ለፕሮጀክት ኩባንያው፤በእያንዳንዱ የስምምነት ጊዜ፤የተወሰነውን የጉልበት (የኃይል) መጠን እንዲያመነጭ መመሪያ ሊያስተላልፍ (ግዴታውም ነው) ይችላል፡፡ የሚሰራጩ ቴክኖሎጂዎች ምሳሌዎች ሁሉንም ዓይነት ሙቀት ፈጣሪ ተቋማትን ለምሳሌ እንደ በጋዝ የሚሽከረከሩ ሞተሮች(ነጠላም ሆነ የተጣመረ ዑደት)፣እርስበርስ የሚተጋገዙ በዲዝል ወይም ከባድ ነዳጅ ዘይት የሚሰሩ ኢንጂኖች፣ እንዲሁም በከሰል የሚለኮሱ አመንጪ መሳሪያዎች፣ በተጨማሪ በውሃ ሃይል የመነጨ ኤሌክትሪክ መሳሪያዎች፤ከአብዛኛው የፈሳሽ ወንዝ መሳሪያዎች በተለየ፤

የማይሰራጩ ቴክኖሎጂዎች በገዢው/ተጠቃሚው ሊሰራጩ የማይችሉ፣ ነገርግን ኃይል ሲኖር በተቀናጀ አውታር/መረብ/ አቅርቦቱ የሚሰራጭ፤ በአጠቃላይ ሁሉም ታዳሽ ቴክኖሎጂዎች፤ ከትላልቅ (ግድብ አቀፍ) ከውሃ ሃይል የሚመነጭ ኤሌክትሪክ በስተቀር፤ የማይሰራጩ ናቸው፡፡ የነዚህ የማይሰራጩ ቴክኖሎጂዎች ምሳሌዎች ንፋስንና የፀሃይ ሃይልን ያጠቃልላሉ፡፡ ጉልበቱ ታዳሽ ሃይልን በመጠቀም ሊመነጭ ይገባል ሃይሉ አስካለድረስ ወይም (ከኮንሰንትሬትድ የፀሃይ ሃይል ፕሮጀክቶች(ኮፀሃ) ጋር በተያያዘ ማንኛውም ውስን የማጠራቀሚያ ዓቅም እጥረት ጊዜ፤ጉልበቱ ይባክናል..

በዚህ ገዳቢ በሆነው ባህሪ የተነሳ፤ ለሚሰራጩና ለማይሰራጩ ቴክኖሎጂዎች የተለያዩ የታሪፍ (ዋጋና ዋጋ ነክ ጉዳዮች) አወቃቀር ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ከዚህ በታች ያሉት ሁለት ክፍሎች፤ ሁለቱን፣ በተለምዶ የሚሰራጩና የማይሰራጩ ቴክኖሎጂዎች ላይ የሚተገበሩትን የተለያዩ የታሪፍ(ዋጋና ዋጋ ነክ ጉዳዮች) አወቃቀር ያብራራሉ፡፡.

# የታሪፍ/ዋጋና ዋጋ ነክ መዋቅሮች ለሚሰራጩ ቴክኖሎጂዎች

የታሪፍ/ዋጋና ዋጋ ነክ ጉዳዮች/ አወቃቀሮች በዓመታት ውስጥ በተለያየ የመወሰን ስልጣን እየተቀያየሩ መጥተዋል፤ ይኸውም በበለጠ ብቃት የጉልበት ሃብትን ለማድረስ እንዲሁም የአከፋፈል ዘይቤዎችን በማሻሻል ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት፡፡ የመጀመሪያዎቹ ታሪፎች ጉልበትን/ኃይልን እና ዓቅምን ወደ አንድ ነጠላ ጉልበት/ኃይል ክፍያ አጠቃለሉት (በተለምዶ እንደሚገለጸው / በዶላር በኪሎዋት በሰዓት/ በ ኪዋሰ).

ቀጣዩ የታሪፎች አሰራር ደግሞ **ውሰድ-ወይም-ክፈል** ግዴታን ጨመረ፤ይኸውም ለሚጠበቀው የሽያጭ ደረጃ አስፈላጊ ምቹ ሁኔታ ዋስትና ይሆን ዘንድ፤

ሦስተኛው የታሪፍ አሰራር **ውሰድ-ወይም-ክፈል** የሚለውን ስነሃሳብ ከኤሌክትሪክ ታሪፎች አስወገደ፤( ሊተገበር ከሚገባው በነዳጅ አቅርቦት ስምምነት ውሰድ-ወይም ክፈል ግዴታዎች በቀር)፤

እንዲሁም ዓቅምና ጉልበት/ሃይል ክፍያዎችን አስተዋወቀ፤ ይኸውም አምራቾችን ከፍላጎት መዋዠቅ ለመጠበቅ እንዲሁም ተጠቃሚዎችን ለማያስፈልግ ጉልበት/ሃይል (ደግሞም ያልተሰራጨ ነው) ከመክፈል ግዴታ ለማዳን፡፡

ዓቅም ተኮር ታሪፎች የተቀመሩት፤ በጉልበት/ሃይል-ብቻ እና ውሰድ-ወይም-ክፈል መዋቅሮች ተተክለው ያሉትን እንቅፋቶች ለመድረስ ነው፡፡ እነዚህ ታሪፎች አወቃቀራቸው የኢንቨስተሮችንና ተጠቃሚዎችን ፍላጎት ኤኮኖሚያዊ ብቃት ባለው ሁኔታ ለማመጣጠን ነው፡፡

ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው፤ ፕሮጀክት ኩባንያው፤ለሚከተሉት የሚውል በቂ የሆነ ገቢ ማግኘት አስተማማኝ እድል እንዳለው በማረጋገጥ ነው ይኸውም (i) ለፕሮጀክቱ የዋለውን መዋዕለ ንዋይ መልሶ መክፈል፤እንዲሁም ተገቢ የሆነ ትርፍ ለፕሮጀክቱ ባለሃብቶች (ii) የፕሮጀክቱን ቋሚ ሥራ ማስኬጃ መሸፈን መቻል፤ ገዢው/ተጠቃሚው ኃይል አመንጪውን ተቋም አንቀሳቀሰው ወይም አላንቀሳቀሰው፡፡ የገዢው/ተጠቃሚው ፍላጎቶች እንደተጠበቁ ናቸው፤ ምክንያቱም የገዢው/ተጠቃሚው ግዴታ ለቀረበለት ዓቅም መክፈል ነው፤ እንዲሁም በገዢው/ተጠቃሚው ለተሰራጨ ጉልበት/ሃይል ደግሞም በትክክል ሊደርስ የሚገባው ቦታ ለደረሰ፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ ታሪፎች ገዢው/ተጠቃሚው ለኩባንያው ፕሮጀክት በየወሩ የሚከፍለውን ያሳያሉ፡

- ክፍያ (**የዓቅም ክፍያ**) ለገዢው/ተጠቃሚው የቀረበለት ለኃይል አመንጪው ተቋም፤ገዢው/ተጠቃሚው ተቋሙን ተጠቀመበት አልተጠቀመበት እንዲሁም
- በMWh/ሜዋሰ/ (ወይም በ kWh/ኪዋሰ/) የሚከፈል ክፍያ፤ (**የጉልበት/ሃይል ክፍያ**) ለጉልበት/ሃይል ለተሰራጨና ለገዢው/ተጠቃሚው ለደረሰለት

**የዓቅም ክፍያው፤** ፕሮጀክት ኩባንያው በኃይል ግዢው ስምምነት መሰረት፤ በቂ ገቢ በመሰብሰብ፤ የሚከተሉትን ማካሄድ ይችል ዘንድ የተሰላ ነው

1. የፕሮጀክቱን ብድሮች መልሶ መክፈል (እንዲሁም በአንዳንድ ሁኔታዎች ተያያዥ የሆኑ መሠረተ ልማቶች፤ እንደ ማስተላለፊያ መስመሮችን)

2. ለስፖንሰሮች /ደጋፊ አካላት/ የባለቤትነት ድርሻንና ተመሳሳይን በተመለከተ ትርፍን መክፈል (እንደ ባለድርሻ ብድሮች) ኢንቨስት ባደረጉት ላይ (እንዲሁም ፕሮጀክት ኩንያው አወቃቀሩ በገንባ-ሥራ-አስተላለፍ ላይ የተመሰረተ ከሆነ በስፖንሰሮች ኢንቨስት የተደረገውን የባለቤትነት ድርሻንና ተመሳሳይን፤ በኃግስ ደንብ መሰረት መመለስ)

3. በፕሮጀክት ኩባንያውና ንብረቶቹ ላይ የተሰሉ ከድርጅቱ ጋር የተያያዙና ሌሎች ግብሮችን መክፈል፤እንዲሁም

4. ለቋሚ ሥራዎችና የጥገና ወጪዎች.እንዲሁም በፕሮጀክቱ ለተፈጠሩ ማንኛውም ሌሎች ስምምነት የተደረገባቸው የፕሮጀክት ወጪዎች፤ከስርጭት ጋር ከተያያዙት በቀር መክፈል.

**የጉልበት/ሃይል ክፍያው** የተሰላው ፕሮጀክት ኩባንያውን በቂ ገቢ መሰብሰብ ለማስቻልና በኃግስ ስር ፕሮጀክት ኩባንያው

ጉልበት/ኃይልን ለማመንጨትና ለገዢው/ተጠቃሚው ለማድረስ የዋለውን ማንኛውንም የነዳጅ ወጪ መመለስ ማስቻል እና

በአመንጪው ተቋም እንደ ተመረተው ጉልበት/ኃይል መጠን መሰረት፤ ለሥራ ማሰኬጃና ለጥገና የዋለውን ወጪ መክፈል

በዚህ የታሪፍ አወቃቀር ምክንያት፤የፕሮጀክት ኩባንያው ለሚሰራጭ የወቅቱ ደረጃ አትኩሮት የለውም፤ ምክንያቱም የፕሮጀክቱ ኩባንያ ካፒታል እና ቋሚ ሥራዎችና የጥገና ወጪዎች በኃይል ክፍያው በኩል ተሸፍነዋል፤ይኸውም ደግሞ ተከፋይ የሚሆነው የሚሰራጨውን መጠን ቁብ ውስጥ ሳያስገባ ነው።

ስለዚህ፤ ለፕሮጀክት ኩባንያው፤ የገበያ ዓደጋን ለመሸፈን የዓደጋ ቅድመ ክፍያን ማስከፈል አስፈላጊ አይደለም፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ፤ ይህ የታሪፍ አወቃቀር እውነተኛውን የፕሮጀክት ኩባንያውን ወጪዎች ምንነት ያሳያል፤እንዲሁም ከኤኮኖሚያዊ ሥርጭት ደንቦች ጋርም አብሮ የሚሄድ ነው ፡፡

የዓቅም ክፍያው (አንዳንዴ **ሰዓት መሠረት ያደረገ የዓቅም ክፍያ** ተብሎ ይጠራል) ሲተነተን ስምምነት በተደረሰበት ወቅት ለቀረበ ለእያንዳንዱ MW ሜጋ ዋት (ያ የቀረበው MW/ሜዋ/ በትክክል ኃይል/ጉልበት ለማመንጨት ዋለም አልዋለ) የሚከፈል ዋጋ ነው፡፡ እያንዳንዱ የስምምነት ጊዜ፤ የዓቅም አቅርቦትን ጠቀሜታ፤ ለገዢው/ተጠቃሚው በዚያ ሰዓት ለማሳየት ይመዘናል፡፡

$$HCP_i = (BCP_i + FOMC_i) \times PWF_i \times AvCap_i$$

በእያንዳንዱ ሰዓት የሚከፈለው ክፍያ እንዲህ ተብሎ ሊገለጽ ይችላል

ይኸውም፡-

$HCP_i$: - ይህ ማለት ሰዓታዊ የዓቅም ክፍያ በሰዓት መጠን ለ ';'

$BPC_i$ :-ይህ ማለት ጠቅላላ የመሠረታዊ ዓቅም ዋጋ መጠን ለሰዓት ';'

$FOMC_i$ :-ይህ ማለት የሰዓታዊ ቋሚ ሥራዎችና የጥገና ክፍያ መጠን ለሰዓት ';'

$PWF_i$--ማለት ወቅት መመዘኛ ፋክተር ለ ሰዓት ';' (ይኸውም ቁጥር ሆኖ ልኩ ለምሳሌ በ 0.65 እና 1.5 ክልል ያለ፤ በስምምነቱ ጊዜ የዓቅምን ጠቀሜታ የሚያሳይ)፤ እና

$AvCap_i$- ማለት በፕሮጀክት ኩባንያው አቅርቦቱ እንዳለ የተገለፀ ዓቅም በሰዓት ';'

ሰዓታዊ የዓቅም ክፍያዎች በወሩ (ወር 'ወ') እያንዳንዱ ሰዓት ተከፋይ የሆኑት ይደመሩና የወሩን የዓቅም ክፍያ ይወስናሉ፡፡

በዚህ አካሄድ ተጠቃሚው የሚከፍለው በትክክል ለቀረበለት ዓቅም ብቻ ይሆናል፡፡

ምንም እንኳን ታሪፉ ብዙ ፎርሙላዎች/ስሌቶች/ ቢኖሩትም እንዲሁም ከላይ ከተገለጹት ጉዳዮች ውጪ በተጨማሪ ሌሎች ጉዳዮችንም የሚደርስ ቢሆንም (ለምሳሌ ደጋፊ ክፍያዎች፣ የሥራ መጀመሪያ ወጪዎች እና ሌሎች ተጨማሪ ዝርዝሮች) ይህ በጣም ጠቃሚ የሆኑትን ጉዳዮች የያዘ ፎርሙላ/ስሌት፤ ዘመናዊ ዓቅም ላይ የተመሰረተ ታሪፍ ቁልፍ ሃሳቦች  እንዴት እንደሚገለጹ ምሳሌ ይሰጣል፡፡


ሆኖም የፕሮጀክቱ ኩባንያ በሰዓት ሊያሰራጭ ከሚችለው በላይ ብዙ የዓቅም አቅርቦት እንዳለ የፕሮጀክቱ ኩባንያ ሲያውጅ፤ ሌሎች የኃይል ግዢው ስምምነት ድንጋጌዎች $AvCap_i$ን ዝቅ አድርገው እንደሚያስተካክሉ ማስተዋል ጠቃሚ ነው፡፡

ፕሮጀክት ኩባንያው፤ገዢው/ተጠቃሚው ሊሸከመው ቃል በገባበት ዓደጋ ምክንያት፤ዓቅምን ለማቅረብ መቻል ሲያቅተው፤ይህን ጊዜ ዓቅም ለተጠቃሚው እንደደረሰ ተደርጎ የሚወሰድ መሆኑን ማስተዋል ጠቃሚ ነው፡፡ የእንደዚህ ዓይነት ዓደጋ ምሳሌዎች፣ማስተላለፊያ ሲስተሙ ኃይልን/ጉልበትን ከኃይል ማመንጫ ጣቢያው ለመውሰድ እንዳለ የመቁጠር ዓደጋ፤ የነዳጅ አቅርቦት (ተጠቃሚው የነዳጅ ማቅረብ ሃላፊነት ካለበት)፣እንዲሁም ፖለቲካዊ ከዓቅም በላይ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ፡፡

ከስር ያለው ማሳያ የመሠረታዊ ዓቅም ክፍያ ዋና ዋና ክፍሎችን እንዲሁም (እንደ አጠቃላይ) **በኃግስ** የመጀመሪያ የሥራ ዘመን ተዛምዶኣዊ የእያንዳንዱን ክፍል መጠን የሚያሳይ ነው፡፡

ወደ በኋላ ባሉ የስምምነት ጊዜ ዓመታት፤ በፕሮጀክቱ ክፍሎች ብድሮች ያለው ወለድ ይቀንሳል፡፡ ይህ ቅነሳ የፕሮጀክት ብድሮችን እንደገና መክፈል መጨመር ይተካና  ነጻ መሆንና ወደ ባለቤትነት ድርሻ ክፍሎች መመለስን ያመጣል፡፡


ዋና ዋና የመሠረታዊ ዓቅም ክፍያ ክፍሎች



ከስር ያለው ማሳያ ዋና ዋና የኃይል/ጉልበት ክፍያ በዓቅም ላይ የተመሠረተ ታሪፍ ለሙቀት ኃይል ማመንጫ ጣቢያ ስር ያሉ ክፍሎችን ያሳያል፡፡

(በታዳሽ ፕሮጀክት፤ በ ኃይል/ጉልበት-ብቻ ታሪፍ ስር ያለ የኃይል/ጉልበት ክፍያ፤ከዚህ በላይ ባለው ምስል የተመለከቱትን ክፍሎች ተመሳሳይ ክፍሎች ይኖሩታል ይኸውም ወደ መሰረታዊ ዓቅም ክፍያ የሚሄዱትን ክፍሎች ያሳያል)

የኃይል/ጉልበት ክፍያ ዋና ክፍሎች




# ቁልፍ/ዋና ነጥቦች

- የዓቅም ክፍያዎች ለፕሮጀክት ኩባንያዎች ቋሚ ወጪዎቻቸውን (ካፒታል ወጪ እና ቋሚ የሥራ ማስኬጃ ወጪ) ለመመለስ ያስችሏቸዋል እንዲሁም ትርፍ ላይ ስምምነት፡፡ እነዚህ ክፍያዎች የሚከፈሉት የኃይል ጣቢያው ለስርጭት ዝግጁ በሆነበት ጊዜ ሁሉ ይሆናል፡፡
- የኃይል ክፍያዎች ሂሳብ መዝገብ ለነዳጅና ተለዋዋጭ የስራ ማስኬጃ ወጪዎች
- ለሰፊ አካባቢ ከፍተኛ የሆነ የኤሌክትሪክ ኃይል አገልገሎት ለማካሄድ፤ በአንዳንድ ሕጎች ተጨማሪ ክፍያዎች በገዢዎች ላይ ይጫናሉ (ለምሳሌ እንደ የመነሻ ክፍያ፣ተጨማሪ ተደጋጋፊ አገልግሎቶች፣ እና ማንኛውም ለአስቸጋሪ ሁኔታዎች የሚያስፈልጉ ክፍያዎች፤ በኃግስ መሰረት የተጠቃሚው ግዴታ የሆኑ)

# ታሪፍ (ዋጋና ዋጋ ነክ ጉዳዮች) መዋቅሮች ለማይሰራጩ ቴክኖሎጂዎች

በተለምዶ፤ ኃግስ ለማይሰራጩ ቴክኖሎጂዎች (በቀዳሚነት ታዳሽ ለሆኑ) ፕሮጀክት ኩባንያው  በኃይል አመንጪው ተቋም የመነጨውን ሁሉንም ኃይል/ጉልበት ለገዢው/ተጠቃሚው ማድረስና መሸጥ ግድ ይላል፡፡

ዋጋው በቀላል አገላለጽ ለምሳሌ እንደ ሣንቲሞች (ወይም ሌላ የገንዘብ ዓይነት) በ kWh ኪዋሰ(ኪሎ ዋት በሰዓት) ወይም ዶላሮች (ሌላም የገንዘብ ዓይነት ) በ MWh ሜዋሰ (ሜጋ ዋት በሰዓት) የመነጨና የተዳረሰ፡፡ ሥራ ላይ የዋለው የገንዘብ ዓይነት ብዙውን ጊዜ በ(ኢግግ) ኢንጂኔሪንግ፣ ግዢ፣ ግንባታ ኮንትራት የገንዘብ ዓይነት ይወሰናል፤ ወይም ብድሮቹ በተሰየሙበት የገንዘብ ዓይነት ይሆናል፡፡

እነዚህ ታሪፎች፤ ገዢው/ተጠቃሚው ወይንም የማስተላለፊያ ሲስተሙ ኦፕሬተር፤ የኃይል/ጉልበት ምርትን በተቋሙ ደረጃ የሚያቋርጥበት ሁኔታ ሊፈጠር እንደሚችል ይገነዘባሉ፤ይኸውም በማስተላለፊያ መስመሩ ላይ፣ አስቸኳይ የዓደጋ ጊዜ፣ ወይም በሌሎች ምክንያቶች  በተፈጠሩ መሰናክሎች የተነሳ፡፡  የተለያዩ ገበያዎች፤ በአገልግሎት መቋረጥ ለሚመጣው ኪሳራ የፋይናንስያዊ ዓደጋ የተለያየ መንገድ ያመቻቻሉ፡፡ እያደጉ ባሉ ገበያዎች ኃግስ፣ እንደ ታሪፉ አንድ አካል፤ገዢው/ተጠቃሚው በኃይል መቋረጥ ምክንያት ለሚመጣው ኪሳራ ይሸፍናል፡፡

ብዙውን ጊዜ፤ ይህ አስቀድሞ በተቀመጠ በኃይል መቋረጥ የሚመጣ ኪሳራ መጠን በላይ ሲሆን በሚል የተወሰነ ነው፡፡ ይህ የተቋረጠው ኃይል አንዳንዴ ሳይኖር ያለ ኃይል ተብሎ ይጠራል፡፡

ለዋናው ማሰራጫ ክፍል የማይታዘዝ ተቋም ገዢ/ተጠቃሚ ለሳይኖር ያለ ኃይል እንዲከፍል ያስፈለገበት ዋና ምክንያቶች፡

- በተለያዩ ምክንያቶች የተራዘመ ኃይል መቋረጥ ሁኔታ መፈጠር ግምት አይቀሬነት፤ እንዲሁም የማሰራጫ ሲስተሙ ሁኔታ ደግሞም በቂ ያልሆነ ኃይል የማመንጨት አቅም አጠቃላይ አካባቢውን ወደ ብርሃን እጥረት ስለሚያስገባ እና

- የአስተናጋጅዋ አገር መንግሥት፤ በሁለቱም ገዢው/ተጠቃሚና በማሰራጫ ሲስተሙ ኦፕሬተር ላይ፤ የመቆጣጣር ፍላጎት ይኖረው ይሆናል

.

ይህ በሚሆንበት ጊዜ፤ገዢ/ተጠቃሚው የማሰራጫ ሲስተሙን ኦፕሬተር፤ ኃይል ስርጭቱን እንዲያቋርጥና ገዢ/ተጠቃሚው ኃይል ከሌላ ምንጭ ባነሰ ዋጋ ለመግዛት ሁኔታዎችን የማመቻቸት እንዳይሆን ብለው ኢንቨስተሮች ይጨነቃሉ፡፡

የተራዘመ የኃይል መቋረጥ ዓደጋ፤ በማደግ ላይ ባለው ገበያ፤ እያለ የሌለውን ኃይል መጠን ማስላት የሚያስችል ጠንካራ የሆኑ ዘዴዎችን ወደ መፍጠር መርቷል፡፡ ይህ ለተራዘመው የኃይል መቋረጥ ዓደጋ  ስነሞገታዊ ምላሽ ነው፡፡

ምክንያቱም በተራዘመ የኃይል መቋረጥ ወቅት፤ ጠቅላላ የእያለ የሌለ ኃይል ክፍያ በጣም ከፍተኛ ሊሆን ይችላል፤ እንዲሁም በእያለ የሌለው ኃይል ስሌትና መለኪያ መሣሪያ ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ይወሰናሉ፡፡

እንደ ምሳሌ፤ አንድ ኃግስ ለንፋስ ፕሮጀክት በተለምዶ የሚጠይቀው፤ ፕሮጀክት ኩባንያው አንድ ወይም ሁለት ሜትሮሎጂካዊ /ስነ አየር ጠባያዊ/ ረጃጅም የብረት ምሰሶዎችን እንዲተክል ነው፤ይኸውም የንፋሱን አማካይ ፍጥነትና አቅጣጫ በእያንዳንዱ ስድስት ደቂቃዎች ውስጥ በከፍያው ወቅት የሆነውን መለካት ይቻል ዘንድ፡፡

በኃግስ መሠረት ከንግዳዊ የሥራ ጅማሬ ቀን በፊት፤ ገዢው/ተጠቃሚው እና ፕሮጀክት ኩባንያው፤/ከነፃ መሐንዲሱ ማረጋገጫ ጋር/፤ለእያንዳንዱ የንፋስ ፍጥነት እና አቅጣጫ፣በነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ፤ የንፋስ ጣቢያው ሊያመነጭ የሚችለውን የተጣራ የኤሌክትሪክ ምርት የሚተነብይ የኃይል/ጉልበት ከርቭ ይቀምራሉ፡፡

የኃይል/ጉልበት ከርቩ፤እንደ ንፋስ ጣቢያው ትክክለኛ የሥራ ውጤት፤ በየዓመቱ ወይም በየግማሽ ዓመት የሚሻሻል ይሆናል፡፡

የኃይል መቋረጥ ሁኔታ ሲፈጠር፤ የኃይል/ጉልበት ከርቩ ከንፋስ ፍጥነት፣ንፋስ አቅጣጫ፣ እንዲሁም በኃይል መቋረጡ ወቅት የእያንዳንዱ ንፋስ ተርባይን ህልውና ጋር የ እያለ የሌለውን ኃይል መጠን፤ይኸውም ገዢው/ተጠቃሚው ሊከፍል የሚገባውን ለመለካት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ኃግስ በፀሓይ ሃይል ለሚሰራ ፕሮጀክት፤ገዢ/ተጠቃሚው የፕሮጀክት ኩባንያው የኃይል/ጉልበት ከርቭ እንዲገነቡ ግድ ይላል፤ ይኸውም መሰረቱ በአንድ ቦታ በሚደርሰው የፀሃይ ኃይል መጠንና መለኪያው ደግሞ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ ፓይራኖሜትሮች ወይም ፓይረሄሊዮሜትሮች (እነዚህ ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ የመጣውን የፀሃይ መጠን እና ቀጥተኛ የሚያንፀባርቀውን ሙቅ ብርሃን በአውሮፕላን ላይ ያረፈን የሚለኩ)

በቅርቡ ዓመታት ኬፕቬርዴ፣ ደቡብ አፍሪቃ፣ እና ኬንያ እያንዳንዳቸው ኃግሶችን ፈርመዋል፤ ከነዚህ ጥቂቶቹ ለንፋስ ማመንጫ ከላይ ያሉትን ስምምነቶች ያመለክታሉ፡፡ ከነዚህ ክፍሎች አንዳንዶቹ ወደ ንግዳዊ ሥራ ገብተዋል፡፡

### ቁልፍ ነጥቦች

- ኃይል/ጉልበት-ብቻ ታሪፎች የሚገለጹት እንደ$/ኪዋሰ ወይም $/ሜዋሰ (ነገርግን በአካባቢው የገንዘብ ምንዛሪም ሊገለጹ ይችላሉ)

- እያለ የሌለ ኃይል መርህ ይሰራል፤ ምክንያቱም ሁሉም የተመረተው ኃይል/ጉልበት በመለኪያ ቦታው ጋር ዋጋ ይሰጠዋል ደግሞም ይከፈልበታል

- ጥንቃቄ የተሞላ ልኬት በገዥውም እና ሻጩም ይካሄዳል፤ ይኸውም ጥቅም ላይ የዋለውን ገዥው/ተጠቃሚው ሊከፍልበት ግዴታ የሆነበትን የኃይል/ጉልበት ደረጃ ለመለየትና ለማረጋገጥ

# ማበረታቻ ታሪፍ

ማበረታቻ ታሪፍ በተለምዶ የሚተገበረው፤ ከታዳሽ ምንጮች ኃይል/ጉልበትን ለማምረት

የሚደረገውን ለማበረታታት ነው፡፡

ማበረታቻ ታሪፍ በአጠቃላይ የሚታየው ለአምራቹ ሦስት ቁልፍ ጉዳዮችን በእርግጠኝነት ከማቅረብ አንጻር ነው፡፡

እነዚህ ሦስት ጉዳዮች ሀ) ለሰፋ ያለ ኤሌክትሪክ ሲስተም ዋስትና ያለው አቅርቦት

ለ) የረዥም ጊዜ ኃግስ ሐ) በአግባቡ የተደነመ የኃይል/ጉልበት ዋጋ

የኃይል/ጉልበት ዋጋ ብዙውን ጊዜ የሚደነገገው፤የሚከተሉትን ግምገማ ካካሄደ በኋላ፤ በዘርፉ ተቆጣጣሪ ነው (i) የቋሚ ንብረት ወጪ፣እና ሥራ ማስኬጃና የጥገና ሥራዎች ወጪ፤ አንድ ብቁ አምራች፤ ለአንድ በተለየ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሠረተ፤ (ለምሳሌ እንደ ንፋስ ወይም የፀሓይ ሃይል)፤ የኃይል/ጉልበት ፋብሪካ ለምስረታ፣ግንባታ፣ሥራ ማስኬጃ፣እንዲሁም ጥገና የሚያወጣቸው ወጪዎች፤ እንዲሁም (ii) አንድ አምራች ሊደርስበት የሚገባ ከፍተኛ መዋቅር

ማበረታቻ ታሪፍ ሥራዎች በአጠቃላይ ለተወሰነ ጊዜ የሚመሰረቱና ሕጋዊ ሆነው የሚቆዩ ሲሆኑ ይኸውም አምራቹ እርግጠኛ ሆኖ በፕሮጀክቱ ላይ ያዋለውን መዋዕለ ንዋይ ተመላሽ ማድረግና ተገቢ የሆነ ገቢ መሰብሰብ ይችል ዘንድ ነው፡፡

እንደ አጠቃላይ ሕግ፤ ሁሉም አምራቾች( የዓቅም መጠንን አስመልክቶ አስቀድሞ በተቀመጠ ልክ መሠረት፤በታሪፍ ማጠናከሪያው እንደተቀመጠው) ንግዳዊ ሥራዎችን የሚያካሂዱ ወይም አስቀድሞ በተወሰነ ጊዜ ግንባታ ሥራ የሚጀምሩ፤ ለታሪፍ ማጠናከሩ ደንቦች በኮንትራት ጊዜያቸው ዘመን ተገዢ ናቸው፡፡

ተቆጣጣሪዎች ለአዲስ ፕሮጀክቶች የሚውሉትን የታሪፎች ማጠናከር በየጊዜው ያሻሽላሉ፤ይኸውም ዓላማው፤ከዚህ የተለየ ቴክኖሎጂ ተጨማሪ የተስፋፋ ተቀባይነት ምክንያት፤የታሪፍ ማጠናከሩን ዝቅ በማድረግ ዝቅተኛ ካፒታል ወጪን ለማካተትና እና ሌሎች ወጪዎችን ለማዳን፤

ፎቶቮላቲክ የፀሃይ ሃይል ፕሮጀክቶች፤የዝቅተኛ ወጪ አዝማሚያና አቅጣጫ የበለጠ ምሳሌ ይሰጣሉ፤ ከ2008 እ/አ/አ ጀምሮ የ ፎቶቮላቲክ ፓነሎች ዋጋ በሚገርም ሁኔታ ያለማቋረጥ ወርዷል

የታሪፎች ማጠናከር በአጠቃላይ አወቃቀሩ ከላይ ባለው ክፍል፤ ታሪፍ/ገንዘብና ገንዘብ ነክ ጉዳዮች/ አወቃቀር ለ በገዢው/ተጠቃሚው ለማይሰራጩ ቴክኖሎጂዎች በሚል ርእስ ከተገለጸው ታሪፎች ጋር አብረው የሚሄዱ ናቸው፡፡ ብዙ የአፍሪቃ አገሮች፤ የታሪፎች ማጠናከርን ለታዳሽ ኃይል ይጠቀሙበታል፡፡

# ውሰድ-ወይም-ክፈል ግዴታዎች በነዳጅ ኮንትራቶች ሥር- ለኤሌክትሪክ ታሪፎች ያላቸው አንድምታ

ብዛት ባላቸው እያደጉ ባሉ ገበያዎች፤ብዙውን ጊዜ ጋዝ አቅራቢዎች፤ የረጅም ጊዜ የጋዝ አቅርቦት ስምምነቶች፤ ውሰድ-ወይም-ክፈል አንቀጽ ይኖራቸው ዘንድ ግድ ይላሉ፡፡

ከፕሮጀክት ኩባንያ አንጻር፤ አንድ ውሰድ-ወይም-ክፈል አንቀጽ፤ ፕሮጀክት ኩባንያው ስምምነት የተደረሰበትን የጋዝ መጠን(ብዙውን ጊዜ በ MMBtus/ሚልዮን እንግሊዛዊ የሙቀት መለኪያዎች/ ወይም GJ (LHV)/ዝቅተኛ ማሞቂያ ዋጋ/ ይገለጻል) በየዓመቱ መግዛት ፤ወይም ለዚያ መጠን ጋዝ ክፍያ መፈጸም፤ ምንም እንኳን ፕሮጀክት ኩባንያው ያን መጠን ቢገዛም ባይገዛም ግዴታ መሆኑን ይደነግጋል፡፡

ለውሰድ-ወይም-ክፈልአንቀጽ በጋዝ አቅርቦት ስምምነት ውስጥ፤ኤኮኖሚያዊ በቂ ምክንያት እጥፍ ነው፡፡አንደኛ፤ ጋዝ አቅራቢው ጋዝ ከማቆሪያው/ዎች የማውጣት መብት ይኖረዋል፤ከዚህም ለተለየና ለተወሰነ ጊዜ በዳሰሳና ልማት ፈቃዱ ላይ እንደተቀመጠው አግባብነት ያለውን ማቆሪያ ጨምሮ በአካባቢው ያሉትን በማሰስ ጋዝ አቅርቦት ያካሂዳል፡፡

ጋዝ አቅራቢው የረጅም ጊዜ የጋዝ አቅርቦት ከፕሮጀክት ኩባንያው ጋር ቢፈራረም፤እናም ፕሮጀክት ኩባንያው ጋዝ አቅራቢው ለፕሮጀክት ኩባንያው ወስኖ ያስቀመጠለትን ትርጉም ያለው መጠን ለመግዛት ባይችል፤ይህን ጊዜ ጋዝ አቅራቢው በኢንቨስትመንቱ ላይ የተቀመጠውን ለአሰሳ፣ለመስክ የጥሬ ኃብት ወጪ፣ጋዝ የማምረት ተቋማት እና ሌላ መሠረተልማት ያወጣውን ወጪ፤ ኤኮኖሚያዊ ዋጋ ያጣል፤

ሁለተኛው፤ ጋዝ አቅራቢው የራሱን ዕዳዎች መክፈል ይቻለው ዘንድ ቀጣይነት ያለው የገቢ ምንጭ ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህ ውሰድ-ወይም-ክፈል ግዴታ አንዱ ጋዝ አቅራቢዎች ዓደጋን ሊከላከሉበት የሚችሉበት ዘይቤ ነው፡፡

ምንም እንኳን ኤኮኖሚያዊ በቂ ምክንያት አብሮት ቢኖርም፤ውሰድ-ወይም-ክፈል ግዴታዎች በጥንቃቄ ሊያዙ ይገባል፤ ምክንያቱም በጉልበት/ኃይል ግዢው ስምምነት ስር ያለውን የታሪፍ ክፍያ ላይ ተፅዕኖ ሊፈጥሩ ይችላሉና፡፡

እያንዳንዱ ውሰድ-ወይም-ክፈል ግዴታ በጋዝ ገዢው (በዚህ ጉዳይ የፕሮጀክቱ ኩባንያ) ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ተያያዥ ችግሮችን፤ **ወደፊት-የማሻገር** እና **ሙሉ-ማድረግ** እርምጃዎችን በመውሰድ ሊያቀል ይገባል፡፡

ሙሉ-ማድረግ አሰራር፤ ጋዝ ገዢው በማንኛውም የውሰድ-ወይም-ክፈል ወቅት(ብዙውን ጊዜ ሁሌም የአንድ ዓመት ወቅት የሆነ)፤ የውሰድ-ወይም-ክፈል መጠኑን መግዛት ካልቻለ፤ እና የውሰድ-ወይም-ክፈል ክፍያ ከከፈለ ፤ይኸውም የመግዣ ዋጋ ሲባዛ በ (i) የውሰድ-ወይም-ክፈል መጠን እና (ii) ጥቅም ላይ የዋለ ጋዝ መጠን በመካከላቸው ባለ ልዩነት እኩል የሆነ፤ ይህን ጊዜ የውሰድ-ወይም-ክፈል ክፍያ ወደ ተከታታይ የውሰድ-ወይም-ክፈል ወቅት የጋዝ ዋጋ እንዲሸፍን ይደረጋል፤ የውሰድ-ወይም-ክፈል መጠኑ በዚያ ወቅት ጥቅም ላይ የዋለ ከሆነ፡፡

ወደፊት-የማሻገር አሰራር ደግሞ ልክ ተቃራኒውን ያካሂዳል፡፡ ጋዝ ገዢው ከውሰድ-ወይም-ክፈል መጠን በላይ የሆነ መጠን በአንድ በተለየ የውሰድ-ወይም-ክፈል ወቅት ከገዛ፤ይህን ጊዜ ወደፊት-የማሻገር መጠን (ከውሰድ-ወይም-ክፈል መጠን በላይ የተገዛው የጋዝ መጠን) በተከታታይ ባሉ የውሰድ-ወይም-ክፍል ወቅቶች የውሰድ-ወይም-ክፈል መጠን ለመቀነስ ይውላል፡፡

የውሰድ-ወይም-ክፈል ግዴታዎች በኃግስ ስር ተከፋይ የሆነውን ተከፋይ ታሪፍ ላይ በሚከተለው መልኩ

ተፅዕኖ ይፈጥራሉ፡፡

ገዢው/ተጠቃሚው ለፕሮጀክት ኩባንያው ፕሮጀክት ኩባንያው በውሰድ-ወይም-ክፈል ወቅት ሊጠቀም የሚችለውን የጋዝ መጠን ከውሰድ-ወይም-ክፈል መጠን ጋር እኩል የሆነ ሊያደርስለት ሳይችል ሲቀር፤ ያን ጊዜ በዚያ በውሰድ-ወይም-ክፈል መጨረሻ ወቅት፤ ገዢው/ተጠቃሚው ፕሮጀክት ኩባንያው የውሰድ-ወይም-ክፈል ክፍያውን ለጋዝ አሰራጩ እንዲከፍል ገዢው/ተጠቃሚው ክፍያ እንዲያዘጋጅ ይገደዳል፡፡

## ቁልፍ ማብራሪያዎች

- ውሰድ-ወይም-ክፈል አሰራሮች፤ለረጅም ጊዜ ነዳጅ አቅርቦት ኮንትራቶች አስፈላጊ ናቸው፤ ምክንያቱም ነዳጅ ለሚያቀርቡና ነዳጅ ማውጫ መሳሪያዎችን ወደ ገበያ ለሚያመጡ ወገኖች የሚኖረውን ዓደጋ ዝቅ ያደርጋሉ፡፡

- ውሰድ-ወይም-ክፈል ስምምነቶች፤ በሆኑ የተለዩ ወራት፤ማለትም ከውሰድ-ወይም-ክፈል ወቅት መጨረሻ ጋር ሲጋጠሙ ታሪፍን የመጨመር ተጽዕኖ ሊኖራቸው ይችላል፤ይህ ደግሞ የገዢ/ተጠቃሚውን፤ የውሰድ-ወይም-ክፈል ጥቅም ላይ ላልዋሉ ኃይል/ጉልበት ክፍያዎችን የሚያካሂደውን፤የገንዘብ ወይም እንደገንዘብ የሚያገለግሉ ኩነቶቹን ያሳንስበታል፡፡

# ታሪፎችና የገንዘብ አቅርቦት መስህብነት

ለኃግስ የተመረጠው ታሪፍ/ዋጋና ዋጋ ነክ ጉዳዮች/አወቃቀር እንዳለ ሆኖ፤ታሪፉ የሚሰላበት የአሰራር ዘይቤ፤ግልጽና ለኃይል/ጉልበት ግዢው ስምምነት ደንብ ጋር የተቆራኘ ሊሆን ይገባል፡፡

ማንኛውም በታሪፉ ላይ የሚደረግ ለውጥ ሊካሄድ የሚገባው፤ ከማስተካከያ ዘዴዎች ጋር በተያያዘ ይኸውም ሁሉም ሊያከብረው የተገባ የሚያስተሳስር ስምምነት የተደረሰበትና እንደ የሻጩ እና አበዳሪው የራስ ትጋት ሂደት የተፈረመ ሊሆን ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ወይም የመወሰን ሥልጣን ላላቸው ተቆጣጣሪዎች ወይም ለፖለቲካዊ ማስተካከያ የተጋለጡ ታሪፎች፤ ከሰሜን አሜሪካ እና ምዕራብ አውሮጳ ውጪ ላሉ አበዳሪዎችና ኢንቨስተሮች፤ የረጅም ዘመን ከፍያን መሠረት ያደረገ ቁጥጥር ባህል ላላቸው፤ በአጠቃላይ ተቀባይነት የላቸውም፡፡

በነዚህ በባለሥልጣናት ጣልቃ ገብነት የሚካሄዱ ውሳኔዎችም ቢሆን፤ በሕዝባዊ አገልግሎት ላይ የሚሰማሩ ኢንቨስተሮች ፤እንደ አዲስ ኃይል ማሰራጨት በመሰሉ፤ ከፍተኛ መጠን ያለው ኢንቨስትመንት ከማካሄዳቸው በፊት፤የቁጥጥርን እርግጠኝነት መጠየቅ እየጀመሩ ነው፡፡ .

# የኤሌክትሪክ ኃይል ግዢ

አንዱ የታሪፍ አካል የሆነው ዋጋ በአብዛኛው የሚመሰረተው አንድም ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ጨረታ በማካሄድ ወይም **open book methodology** በመጠቀም ነው፤(አንዳንዴ **price discovery/ዋጋ ግኝት/ፈጠራ** ተብሎ ይጠራል)፡፡ እነዚህ ሁለት ዘዴዎች ከዚህ በታች ባሉት ክፍሎች ተገልፀዋል፡፡

# ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ጨረታዎች

በአብዛኞቹ የሕግ ሥልጣን ስር ባሉ አካባቢዎች፤ የግዢ ሕጎች፤ በተወዳደሪ ጨረታ እቃዎችንና አገልግሎትን ለመግዛት፤መንግሥትንና በመንግሥት የሚተዳደሩ ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያሉ ተቋማትን ይፈልጋሉ፤ ከአንዳንድ የተወሰኑ በቀር፤

ለነዚህ ሕጎች የሕዝባዊ ፖሊሲው መርህ የሚስማማ ነው፤በአግባቡ የተካሄደ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ጨረታ፤ውድድርን ተጠቅሞ የዓቅምና የኃይል/ጉልበት ዋጋ ላይ ቅናሽ ለማምጣት፤ እንዲሁም ግልጸኝነትን በኃይል/ጉልበት ገበያ ለመጨመር፤ በጣም ውጤታማ መሳሪያ ነው፡፡

እንዳለመታደል፤ የረጅም ጊዜ ኃይል/ጉልበት ግዢ ስምምነት ብዙውን ጊዜ የተራዘመና ውድ ሂደት ነው፡፡ በተጨማሪ፤አንዳንድ የግዢ ሂደቶች በጣም ውስብስብ ወይም ቴክኒካዊ ስለሆኑ፤ ድርቅ ያለ ቀመር አዘል አቀራረብ ወደ ጨረታ ሂደቱ ይዞ መቅረብ፤ለአስተናጋጁ አገር ምናልባት ምርጥ ውጤት ላያስገኝ ይችላል፡፡

በአንዳንድ ጉዳዮች፤ትርጉም አዘል ውድድርም እያለ፤ እንዲሁም ፕሮጀክቱ ለአገሪቱ ጥሪ ገቢ የሚያስገኝ ሆኖ እያለ፤የአንድን ድብልቅ ፕሮጀክት ለየት ያሉ ባህሪያት ለቀቅ ብሎ ማሰተናገድ አለመቻል፤ አንድን ፕሮጀክት ወደፊት እንዳይሄድ ማገድ ይሆናል፤

ግዙፍ መጠን፤ የፕሮጀክት ፋይናንስ ያላቸው የኃይል/ጉልበት ፕሮጀክቶች ቀዳሚ ምሳሌ ናቸው፡፡ በተካሄደው ከሁኔታዎች ጋር አብሮ መሄድ /መለሳለስ/፤ሁሉም በነዚህ ፕሮጀክቶች የተሳተፉ አካላት ፤ ጨረታ-ቀደም ውይይት ከአስቀድሞ የተመረጡ ተጫራቾች ጋር ለማካሄድ እንዲሁም ጨረታ-መለስ ድርድሮችን በ ሀ) በገዢው/ተጠቃሚው በተላለፈው የሃሳብ ሰነድ አቅርቡ ጥያቄ መሰረት ምላሽ የሆነ፤በሚያቀርቡት የሃሳብ ሰነድ ላይ፤በተመረጠው ተጫራች የተወሰዱ ልዩነቶች እንዲሁም ለ)የኃይል ግዢ ስምምነቱ ሥራ ላይ ሲውል፤በአበዳሪዎች ሊቀርቡ በሚችሉ ትችት/አስተያየት ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ አገላለጽ፤ አንድ ኤኮኖሚያዊ ታሪፍ በበለጠ ሁኔታ ሊፈጸም የሚችለው፤ በቂ ቁጥር ያላቸው አስቀድመው ያልተለዩ ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሃሳብ ሰነድ ማቅረባቸው ሲረጋገጥና የዚህ የውድድር ተፅእኖ ውጤቱ፤ ኤኮኖሚክ ታሪፍ ሲሆን ነው፡፡

በሌላ በኩል አስቀድመው ያልተለዩ ተጫራቾች ቁጥር እንደተጠበቀ ለማቆየት

1. የሃሳብ ሰነድ ማቅረቢያ ጥያቄው ውስጥ ምክንያታዊ፣ ፋይናንሲያዊ ደንቦችን እና ሁኔታዎችን ማካተት፤እንዲሁም አብረው የሚያያዙትን ረቂቅ የፕሮጀክት ስምምነቶች፤ በተጨማሪ ምክንያታዊና የተመጣጠነ ደንቦች የሚከተሉትን በተመለከተ ሀ) የጨረታ ደህንነት መጠን ለ) ገዢው/ተጠቃሚው በጨረታ ደህንነት ላይ ለማውጣት እድል የሚሰጡት ሁነቶች ሐ) የጨረታው ተገቢነት ቆይታ ጊዜ እና መ) በፕሮጀክቱ ስምምነቶች (እንዲሁም ኃግስን በመጨመር) ቅጽ መሰረት ለድርድሮች ጊዜ

2. በተለይ በውሃ ኃይል የሚመነጩ የኤሌክትሪክ ኃይል ፕሮጀክቶችን፤ እና ሌሎችም

በቦታውና በታሪፉ ምክንያት ዲዛይኑ በከፍተኛሁኔታ የሚጨናነቅ ፕሮጀክቶችን በተመለከተ፤ለፕሮጀክት ዲዛይኑ ተስማሚ ቴክኒካዊ መሰረት ለመፍጠር፤ ይኸውም የግንባታ ጊዜውን ርዝመት እና ለፕሮጀክቱ ቋሚ ንብረት የሚወጣውን ወጪ ተአማኒነት ያለው ትንበያ ለማካሄድ ስለስራው ተግባራዊነትና ደረጃ ማወቂያ ቅድመ ጥናት ማካሄድ፡፡

አንድ የተዋጣለት ጨረታ ከሌሎች ተጨማሪ ነገሮች ጋር የሚያስፈልጉት ሀ) ግልጽና እጥር ምጥን ያለ የሃሳብ መጠየቂያ ሰነድ፤ ይኸውም በደንብ የተገለጹ የፕሮጀክት ስምምነቶችን ረቂቅ የአያያዝ (ኃግስንም ጭምር)፤ ወይም ቢያንስ ፕሮጀክት ስምምነቶችን በተመለከተ ግልጽ፣እጥር ምጥን ያለ የደንብ ጽሁፎች ያለው እና ለ) አማካሪ የሆነ የጨረታ ሂደት፤ክፍት/ግልጽ የሆነ ውይይት በአስቀድመው በተለዩት ተጫራቾች እና ገዢው/ተጠቃሚው መካከል የሚያመቻች

# ተወዳዳሪ ጨረታዎች ለውስን ታሪፎች

በውስን ዋጋ ታሪፍ መዋቅር ስር፤ የሰነድ ሃሳብ መጠየቂ ደንቦች፤ ተጫራቾች ምናልባት ሊጨምር ለሚችል ዓቅም ውስን ዋጋ ይሰጡ ዘንድ ይፈለጋል፤ ነገርግን ይህ ለከፍተኛ ወጪ ከፋቾች ግዴታ አይደለም፡፡

ዓቅም ላይ የተመሠረተ አወቃቀሩ ከላይ እንደተገለጸው ሁኔታ የሆነ ታሪፍን በተመለከተ፤የሃሳብ ሰነድ መጠየቂያው በተለምዶ ተጫራቾችን በሚከተሉት ላይ ዋጋ እንዲሰጡ ይጠይቃል

1. ሰዓታዊ የመሰረታዊ ዓቅም ክፍያን (ይኸውም ሰዓታዊ የዓቅም ክፍያን ለማስላት የሚውለውን ደግሞም የወርሃዊ ዓቅም ክፍያን)
2. ተለዋዋጭ የሆነውን የሥራና የጥገና ክፍያ (ይኸውም የኃይል/ጉልበት ክፍያን ለማስላት የሚውል)
3. ሙቀት አመንጪ ተቋማትን በተመለከተ፤ የሙቀቱ መጠን (ይኸውም ደግሞ የኃይል/ጉልበት ክፍያን ለማስላት ይውላል) እና
4. በከሰል የሚለኮስ ኃይል አመንጪ ተቋማትን በተመለከተ፤ቀዝቃዛ ጅማሬ፣ሙቅ ጅማሬ፣የጋለ ጅማሬ ለማካሄድ የሚያስፈልገው የከሰል መጠን

ተጫራቾች ነጠላ ሰዓታዊ መሠረታዊ የዓቅም ክፍያ፤ይኸውም በኃይል/ጉልበት ግዢ ስምምነቱ እያንዳንዱ ዓመት የሚሰራ ጨረታ እንዲያስገቡ ሊጠየቁ ይችላሉ፤ ወይም የተለየ ሰዓታዊ መሠረታዊ የዓቅም ክፍያ ደረጃ ለእያንዳንዱ ዓመት እንዲጫረቱ ፈቃድ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

የሰዓታዊ መሠረታዊ የዓቅም ክፍያ ክፍል፤ ይኸውም ከቋሚ ወጪዎች ክፋይ ጋር የሚያያዝ፤ ከቋሚ ሥራዎችና ጥገና ወጪዎች ምክንያት የተፈጠረ ፤ብዙውን ጊዜ ከግሽበት ጋር ይደረደራል፤ ልክ እንደ ተለዋዋጭ ሥራዎችና ጥገና ክፍያ፡፡

የማይሰራጭ ቴክኖሎጂ በመጠቀም (በቀዳሚነት ታዳሽ ኃይል) የኤሌክትሪክ ሃይል የሚያመነጭ ፕሮጀክት ኩባንያን በተመለከተ፤ የሃሳብ ሰነድ መጠየቂያው ተጫራቾችን የአንድን ጉልበት/ኃይል ዋጋ በሣንቲም በተገለፀ መልኩ (ወይም ሌላ የገንዘብ ዓይነት) (kWh) ለኪዋሰ ወይም ዶላሮች (ወይም ሌላ የገንዘብ ዓይነት) (MWh) ለሜዋሰ እንዲጫረቱ ግድ ይላል፡፡

# ተወዳዳሪ ጨረታዎች ለታሪፎች ከወጪ ከፋቾች ጋር (ቁጥጥር በኮንትራት)

አንድ የቋሚ ዋጋ ታሪፍ መዋቅር በተፈጥሮው፤ ለፕሮጀክት ኩባንያው ብዙ ዓደጋዎችን ይመድባል፤ (እናም እንደዚሁ ለፕሮጀክቱ ስፖንሰሮችና አበዳሪዎች) ፡፡ በዚህም ምክንያት፤አሉ

የሚባሉ ተጫራቾች፤ ጨረታ ውስጥ ከመግባታቸውበፊት፤እነዚህን ዓደጋዎች ሊሸከሙት ወደሚችሉበት ደረጃ ማቅለል እስካልቻሉ ድረስ ወደ ጨረታው አይገቡም፤

ተጫራቾች እነዚህን ዓደጋዎች መቀነስ እስካቻሉ ድረስ፤ያን ጊዜ (i) የጨረታ ዋጋን በመጨመር፤ ዓደጋውን ለመሸፈን የሚያስችል መንገድ መጠየቅ፤ወይም (ii)ጨረታው ውስጥ ጨርሶ አለመግባት፡፡ በአብዛኛው ሁኔታዎች፤ገዢው/ተጠቃሚዎች (እናም ቀጥሎም፤ በታሪፍ ውስጥ፤ኤሌክትሪክ ተጠቃሚዎች) አንዳንድ የዓደጋ ዓይነቶችን ለመሸከም በተሻለ ሁኔታ ላይ ናቸው፡፡ እነዚህን ዓደጋዎች ወደ ገዢው/ተጠቃሚው ማምጣት፤ ውጤቱ ዝቅ ያለ ታሪፍ ይሆናል፤ እንዲሁም እነዚህን ዓደጋዎች ፕሮጀክት ኩባንያው እንዲሸከማቸው ቢደረግ፤ ፋይናንስ ማግኘት ያልቻሉ ፕሮጀክቶችን ፋይናንስ የማድረግ አቅም ይፈጠራል፡፡

ለምሳሌ እንደ አጠቃላይ፤መደበኛ ተጫራቾች ምንም ቢሆን ቋሚ የጨረታ ዋጋ አያቀርቡም፤ከኢንጂኔሪንግ፣ግዢ፣እና ኮንስትራክሺን (ኢግኮ) ኮንትራክትር ጋር ቢያንስ ስለወሳኝ የሆኑ ደንቦች እና ሁኔታዎች እንዴት የኢግኮ ኮንትራክተሩ የፕሮጀክቱን ምህንድስና፣ግዢ፣ግንባታ፣ መትከል፣ እና ኮሚሽን ማካሄድ እንዲሁም የኢግኮን ኮንትራት ዋጋ፤በተመለከተ ስምምነት ሳይደርሱ፤ይህ ደግሞ አብዛኛውን ጊዜ፤ መደበኛ ተጫራቾች የኢግኮ ኮንትራክተር የእነርሱን የጨረታ ቡድን እንዲቀላቀል እንዲጋብዙ ያደርጋቸዋል፤ ይህ ደግሞ ብዙ ወደኋላ መንተቶችን ይፈጥራል፡፡

አንደኛ፤ ተጫራቾች በጨረታው የመጀመሪያ ሂደት ከኢግኮ ኮንትራክተሮች ጋር ስምምነት ለመድረስ ተጨማሪ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል፡፡ከዚያም በኋላ ኢግኮ ኮንትራክተሮች የእነርሱ ዋና መሣሪያ አቅራቢዎች ጋር ስምምነት ሊያደርጉ ይገባል፡፡

ሁለተኛ፤ ለአንድ የተለየ ፕሮጀክት የግንባታ ሥራ፤ በገበያ ያሉት የኢግኮ ኮንትራክተሮች ቁጥር ጥቂት ከሆነ፤ ወይም የተፈለገውን የመሣሪያ ዓይነት ማቅረብ የሚችሉ አቅራቢዎች ቁጥር ትንሽ ከሆነ፤ያን ጊዜ ለሁሉም ፍላጎቱ ለአላቸው ተጫራቾች ሊበቁ የሚችሉ የኢግኮ ኮንትራክተሮች ላይኖሩ ይችላሉ፡፡

ለምሳሌ፤ በሰብሰሓራአፍሪቃ፤በውሃኃይል ኤሌክትሪክ የሚያመነጨ/ሃይድሮኤሌክትሪክ/ ረቀቅ ያሉ ፕሮጀክቶችን መገንባት ለሚችሉ ለኢግኮ ኮንትራክተሮች፤ ያለው ገበያ ውስን ነው፤ ደግሞም ሌላም ዓደጋ አለ፤ለቋሚ ዋጋ ታሪፍ ጨረታ ማካሄድ ለአንዳንድ አቅሙ ላላቸው ገንቢዎች ውጤቱ በጨረታው መሳተፍ እንዳይችሉ ማድረግ ይሆናል፤ ምክንያቱም ከእነርሱ ጋር አብረው ሊወግኑ የሚችሉ የኢግኮ ኮንትራክተሮች የሉምና፡፡

**ቁጥጥር በኮንትራክት/ Regulation by Contract** / ለቋሚ ዋጋ ታሪፍ ሞዴል ሌላ አማራጭ ነው፡፡ ቁጥጥር በኮንትራክት በእያደጉ ያሉ የገበያ ኤኮኖሚዎች ተፈታታኝ የሆኑ ፕሮጀክቶችን ለማስነሳት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

የቁጥጥር በኮንትራክት ባህርዩ፤በአንድ ወይም ተጨማሪ መደበኛ ስምምነቶች(በተለምዶ ኃግስ)፤ አስቀድሞ ዝርዝር ስምምነቶችን መዳሰስ፤ ይኸውም፤ አንድ ነፃ ኃይል/ጉልበት አምራች ፕሮጀክት /ነኃአፕ/ የሚጠይቀውን ዋጋ ለመወሰን የሚያስችልውን /ፎርሙላ/ ቀመሮች፤ ይህ ማለት ግን **ዋጋው** በኮንትራቱ ተለይቶ ይቀመጣል ማለት አይደለም፡፡

*በዚያ ፈንታ፤ ይህ ማለት፤ ታሪፉን በጋራ የሚወስኑት የእያንዳንዱ ወጪ መሰረታዊ ነገሮች* ***እያያዝ*** *፤ የሚገለጹት በኮንትራቱ ውስጥ በሚገኙ ዝርዝር ቀመሮች ነው፡፡*

ከ/ IPP/ **ነኃአፕ** አግባብ አንጻር፤ ቋሚ-ዋጋ ታሪፍ ሞዴል

- በጨረታ መዝገቦች ገዢው/ተጠቃሚው የሚከፍለውን ታሪፍ ለመመስረት የሚጠቀመውን ስሌት በመግለጽ፤ ገዢ/ተጠቃሚዎችን እውነተኛ ተወዳዳሪ ጨረታ እንዲያካሂዱ ይፈቅድላቸዋል፤

- ገዢ/ተጠቃሚዎች፤ ከላይ የተገለጹትን ዓደጋዎች በከፍተኛ ሁኔታ እንዲዘጋጁባቸው በማድረግ፤ በዚያውም ታሪፍን ዝቅ በማድረግ እና ብዙና ሰፋ ያሉ የገንቢዎች ቁጥር ፕሮጀክት ለማካሄድ፤በጨረታው ለመሳተፍ ፍላጎት እእንዲያድራባቸው ማድረግ

- ተጫራቾች፤በቁጥር ውስን ከሆኑ፤ ምናልባትም ከቴክኒክ አንጻር የሚፈታተን ፕሮጀክት የመገንባት ፍላጎት ካላቸው  የኢግኮ ኮንትራክተሮች ጋር እንዲተባበሩ አያስገድድም፤

ከላይ በተጠቀሰው መልኩ የተዋቀረውን ዓቅም ተኮር ታሪፍ በተመለከተ፤ የሃሰብ ሰነድ ጥያቄ፤ በቁጥጥር በኮንትራት ስሌት የተቀመጠ ታሪፍን የሚጠቀም ፕሮጀክትን፤እንደተለመደው ተጫራቾች ለ -እንዲጫረቱ ይጠይቃል

1. የሚታሰበው ዓመታዊ ግኝት፤ ስፖንሰሮች ከኢንቨስትመንታቸው የሚጠብቁት፤ የታቀደው ፋብሪካ ህልውና ከእውነታው ፋብሪካ ህልውና ጋር እኩል ነው ብሎ በመገመት
2. ነኃአ ፕሮጄክት በልማት ወጪዎች ላይ ሊጨምር የሚችለውን በመሠረታዊ የክፍያ መጠን ላይ፤ይኸውም መሠረታዊ የዓቅም ክፍያን ለማስላት የሚውለው ላይ  ጣሪያ ማበጀት
3. ወርሃዊ ቋሚ የሥራና የጥገና ክፍያዎች፤እንዲሁም
4. ተለዋዋጭ የሥራና የጥገና ክፍያ

እጅግ ኤኮኖሚካዊ ጠቀሜታ ያለው የጨረታ ዋጋ የሚመረጠው፤ ፋይናንሲያዊ ሞዴል በመጠቀም ሲሆን፤ ይኸውም የትኛው የጨረታ ዋጋ፤ዝቅተኛ የተጣራ ፋይናንሲያዊ ግዴታዎች ለገዢው/ተጠቃሚው በሜዋ /MW/ ዓቅም በኃግስ ዘመን፣በየተጣራ የአሁን ዋጋ አገላለጽ ያመጣል የሚለውን በመለየት ነው፡፡

የገዢው/ተጠቃሚውን የተጣራ ፋይናንሲያዊ ግዴታዎች የተጣራ የአሁን ዋጋ ለማስላት፤ ፋይናንሲያዊ ሞዴልን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ለመጠቀም፤የሚከተሉትን በተመለከተ ግልፅ ግምቶችን መጠቀም ያስፈልጋል፡- (i) የኮንትራትዋጋበኢግኮኮንትራትሥርተከፋይየሚሆን (ii) ዕዳና ነጻ ሃብት ምዘና (iii) ከፕሮጄክቱ ብድሮች የሚጠበቁ ፋይናንሲያዊ ደንቦች እና (iv) ብዛት ያላቸው ሌሎች ግምቶች

በኃግስ ድርድር ወቅት፤ ፋይናንሲያዊ ሞዴሉ ለሁሉም ፓርቲዎች ይጋራል፡፡ ገዢው/ተጠቃሚው፣ነኃአፕ፣ እና አበዳሪዎች፣ ሁሉም በቡድናቸው ውስጥ ፋይናንሲያዊ ሞዴሉን ኦዲት ለማድረግና ለመመርመር አንድ ሰው ሊኖራቸው ይገባል፡፡


በቁጥጥር በኮንትራት አቀራረብ ስር፤ ኃግሱ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ነኃአፕ በኃግስ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ይፈለጉበታል ሀ) ኢግኮ ኮንትራክተርን ለመምረጥ ዓለምአቀፋዊ ተወዳዳሪ ጨረታ ማካሄድ እና ለ) ለፕሮጀክቱ ፋይናንስ ዝግጁ ማድረግ፡፡ የመሠረት ዓቅም ዋጋ ያን ጊዜ ይገመታል በፋይናንሲያዊ መዘጋት በኢግኮ ኮንትራት ስር ተከፋይ ትክክለኛውን ኮንትራት ዋጋ ፤ ትክክለኛ የዕዳ ዝርዝሮች፤ እና ትክክለኛ እስከ ዛሬ የወጡ የልማት  ወጪዎች፤እንዲሁም በንግዳዊ ሥራዎች ቀን የሚፈጠሩ የልማት ወጪዎችንም በመጨመር

እነዚህ ስሌቶች፤ ከንግዳዊ የሥራ ቀን በኋላ፤ የመጨረሻውን የዓቅም ዋጋ ለመወሰን የሚካሄዱ ይሆናል፡፡

የዚህ መዋቅር የተጣራ ውጤት፤ የተለዩ የወጪ ከፋቾች ( የሰነድ ሃሳብ ማቅረብ ጥያቄን ተከትሎ የጨረታ ዋጋዎች ከተሰጡ በኋላ፤ ወጪያቸው የሚወሰን ዓይነቶች) የልማት ገንቢዎችን ዓደጋ ወሳኝ በሆነ መልኩ ለመቀነስ ሊውል ይችላል፤ ይህ ደግሞ በሌላ በኩል የሃሳብ ሰነድ የሚያቀርቡ ቀድመው የተለዩ ተጫራቾችን ቁጥር ለመጨመር እና በመጨረሻ ውጤቱ ይበልጥ ተወዳዳሪ ዋጋ ይሆናል፡፡

## አመላካች ሕዝባዊ የግዢ ሂደት

ከታች የሚታየው ጊዜን ወካይ መሥመር እንዲሁ ማሳያ ነው፤ምናልባት ሊደራረብም ይችላል፤



Call for expressions of interest
Develop PQ
Bid preparation & submission
Evaluate and shortlist bidders
Develop & issue RFP, PPA, other key project documents
Bidder consultations
Bid preparation & submission
Bidder submission of finance, construction & operation term sheets
Evaluation of Bids & selection of preferred bidder
Negotiation of exceptions & signature of PPA
2-4 months
6-9 months
1-2 months
2-6 months
RFQ
RFP & Bid Submission
Evaluation
Negotiation

# የሽያጭ ዝርዝር  እና ክፍያዎች

## የሽያጭ ማሳወቂያ - Invoices

ለአቀረበው ጉልበት/ኃይል ክፍያ ለማግኘት፤ በተጨማሪ ማንኛውም ተያያዥ የዓቅም ክፍያ፤ ሻጩ ለገዢው በየጊዜው የሽያጭ ማሳወቂያ ሊልክ ይገባል፤የክፍያው መጠን በኃግስ ስምምነት በተደረሰበት የገንዘብ ዓይነት የሆነ የክፍያ ዝርዝር ሰነድ የሚላከበት ጊዜ በአብዛኛው በየወሩ ነው፡፡ የሽያጭ ዝርዝሩ በአጠቃላይ የሚከተሉትን ክፍሎች የሚያካትት ይሆናል፡፡ ሀ) የዓቅም ክፍያ ለ) የጉልበት/ኃይል ክፍያ ሐ) ተያያዥ ክፍያዎች( ስምምነት ከተደረሰበት በላይ ለሆኑ ማንኛውም አዲስ ጅማሬ) እና መ) መፍትሄ ለተሰጣቸው ጉዳቶች እና ገዢው ሊከፍል የሚገባው የቅጣት መጠን ካለ፡፡ በሻጩ የተዘጋጀውን የሽያጭ ዝርዝር ገዢው የመመርመር መብት አለው፤ እንዲሁም ለቀረበለት የሽያጭ ዝርዝር ሰነድ ላይ ካልተስማማ፤በመካከላቸው ስምምነት በተደረሰበት ቀናት ውስጥ፤ የሽያጭ ሰነዱን በተመለከተ ማብራሪያና ማረጋገጫ  እንዲቀርብለት መጠየቅ ይችላል፡፡

## ጥቅም ላይ የዋለ ኃይል/ጉልበት መጠን አለካክ

ከታሪፍ ድርድር በኋላ አንዱ ጠቃሚ ነገር፤ ለገዢው የሚላከውን የኃይል/ጉልበት እና ዓቅም መጠን እንዴት መለካት የሚለው ነው፡፡ በመሠረቱ ሻጩ የኃይል/ጉልበት ፋብሪካው ምርትን መለኪያ ቆጣሪ /ሜትር/ መግዛትና መትከል ሃላፊነት አለበት፡፡ የተጣራው ምርት እና ኃይል ለገዢው ክፍያ ይፈጽምበት ዘንድ የሚላከው በአብዛኛው የሚለካው በተቆጣጣሪው የታተመ የመለኪያ ኮድ መሠረት ነው፡፡ ፓርቲዎቹ/ባለጉዳዮቹ/ በሜትሮቹ ላይ (ዋና ሜትር እና ተለዋጭ/ደጋፊ ሜትር) ለመለካት ስራ የሚውሉት ላይ፤ ስምምነት ያደርጋሉ፤ እንዲሁም እነዚህ መለኪያዎች የሚለኩትን የየትኛውን የአቅርቦት ቦታ እንደሆነ፡፡ እነዚህ ሜትሮች/መለኪያዎች/ በየጊዜው በሁለቱም ቡድኖች ምርመራና ሙከራ ይካሄድባቸዋል፡፡ የሽያጭ ዝርዝር ለመላክ የሜትሮች ንባብ በሚካሄድበት ቀን፤ የሁለቱም ቡድኖች ተወካዮች በአጠቃላይ ሊገኙ ይገባል፡፡

## ክፍያዎች

ክርክር የሌለባቸው ክፍያዎች፤ በፓርቲዎቹ በኃይል ግዢ ስምምነቱ  እንደተገለጸው ስምምነት በተደረሰበት የገንዘብ ዓይነት ሊካሄዱ ይገባል፡፡

**የገንዘብ ዓይነት ወይም ምንዛሪ፡** በኃይል ግዢ ስምምነቱ ለክፍያ የሚውለው የገንዘብ ዓይነት ድርድር የተካሄደበት ጉዳይ ነው፤ እናም እንደ ተስማሚዎቹ ሊለያይ ይችላል፡፡

እያደጉ ባሉ ገበያዎች፤ሻጮች ብዙውን ጊዜ የውጭ ምንዛሬ አትኩሮት አላቸው፡፡ የውጭ ምንዛሬ ትኩረት የሚነሳባት ምክንያት፤ ጠቀም ያለው የፕሮጀክቱ ወጪ በውጭ ምንዛሬ (ለምሳሌ እንደ የአሜሪካ ዶላርና ዩሮ) ገንዘብ ስራ ላይ የዋለ ከሆነ ነው፡፡ ሻጩ ክፍያውን ከገዢው የሚያገኘው በአካባቢው የአገር ገንዘብ ከሆነ ለአበዳሪዎቹ በውጭ ምንዛሪ መመለስ መቻሉን ማረጋገጥ አለበት፡፡

ክፍያ የሚካሄድበት የገንዘብ ዓይነት ብዙውን ጊዜ በአገር ውስጡ የገንዘብ ዓይነት ጥንካሬ

እንዲሁም ምን ያህል ገንዘቡ በቀላሉ ተለዋጭ ነው የሚለው ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች የአገርውስጡ የገንዘብ ዓይነት የረዥም ጊዜ ጥንካሬ እና በአጠቃላይ ይህንኑ ጥንካሬውን ይዞ እንደሚቀጥል ከተረጋገጠ፤ንግስ በአገርውስጥ ገንዘብ የሚከፈል ይሆናል፡፡

ይህ የጥንካሬ ታሪክ በማይታይባቸው በሌሎች ገበያዎች ክፍያው የሚካሄደው 1) የገዢውን ክፍያ በአገር ውስጥ ገንዘብ፤ በገበያ ባለው የገንዘብ ምንዛሪ መጠን፤ከውጭ ምንዛሪው ጋር ልክ ማውጣት ወይም 2) ገዢው ለሻጩ በቀጥታ በውጭ ምንዛሪ መክፈል

እንደ አማራጭ፤ታሪፉ ይበልጥ የተቀመረ የውጭ ምንዛሪ የወቅቱን ልክ ቀማሪ ስሌት ሊያካትት ይችላል፡፡ ይህ የወቅቱን ልክ ቀማሪ ስሌት ፤ ጥቅም ላይ የሚውለው፤ ሻጩ የውጭ ምንዛሪ ትኩረቱን እንደ ከኪሣራ ራስን መጠበቂያ የሚጠቀምበት ከሆነ ነው፡፡ ይህ የውጭ ምንዛሪን እንደ ራስ መጠበቂያ መጠቀም በአብዛኛው ጥቅም ላይ የሚውለው የአገርውስጡ ምንዛሪ ገበያ በከፍተኛ ሁኔታ ተለዋዋጭ በሆነበት ነው፡፡

**የአከፋፈል ዘይቤዎች፡** የአከፋፈል ዘይቤ ከፓርቲዎቹ/ባለጉዳዮቹ/ ስምምነት ጋር የተያያዘ ነው፤ነገርግን ብዙውን ጊዜ ኤሌክትሮኒክ ሲስተምን በመጠቀም ወደ ተሰየመው የሻጩ የሂሳብ መዝገብ በማስተላለፍ ነው፡፡

***መግባባት ያልተደረሰባቸው የክፍያ መጠኖች*፡** በተለምዶ ክፍያ ይፈጸምባቸው ዘንድ ወደ ገዢው ከተላኩ የክፍያ ዝርዝሮች፤ የትኛውም መጠን ተቀባይነት ባያገኝ፤ ይህ ከክፍያው እንዲወጣ ተደርጎ፤በኃይል ግዢ ስምምነቱ ስር ባለው አለመግባባትን መፍቻ ሥርአት ውስጥ እንደ አንድ የመከራከሪያ ነጥብ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ገደብ ለተደረገባቸው ለነዚህ ሁሉ መሰል ክፍያዎች፤ በአለመግባባትን መፍቻ ሥርዓት ውስጥ እንደተገለጸው፤ በኋላ ላይ ለሻጩ ተከፋ የሚሆን፤ ወለድ መጠን ይታሰብባቸዋል፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች፤ ባለጉዳዮቹ እነዚህን አለመግባባትን የፈጠሩ ክፍያዎችን በተመለከተ አለመግባባቱ እስኪፈታ ድረስ በ escrow ሂሳብ መዝገብ እንዲቀመጡ ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

**የዘገየ ክፍያ፡** ማንኛውም የዘገዩ ክፍያዎች ( ይህም ሲባል፡ በባለጉዳዮች ስምምነት ከተደረሰበት ጊዜ ገደብ በኋላ የተደረጉ ክፍያዎች) ወለድ ይታሰብባቸዋል፤ይኸውም በወለድ መጠን (አንድም በአገር ውስጥ የወለድ መጠን ወይም በውጭ አገር የወለድ መጠን) ስምምነት የተደረሰበት በባለጉዳዮቹ ክፍያው ሊካሄድ ይገባ ከነበረበት ቀን ጀምሮ እስከ ክፍያው የሚካሄድበት ቀን ድረስ ላለው ጊዜ፡፡ ለወለድ መጠኑ መሠረቱ በአጠቃላይ፤ በባንኮች መካከል ያለ መጠን ለገንዘብ ገበያው፤ በአገሪቱ ማእከላዊ ባንክ የታተመ ለ አገር ውስጥ የገንዘብ አይነት ጉዳዮች ወይም ለ LIBOR(ለንደን ዓለም አቀፍ ባንክ የተሰጠ ዋጋ/ለኢባተዋ/) /EURIBOR(ዩሮ ኢንተርናሽናል ባንክ የተሰጠ ዋጋ/ዩኢባተዋ/) ለ US/EUR/አሜሪካ፣ አውሮጳ/ የውጭ ምንዛሪ ጉዳዮች።

# ለገዢ/ተጠቃሚ ግዴታዎች የብድር ድጋፍ

## የብድር ድጋፍ ለምን?

ይህ ክፍል፤ በኃግስ ስር ያሉትን የገዢው/ተጠቃሚው የክፍያ ግዴታዎችን ድጋፍ ለመስጠት፤ አንዳንዴ ጥቅም ላይ የዋሉ ዋና መሳሪያዎች ወይም ስልቶች ውስጥ ጥቂቶቹን ያነሳል፡፡

ይህ በጣም ጠቃሚ ጉዳይ ነው፤ በተለይ አንዳንዴ ገዢው/ተጠቃሚው በኃግስ በተቀመጠው ደንብ መሰረት የክፍያ ግዴታዎቹን ለመወጣት አቅምን በተመለከተ የሚያሳስብ ሁኔታ ሲኖር፡፡ ገዢው/ተጠቃሚው፤ የረጅም ጊዜ የኃግስ ክፍያዎች ግዴታዎችን የመወጣት አቅምን በተመለከተ አሳሳቢ ሁኔታ፤ በተለያዩ ምክንቶች ሊነሱ ይችላሉ፡፡

ከእነዚህ ውስጥ፤በማደግ ላይ ባሉ ገበያዎች የተለመደው ክስተት፤በመጨረሻ ስራ የሚውለው ታሪፍ ወጪ-ገላጭ አይደለም፡፡ በሌላ አገላለጽ በገዢው/ተጠቃሚው የኤሌክትሪክ ኃይል ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ በታሪፍ አከፋፈል መጠን የሚፈጠረው ገቢ፤ ገዢው/ተጠቃሚው ከኃይል አምራቾቹ የኤሌክትሪክ ኃይሉን ለመግዛት ያወጣውን ወጪ ( እንዲሁም ለራሱ ያወጣውን ወጪ፤ተግባራዊ በሆነበት) በተጨማሪ የማስተላለፍና የማሰራጨት ወጪዎችን የሚመልሱ አይደሉም፡፡ በዚህ ክስተት፤ ትክክለኛውን ወጪ ለማሳየት፤ የአገልግሎቱን ታሪፍ ከፍ ማድረግ ብዙ ጊዜ እንደ አማራጭ ያለ ፖሊሲ አይደለም፤ ቢያንስ በዚህ በቅርብ ጊዜ፤ ምክንያቱም ይህ በተጠቃሚዎች ላይ ሊፈጥረው የሚችለው ጎጂ ተፅእኖ እና እንዲሁም በተያያዥ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች፡፡ በዚህም ምክንያት ገዢው/ተጠቃሚው ብዙውን ጊዜ በበቂ ሁኔታ የብድር ተጠቃሚ አይደለም፤ እናም የመንግሥት ድጎማዎችን ይፈልጋል፤ ታሪፎች ሙሉበሙሉ ወጪን ገላጭ የሚሆኑበት ጊዜ እስኪመጣ ድረስ፡፡ የሆነ ዓይነት የብድር ድጋፍ ከሌለ በስተቀር፤ በእንዲህ ዓይነት የፋይናንሲያዊ ሁኔታ፤ ዓቅም እና ኃይል/ጉልበት ለገዢ/ተጠቃሚ ለሚሸጥ አንድ ነኃአፐ፤ ፋይናንስ ማስገኘት የሚቻል አይደለም፡፡

# የመንግስት ዋስትና (Sovereign Guarantees) እና የብድር ማስገኛ ደብዳቤዎች

እያደጉ ባሉ ገበያዎች፤ ገዢው/ተጠቃሚው በመንግሥት ባለቤትነት ሥር ያለ ተቋም በሆነበት፤ አበዳሪዎች በኃግስ መሰረት ለገዢው/ተጠቃሚው የክፍያ ግዴታዎች የብድር ድጋፍ ለመስጠት፤ አንዳንዴ ከመንግስ ዋስትና ያስፈልጋቸዋል፡፡ በዋስትናው ስር፤ መንግሥት፤ግዴታው ስለሆነ፤ ይህ በመንግሥት ስር ያለ ገዢ/ተጠቃሚ ዕዳውን መክፈል ባይችል፤ የክፍያውን ግዴታዎች ለመወጣት ይስማማል፡፡ ቢሆንም ቅሉ፤ ዋስትና በእውን ጠቃሚ የሚሆነው ዋስትና ሰጪው ተአማኒነት ሲኖረው ብቻ ነው፡፡

የአንድን ባለሥልጣን የብድር ተአማኒነት የሚያሳስቡ ጉዳዮች ካሉ፤ያን ጊዜ ይህን በባለሥልጣኑ ክፍያን አለማካሄድ ዓደጋ ለመድረስ አንዳንድ አስፈላጊ ነገሮችን አስቀድሞ ዝግጁ ማድረግ ያስፈልጋል፤የሚከተሉትን ጨምሮ

- ከፊል የዓደጋ ዋስትና ከዓለም ባንክ ወይም ከ አፍሪቃ ልማት ባንክ (አልባ)
- የማያስከብር የባለሥልጣን ዋስትና ኢንሹራንስ ፖሊሲ፤ ከባህር ማዶ የግል ኢንቨስትመንት ኮርፖሬሽን (ባግኢኮ)፤
- የፖለቲካ ዓደጋ ኢንሹራንስ ከ ብዙጎንዮሽ ኢንቨስትመንት ዋስትና ኤጀንሲ (ብኢዋኤ) እና
- ዋስትና ከ (ባግኢኮ) ወይም አንድ የኤክስፖርት ብድር ኤጀንሲ

በተጨማሪ፤የባንክ የብድር ደብዳቤዎች፤ ከየልማት ፋይናንስ ተቋማት(ልፋተ) ወይም ኤክስፖርት ብድር ኤጀንሲ የብድር ድጋፍ ጎን ጥቅም ላይ ሲውሉ የአጭር ጊዜ የገንዘብ ችግሮችን ለመፍታት ይችላሉ፡፡ እነዚህ የብድር ደብዳቤዎች ሊሰራጩ የሚገባው የብድር ተኣማኒነት ባለው የፋይናንስ ተቋም ሊሆን ይገባል፡፡

በመንግሥት ባለቤትነት ሥር ያሉ ገዢዎች/ተጠቃሚዎች፤ የኃግስ የክፍያ ግዴታዎቻቸውን ለመሸፈን የሚደረግ የመንግስት ዋስትናዎች ዝግጅት፤የመንግሥትን ቀጥተኛ የውጭ ኢንቨስትመንትን የመሳብ አቅም፤ ለትልቅ የኃይል/ ጉልበት ፕሮጀክቶች ፋይናንስ ግኝት ያጠናክራል፡፡

ያ ሲባል፤በዚህ መልኩ ድጋፍ እንዲሰጥ የተጠየቀ መንግሥት፤ዋስትና ከመስጠቱ ወይም የብድር ደብዳቤ ከማዘጋጀቱ በፊት፤የታሰበው ፕሮጀክት ንግዳዊ አዋጭነቱን ለራሱ ለማረጋገጥ ጠንከር ያለ ጥናት ማካሄድ አለበት፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አሰሳ በተጨማሪ መንግሥትን ዋስትናውን ወይም የብድር ደብዳቤውን ስራ ላይ ሊያውለው ከመረጠ፤ ተያያዥ ፋይናንስያዊ መጋለጥን ማስላት እንዲችል ያደርገዋል፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ፤ መንግሥታት፤ በመንግሥት ባለቤትነት ስር ላሉ ተቋማት፤ ግልጽ የሆነ የብድር ድጋፍ ለ ክፍያ ግዴታዎች ለመስጠት፤ የመንግስ ዋስትናዎች ወይም የብድር ደብዳቤዎች ለማውጣት፤ ሁል ጊዜ ዝግጁ አይደሉም፡፡ በአንዳንድ ጉዳዮች፤ የመንግሥታት

እነዚህን መሰል ድጋፎች ለመወሰን ያላቸው ዓቅም፤ መንግሥት ባለበት ዘላቂ ሕዝባዊ የዕዳ ደረጃዎችን የማስጠበቅ ሃላፊነት ምክንያት፤ሊታቀብ ይችላል፡፡

በነዚህ አኳኋኖች፤መንግሥታት አንዳንዴ ሕጋዊ ማሰሪያ የሌላቸው የምቾት ደብዳቤዎች ሊያወጡ ይችላሉ፤ ነገርግን ለኢንቨስተሮችና አበዳሪዎች "ለስላሳ ምቾት" የሚሰጡ፤ ይኸውም መንግሥት ገዢው/ተጠቃሚው ኪሳራ ላይ እንዲወድቅ የማይፈቅድለት፤ ጣልቃ በመግባት ገዢው/ተጠቃሚውን በመርዳት ለአበዳሪዎች ያለበትን ግዴታዎች እንዲወጣ እንደሚያስችል፡፡ እነዚህ የለስላሳ ምቾት ዘይቤዎች፤ ብዙውን ጊዜ አንድ ፕሮጀክት ትልቅ የውጪ ኢንቨስትመንት መጠኖችን መሳብ እንዲችል ለማድረግ በቂ አይደሉም፡፡

# ኤስክሮው አካውንት (Escrow Account)

ሥራ ላይ የሚውል ተንቀሳቃሽ ገንዘብ አቅርቦትን በተመለከተ፤ ገዢው/ተጠቃሚው በኃግስ ስምምነት ሥር ለአለበት የክፍያ ግዴታዎች **ኤስክሮው አካውንት** ለማቋቋም ግድ ሊለው ይችላል፡፡ ይህ የ **ኤስክሮው አካውንት** በኃግስ ስር በተቀመጠው መሰረት የተወሰኑ ወራት ክፍያን የሚያክል መጠን ሊይዝ ይገባል፤ ለምሳሌ ለተወሰኑ ወራት የሚጠበቀውን ጠቅላላ ክፍያ መሰረት በማድረግ ወይም ለተወሰኑ ወራት የሚከፈል የዓቅም ክፍያን ብቻ መሰረት በማድረግ፡፡

ገዢው/ተጠቃሚው በኃግስ መሰረት ሲጠየቅ ክፍያ ማድረግ ባይችል፤ ያን ጊዜ ፕሮጀክት ኩባንያው ከዚህ **ኤስክሮው አካውንት** ማውጣት ይችላል፤ ይህ ደግሞ ግጭትን ማስታረቂያ ሆኖ፤ ፕሮጀክት ኩባንያው ስራውን እንዲቀጥል እንዲሁም ያለበትን ዕዳ እንዲከፍል ያስችለዋል ምንም እንኳን ገዢው/ተጠቃሚው መክፈል ባይችልም፡፡

ከ **ኤስክሮው አካውንት** ሂሳብ ወጪ ከሆነ በኋላ፤ ገዢው/ተጠቃሚው ወዲያውኑ (ወይም በተወሰኑ ጥቂት ቀናት ውስጥ) ወጪውን መተካት አለበት፡፡ ነገርግን ገዢው/ተጠቃሚው ይህን የ**ኤስክሮው አካውንት** መተካት ካልቻለ (ወይም በአንዳንድ ሁኔታዎች የሆነ ዓይነት የመተካት ዋስትና ማግኘት መቻል) በኃግስ መሰረት ደንብን የመጣስ ወቅት ይሆናል፡፡ አንድ **ኤስክሮው አካውንት** ከአሰራር አንጻር ከብድር ደብዳቤ ጋር እኩል ሲሆን እናም የአጭር ጊዜ ለስራ የሚውል የጥሬ ገንዘብ እጥረትን ለመድረስ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡

# አስቀምጥ እና ጥራ አማራጭ ስምምነቶች

አስቀምጥ እና ጥራ አማራጭ ስምምነቶች፤ አንዳንዴ የክፍያ ዓደጋን፤ ከመንግሥት ባለቤትነት ሥር ካለ ገዢ/ተጠቃሚ፤ በቀጥታ ወደ መንግሥት ለማስተላለፍ እንደ አንድ የአሰራር ዘይቤ ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

**የአስቀምጥ አማራጭ** (put option) የአማራጩን ባለቤት፤ ብዙውን ጊዜ ሻጩን፤ የኃይል/ጉልበት ፕሮጀክትን፤ የሆነ ቆስቋሽ የሆነ ክስተት/ቶች/ ሲፈጠር -በዋነኝነት ማብቃያ ዘመን፤ ቅድሚያ በተወሰነ ዋጋ፤ መንግሥት ተገድዶ እንዲገዛ የማድረግ ስልጣን ይሰጠዋል፤

በሌላ በኩል **የጥራ አማራጭ** (call option)፤ የአማራጩን ባለቤት ብዙውን ጊዜ ባለሥልጣኑን፤ የኃይል/ጉልበት ፕሮጀክትን፤ የሆነ ቆስቋሽ የሆነ ክስተት/ቶች/ ሲፈጠር፤ ቅድሚያ በተወሰነ ዋጋ፤ ሻጩ ተገድዶ ለመንግሥት እንዲሸጥ የማድረግ ስልጣን ይሰጠዋል፤

በሁለቱም ክስተቶች መንግሥት በስተመጨረሻ የንብረት ባለቤት ይሆናል፡፡ በሁለቱም ክስተቶች የአገዛዙ ሁኔታ የሚወሰነው የፕሮጀክት ኩባንያው ቋሚ ዕዳ ከሌሎች የይገባኛል ጥያቄዎች በፊት

ተከፋይ ይሆናል ከሚል አንጻር ሲሆን፤ይህን በማድረግም አበዳሪዎችን ለመንከባከብ፡፡

የመሸጫ ዋጋውን መወሰኛ ቀመር ደግሞ፤ ትክክለኛው ቆስቋሽ ወቅት በሻጩ ስህተት፣በገዢው ስህተት፣ወይስ ሌላ ክስተት ስህተት፤ የሚለውን ግምት ውስጥ ያስገባል፡፡ በመጀመሪያው ሁኔታ፤ብዙውን ጊዜ ገዢው የታቀዱ ትርፎቹን እንደ መግዣ ዋጋ አካል አድርጎ እንዲወስድ መብት አይኖረውም፡፡ ይህ ሰፋ ባለ ሁኔታ ከስራዘመን መገባደድ በኋላ ግዴታዎች በሚል ስር ይነሳል

# ከፊል ዓደጋ ዋስትናዎች

ከፊል ዓደጋ ዋስትናዎች (ከዓዋ)፤እያደጉ ባሉ ገበያዎች፤በብዙኀንዮሽ የልማት ባንኮች እየቀረቡ ያሉ፤እንደ ዓደጋ ማቅለያ መሣሪያዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ከዓዋ በተለይ ጠቃሚ የሚሆኑት፤ በመንግሥት ባለቤትነት ስር ያለ ገዢ ወይም ባለሥልጣን የፕሮጀክት ኮንትራት ግዴታዎቻቸውን የሚሟላት ዓቅምን በተመለከተ አሳሳቢ ሁኔታ ሲኖር ነው፡፡

ከዓዋ በተለይ ከፊል ብድር ጥበቃ ለግል አበዳሪዎች ይሰጣል፤ ይኸውም በመንግሥት ባለቤትነት ስር ያለው ገዢ ወይም መንግሥት ራሱ ያለባቸውን የክፍያ ግዴታዎች በኃግስ በተቀመጠው መሰረት ሳይፈጽሙ የሚቀሩበት ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡

የቆስቋሽ ክስተቶች ዝርዝር ለከዓዋ፤ ለፖለቲካዊ ዓደጋዎች ወቅቶች የተወሰነ ነው፤ፋይናንሲያዊ ግዴታን በባለሥልጣን አለማክበር ጨምሮ፤ በተጨማሪ የኃግስ የሥራ ዘመን ማብቂያ ተከትሎ፤ ኃይል/ጉልበት ፋብሪካን የመግዛት ግዴታ ጋር በተያያዘ፡፡


ከፊል ዓደጋ ዋስትናዎች (ከዓዋ)፤እያደጉ ባሉ ገበያዎች፤በብዙኀንዮሽ የልማት ባንኮች እየቀረቡ ያሉ፤እንደ ዓደጋ ማቅለያ መሣሪያዎች ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ከዓዋ በተለይ ጠቃሚ የሚሆኑት፤ በመንግሥት ባለቤትነት ስር ያለ ገዢ ወይም ባለሥልጣን የፕሮጀክት ኮንትራት ግዴታዎቻቸውን የሚሟላት ዓቅምን በተመለከተ አሳሳቢ ሁኔታ ሲኖር ነው፡፡

ከዓዋ በተለይ ከፊል ብድር ጥበቃ ለግል አበዳሪዎች ይሰጣል፤ ይኸውም በመንግሥት ባለቤትነት ስር ያለው ገዢ ወይም መንግሥት ራሱ ያለባቸውን የክፍያ ግዴታዎች በኃግስ በተቀመጠው መሰረት ሳይፈጽሙ የሚቀሩበት ክስተት ሲፈጠር ነው፡፡

የቆስቋሽ ክስተቶች ዝርዝር ለከዓዋ፤ ለፖለቲካዊ ዓደጋዎች ወቅቶች የተወሰነ ነው፤ፋይናንሲያዊ ግዴታን በባለሥልጣን አለማክበር ጨምሮ፤ በተጨማሪ የኃግስ የሥራ ዘመን ማብቂያ ተከትሎ፤ ኃይል/ጉልበት ፋብሪካን የመግዛት ግዴታ ጋር በተያያዘ፡፡

ከዓዋ፤እነዚህን ዓደጋዎች ለሦስተኛ አካል ብዙኀንዮሽ ተቋማት፤ይኸውም ከግል ቡድኖች በተሻለ ዓቅም ማስተዳደር ለሚችሉ በብቃት ያስተላልፋሉ፡፡ የዓለም ባንክ ቡድን እና የአፍሪቃ ልማት ባንክ ለምሳሌ፤ ከፊል ዓደጋ ዋስትና ውጤቶችን ያቀርባሉ(እባክዎ ለዝርዝር መረጃ የግላቸውን ድረገጽ ይመልከቱ)፡፡ እነዚህ ከዓዋ፤ ፕሮጀክት ብድሮች በፕሮጀክት ኩባንያ እና ገዢው/ተጠቃሚውን በመወከል የብድር ደብዳቤ የጻፈውን ባንክ ያወጣውን ወጪ የመመለስ ግዴታ ዋስትና በመሆን ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ፡፡

### የከዓዋ መዋቅር ምሳሌዎች




# ፖለቲካዊ ዓደጋ ኢንሹራንስ

ብዙጎንዮሽ ኢንቨስትመንት ዋስትና ኤጀንሲ(ብኢዋኤ) እና ሓገራዊ ኤክስፖርት ብድር ኤጀንሲዎች በተጨማሪ ፤በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ለሚገኙ የኃይል/ጉልበት ፕሮጀክቶች፤ብድር የማጠናከር ፎርሞችን በማቅረብ ፤ ጠቃሚ ሚና በመጫወት ላይ ናቸው፡፡

ብኢዋኤ በዋናነት ፖሊቲካዊ ዓደጋ ኢንሹራንስ ይሰጣል፤ ይኸውም በቀዳሚነት የኩባንያ ሼር ኢንቨስትመንትን እና የሼር ባለቤቶች ብድሮችን በፕሮጄክቶች ውስጥ ለመደገፍ፡፡

ሃገራዊ ኤክስፖርት ብድር ኤጄንሲዎች፤አበዳሪዎችን እና/ወይም የኩባንያ ሼር ኢንቨስተሮችን ከአንዳንድ ግልጽ የሆኑ ፖለቲካዊ ዓደጋ ክስተቶች ለመጠበቅ ጥቅም ላይ የሚውሉ ፖለቲካዊ ዓደጋ ኢንሹራንስ ይሰጣሉ፡፡

ሃገራዊ ኤክስፖርት ብድር ኤጀንሲ ሽፋን፤ በተለይ ከአግባብ ያለው ኤጀንሲ አገር ኤክስፖርቶች ጋር የተሳሰረ መሆኑን ማስተዋል የሚገባ ነው፡፡ ከስር ያለው የኃይል/ጉልበት ፕሮጀክት፤በቂ የሆነ ኤክስፖርት መቶኛ ይዘት፤ ከኤክስፖርት አድራጊዎች በኤክስፖርት ብድር ኤጀንሲው አገርሊኖረው ይገባል፤ ከዚያ ኤክስፖርት ብድር ኤጀንሲ የፖለቲካ ዓዳጋ ኢንሹራንስ ለማግኘት ብቁ ለመሆን፡፡

ከከዓዋ ጋር በተመሳሳይ፤ እነዚህ ምርቶች እነዚህ ዓደጋዎችን ከግል ተዋናይ በተሻለ ሁኔታ ሊሸከማቸው ወደሚችል፤ ለሦስተኛ አካል እንዲለዩ ያስችሉዋቸዋል፡፡

# ለፕሮጄክት ኩባንያው ግዴታዎች የብድር ድጋፍ

በዚህ ክፍል፣ አሰተናጋጁ አገርና አበዳሪዎች ከፕሮጄክት ኩባንያው ይጠብቃሉ ተብሎ የሚታሰበውን የብድር ድጋፍን ምንነት እናያለን (ለመፍትሔ የሚሆን ፋይናንስ ውስን በሚሆንበት ጊዜ ከስፖንሰሮች ጭምር)

ለመንግሥት፣ የኃግስ ድርድርና መጠናቀቅ ሁልጊዜ ለገዢው/ተጠቃሚው ከፍተኛ ወጪ ያስከትልበታል፤ ይኸውም በአብዛኛው ለሕጋዊ፣ፋይናንስያዊ እና ቴክኒካዊ የማማከር አገልግሎቶች፤ ተካፋይ የሆኑ ወጪዎች፡፡ ገዢው/ተጠቃሚው እነዚህን ወጪዎች በላዩ ላይ ሲጨምር፤ ፕሮጄክት ኩባንያው፤ ኃግስን እስከ ማጠናቀቂያው ድረስ ሙሉበሙሉ በመስጠት ለመደራደር ዝግጁ መሆኑን ፤በቂ ፋይናንስ ለማግኘት አስፈላጊ ፋይናንስን ማዘጋጀት፤ እንዲሁም በትጋት ፕሮጄክቱን ማሳደግ ማለትም ግንባታ ሥራዎችን መጨረስና ስምምነት የተደረሰበትን ንግዳዊ ሥራዎች ቀን(ንሥቀ) በጊዜው ማጠናቀቅ ለመሳሰሉት አንዳንድ ማረጋገጫ ይፈልጋል፡፡


በተጨማሪ፤ አብዛኛውን ጊዜ ገዢው/ተጠቃሚው፤ ኃይል/ጉልበትን የሚገዛው፤ ለማሰራጫ ኩባንያዎች ወይም ተጠቃሚዎች እንደገና ለመሸጥ እንደመሆኑ መጠን፤ ስምምነት በተደረሰበት ቀኖች የተወሰነ የኃይል/ጉልበት መጠን ለእነዚህ አካላት ለማቅረብ የጸኑ የኮንትራት ስምምነቶች ይኖሩታል፡፡ በእነዚህ ምክንያት፤ ገዢው/ተጠቃሚው፤መጠናቸው ተገቢ የሆነ የመዘገየት ጉዳቶች ላይ ወይም ከፕሮጄክት ኩባንያው በኩል፤ ያልተፈፀሙ ክፍያዎችን በተመለከተ ምናልባት አጠንክሮ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

የፕሮጄክት ኩባንያው ዋና የመጀመሪያ ግዴታ፤ የኃይል/ጉልበት ፋብሪካውን በተሰጠው የሥራ ዝርዝሮች፤ አስቀድሞ በተወሰነው (ንሥቀ) ማጠናቀቅ እንደመሆኑ መጠን፤ ለፕሮጄክት ኩባንያው የብድር ድጋፍ የማስገኘት ፍላጎት ብዙውን ጊዜ ለፕሮጄክቱ የግንባታ ምዕራፍ ጊዜ የተወሰነ ነው፡፡

አንድ ኮንስትራክሽን የኢግኮ ኮንትራት ፎርምን ሲወስድ፤ የኮንስትራክሽን ዓደጋው ከፕሮጀክት ኩባንያው ወደ ኢግኮ ኮንትራክተሩ እንደሚዞር ማስተዋል ጠቃሚ ነው፤ ኋለኛው በኢግኮ ኮንትራት መሰረት የማጠቃለያ ድጋፍ ዋስትና ወይም ለግዴታዎቹ ሌላ ሴኩሪቲ  መስጠት ይኖርበታል፡፡

ከፕሮጀክት ኩባንያው አንጻር፤ ለገዢው/ተጠቃሚው ከተሰጠው የብድር ድጋፍ ጋር በተያያዘ ያሉበት ዕዳዎቹ፤ከተከፈሉ ጉዳቶች በኢግኮ ኮንትራክተር ተከፋይ የሆኑ እና የብድር ድጋፍ በኢግኮ ኮንትራክተር የተሰጠ የበለጠ እንዳይሆኑ ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው፡፡

ከሥር ያለው የአንድን የኃይል/ጉልበት ፋብሪካ ተቋማት ሥነ ዕድገት ከመነሻ ልማት  (ተያያዥነት ያላቸውን የፕሮጀክት ሰነዶች አንድ ላይ ከማድረግ ጀምሮ፤ እንዲሁም ለሚመለከታቸው አካላት ኃላፊነት መስጠት) እስከ ንግዳዊ ሥራዎች  ማሳያ ነው፡፡ የተቀመጡት የጊዜ ቀመሮች እንዲያው ማሳያ ናቸው እናም አንዳንዶቹ ሊደራረቡም ይችላሉ፡፡



ፕሮጀክት ኩባንያው ንግዳዊ ሥራዎችን አስቀድሞ በተቀመጠው ንሥቀ ማካሄድ ባይችል፤ በኃግስ ሥር የተከፋይ ጉዳቶችን አፈጻጸም የሚያጓትት ነገር ሊቀሰቅስ ይችላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አነስተኛ የዓቅምና ኃይል/ጉልበት ጠርዝ/ገደብ ማሟላት አለመቻል፤የአፈጻጸም ጉዳቶችን ሊያስነሳ ይችላል፡፡

ፕሮጀክት ኩባንያው ንግዳዊ ሥራውን በ long-stop ቀን መፈጸም ካልቻለ፤ ይህ ባለጉዳዮቹ ኃግስን እንዲሰርዙ መብት ይሰጣቸዋል (እንዲሁም ሌሎች ስምምነቶችን ጭምር)

በእንዲህ ያለ አፈጻጸም የለሽ ጉዳይ፤ ለፕሮጀክት ኩባንያውና ለኢግኮ ኮንትራክተር ፋይናንሲያዊ ሳንካ ሊያመጣ ይችላል፡፡ በአብዛኛው ሁኔታዎች፤ንግዳዊ ሥራዎችን ለማካሄድ አለመቻል ምክንያቱ መፍትሔ የለሽ ካልሆነ በቀር፤ ኃግስን ማቆም የመንግሥት ፍላጎት አይሆንም፡፡

ችግር ወደ አለበት ፕሮጀክት አዲስ ኢንቨስተሮችን ለመሳብ መሞከር አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ፋይናንሲያዊ ግዴታዎች እንዲሟሉ ለማድረግ፤ አስተናጋጁ መንግሥት፣ገዢው/ተጠቃሚው፣ እና አበዳሪዎች ከፕሮጀክት ኩባንያውና ኢግኮ ኮንትራክተር ከታች በተገለጹት ፎርሞች መሰረት የብድር ድጋፍ እንደሚጠብቁ የተለመደ ነው፡፡

# በግንባታ ጊዜ የተለመዱ የብድር መሣሪያዎች

**የአፈጻጸም ቦንድ፡-** የአፈጻጸም ቦንድ በተለምዶ የብድር ደብዳቤን ወይም የባንክ ዋስትና ቅፅ ሊመስል ይችላል፡፡ የዚህ ቦንድ ዋጋው በተለምዶ የፕሮጀክቱ ኢንቨስትመንት ዋጋ ጥቂት ክፍል ሲሆን እና በፅንሰ ሃሳብ ደረጃ፤ በአስተናጋጁ አገር ምክንያት የጠፋውን ዋጋ እና የጠፋውን የማመንጨት ዓቅም ግምት ውስጥ ማስገባት አለበት፡፡ በተግባር፤ ዋናው የቦንዱ አስፈላጊነት፤የመተካት ዋጋ ነው፤ እናም እንደተለመደው አፈጻጸም በማይኖርበት ጊዜ መንግሥት የሚደርስበትን ተጨባጭ ወጪ ለመሸፈን በቂ አይደለም፡፡

**የልማት ቦንድ፡-** በአንዳንድ የመወሰን ሥልጣኖች፤ የፕሮጀክት ኩባንያው ምናልባት የልማት ቦንድ እንዲያወጣ ይፈለግ ይሆናል፤ ለመንግሥት ፈቃድ እና ድጋፍ ወይም የፈቃድ ስምምነት ሲባል (የመንግሥት የድጋፍ ስምምነት ግን ዋስትና እንዳልሆነ አስተውል)፡፡ ፕሮጀክቱ በልማት ጉዞው በኢንቨስተሩ/ስፖንሰሩ በተፈጠሩ ምክንያቶች የተወሰነ ደረጃ መድረስ ካልቻለ፤ በዚህም ምክንያት ኃግስ በተሰጠ ጊዜ ውጤታማ ካልሆነ፤ ገዢው/ተጠቃሚው የልማት ቦንድ ሊወስድ ይችላል፡፡

**ስፖንሰር ደጋፊ ስምምነት፡-** ምንም እንኳን ይህ ስምምነት የኃግስ አካል ባይሆንም፤ ብዙውን ጊዜ ለኮሜርሺያል ባንኮች የተወሰነ የችግር ጊዜ መወጫ ብድር ለመስጠት ማእከላዊ ሁኔታ ነው፡፡ በመሰረቱ፤ ይህ ማለት ማንኛውም የፈንድ እጥረት በግንባታ ጊዜ በስፖንሰሩ ይካሄዳል እንዲሁም ስፖንሰሩ ምናልባት የተፈለገውን የፈንድ ግዴታ ዋጋ እንዲያስቀር ይፈለጋል፡፡ የስፖንሰር ድጋፍ በመሠረቱ አስፈላጊ የሚሆነው በፕሮጀክት ያለ የመጠባበቂያ በጀት ትንሽ ሲሆን ወይም የወጪ መጥለቅለቅ ዓደጋ ከፍተኛ እንደሚሆን አስቀድሞ ከተገመተ ነው፡፡ በቂ ኃብት ያላቸው ፕሮጀክት ስፖንሰሮች/ባለድርሻዎች ሰፖንሰር ድጋፍ ለመስጠት የተመቹ ናቸው፡፡

# ለነዳጅ አቅርቦት ስምምነት የብድር ድጋፍ

ነዳጅ ከታቀደው የኮሚሽን ቀን በፊት ሊዘጋጅ ይገባል፤ ይኸውም ሙከራና የኮሚሽን ሥራ መካሄድ እንዲችል። ነዳጁን አቅራቢው አካል፤በነዳጅ አቅርቦቱ ኮንትራት ለአለበት የክፍያ ግዴታዎች፤ የፕሮጀክት ኩባንያው የብድር ድጋፍ ይሰጣል ብሎ ይጠብቃል።

ለምሳሌ በጋዝ አቅርቦት ኮንትራቶች፤ የብድር ድጋፍ የተለመደው በብድር ደብዳቤ መልክ ነው(ብደ)።በብዙ አጋጣሚዎች፤ ይህ ለሥራ ጊዜው የተገመተ የጋዝ አቅርቦቶችን ይወክላል።

ፕሮጀክት ኩባንያው ምናልባት የሆነ ወር ክፍያን ቢያሳልፍ፤ ጋዝ አቅራቢው ከብደው ሊያወጣ ይችላል፤ ይህ ሁኔታ ከተፈጠረ፤ፕሮጀክት ኩባንያው የብደውን ማሟላት ይጠበቅበታል።

እንዲህ ዓይነቱ አሰራር፤ ፕሮጀክት ኩባንያው ያለበትን የክፍያ ግዴታ ወቅታዊ በሆነ ሁኔታ እንደሚፈጽም፤ ለጋዝ አቅራቢው ተጨባጭ ማረጋገጫ ይሰጠዋል።

በተለምዶ፤ ለዚህ የብድር ድጋፍ የሚያስፈልጉ ነገሮች አስቀድመው ከፋይናንሲያዊ መዘጋት በፊት ይደራጃሉ፤ ነገርግን ትክክለኛ የፋይናንስ ማዘጋጃ መሣሪያዎቹ ከመጀመሪያው የጋዝ እደላ በፊት በቦታው ሊኖሩ ይገባል።

በኮንትራቱ ደንብ መሠረት፤ አንዴ ጋዝ በጋዝ ቧንቧዎቹ መፍሰስ ከጀመረ፤ ነገርግን ከንግዳዊ ሥራዎች ቀን በፊት፤ ይህ ብደ በተለምዶ በቦታው ይጠበቃል።

በኣጠቃላይ፤ ከላይ ያሉት ግዴታዎችና የአሰራር ዘይቤዎች፤ንግዳዊ ሥራዎች ቀን ላይ ይጠፋሉ፤ ከንግዳዊ ሥራዎች ጋር ከሚቀጥለው ብደ ለጋዝ(ነዳጅ) አቅርቦት ስምምነት በቀር።

# ሌሎች የብድር ድጋፍ መሣሪያዎች ንሥቀ-በኋላ

**ዕዳ አገልግሎት መጠባበቂያ ሂሳብ (ዕአመሂ)፡-** ይህ የታቀደው የፕሮጀክቱን ክሬዲት ለማበልፀግ እና ፕሮጀክቱ ያሉበትን የዕዳ ግዴታዎችን መወጣት መቻል ማረጋገጥ፤ ይህም ክፍያዎች ከገዢው/ተጠቃሚው ለጊዜው በቂ ባልሆኑበት ዋናውንና ወለድን አገልግሎት መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ እንኳን።

በተጨማሪ በውጭ ምንዛሪ ዋጋ ላይ መዋዠቅ እንዳይኖር ለመጠበቅም ይውላል፤ የምንዛሪ ክፍያ በታግስ መሰረት ለዕዳ ክፍያ ከሚውለው ምንዛሪ ጋር ተመሳሳይ በማይሆንበት ጊዜ።

ዕአመሂ በተለምዶ መጠኑ ከተወሰኑ ቁጥር ወሮች የዕዳ አገልግሎት ክፍያዎች ጋር የተሰላ ነው፤ እንዲሁም ከመጀመሪያው ጥቅም ላይ መዋል ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ፈንድ ይኖረዋል። ከዚያ በኋላ፤ፕሮጀክት ኩባንያው ሂሳብ መቀነስ ሲጀምር መተካት ይኖርበታል፤ ዕአመሂን በኮንትራቱ ደረጃ የማቆየት ግዴታ በተለምዶ እንደ ታሪፍ ቀመር አንድ ክፍል ድርድር የሚካሄድበት ነው።

**ለሥራ ማስኬጃ ካፒታል የብድር ደብዳቤ፡-** በአንድ ፕሮጀክት ሥራ መጀመሪያ ዘመን፤ወጪና ገቢ አይጣጣሙም። በዛ ያሉ ወጪዎች በፕሮጀክቱ ላይ ሊፈጠሩ ይገባል፤ይህን የሚሸፍን ገቢ ከመምጣቱ በፊት። በዚህን ጊዜ፤ የፕሮጀክቱ ስፖንሰር የብድር መስመር መዘርጋት ሊያስፈልገው ይችላል፤ ወይም የገንዘብ እጥረቱን ለመሸፈን ፈንድ ማድረግ፤ ይኸውም ፕሮጀክቱ ከጅማሬው መንቀሳቀሱን እንዲቀጥል።

# ከታክስ/ግብር/ ነጻ

በአንድ ዘርፍ ያለ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት ከሚካሄድ ጥረት አንጻር፤ መንግሥታት አንዳንዴ ከታክስ ነጻ መሆንን እንደ ማበረታቻ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡ ይህ ምናልባት ታክስን ሙሉበሙሉ ማንሳት ወይም ታክስን ቅነሳ፤ በተለዩ አንዳንድ ዓይነቶች ላይ ወይም በፕሮጄክት የግንባታ ምዕራፍ ለሚገዙ መሳሪያዎች የሚውል ይሆናል፡፡ ይህ በተጨማሪ፤ በፕሮጄክት የስራ ዘመን፤ ለተወሰኑ ዓመታት ከገቢ ታክስ ነጻ መሆንንም ሊያጠቃልል ይችላል፡፡

ከታክስ ነጻ መሆን ምናልባት የፕሮጄክትን ከፋይናንስ አንጻር ራስን የመቻል አቅም ሊያሻሽል፤ እንዲሁም ኢንቨስትመንትን ማበረታታት፤ በመጨረሻ ተጠቃሚው ላይም ዝቅተኛ ታሪፍ በመፍቀድ ተጠቃሚዎችን የጥቅሙ ተጋሪ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ከሚሰጡ ነጻ የመሆን ዓይነቶች ምሳሌዎች ውስጥ፤ በግንባታ ጊዜ አስፈላጊ ሆነው ወደ ሃገር ውስጥ በሚገቡ ላይ ከሚውሉ ታክስ፣ ግዴታዎችና ተጨማሪ ክፍያዎች፤ ዝቅተኛ የምዝገባ ክፍያዎች፣ ለቫት ድርድር የተካሄደባቸው መጠን፣ እንዲሁም የታክስ በዓላትን በፕሮጄክት ሥራ ጊዜ ማዘጋጀት ይገኙበታል፡፡

ለፕሮጄክቱ የተሰጡ ከታክስና ከቀረጥ ነጻነቶች፤ በታክስ ባለሥልጣን እና በአንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ በሕግ አውጪው አካል ወይም በአገሪቱ ዋና ባለሥልጣን ሊረጋገጡ ይገባል፡፡ ይህ ሂደት ምናልባት ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድ ይችል ይሆናል፡፡ ለአንድ የኃይል/ጉልበት ፕሮጄክት የታክስ/ግብር ነጻ መሆን አሳሳቢ/ጊዜ ወሳጅ/ በሚሆንበት ጊዜ፤ ባለጉዳዮቹ ይህን የጊዜ ገደብ/ችግር/ በድርድር ጊዜ እንደ አንድ ነጥብ ሊወስዱት ይገባል፡፡

ለፕሮጄክት ኩባንያው ብቁ የታክስ/ግብር/ማማከር አገልግሎቶችን መጠቀም ጠቃሚ ነው፤ ይኸውም በእርግጠኝነት በአስተናጋጅዋ አገር ያሉ ሁሉንም የታክስ ጥቅሞች ለመለየትና ጥቅሞቹን ለመጋራት፡፡

# የዋና ነጥቦች ማጠቃለያ

## የታሪፍ መዋቅሮች

- **የሚሰራጭ፡**- ለሚሰራጩ ቴክኖሎጂዎች (ሙቀት ሰጪ፣ ኤሌትሪክ) የታሪፍ መዋቅሩ፤ ለገዢው/ተጠቃሚው የቀረበለትን የዓቅም ክፍያ፤ እንዲሁም ገዢው/ተጠቃሚው በትክክል ያሰራጨውን የኃይል/ጉልበት ክፍያ ያጠቃልላል፡፡

- **የማይሰራጩ፡** ለማይሰራጩ ቴክኖሎጂዎች (የንፋስ፣የፀሃይ፣ እና ትናንሽ ግድብ የለሽ የውሃ ኃይሎች)፤ የታሪፍ መዋቅሩ በቀዳሚነት በአመንጪው ተቋም የመነጨውን ኃይል/ጉልበት ክፍያ ይይዛል፡፡ ድጎማ የተደረገለት ታሪፍ ባለ ታደሽ ኃይል/ጉልበት ፕሮጀክቶችን ለማበረታታት ሊውል ይችላል፡፡

## ነዳጅ አቅርቦት ስምምነቶች

- **ውሰድ ወይም ክፈል፡**- ነዳጅ አቅርቦት ስምምነቶች፤አብዛኛውን ጊዜ ውሰድ ወይም ክፈል አንቀጽ ይኖራቸዋል፤ ይኸውም ኃይል/ጉልበት አምራቹ/ፕሮጀክት ኩባንያው/ ስምምነት ለተደረሰበት የነዳጅ መጠን (በተለይ ጋዝ) የግድ ሊከፍል እንደሚገባ የሚገልጽ፤መጠኑን ወሰደ አለወሰደ ግምት ውስጥ ሳያስገባ፡፡

## የገንዘብ ዓይነትና ታክስ

- **መመንዘር የመቻል ዓደጋ፡**- በኃግስ መሰረት ክፍያዎች በአገር ውስጥ የገንዘብ ዓይነት ከሆነ፤ እናም የፕሮጀክቶቹ ዕዳ ደግሞ በውጭ አገር ገንዘብ ከሆነ፤ ኃይል/ጉልበት አምራቹ፤ የውጭ አገር ምንዛሬ ዕዳዎቹን ለመክፈል፤ የአገር ውስጡን ገንዘብ ለመቀየር ያለመቻል ዓደጋ ውስጥ ይገባል፡፡ በኃግስ ውስጥ ይህን ዓይነቱን መጋለጥ ለመድረስ የተለያዩ አቀራረቦች አሉ፡፡

- **ከታክስ ነጻ፡** ለኃይል/ጉልበት ፕሮጀክቶች ኢንቨስትመንትን ለመሳብ፤ አስተናጋጁ አገር ምናልባት ልዩ ከታክስ ነጻነት መልካም ፍቃድ ሊሰጥ ይችላል፤ ይኸውም በሁሉም ኩባንያዎች ላይ ከሚተገበረው አጠቃላይ ሕጎች ውጪ፡፡

## የብድር ድጋፍ

- **የገዢው/ተጠቃሚው ብድር ድጋፍ፡** ገዢው/ተጠቃሚው፤ በኃግስ ስር ያሉትን የክፍያ ግዴታዎች በበለጠ አስተማማኝ ለማድረግ፤ በተለምዶ የሆነ ዓይነት ብድር ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ይህ ደግሞ አንዳንድ የሥልጣን ዋስትናዎች ድብልቅ፣ የምቹት ደብዳቤዎች፣ አስቀምጥ እና ጥራ አማራጭ ስምምነቶች፣ የብድር ደብዳቤ፣ እና escrow account የክፍያ ሁኔታን ምቹ ለማድረግ፡፡

- **ፖለቲካዊ ዓደጋ ሽፋን፡** በአስተናጋጁ ገበያ እንዳለው የፖለቲካ ዓደጋ ጭንቅ ሁኔታ፤ ፕሮጀክት አበዳሪዎች፤ በኃግስ ስር ተጨማሪ የኢንቨስትመንት ከለላ ለመስጠት፤ ምናልባት ከፊል የዓደጋ ዋስትና ከብዙጎንዮሽ ልማት ባንኮች ወይም ከሌላ የልማት ፋይናንስ ተቋማት ሊፈልጉ ይችላሉ ፡፡

- **ሻጭ ብድር ድጋፍ፡** ፕሮጀክት ኩባንያው፤በኃግስ ስር ያሉበትን የአፈጻጸም ግዴታዎችን ለመደገፍ፤በተለምዶ አንዳንድ የብድር ድጋፍ ዓይነቶች ይሰጣል፡፡ ይህ ትኩረቱ ምናልባት የፕሮጀክት ግንባታ ዓደጋ ላይ፤ወይም በፕሮጀክት ኩባንያው ግዴታዎች፤ የነዳጅ አቅርቦት እና ፋይናንሲያዊ ስምምነቶች በተመለከተ፡፡

# ስጋቶችን መመደብና መግታት

መግቢያ

የልማትና የግንባታ ምዕራፍ ስጋቶች

የሥራ ሂደት ወቅት ስጋቶች

ሌሎች ስጋቶች

አስገዳጅ ሁኔታዎች

ዋስትና

የዋና ነጥቦች ማጠቃለያ

# መግቢያ


የስኬታማና አዋጭ ሃይል ግዢ ስምምነት መሰረት የስጋት ሚዛንና ድልድል የሃግስ ውል በሚገቡት መካከል በመጠብቅ ነው። የፕሮጀክት ፋይናንስን በተመለከተ እድሜ ጠገቡ የውል ስጋቶች ድልደላ መርህ ለሃግስ በተለየ መልኩ እውን ነው፣ የዚህ መርህ ጭብጥ የሚለው **ስጋቶችን በተሻለ መቆጣጠር ለሚችለው ወገን ስጋቶቹ መመደብ አለባቸው**።

የስጋቶች መቆጣጠር ስራ በሶስተኛ ወገን ቢከናወን የተሻለ ይሆናል፣ ለምሳሌ የሃይለ ማመንጫውን ለመበንባት የተመደበው ኮንትራክተር ወይንም የኢንተርኮኔክሽን ማዕከላት የሚገነባው የሃይል ማስተላለፊይ ኩባንያ። ነገርግን እነዚህ ሶስታኛ ወገኖች የሃገስ ውል ወገኖች አይደሉም፣ ሆኖም ስጋቶቹ ለአንዱ የሃገስ ወገን መመደብ አለባቸው። ታዲያ ይህ ክፍተት እንዴት ነው የሚጠበው?

ስጋቶች እንዴት ይገታሉ የሚለው ነጥብ የሃገስ አስፈላጊ አካል ነው። በሶስተኛ ወገን ቁጥጥር ስር ሆነው ለአንዱ የሃግስ ወገን የተሰጡ ስጋቶች፣ ለምሳሌ የ ሃግስ ተዋረድ ድንጋጌዎችንና ከሶስተኛው ወገን የተደረገውን ውል በመጠቀም ለሶስተኛው ወገን ማስተላለፍ ይቻላል።

አንድ ወገን በተለምዶ የማይመደብለትን ስጋት ከወሰደ ይህ ወገን ይሄን የመሰለ ሰጋት በመረከቡ የተወሰነ ጥቅም ይጠብቃል፡፡ ሃይል ገዢው ከሆነ የሚጠብቀው ዝቅ ያለ ዋጋ ይሆናል፡፡ የፕሮጀክቱ ኩባንያ ከሆነ የሚጠብቀው ተገቢ የሆነ የኢንቬስቲስመንት ትርፍ እድገት ያን ስጋት በመሸከሙ፡፡ ስለዚህም አንድ ወገን ስጋቶችን ለሌላ ወገን በማስተላለፉ የንግድ ድል ቢጎናጸፍም የስጋቶቹን ኪሳራ በአንድ መልክ ወይም በሌላ የሚሸከመው ይኸው ወገን ነው፡፡ በአንድ ሃግስ ውስጥ ተገቢ የስጋት ማመጣጠንና ድልደላ ለማድረግ ተዋዋይ ወገኖች ግዴታዎቻቸውን በሃግስ መሰረት እንዲወጡ በቂ ማበረታቻ በመስጠት ነው፡፡

አንዳንድ ስጋቶች በሁሉም የፕሮጀክቱ ምዕራፎች አሉ፡፡ አንዳንድ ስጋቶች የሚከሰቱት በልማቱና ግንባታ ምዕራፍ ላይ ነው፣ ሌሎች ደግሞ የሚከሰቱት ፕሮጀክቱ ወደ ተግባር ሲሄድ ነው፡፡




ይህ ምዕራፍ ዋና ዋና በሃግስ ዙሪያ ሊከሰቱ የሚችሉ ስጋቶችን የመፈተሽ ዓላማ ነው ያለው፡፡ በዚህ ምዕራፍ የሚዘረዘሩት ስጋቶች ሁሉንም አያጠቃልሉም፡፡ ስጋቶችና የሚገቱበት ስልቶች እንደ ፕሮጀክቱ ሊለያዩ ይችላሉ የሥልጣኑን ክልል፣ ከበሰተጀርባ ያለ የደንብ ማዕቀፍ፣ የገዢው መዋቅርና የማመንጫው ቴክኖሎጂ ወዘተ መሰረት ባደረገ መልኩ፡፡ እነዚህ የተለላዩ ስልፈቶች በዚህ መምሪይ መጽሀፍ ሌላ ምዕራፎች ይዳሰሳሉ፡

# የልማትና የግንባታ ምዕራፍ ስጋቶች

## ቅድመ ግንባታ

### መሬት ግዢ

የሃይል ማመንጫው ጣቢያ የሚገነባበትና የሚሰራበትን መሬት መረከብ የፕሮጀክቱ ኩባንያ በዋናነት የሚወስደው ሃላፊነት ነው። ገዢው/መንግስት የመሬቱ ባለቤት ከሆነ፣ ሊዝ ወይም ልዩ መብት የሚሰጥበት ከሆነና መሬቱን ለፕሮጀክቱ ኩባንይ ካቀረበ ሃለፊነቱ በአግባቡ የገዢው ይሆናል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የፕሮጀክቱ ይዞታ ሊዝ ሰጪ የመንግስት ባለስልጣን ወይም አንድ በመንገስት ወይም በገዢው ስር ያለ አካል ከሆነ የፕሮጀክቱ ኩባንያ ከመንግስት/ገዢ የሊዝ ውሉን በሊዝ ሰጪው ስለመከበር በተመለከተ ተጨማሪ ዋስትና እንዲሰጠው ይጠይቃል። ለሙሉ የሃግስ የስራ ዘመን የፕሮጀክቱን ቦታ የመያዝ መብት ማረጋገጥ ለገዢውና ለፕሮጀክቱ ኩባንያ ጠቃሚ ነው። የሃግስ የስራ ዘመን ከታደሰ የፕሮጀክቱን ቦታ የመያዝ መብት ለተጨመረው ጊዜ መረጋገጥ አለበት።

### ስራ አለመጀመር

ገዢው የፕሮጀክቱ ኩባንያ የሃግስ በጸና በአጭር ውስጥ የግንባታውን ስራ ስለመጀመሩ ዋስትና ይፈልጋል። የግንባታውን ስራ አለመጀመር የፕሮጀክቱ ቀጥተኛ ገቢር ባይሆንም፣ ለምሳሌ የኢግግ ኮንትራክተር ስራውን በኢግግ ስምምነት መሰረት ማከናወን ቢሳነው፣ በዚጉድለት ሳቢያ ሊከሰቱ የሚችሉ ጉዳቶች የፕሮጀክቱ ኩባንያ ሃላፊነት ናቸው። በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግንባታ አለመጀመር ውይም ሃግስ እንዲቋረጥ ያደርጋል አሊያም ለገዢው ሃግስን የማቋረጥ መብት ይሰጠዋል። የፕሮጀክቱ ኩባንያ ስራ አለመጀመር የግንባታ ወይመ የፔርፎርማንስ ቦንድ ክፍያ ሊያስከትለ ይችላል።

አብዛኛውን ጊዜ የፕሮጀክቱ ኩባንያ የግንባታ አለመጀመርን የሚያርቅበተ አጋጣሚዎች ውስን ናቸው። አንዳንድ ሃግስ ለፕሮጀክቱ ኩባንያ የግንባታው ስራ በመዘግየቱ ለሚያስከትለው ጉዳት ካሳ ከፍሎ ስራውን የሚጀመርበትን የጊዜ ገደብ የማራዘም አማራጭ ይሰጣሉ። የስራው መዘግየት ምክንያቱ አስገዳጅ ክስተት (force majeure event) (ፓለቲካዊ አስገዳጅ ክስተት) ወይም በገዢው ጉድለት (ወይም በየትኛውም በፕሮጀክቱ ስምምነቶች የተካተተ ተጓዳኝ አካል ወይም የመንግስት ባለስልጣን መስሪያ ቤት) ከሆነ ስራው የሚጀምርበት የጊዜ ገደብ በዘገየበት ቀን ልክ ይራዘማል። ይህ የማራዘም ሂደት አስገዳጅ ክስተቱ ወይም ጉደለቱ የፕሮጀክቱ ኩባንያ የግንባታ ስራውን መጀመር እስካወከው ድረስ ይቀጥላል።

## ግንባታ

### ስራውን ማቋረጥ

የግንባታው ስራ ከተጀመረ በኋላ ገጂው ስራው መቀጠሉንና ፕሮጀክቱ አለመቋረጡን ማረጋገጥ ይፈልጋል። የስራ ማቋረጥ የሚይዛቸው መልኮች የፕሮጀክቱ ግንባታና አፕሬሽን ዘላቂ በሆነ ሁኔታ ሲቆም፣ ወይም ግንባታው ወይም አፕሬሽኑ ለተራዘመ ጊዜ ሲቆም ናቸው። ሁለቱም

ክስተቶች እንደ የፕሮጀክቱ ኩባንያ ጉድለቶች በመታየታቸው ለገዢው የሃይ ገዢ ስምምነቱን የማቋረጥ መብት ይሰጠዋል። ፕሮጀክቱ ወደ ስራ ከገባ በኋላ የስራ ማቋረጥ ጽንሰ ሃሳብና የጸናበት የጊዜ ገደብ የፕሮጀክቱን ቴክኖሎጂ መሰረት ባደረገ መልኩ ተለዋዋጭ ይሆናሉ፣ ይህም የኦፕሬሽን ክብደት ደረጃን ታሳቢ ለማድረብ ነው (ለምሳሌ በሙቀት ሃይል ማመንጫ ንቁ አስተዳደር ከጸሃይ ሃይል ማመንጫ ጉልት አስተዳደር ሲነጻጸር)

## የማምረት ስራ ቀን የማሳካት መጓተቶች

የሃይል ማመንጫ ተቋሙን ግንባታ በሃግስ በተቀመጠው ቀነ ገደብ መጨረስ የፕሮጀክቱ ኩባንያ ዋና ገዴታዎች አንዱ ነው። በዚህ መሰረት የተቋሙን ገንባታ በተሰጠው ቀነ ገደብ አለመጨረስ፣ ምንም አይነት አስገዳጅ ክስተት በሌለበት ሁኔታ እንደ የሃግስ ውል ጥሰት ታይቶ ለገዢው ከመዘግየትጋ በተያያዘ የካሳ ክፍያ እንዲጠይቅ ከማድረጉም በላይ የሃል ግዢ ሰምምነቱን የማፍረሰ መብት ይሰጠዋል። የፕሮጀክቱ ኩባንያ በተራው ምንም አይነት ከመዘግየትጋ የተያያዘ የካሳ መክፈል ገዴታ በተዋረድ ወደ ኢግግ ኮንትራክተር በኢግግ ውል መሰረት መስተላለፉን ያረጋትጣል (በውሉ የተቀመጠው ከመዘግየትጋ የተያያዘው የካሳ ክፍያ መጠን በሃግስ ስር መከፈል ያለበትን ብቻ ሳይሆን በብድር ሰነዶች የተካተተውን የዕዳ ሰርቪስ እንዲሸፍን መሆን አለበት)። በዘለቀ መጓተት ምክንያት የሃል ግዢ ስምምነቱ ከፈረሰ ብኋላ የፕሮጀክቱ ኩባንያ የኢግግ ውልን የማፍረስና ተገቢ ካሳ የመጠየቅ መብት እንደሚኖረው በኢግግ ውል መካተት አለበት።

## እንደተጠናቀቀ መውሰድ (Deemed completion)

በተወሰኑ አጋጣሚዎች የፕሮጀክቱ ኩባንያ (እና ኮንትራክተሮቹ) ከመጓተትጋ በተያያዘ እፎይታ የመጠየቅ መብት አላቸው። እፎይታው የጊዜ ብቻ ሊሆን ይችላል (ማለት የፕሮጀክቱ ኩባንያ የጊዜ መራዘም ብቻ ይሰጠዋል)፣ ወይም የጊዜና የገንዘብ **"እንደተጠናቀቀ መውሰድ"** በሚለው ጽንሰ ህሳብ መሰረት ሊሰጠው ይችላል፡፡ "እንደተጠናቀቀ መውሰድ" የሚከሰተው ገዢው ( እና/ወይም መንግስት) ሃላፊነት በወሰደባቸው ስጋቶች ሳቢያ ስራው ሳይጠናቀቅ ከቀረ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ "እንደተጠናቀቀ መውሰድ" የሚከሰተው ይጠናቀቃል ተብሎ በተያዘው ቀን ወይም የሃል ማመንጫው ተቋም ስጋቱ ባይከሰት ኖሮ ስራ የሚጀምርበት ቀን ከሁለቱ ረፍዶ የሚደርሰውን በመምረጥ ይሆናል፡፡ እንደተጠናቀቀ መውሰድ ከጀመረበት እለት አንስቶ ገዢው የሃይል ማመንጫውን ውሉ ላይ የሰፈረ አቅም መሰረት ባደረገ የተተመነ የአቅም ክፍያ (ወይም የሃይል ክፍያ) የመቀበል መብት ይኖረዋል፡፡ ቀጥሎም የማጠናቀቂያ ፍተሻ ተደርጎ የማመንጫው የአፈጻጸም ፍተሻ ውሉ ላይ ከተቀመጠው አቅም ዝቅ ያለ ካሳየ የፕሮጀክቱ ኩባንያ ልዩነቱን ታሳቢ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## የግንባታ ወጪ ማሸቀብ

በገዢው እይታ የሃይል ማመንጫ ፕሮጀክት ግንባታ ዙሪያ ከግሉ ሴክተር ጋር መደራደር ወይም ጨረታ ማቅረብ ዋና ዓላምዎች አንዱ  የዋጋ (ብሎም የተመን) እርግጠኝነት ከፕሮጀክቱ ኢንቬስቲስመንት ወጪ አንጻር ለመፍጠር ነው፡፡ ስለሆነም ተመኑ የሚወሰነው የጨረታ ዋጋ ፋክክርን ወይም በመግባባት የተወሰነ የግንባታ ወጪን መሰረት ባደረገ መልኩ ነው፡፡ የፕሮጀክቱ ኩባንያ በተራው የግንባታውን ወጪ ለመቆለፍ ይጥራል፣ ይህንንም ከኢግግ ኮንትራክተር ጋር አንድ ክፍያ፣ የተቆረጠ የመረከቢያ ቀን፣ አጠቃላይ ስራ ያካተተ ውል በመደራደር ነው። ከዚህ በኋላ መሰረታዊው ጽንሰ ሀሳብ የሚሆነው ምንም አይነት የወጪ የማለፍ ስጋትን የሚሸከሙት የፕሮጀክቱ ኩባንያና (በሃግስ መሰረት) የኢግግ ኮንትራክተር (በኢግግ ውል መሰረት) ይሆናሉ፡፡ ሆኖም ግን በዚህ አካሄድ የማይካተቱ ሁኔታዎች አሉ።  የግንባታው ወጪ ማሻቀብ የተፈጠረው በገዢው የለውጥ ጥያቄ ወይም ህጉ በመቀየሩ (**የህግ መለወጥ** የሚለውን ከታች ይመልከቱ ) ከሆነ ቀጥተኛ ካሳ በገዢው የሚከፈል የግንባታውን ወጪ መጨመርን ለመሸፈን ወይም የተመን ማሻሻያ ኢንቬስት የተደረገውን ወጪ ጭማሪ (እና ማንኛውንም የተያያዘ ወጪ) ለመሸፈን በሃግስ ውስጥ መካታት ይኖርበታል፡፡

# የቦታ መዳረሻና አቅርቦት

ለፕሮጀክቱ በተመረጠው ቦታ ዙሪያ የተወሰኑ ከግንባታ ጋር የተያያዙ እምቅ ስጋቶችና ጉዳዮች አሉ፡፡ እነዚህ ስነ ምድራዊ ስጋት (ማለት ቦታው ከስነ ምድር አንጻር ለግንባታ ስራ ሰለማመቸቱ) ስነ ቅሪታዊ ስጋት (በኩፋሮ/ግንባታ ወቅት ሰነ ቅሪታዊ ግኝት ስለመደረጉ፣ እና ይህ ግኝት እንዴት ይስተናገዳል)፣ እና የትኛውም አይነት የነበረ አካባቢያዊ ብክለት በግንባታ ስራ ወቅት ሊገኝ የሚችለ፡፡

## ቦታውን የመያዝ መብት

የፕሮጀክቱ ኩባንያ የፕሮጀክቱን ቦታ የመያዝ መብት የሃይል ማመንጫውን ለመገንባትና ለማንቀሳቀስ ዓላማ ለፕሮጀክቱ ህልውናና አዋጪነት መሰረተታዊ ነው፡፡ ይህ መብት የተለያየ መልክ ሊላበስ ይችላል፣ ከፕሮጀክቱ ቦታ ቀጥተኛ በለቤትነት (ከሶስታኛ አካል በመግዛት) እስከ የተለያዩ የሊዝ ይዞታ፣የልዩ መብት ስምምነት መልኮች ወይም ሌሎች የይዞታ መብቶች፡፡ እነዚህ የሚወሰኑት በስልጣን ክልልና በፕሮጀክቱ ዙሪያ በሉ ሁኔታዎች ነው፡፡ በሱ ሃላፊነት ስር ያለ ተያያዥ መሰረተ ልማት እንደ ማስተላለፊያ መስመር ግንባታ ለማካሄድ የፕሮጀክቱ ኩባንያ ተጨማሪ የይዞታ መብት፣ የማቋረጥ መብት ወይም በጽሁፍ ፈቃድ እንዲሰጠው ሊጠይቅ ይችላል፡፡ የፕሮጀክቱ ቦታ መዳረሻ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፣ ይህም ለሃይል ማመንጫ ፕሮጀክቱ ግንባታ ማንቀሳቀስና አጠባበቅ ብቻ ሳይሆን ለገዢውም በሃግስ መሰረት የተሰጠውን የመፈተሽ መብት ለመተግበር መዳረሻ እንዲኖረው ነው፡፡

## የቦታው አመቺነት

የፕሮጀክቱን ቦታ አመቺነት በዋናነት የፕሮጀክቱ ኩባንያ ሃላፊነት ነው፡፡ የፕሮጀክቱ ኩባንያ ሙሉ የቦታውን ጥናት፣ የአፈር ናሙናና የምደረ ቴክኒካዊ ትንታኔ የማካሄድ አጋጣሚ ካገኘ የፕሮጀክቱ ኩባንያ/ኮንትራክተር የስነ ምድራዊ ስጋት ሃላፊነት ቢወስድ ተገቢ ይሆናል (ማለት ቦታው ከምደረ ቴክኒካዊ አንጻር ለግንባታ ስራ አመቺ ስለመሆኑ) በተለይ የፕሮጀክቱ ኩባንያ የቦታው ምርጫ ላይ ዋና ሚና ከተጫወተ፡፡ በአንጻሩ የፕሮጀክቱን ቦታ የመረጠው ገዢው/መንግስት ከሆነና/ወይም የፕሮጀክቱ ኩባንያ ጥናቶቹን ለማካሄድ ብዙ አጋጣሚ ጋላገኘ ገዢው የስጋቱን ሃላፊነት ቢወስድ ተገቢ ይሆናል፡፡ በተለይ ይህ እውን የሚሆነው ለፕሮጀክቱ ኩባንያ የሚሰጠው ቦታ ከዚህ ቀደም ለልማት ውሎ የሚያውቅ ከሆነ ነው፡፡ እንደዚህ ሁኔታ ካጋጠመ የፕሮጀክቱ ኩባንያ ተገቢ ከለላ መጠየቁ አይቀርም፣ ይህም የጊዜ እፎይታና እንደተጠናቀቀ እንዲታይ እንዲሁም ከነበረ አካባቢያዊ ብክለት ጋር በተያያዘ ለሶስተኛ ወገን ጥያቄ ዳጎስ ያለ ካሳ ያካትታል፡፡

## ከቦታው ጋር የተያያዘ መሰረተ ልማት

በአብዛኛው የፕሮጀክቱ ኩባንያ ከ ወይም ወደ ፕሮጀክቱ ቦታ መንቀሳቀሻ መንገድና የባቡር መስመር (ወይም ሌላ የመጓጓዣ መስመሮች) አግባብነት የሚወስነውና ሃላፊነት የሚወስደው ፡፡ ይህም ለፕሮጀክቱ ቦታ ፍጆታ አቅርቦት አስፈላጊ የሆኑ የነበሩ የሃይል መስመሮችና የውሃ ቧንቧዎችን ማዛወር ሊያካትት ይችላል፡፡ ለፕሮጀክቱ ቦታ ፍጆታ አቅርቦትን ማረጋገጥ የፕሮጀክቱ ኩባንያ ሃላፊነት ነው፣ ምንም እንኳ ገዢው ወይም የመንግስት መስሪያ ቤት ወይም ሌላ ግንኙነት ያለው አካል ኩታ ገጠም ቦታ ላይ እየተንቀሳቀሰ ከሆነ ይህን ሰርቪስ ለማቅረብ ውል ቢገባ ጉዳዩ ሊቀየር ይችላል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ከፍተኛ የመሰረተ ልማት ክፍልን (እንደ ማስተላለፊያ መስመር፣ የጋዝ ቧንቧ ወይም መንገድ) ግንባታ ገዢው ወይም የመንግስት አካል እንዲሰራው ስምምነት ካለ ከመሰረተ ለማቱ ጋር የተያያዘው የማጠናቀቅ ስጋት የገዢው ሃላፊነት ይሆናል፡፡ የፕሮጀክቱን ቦታ ለመረከብ ተፈናቃዮችን ማስፈር ይጠይቅ ይሆናል፡፡ የማስፈሩ ሂደት የፕሮጀክቱ የጊዜ አጠባበቅ ላይ የሚኖረውን ተጽኖ በሃግስ ወገኖች በጥንቃቄ መታየት አለበት፡፡

# የማገናኛ መሰረተ ልማት

የአንድ አዲስ ሃይል ማመንጫ ተቋም ግንባታና ስራ መጀመር በተሟላ ደጋፊ መሰረተ ልማት መረዳት አለበት፡፡ ከሃይል ማሰራጫው መረብ ጋር ርዝመታቸው ከጥቂት ኪሎሜትር እስከ በመቶዎች ኪሎሜትር የሆኑ የማስተላለፊያ መስመሮችን በመጠቀም ከማገናኘት በተጨማሪ የግንባታው ሂደት በፍጆታዎችና የመድረሻ መንገዶች አቅርቦት መታገዝ አለበት፡፡

የጊዜ አጠባበቅን በተመለከተ የሃይል ማመንጫ ተቋሙና ተጓዳኝ የማስተላለፊያ መረብ ልማት መቀናጀት ይኖርበታል፣ ይህም በርክክብ ወቅት የሃይል ማመንጫ ተቋሙ ከሃይል ማሰራጫው መረብ ጋር ለመገናኘት ዝግጁ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የነዳጅን አቅርቦትና ነዳጁን ለማምጣት የሚያስፈልገውን መሰረት ልማት አስቀድሞ ማቀድ ይጠይቃል፡፡

## የማገናኛ ማስተላለፊያ

የፕሮጀክቱ ኩባንያና ገዢው የማስተላለፊያውን መስመር ግንባታ የየትኛ ወገን ሃላፊነት እንደሚሆንና የመሰመሩ ባለቤትነትና ጥገና ለማን እንደሚሰጥ በጊዜ መወሰን አለባቸው፡፡

## በገዢው የሚከናወን ግንባታ

ከገበያ አንጻር ገዢው የማስተላለፊያ መስመር ግንባታ ድጼታ ውስጥ የሚገባት ዋነኛው ምክንያት በፕሮጀክቱ ኩባንያ ቢሰራ ከሚያስከትለው የወጪ ማሻቀብ ለማምለጥ ነው፡፡ ምክንይቱም የፕሮጀክቱ ኩባንያ የሚፈጥረው ይህ ተጨማሪ የግንባታ ወጪ ለገዢው በተመን ጭማሪ መልክ ለተላለፉ አይቀሬ ስለሆነ ነው፡፡

ገዢው የሚገኘው የግንባታ ወጪ ቁጠባ ጥቅም ከሁለት ሊፈጠሩ የሚችሉ ጉዳቶች ጋር መመዘን አለበት፡

ገዢው ግንባታውን ለማካሄድ በቂ መዋለ ነዋይ ላይኖረው ይችላል፣ ይህ ችግር በርካታ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ ህጋራትን የሚመለከት ነው፡፡

ገዢው የማስተላለፊያ መስመሩን ለመገንባት ሃላፊነት ከወሰደ፣ የሃይል ማመንጫው ተቋም ለርክክብ ዝግጁ ሲሆን የማስተላለፊያ መስመሩን ዝርጋታ ካልጨርሰ ሃለፊነቱን ይወስዳል፡፡ በሃግስ መሰረት ይህ ሁኔታ በመሰረቱ ገዢው ለሃይል ማመንጫው ተቋም ሃይል እንዳቀረበ ታስቦለት ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ በካሳ መልክ እንዲከፍለው ያስገድደዋል፡፡ ከግንባታ መዘግየት ጋር የሚያያዘውን ስጋት ለመቀነስ ገዢው አስቀድሞ የገንዘብና የመሳሪያ አቅርቦት በማቀድ ግንባታው የሚያልቅበትን ጊዜ ከሃይል ማመንጫው ግንባታ ማለቂያ ጋር ማጣጣም ይችላል፡፡

## በፕሮጀክቱ ኩባንያ የሚከናወን ግንባታ

የፕሮጀክቱ ኩባንያ የማስተላለፊያ መስመሩ ግንባታ ሃላፊነቱ ከሆነ ገዢው የማስተላለፊያ መስመር መዘርጊያ ወጪ ለመቆጣጠር ይሞክራል ምክንያቱም ይሄ ወጪ በመጨረሻ ወደ ገዢው በተመን ማስተካከያ መመለሱ አይቀርም፡፡ ገዢው ሁሉም ከፍተኛ ይአቅርቦት ውሎች በጨረታ መልክ እንዲሆኑ በመጠየቅና የማስተላለፊያ መስመር ተከላን የሚከታተል ክህሎት ያለው ኢንጊነር በመቅጠር ወጪውን ለመቆጣጠር መሞከር ይችላል፡፡

## ኃይል/ጉልበት መድረሻ ቦታ

የማስተላለፊያ መሥመሩ ከተጠናቀቀ በኋላ፤ ኃግስ ፕሮጄክት ኩባንያው ኃይል/ጉልበትን ወደ ኃይል/ጉልበት መድረሻ ቦታ ለማድረስ ያለበትን ግዴታ ይለያል፡፡ ይህ ኃይል/ጉልበት መድረሻ ቦታ፤ በኃግስ ተለይቶ የተቀመጠ ቁስአካላዊ አቅጣጫ ነው፡፡ ፕሮጄክት ኩባንያው የኃይል/ጉልበት መዳረሻ ቦታው በተቻለ መጠን ከኃይል/ጉልበት ፋብሪካው አጠገብ እንዲሆን ይፈልጋል፡፡ ያን ጊዜ፤ ገዢው/ተጠቃሚው፤ ከኃይል/ጉልበት መዳረሻ ቦታው በኋላ ያለውን፤ የማሰራጫ መስመሩን ዓደጋ ይወስዳል፡፡ ሆኖም

ይህ ምናልባት በዝርዝር ድርድር ሊካሄድበት ይችላል፤ በተለይ የማሰራጫ መስመሩ ሥራ የሚሰራውና የሚተዳደረው ከገዢው/ተጠቃሚው ጋር ግኑኝነት በሌለው የማሰራጫ ኩባንያ ከሆነ፡፡ ይህ፤ ከላይ ባለው *የኃይል/ጉልበት ማመንጨት ገበያዎች* በሚለው *ስር፤ጥቅል የሆኑና ጥቅል ያልሆኑ ሲስተሞችን/የአሰራር ዘይቤዎችን/* ከማወዳደር አንጻር በይበልጥ ተገልጧል፡፡

# ሙከራ እና ኮሚሽን/የማጣራት ሥራ/ ማካሄድ

## ሙከራ እና ኮሚሽን/የማጣራት ሥራ/ ማካሄድ

የኃይል/ጉልበት ፋብሪካው ሙከራና ኮሚሽን /የማረጋገጥ ሥራ/ ማካሄድ መደረግ ያለበት ከንሥቀ በፊት ነው፤ ይኸውም እያንዳንዱ ፋብሪካና መሣሪያ መጀመሪያ እንደተቀመረው እና ኮንትራት የተካሄደበት የኃይል/ጉልበት ፋብሪካው የአፈጻጸም ውጤት መሰረት፤ እየሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ፡፡ እያንዳንዱን መሣሪያ ከመሞከር በተጨማሪ፤ አንድ ሙሉ የኃይል/ጉልበት ፋብሪካ ሙከራ ሊካሄድበት ይገባል፤ አጠቃላይ የውጤት ማለኪያዎችን ለመወሰን፤ ይኸውም ከሌሎች ጋር፤ እንደ የተገጠመ ዓቅም፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ምርት፣ ዝርዝር የነዳጅ አጠቃቀምና ድምፃምሽ ጨምሮ፡፡ የኃይል/ጉልበት ፋብሪካን ሙከራ እና ኮሚሽን /የማረጋገጥ ሥራ/ ማካሄድ ግዴታ በፕሮጀክት ኩባንያው ላይ ይወድቃል፤ ይኸው አካል ኤክስፐርቶችና አሰፈላጊ የሙከራ መሣሪያዎች በሚፈለጉበት ጊዜ ከንሥቀ በፊት ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡ ለገዢው/ተጠቃሚው እና ለአበዳሪዎች ከበቂ ጊዜ በፊት ስለጉዳዩ ማሳታወቂያ ሊደርሳቸው ይገባል፤ ምክንያቱም እነርሱ ሙከራውን ከፕሮጀክት ኩባንያው ኤንጂነር/መሐንዲስ/ ጋር የሚመሰክሩ የራሳቸውን ኤክስፐርቶች ሊያሰማሩ ይችላሉና፡፡

የፋብሪካውን ዓቅም ማረጋገጫ ለመስጠት የሚካሄደው የሙከራ ሂደት አንዳንድ ዘርፍ፤ የኤሌክትሪክ ኃይል ስለሚያስፈልገው፤ ገዢው/ተጠቃሚው ይህንን ኃይል/ጉልበት ለመቀበል፤ ሙከራ እና ኮሚሽን/የማረጋገጥ ሥራ/ ማካሄድ ሂደት ከመጀመሩ በፊት ዝግጁ ሊሆን ይገባል፡፡ የመገናኛ መሥመሩ ወይም አውታሩ ከሌለ፤ ያን ጊዜ በኃይስ ደንቦች መሠረት፤ ፕሮጀክት ኩባንያው ለዘገየ ንሥቀ የጉዳት ክፍያ የመጠየቅ መብት አለው፤ ይኸውም በኃይስ የተቀመጡትን የማጠናቀቅ አንቀጾች በመጥቀስ ፡፡ ስለዚህ፤ የኃይል/ጉልበት ፋብሪካውን እና ተያያዥ ተቋማትን፤ አስፈላጊም በሆነበት የማስተላለፊያ መስመሩንም ባጠቃለለ መልኩ፤ ኮሚሽን ማድረግ /የማረጋገጥ ሥራ/ በሚካሄድበት ጊዜ፤ የእያንዳንዱን ወገን ፍላጎት የቅርብ ትስስር መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ሙከራ እና/ወይም ኮሚሽን /የማረጋገጥ ሥራ/ ማካሄድ በሚፈለግበት ጊዜ፤ የገዢው/ተጠቃሚው ተቋማት ከሌሉ፤ ፕሮጀክት ኩባንያው ከዚህ ጋር ተያያዥ ለሆኑ ጉዳቶች ያለውን የመጠየቅ መብት ተግባራዊ ማድረግ ይችላል፤ ጥቅም ላይ ሊውል ይችል ነበር ተብሎ የሚታሰበውን ዓቅምና ኃይል/ጉልበትንም በመጨመር፡፡ ስለዚህ ገዢው/ተጠቃሚው፤ የኃይል/ጉልበት ፋብሪካውን ሙከራ እና ኮሚሽን ሥራ /የማረጋገጥ ሥራ/ ለማካሄድ የሚያስፈልጉትን ለሚሟላትና፤ያሉበትን ግዴታዎች ለመወጣት፤ በጥንቃቄ ዓቅሙን ሊገምግም ይገባል፡፡

## ውል የተገባበትን ዓቅም መድረስ አለመቻል

ሙከራ እና ኮሚሽን /የማረጋገጥ ሥራ/ ማካሄድ፤ ምናልባት ውል ከተገባበት በታች የሆኑ ውጤቶችን እና/ወይም የተፈለገውን የአፈጻጸም ደረጃዎች መድረስ አለመቻልን፤ ለምሳሌ እንደ ተዓማኒነት ያለው ዓቅም፣ የተመደበ ነዳጅ አጠቃቀም(የሙቀት ደረጃ) እና ሌሎች ጉዳዮችን ሊያጋልጥ ይችላል፡፡ የሙከራ ውጤቶች ምን ያህል አስቀድሞ ከተለየው ውጤት የራቁ መሆናቸውን መሰረት በማድረግ፤ ምናልባት ፋብሪካው የሚጠበቅበትን የውጤት አፈጻጸም እንዲያሟላ፤ የማስተካከል ሥራ ሊያስፈልግ ይችላል፤ይህ ደግሞ ምናልባት የንሥቀን መዘግየት ሊያመጣ ይችላል፡፡

የኃይል/ጉልበት ፋብሪካውን የሥራ አፈጻጸም የማሻሻል ዕድል ከሌለ፤ ይህን ጊዜ ገዢው/ተጠቃሚው ሁለት የተለመዱ አማራጮች አሉት

የተገኘውን ምርት መቀበል፣ ዋስትና የተሰጠበትን ምርት ተግባራዊ ባለማድረግ ከሚሆኑ ከተያያዥ ቅጣቶች

ጋር

## ስምምነቱን መሰረዝ፤ እናም ስለዚህ ኃግስን ማቋረጥ

ኃግስ ዝቅተኛ የአፈጻጸም ውጤት ደረጃዎችን ለመድረስ ተገቢ የሆኑ አንቀጾች ይኖሩታል (ብዙውን ጊዜ፤ በሚሰራጩ ሃይል አመንጪ ፋብሪካዎች፤ በዓቅም ወጪዎች ክፍያ እንደተገለጸው)፡፡ የሙከራው ውጤቶች ተቀባይነት ሳያገኙ ሲቀሩ፤ ያን ጊዜ ኃግስ ምናልባት ሊቋረጥ ወይም አፈጻጸምን ተቀባይነት ወዳለው ደረጃዎች ለማሻሻል፤ ከሌሎች የማስተካከያ እርምጃዎች ጋር፤ ከመሰረቱ ሊሻሻል ይገባል፡፡ በኃግስ መላው ዘመን፤ ፕሮጄክት ኩባንያው የኃይል/ጉልበት ፋብሪካውን የአፈጻጸም ዓደጋዎች ይሸከማል፡፡

## ምርት/የሙቀት መጠን ዓደጋ መለየት

በሙከራ ወቅት፤ የፋብሪካው ምርትና ነዳጅ አጠቃቀም ዓቅም፤ ውል የተገባበትን የአፈጻጸም ደረጃዎች ለመድረስ ካልቻሉ፤ ፕሮጄክት ኩባንያው ምናልባት በኢግኮ ኮንትራቱ ውስጥ መብቱን የመጠየቅ ዕድሎች በሚከተሉት ላይ ሊኖረው ይችላል (i) የኢግኮ ሥራ ተቋራጭ እና (ii) የመሣሪያዎች አምራቹ ስምምነቶችና ዋስትናዎች፡፡ ቢሆንም የሚከተለውን ማስተዋል ጠቃሚ ነው፤ በኃግስ ደንቦች ሥር እነዚህ ጥበቃዎች በቀጥታ ለገዢው/ተጠቃሚው አይሰሩም፤ ምክንያቱም ገዢው/ተጠቃሚው የኢግኮ ኮንትራት ወይም የመሣሪያዎች አቅርቦት ኮንትራት አባል አይደለምና፡፡

# የሥራ ሂደት ወቅት ስጋቶች

# የገበያ ዓደጋ

## የግዢ ግዴታዎች

የገዢው፤በአንድ የኃይል/ጉልበት አምራች ፋብሪካ የሚመነጭን ዓቅምና ኃይል/ጉልበት የመግዛት ግዴታዎች፤ (**የግዢ ግዴታዎች**) የኃይል/ጉልበት ፕሮጀክቱን ተፈጥሮ መሠረት በማድረግ የሚዋቀሩ ይሆናል፡፡

የሚሰራጩ ኃይል/ጉልበት ፋብሪካዎችን በተመለከተ፤ (በተለይ የሙቀት ኃይል/ጉልበት ፋብሪካዎች እና የውሃ ኃይል/ጉልበት ፕሮጀክቶች ከበቂ ስፋት ግድቦች ጋር)፤የግዢ ግዴታው በአጠቃላይ እንደ ግዴታ ይዋቀራል (i) ለቀረበ(ቀርቧል ተብሎ ለታሰበ) ዓቅም ለገዢው/ተጠቃሚው ክፍያ መፈጸም እና (ii) በገዢው/ተጠቃሚው የተሰራጨ እና በፕሮጀክት ኩባንያው መድረሻ ቦታው ድረስ የቀረበ ሃይልን መውሰድና መክፈል፡፡

በተቆራራጭ ታዳሽ ሃይል ምንጮች ላይ የሚወሰኑ ቴክኖሎጂዎችን በተመለከተ (በይበልጥ ነፋስ እና ፎቶቮላቲክ የፀሓይ ሃይል ፕሮጀክቶች)፤ግዴታው በተለምዶ የሚደነገገው እንደ ውሰድ እና ክፈል ግዴታ ሆኖ ይኸውም በኃይል/ጉልበት ፋብሪካው ለ በትክክል የመነጨ ኃይል/ጉልበት ወይም የሚገድብ ነገር እስከሌለ ሊመነጭ ይችል ለነበረ ኃይል፡፡

በሁለቱም ሁኔታዎች፤ መሠረታዊው መመሪያ፤ የገበያው ዓደጋ (የኃይል/ጉልበት ፋብሪካው ዓቅም ወይም በፋብሪካው የመነጨ ኃይል ምናልባት አስፈላጊ ሳይሆን ቢቀር የሚል ዓደጋ) ለፕሮጀክት ኩባንያው ሳይሆን ወደ ገዢው/ተጠቃሚው ሊመደብ ይገባል ነው፡፡ ሃይል ባለበት ሁኔታ፤ ገዢው/ተጠቃሚው አሁንም ክፍያ ሊፈጽም ይገባል፤ይኸውም ፕሮጀክት ኩባንያው በትክክል ኃይል/ጉልበት ፋብሪካውን ምርት እንዲያመርት አደረገ ወይም የመነጨውን የኤሌክትሪክ ሃይል ወሰደ ትኩረት ሳይሰጥ፡፡

እነዚህ ክፍያዎች በተለምዶ **የአቅርቦት ክፍያዎች** ወይም **ጥቅም ላይ የዋለ ኃይል እሳቤ ክፍያዎች** ተብለው ይገለጻሉ፡፡ እናም የፕሮጀክት ኩባንያው ካፒታል ወጪዎች ( የብድር ወለድ ክፍያ፣ **የተጣራ** የባለድርሻ ገቢ) እንዲሁም ቋሚ የሥራ ማስኬጃ ወጪዎች መሸፈናቸውን ለማረጋገጥ የተቀመሩ ናቸው፡፡

የኃይል/ጉልበት ፋብሪካው በሌለበት ሁኔታ ወይም የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት፤ገዢው/ተጠቃሚው (ወይም መንግሥት) ዓደጋውን ለመውሰድ በተስማሙበት በአጋጠሙ ሁኔታዎች ባልቻለበት ምክንያት፤ (ከሌሎች ነገሮች በተጨማሪ፣ ፖለቲካዊ ያልተጠበቁ ክስተቶች፣ ገዢው/ተጠቃሚው ላይ ተፅእኖ የፈጠሩ ያልተጠበቁ ሁኔታዎች፣ የሕግ ለውጥ፣ ከፍተኛ የኃይል ማስተላለፊያ ሲስተም አለመኖር፣ እናም የገዢው/ተጠቃሚው በቃሉ አለመገኘት)፤ ፕሮጀክት ኩባንያው **ለታሰበ አቅርቦት** ወይም **ለታሰበ ሃይል** ክፍያዎች ምናልባት መብት ያገኝ ይሆናል፤ እነዚህ ክፍያዎች ደግሞ ካፒታል እና ቋሚ የሥራ ማሰኬጃ ወጪዎችን እንዲሸፍኑ የታሰቡ ናቸው፡፡ እነዚህ የኮንትራት ዘዴዎች፤ ለኃይል/ጉልበት ፕሮጀክት ዓደጋዎችን ከመለየትና ከመመደብ አንጻር ወሳኝ ናቸው፡፡

## ኃይል የመቀነስ ትዕዛዝ

ከላይ ለተገለፁት መሠረታዊ መመሪያዎች ቁብ ሳይሰጡ፤ አንዳንድ ገዢ/ተጠቃሚዎች እና/ወይም የሚመለከተው ማስተላለፊያ ሲስተም ኦፕሬተር፤ ምናልባት አንዳንድ ተቆራራጭ ሃይል **በሃይል የመቀነስ ትዕዛዝ ስር ባለው መብቶች** ጋር የተያያዘ ግዴታ ላይ ጥቂት የማላላት ስራ

ለማካሄድ ይፈልጉ ይሆናል፡፡ ይህ በብልሃት ድርድር የተካሄደበት ጉዳይ ይሆናል፡፡ ከፕሮጀክት ኩባንያው (እንዲሁም አበዳሪዎች) አንጻር፤እነርሱ በእርግጠኝነት አነስተኛው የግዢ ውሳኔ ሁሉንም ቋሚ ወጪዎችን እንደሚሸፍን (የብድር ዕዳን እና አነስተኛ የባለድርሻ ክፍያን ጨምሮ) ነው፡፡ ኃይል የመቀነስ ትዕዛዝ መብት የሚተገበር ከሆነ፤ ምናልባትም እነርሱ ኃግስ ለተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጥ ሊጠይቁ ይችላሉ፤ ወይም እነርሱ ከፕሮጀክቱ ሁኔታ አንጻር፤ ከሃይል መቀነስ ትዕዛዝ መብቶች ጋር ሊስማሙ ይችላሉ፡፡

# የሥራ አፈጻጸም

የኮንትራቱ አባላት፣ ኃግስ ውስጥ ሲገቡ፣ ኮንትራት የተገባለት የኃይል/ጉልበት ፋብሪካ ዓቅም ምን መሆን እንዳለበት ስምምነት ያደርጋሉ፡፡ የንሥቀን ለመድረስ፣ የኃይል/ጉልበት ፋብሪካው የግድ ሙከራ ሊካሄድበትና እንዲሁም ኮንትራት የተገባለትን ዓቅም ድርሻ ማሟላቱ መረጋገጥ አለበት፡፡ ይህ በአጠቃላይ አነስተኛ የሚጠበቅ ዓቅም ተብሎ ይጠራል፡፡ ይህ ሙከራ በተለምዶ የፕሮጀክት ኩባንያውን፣ ገዢው/ተጠቃሚው እና፣ በአባላት የተሰየመ ማንኛውም ነፃ መሐንዲስን ተሳትፎ ያካትታል፡፡ ለጉልበት/ኃይል ፋብሪካዎች፣ ለዓቅምና ለሃይል/ጉልበት ለሁለቱም ወጪ የሚከፈላቸው፣ ሙከራ የተካሄደበት ዓቅም በንሥቀ ምናልባት (ታሪፉ እንዴት እንደተቀመረ መሰረት በማድረግ) ገዢው/ተጠቃሚው ለፕሮጀክት ኩባንያው ሊከፍል የሚገባውን የዓቅም ክፍያ ሊወስን ይችላል፡፡ ይህ ሙከራ በአጠቃላይ በየዓመቱ የሚደጋገም ነው፣ እንዲሁም በየሙከራው ጊዜ፣ በአዲስ ሁኔታ የተሞከረው ዓቅም ለፕሮጀክት ኩባንያው የሚከፈለው የዓቅም ዋጋ ላይ ተፅእኖ ይኖረዋል፡፡

የኃይል/ጉልበት ፋብሪካው አነስተኛውን የሚጠበቅበትን ዓቅም ወይም ከዚያ በላይ፣ ስምምነት በተደረሰበት በታቀደው የንሥቀ ቀን ከተወጣ፤ነገርግን አሁንም ኮንትራት የተገባለትን ዓቅም መጠን ማስገኘት ካልቻለ፣ ያን ጊዜ ፕሮጀክት ኩባንያው፤ኮንትራት የተገባለትን ሙሉ ዓቅም ማቅረብ ይችል ዘንድ ያለው አማራጭ፣ ችግር የታየበትን የኃይል/ጉልበት ፋብሪካውን ክፍል፣ ስምምነት በተደረሰበት ጊዜ ውስጥ፣ ወይ መጠገን አለያም መተካት ነው፡፡ በሆነ ወቅት ላይ፣ ፕሮጀክት ኩባንያው ምናልባት ሊያቀርብ ከቻለው ዓቅም ጋር ብቻ እንዲቆይ ሊገደድ ይችላል፣ እናም ወደፊት በሙከራ የታየውን ዓቅም ወደ ኮንትራት የተገባለት መጠን ለማድረስ፣ ጉድለቶችን በማስተካከል ወደ ከፍተኛ የኃይል/ጉልበት የፋብሪካውን ዓቅም የመጨመር ችሎታ በፍፁም አይኖረውም፡፡ አነስተኛው ዓቅም፣ ከስምምነት ውጪ ወይም በንሥቀ የመጨረሻ ማስፈፀሚያ ቀን፣ መተግበር ካልቻለ፣ ገዢው/ተጠቃሚው፣ በተለምዶ ኃግስን የማስቆም መብት ይኖረዋል፡፡ አንዳንድ ኃግስ፣ ፕሮጀክት ኩባንያውን ፣ በሙከራ ከታየው በንሥቀ ከተቆለፈው በላይ የሆነ ዓቅም፣ ምንም ኃይል እንዳያቀርብ ምናልባት ሊገድቡ ይችላሉ፡፡ ወይም ገዢው/ተጠቃሚው፣ ለእንዲህ ዓይነት ተጨማሪ መጠን ሊከፍል አይገባም የሚል ውሳኔ ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

ታሪፉ፤የዓቅምንና የኃይል ዋጋን፣ ሁለቱንም ባካተተበት ኃግስ፣ ምክንያቱም ገዢው/ተጠቃሚው ለፋብሪካው ዓቅም ለመክፈል ግዴታ በሆነበት፣ ገዢው/ተጠቃሚው በተለምዶ ይህ ዓቅም ለራሱ አገልግሎት የሚውል መሆኑን ማረጋገጥ ይፈልጋል፡፡ ለነገሩ፤ገዢው/ተጠቃሚው በተለምዶ አነስተኛ የአቅርቦት ግዴታዎችን መጠየቁ አይቀርም፡፡ አቅርቦት በመሠረቱ የሚለካው ስምምነት በተደረሰበት ጊዜ ነው፡፡ አነስተኛ የአቅርቦት ልኮች በተለምዶ በባለጉዳዮች ድርድር የሚካሄድባቸው ሲሆኑ፣ እንዲሁም ለየት ባለ ሁኔታ በፕሮጀክት ቅጥረ ግቢ አኳኋን ላይ ይመረኮዛሉ፣ ለምሳሌ የአካባቢው ባህሪ፣ የተለየ ቴክኒካዊ የኃይል/ጉልበት ፋብሪካው ቅንብር እናም ሌሎች በኃግስ ተለይተው የተቀመጡ የብቃት መለያዎች፡፡ ኃግስ ይህን ጊዜ፣ ፕሮጀክት ኩባንያው ማድረስ ላልቻለው አነስተኛ የአቅርቦት ደረጃዎች ችግር፣ ለገዢው/ተጠቃሚው መፍትሔ ይሰጣል፡፡ ይህ ደግሞ ምናልባት ኃግስን የማስቆም መብትን ቅርጽ ወይም ከአፈጻጸም ጋር ለተያያዙ ጉዳቶች ፕሮጀክት ኩባንያውን የማስከፈል ዘይቤ ሊወስድ ይችላል፡፡ በማንኛውም ሁኔታ፤በደንብ በተዋቀረ ታሪፍ ሥር፣ ገዢው/ተጠቃሚው ለአልቀረበት ኃይል እንዲከፍል ሊደረግ አይገባም፡፡

## ለኤሌክትሪክ ኃይል ምርት ትዕዛዝ

በኃግስ ስር፣ ፕሮጀክት ኩባንያው፣ በከፍተኛ ኃይል ኬፐሎች ሲስተም ኦፐሬተር ለሚቀርቡ የኤሌክትሪክ ኃይል ምርት ትዕዛዝ መመሪያዎች በጥብቅ ሊታዘዝ ይገባል፡፡ ፕሮጀክት ኩባንያው በኃይል ስርጭት ላይ ለሚደርስ የአፈጻጸም ውድቀቶች ዓደጋ ላይ ሃላፊነቱን ይወስዳል፡፡ የከፍተኛ ኃይል ኬፐሎች ሲስተም የማሰራጫ ፕሮቶኮል፤በኃግስ ሊጠቀስ እንዲሁም የኃግስ አካል መሆን፤ወይም በፕሮጀክት ኩባንያው እና የማስተላለፊያ ኩባንያው የሚፈረም የማስተላለፊያ

ግኑኝነት ስምምነት አካል መሆን ይችላል፡፡ ወርሃዊ፣ሳምንታዊ እና ዕለታዊ የምርት መጠን ዕቅዶችን ማስተናገድ እንዲችል፤ የማሰራጨት ዕቅዶች፤ ለፕሮጀክት ኩባንያው እንዲደርሱት ይደረጋል፡፡

### ለታዳሽ ኃይል/ጉልበት ፕሮጄክቶች ልዩ እሳቤዎች

በታዳሽ ኃይል ፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ዓደጋን መለየት የተወሳሰበ ነው፤ ይኸውም በነዚህ ፕሮጀክቶች ባለው የማመንጨት ሂደት ቅርጽ የተነሳ፤ ለመጠቀስም ያህል፤ ኃይል/ጉልበት ማመንጨት በየጊዜው ከሚቆራረጥ ታዳሽ ኃይል አቅርቦት ጋር የተጣመረ ነውና፡፡

በታዳሽ ኃይል ኃግስ፤ ገዢው/ተጠቃሚው የሚከፍለው ለቀረበለት ሃይል ብቻ ነው፡፡ የገዢው/ተጠቃሚው፤ ለቀረበለት ሃይል፤ በተቀመጠው ታሪፍ መጠን እንዲከፍል ያለበት ግዴታ አንዳንዴ በኃግስ በተቀመጠው መጠን እንዲወሰን ይደረጋል፤ ማንኛውም ከተፈለገው በላይ ኃይል በወቅቱ ባለው የቦታው ዋጋ የነቁጣ ገበያ ካለ እንዲሸፈን ይደረጋል፡፡ ምንም እንኳን ገዢው/ተጠቃሚው የተቻለውን ያህል ዓቅም ማግኘት እንዲችል ቢጠይቅም፤ ደርዙ ከአሰራጭ ፋብሪካዎች በጣም ዝቅ ያለ ሊሆን ይገባል፤ ምክንያቱም ፕሮጀክት ኩባንያው የታዳሽ ኃይል ፕሮጀክቱን ምርት ለመቆጣጠር ዓቅም ስሌለለው፡፡

ይህን በግልጽ ለማስቀመጥ፤ ታዳሽ ኃይል ፕሮጀክቶች በብዙ መንገድ ለድንገተኛ የፀሓይ፣ዝናብ እና ንፋስ ሁኔታ የተጋለጡ ስለሆኑ፤የተለየ ዓቅም በማንኛውም የተለየ ቀን ለማቅረብ ዋስትና የላቸውም፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ ገዢው/ተጠቃሚው፤የታቀደ የተጣራ የኃይል/ጉልበት ዓቅምን ለመደገፍ አነስተኛ የአቅርቦት ግዴታ ለመመደብ ቢመርጥም፤ ዓደጋውን ወደ ፕሮጀክት ኩባንያው ማሻገር፤ በታዳሽ ኃይል ፕሮጀክቶች ላይ ሊካሄድ የሚችልን የመዋዕለ ንዋይ አቅርቦት ሊያግድ/ሊያርቅ ይችላል፡፡ አስታራቂ የሆነ መፍትሔ ሊሆን የሚችለው፤ ዝቅተኛ የአቅርቦት ግዴታዎችን መመሥረት፤ ይኸውም ከአሰራጭ ኃይል/ጉልበት ፋብሪካዎች በብዙ ሁኔታ ዝቅ ያሉ፤ፕሮጀክት ኩባንያው ከአየር ጠባይ ጋር የተያያዙ ያልታሰቡ አካባቢያዊ ባህርያት ጋር በሚስማማ ሁኔታ መጓዝ እንዲችል፤ይህ እንዳለ ሆኖ፤ ፕሮጀክቱ ዝቅተኛውን የአቅርቦት ግዴታ ለረጅም ጊዜ ካላሟላ፤ ገዢው/ተጠቃሚው፤ፕሮጀክቱን የማቆም መብቱን እንደተጠበቀ በመተው፡፡

# ነዳጅ እና ተያያዥ ጥሬ ነገሮች አቅርቦት


ለኃይል/ጉልበት ፕሮጀክቶች አንዱ እጅግ አሳሳቢ የሆነው ጉዳይ፤ ረጅም ለሆነ ጊዜ በቂ አቅርቦት ማግኘት መቻል፤እንዲሁም የነዳጅና ሌሎች ተያያዥ ጥሬ ነገሮች ዋጋ ነው፡፡ የነዳጅ አቅርቦትን ዓደጋ መለየት በብዙ ጉዳዮች ላይ የሚመረኮዝ ሲሆን፤ በተለይ ደግሞ የትኛው አካል ነው አቅርቦቱን ለመደራደር በበለጠ ሁኔታ ላይ ያለው፣ የነዳጅ አቅራቢው ፋይናንሲያዊ አቅም፣ የሌሎች አማራጭ ነዳጅ አቅራቢዎች ህልውና፣እና ለነዳጅ አቅርቦት የሚስማማው ገበያ የዕድገት ደረጃ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፡፡

### ጥሬ ዕቃን አቅርቦ ውጤት አገልግሎትን የመጠቀም አሰራር

ፕሮጀክት ኩባንያዎች፤ ተደራድሮ ቋሚ እና አስተማማኝ የሆነ የነዳጅ ሃብት አቅርቦት፤ ለምሳሌ እንደ ዘይት፣ ከሠል፣የተፈጥሮ ጋዝ፣ ባዮማስ ወይም እንፋሎት ለማግኘት፤ሁልጊዜ በአመቺ ሁኔታ አይደሉም፡፡ ገዢው/ተጠቃሚው ወይም መንግሥት ምናልባት ይህን ለመሥራት የተሻሉ ሳይሆኑ አይቀሩም፡፡ በእንዲህ ያሉ ሁኔታዎች፤ ገዢው/ተጠቃሚው የኃይል/ጉልበት ፕሮጀክቱን እንደ ጥሬ ዕቃን አቅርቦለት ውጤት አገልግሎቱን የሚጠቀምበት አድርጎ ቢያዋቅረው ይመርጣል፡፡ ይህ በተለይ ነዳጅ አቅራቢው በመንግሥት ባለቤትነት ሥር በሆነበት ወይም ከገዢው/ተጠቃሚው ጋር የተዛመደ ሲሆን ያስኬዳል፡፡

በዚህ ጥሬ ዕቃን አቅርቦ ውጤት አገልግሎቱን የመጠቀም አሠራር፤ገዢው/ተጠቃሚው፤ ለኃይል/ጉልበት ፋብሪካው ነዳጅ የመግዛትና (ክፍያውን ጨምሮ) የማቅረብ ሙሉ ኃላፊነትን ይወስዳል፡፡ ገዢው/ተጠቃሚው የኃይል/ጉልበት ፋብሪካውን ለማዘዝ ከፈለገ፤ በቂ የነዳጅ መጠን ለኃይል/ጉልበት ፋብሪካው እንደደረሰ ማረጋገጥ አለበት፤ ይኸውም የተፈለገውን በኋላ በእርሱ የሚሰራጨውን የኤሌክትሪክ ኃይልን ማመንጨት እንዲቻል፡፡ ፕሮጀክት ኩባንያው ያን ጊዜ፤ ለኃይል/ጉልበት ፋብሪካው የደረሰው ነዳጅ ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ሃላፊነቱን ይወስዳል፡፡ ይህ የሚከናወነው፤ ፕሮጀክት ኩባንያው ነዳጅን ወደ ኃይል፤ በኃይል መለወጥ ፍጥነት፤ይኸውም የከባቢው አየር  እና የማስተላለፍ ሁኔታ እንዳለ በሆነበት፤ ስምምነት የተደረሰበትን የኃይል/ጉልበት ፋብሪካውን ብቃት በሚያሳይ መልኩ፤እንዲተገበር ማድረግ ሲቻል ነው፡፡

Tolling Arrangement




Conventional Power Purchase Agreement




ስለዚህ በዚህ ጥሬ ዕቃን አቅርቦ ውጤት አገልግሎቱን የመጠቀም አሠራር፤ገዢው/ተጠቃሚው ወይም አስተናጋጁ መንግሥት፤ በቀጥታ ከሦስተኛ አካል ነዳጅ አቅራቢዎች ጋር፤ወደ ነዳጅ አቅርቦት ስምምነት ይገባሉ፤ እንዲሁም ለነዳጅ ሃብቱ ክፍያ ሃላፊነትን ይወስዳሉ፡፡ ያንጊዜ፤ገዢው/ተጠቃሚው ወደ የተለየ ስምምነት ይገባል፤ ይኸውም  የኃይል/ጉልበት ግዢ ስምምነት፣ ጥሬ ዕቃን አቅርቦ ውጤት አገልግሎቱን የመጠቀም አሠራር ስምምነት፣ ወይም ሃይልን የመለወጥ ስምምነት ከፕሮጀክት ኩባንያው ጋር  ተብሎ የሚጠራ ይሆናል፡፡

ይህ የተለመዱ የኃግስ ደንቦችን እንዲሁም አንዳንድ የነዳጅ አቅርቦቱ ደንቦችን የያዘ ይሆናል፡፡ ለአስተዳደር ቀለል እንዲል፤ ፕሮጀክት ኩባንያው ምናልባት መመሪያዎችን በቀጥታ ለሦስተኛው አካል ነዳጅ አቅራቢ ነዳጅ አቅርቦትን በተመለከተ ያስተላልፍ ይሆናል፤ እንዲሁም የሚላክ ነዳጅ መጠንን የመጠቀም እና፣ ያንን ነዳጅ የማድረስ ፕሮቶኮሎችን በተመለከተ ሊስማማ፤ ነገርግን ፕሮጀክት ኩባንያው የክፍያ ሃላፊነትን ፣ እንዲሁም ምናልባት ነዳጅ አቅራቢው በፕሮጀክት ኩባንያው በአግባቡ የተሰጠውን የማድረስ ግዴታዎቹን ቢጥስ ለሚደርሰው ዓደጋ ተጠያቂነትን አይወስድም፡፡

## የነዳጅ አቅርቦት ውሎች

የሀይል አቅርቦትን የሚገዙ ተዋዋዮች አብዛኛውን ጊዜ የነዳጅ ሃይል ግዢን አስመልክቶ ከፍተኛውን ሃላፊነት የሚሰጡት በፐሮጀክት ኩባንያው ላይ በመሆኑ የፕሮጀክት ኩባንያው ከሶስተኛ የነዳጅ ሃይል አቅራቢ አካል ጋር የሃይል አቅርቦት ውል መፈፀም የሚኖርበት ይሆናል፡፡ በዚህም ምክንያት የፕሮጀክት ኩባንያው በሃይል አቅርቦቱ ስምምነት መሰረት የግንባታ ስምምነቱን ማስጠበቅ የሚያስችለው የበቂ ነዳጅ አቅርቦት ውል ይፈፅማል፡፡ የሃይል አቅርቦት ገዢው መሰረተ-ልማቱን ምናልባት ወደሌላ ስፍራ ማዛወር በሚያስፈለገው ጊዜ የፕሮጀክት ኩባንያው የነዳጅ ሃይል አቅርቦት እጥረት አያጋጥመውም፡፡ በአንፃሩ የፕሮጀክት ኩባንያው ጥቅም ላይ የማያውለው አላስፈላጊ የነዳጅ ክምችት ውል መግባት ወይም ሃይል ለማመንጨት ስራ ለማይውል ነዳጅ አላስፈላጊ ክፍያዎች መፈፀም አይኖርበትም፡፡

የነዳጅ ሃይል አቅርቦት ስምምነነቱን ዝርዝር ሁኔታ በዚህ መመሪያ በጥልቀት ማቅረብ የሚቻል አይደለም፡፡ ይሁንና የፕሮጀክት ኩባንያው በርካታ ወሳኝ ጉዳዮችን በማካተት ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ከእነዚህ ወሳኝ ጉዳዮች መካከል  የሚከተሉት ይካተቱበታል፡-

- የነዳጅ ሃይል አቅራቢው በውሉ መሰረት ጥራቱን የጠበቀ ነዳጅ የሚያቀርብ መሆኑን የሚያረገግጥ የኮንትራት ውል መኖር ይገባዋል፡፡ ይህ ስምምነት የነዳጅ አቅርቦቱ አስጊ በሚሆንበት ጊዜ የመሰረተ ልማት ገንቢው አካል የግንባታ ስራው የሚስተጓጎል በመሆኑ ይህን ታሳቢ የሚያደርግ የ"ብርቱ ጥንቃቄ" (best endeavors) ግዴታ ውል መሆን ይኖርበታል፡፡

- የነዳጅ አቅርቦቱ ወርሃዊና ዓመታዊ የአቅርቦት መጠኑና ጥራቱ ሳይስተጓጎል የሃይል ማመንጫው ስራ ላይ በማይሆንባቸው አጋጣሚዎች ሁሉ ሳይቀር የሚፈፀም ይሆናል፡፡

- የሚቀርበው የነዳጅ ሃይል ከተወሰነው የጥራት ደረጃ አንፃር ተገቢው ጥበቃ ይደረግለታል፡፡ የነዳጁ ደረጃም ተፈላጊውን መስፈርት ሟሟላት ይኖርበታል፡፡ ነዳጅ በሚቀዳበትና በሚዘጋበት እንዲሁም የጽዳት ሥራ በሚሠራበት ጊዜ በፍሰት የሚባክን የነዳጅ መጠንን ታሳቢ የሚያደርግ ተጨማሪ ወጪ በአቅራቢው የሚሸፈን መሆኑን ገዢው ማረጋገጥ ይኖርበታል፡

- በኃይል ግዢ ስምምነቱ መሰረት የፕሮጀክት ኩባንያው ለሚያገኘው ነዳጅ ኃላፊነቱን የሚቀበለው ነዳጅ አቅራቢው እንደመሆኑ መጠን ለሚያጋጥመው የነዳጅ እጥረትም እንዲሁ በተመሳሳይ ኃላፊነቱን የሚወስድ ይሆናል፡፡ እንዲህ ያለውን ኃላፊነት የሚወስድ አቅራቢ ማግኘት አብዛኛውን ጊዜ አይቻልም ወይም ደግሞ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የሚስማማ አቅራቢ አይኖርም፡፡ በመሆኑም

- በኃይል ግዢ ስምምነቱ መሰረት የሚፈጸመውን የነዳጅ አቅርቦት ከኃይል ማመንጫው ፍተሻና ስራ የመጀመር ሂደት ጋር በማጣመር ማመንጫው በታቀደለት የCOD መርሃ-ግብር መሰረት ወደ መደበኛው ስራ ከመገባቱ በፊት በሃይል ግዢው ስምምነት የነዳጅ አቅርቦቱን አስተማማኝነት ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ይሁንና የነዳጅ አቅርቦቱ የሚጀምርበት ቀን እጅግ አስቀድሞ መሆን የለበትም ያለበለዚያ ፕሮጀክት ኩባንያው የሚያስፈልገውን ነዳጅ ከማገኘቱ በፊት በስምምነቱ አስገዳጅነት አላስፈላጊ ወጪ እንዲያወጣ የሚገደድ ይሆናል፡፡

በነዳጅ አቅርቦት ስምምነቱ መሠረት የሚፈጸመው ያልቀረበው ነዳጅ ክፍያ በውሉ አእና በሃይል ግዢ ስምምነቱ ግዴታዎች መሰረት ወደ ነዳጅ አቅራቢው መተላለፍ ይኖርበታል፡፡ በሌላ አገላለጽ የፕሮጀክት ኩባንያው ያልተጠቀመበት ነዳጅ ክፍያ በሚያጋጠመው ጊዜ በስምምነቱ መሰረት ነዳጅ አቅራቢው የካሣ ክፍያ የሚፈጽምለት ይሆናል፡፡

በመሆኑም በነዳጅ ግዢ ስምምነቱ መሰረት የተመለከቱት ዝርዝር ውሎች በሙሉ በቀጥታ የነዳጅ ግዢውን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ከላይ ስለ ዋጋ እንደተመለከተው የነዳጅ ዋጋው በስምምነቱ መሰረት አበዛኛውን ጊዜ ወደ አቅራቢው የሚተላለፍ ይሆናል (ይህ የሚሆነው የሚቀርበው ነዳጅ ከኃይል አቅርቦት ጋር ያለው ቁርኝት ቀጥተኛ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ነው)፡፡ ስለሆነም ኃይል ገዢው በኩባንያው የሚቀርበውን የኤሌክትሪክ ኃይል ታሳቢ በማድረግ የነዳጅ ዋጋ ከኢንዱስትሪ ዋጋ ጋር የተመጣጠነ መሆኑን በሚገባ ማጤን ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ነዳጅ ገዢው አካል በነዳጅ ግዢ ስምምነቱ የሚመለከተውን የክፍያ መጠን የተቻለውን ያህል ዝቅተኛ በማድረግ ቁርጠኛ መሆኑን በስምምነቱ ማመልከት ይኖርበታል፡፡ በውል ስምምነቱ መሰረት በጥገና ወቅት የሚኖረው የኃይል አቅርቦት ሁልጊዜ ከመቶ ፐርሰንት በታች እንደመሆኑ መጠን በነዳጅ ግዢ ውሉ የሚመለከተው የክፍያ መጠን የኃይል ማመንጫው በተያዘለት ጊዜ ጥገና ላይ ሲሆን ነዳጅ የማይጠቀምበትን ሁኔታ ታሳቢበማድረግ ለከፍተኛ ወጪ እንዳይዳረግ ጥበቃ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በተመሳሳይ ፕሮጀክት ኩባንያው የኃይል ማመንጫውን የጥገና ጊዜ ከነዳጅ ማስተላለፊያ መሳሪያዎች (ምናልባት የኃይል ማመንጫው በነዳጅ የሚሰራ ከሆነ) ጥገና ጋር በማጣጣም አላስፈላጊ የኃይል አቅርቦት እጥረት እንዳይኖር ማድረግ ይኖርበታል፡፡

እንደዚሁም በነዳጅ ገዢውና ሻጩ መካከል ራሱን የቻለ የውል ስምምነት መኖር አለበት ሲባል በነዳጅ ግዢ ስምምነቱ መሰረት የሚፈጸመው የነዳጅ አቅርቦት ስጋት ኃላፊነት ሙሉ በሙሉ የሚጣለው በገዢው ላይ ብቻ አለመሆኑን በሚገባ መጤን ያስፈልገል፡፡ ገዢው አካል በነዳጅ ግዢ ውሉ መሰረት የአቅርቦት ስጋት የሚኖርበትን ሁኔታ የሚቀበለው በአቅራቢው በኩል አማራጭ የነዳጅ አቅርቦት የሚኖር መሆኑን ወይም አቅራቢው ለአማራጭ የነዳጅ አቅርቦት ያለውን ቀረቤታ በማረጋገጥ ይሆናል፡፡ ነዳጅ አቅራቢው ብቸኛ የነዳጅ አቅራቢ አካል ወይም ምንጭ ከሆነ ገዢው አካል የነዳጅ አቅርቦት እጥረት የማያጋጥመው መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ካልሆነም በነዳጅ እጥረት ምክንያት የአቅርቦት መቋረጥ እንዳይኖር አማራጭ ምንጭ ያለው ስለመሆኑ መተማመኛ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም በእጥረት ምክንያት ለሚፈጠር ኪሣራ ካሣ የመክፈል እና በስምምነቱ እንደአስፈላጊነቱ ውል ማቋረጥ የሚቻል መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ ገዢው አካል በነዳጅ አቅራቢው በኩል የሚኖር ዕዳ ነክ ጉዳይን በሚገባ ማወቅ አለበት፡፡ ነዳጅ አቅራቢው ዕዳ ያለበት ከሆነ ይህን መክፈል የሚያስችል የገንዘብ አቅም አለው? ይህ የማይሆን ከሆነ በምን አይነት ሁኔታ የውል ስምምነት ማቋረጥ እንደሚችል ወይም የሚኖረው ዋስትና ምን ሊሆን እንደሚችል (የተሟላ ዋስትናን ጨምሮ) ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## ነዳጅ የማጓጓዝ ሂደት ግዴታዎች

እነዚህ የውል አግባቦች የነዳጅ አቅርቦት እና የማጓጓዝ የስራ ክፍፍል ኃላፊነት በሚኖርበት ጊዜ ይበልጥ የሚወሳሰቡ ይሆናሉ፡፡ የኃይል ማመንጫው ለነዳጅ ምንጩ በሚኖረው ቅርበትና በነዳጁ አይነት ላይ በመመስረት ከነዳጅ ማጣሪያው ወደ ኃይል ማመንጫው ስለሚደረገው ነዳጅ የማጓጓዝ ሂደት ነዳጁን ከሚያጓጉዝ ሌላ አካል ጋር የተለየ የውል ስምምነት መፈጸም ያስፈልጋል፡፡ በእርግጥ ይህ ሁኔታ ነዳጅ አቅራቢው ከነዳጅ አቅርቦት ጋር የተያያዙ ስጋቶችን ኃላፊነት በአጓጓዡ ላይ ወይም በገዢው ላይ የሚጥል በመሆኑ በማጣሪያውና በኃይል ማመንጫው መካከል ባለው ርቀት የማጓጓዝ ሂደት የሚኖረውን ስጋት በፕሮጀክት ኩባንያው ላይ እንዲጨምር ያደርገዋል፡፡ አቅራቢው ነዳጁን የጥራት ደረጃውን እንደጠበቀ ካለበት ስፍራ አጓጉዞ የኃይል ማመንጨው ድረስ ከማቅረብ ጋር ተያያዥ የሆኑ ስጋቶችን ኃላፊነት መቀበል ይኖርበታል፡፡ ነገር ግን ከነዳጅ አጓጓዡ ጋር ተያያዥ የሆኑ ስጋቶችን ኃላፊነት የሶስትዮሽ ማለትም ለገዢው፤ ለአቅራቢው እና ለአጓጓዡ ማጋራት የሚቻል ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ደረጃውን ያልጠበቀ ነዳጅ ለኃይል ማመንጫው ቢቀርብ ስህተቱ የአጓጓዡ ሳይሆን የአቅራቢው በመሆኑ ከዚህ ጋር ተያያዥ የሆኑ ኪሳራዎችን ካሳ የመክፈል ግዴታ በውል ስምምነቱ መሰረት ሊኖር ይገባል፡፡ ነዳጅ አጓጓዡ የመንግሥት ተቋም ከሆነ የፕሮጀክት ኩባንያው በግዢ ፈጻሚ ክፍሉ አማካይነት ነዳጅ አጓጓዡን ስለማጓጓዝ ከተገባው ግዴታ በተጨማሪ በአፈጻጸም ጉድለት ተጠያቂ የሚያደርገው

ይሆናል፡፡ ይሁንና አጓጓዡ ተቋም የቱንም ያህል ብቃት ያለው አካል ቢሆንም እንኳን በአንድ መንግሥት ስር በሚተዳደሩ ተቋማት መካከል ፖለቲካዊ አንድምታዎች እንዳይከሰቱ ለመከላከል አንደኛው ወገን (ነዳጅ አጓጓዡ) ኃላፊነቱን የግድ መቀበል ይኖርበታል፡፡

# ማስተላለፍ

ከምንጭ ቀጥታ የሀይል አቅርቦት ስርዓት (bundled system) ኃይል የመግዛት፤የማስተላለፍ እና የማሰራጨት ሂደት ሚና የሚከናወነው በአንድ አካል ይህም በኃይል ግዢ ፈጣሚው ይሆናል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ግዢ ፈጻሚው አካል በፕሮጀክት ኩባንያው የሚቀርበውንና የሚሸጠውን ኃይል የማስተላለፍ ኃላፊነትን ይወስዳል፡፡ በተመሳሳይ ግዢ ፈጻሚው በዚህ ስርዓት ውስጥ የኃይል ማመንጫው ከኃይል ተቀባዩ ማዕከል ጋር ያለው የኃይል ግንኙነት ተስተካክሎ እንዲቀጥል የማድረግ ግዴታ ይኖርበታል፡፡

በተቃራኒው የዲስትሪቢዩሽን (የተዘዋዋሪ) መስመር (unbundled system) ኃይል የመግዛት፤የማስተላለፍና የማሰራጨት ተግባር የኃይል ግዢ ፈጻሚው ኃላፊነት አይሆንም፤ የሚፈጸመውም በሌላ አካል ይሆናል፡፡ ይህ ኃላፊነት በተለየ የኤሌክትሪክ ሃይል አቅርቦት ውል የሚሸሻል ሲሆን ለዚህ ተግባር የተሰየመ ሌላ የህግ አካል የሚያስፈጽመው ይሆናል፡፡

በተዘዋዋሪ መስመር አቅርቦት ስርዓት የተለዩ የማስተላለፍ ስጋቶች ይኖራሉ፡፡ በተዘዋዋሪ የመስመር አቅርቦት ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው ስጋት ይህን ለማስፈጸም የሚዋዋለው ኩባንያ ተዓማኒነት ሲሆን ይህም የኃይል ማመንጫው፡- ሀ) ኃይል ለማቅረብ ዝግጁ በሆነበት ጊዜ እና ለ) ለኃይል ግዢ ስምምነት ተገዢ በመሆን የአቅርቦት መቋረጥ ሲያጋጥም ለሚፈጠረው ኪሳራ ካሳ ለመክፈል ያለው አቅም ነው፡፡ ከኃይል ገዢው አካል አንጻር ሲታይ ኃይል የማስተላለፍ ኃላፊነት ከራሱ ቁጥጥር ውጪ በመሆኑ ይህን ኃላፊነት የሚቀበለው አይሆንም፡፡ ከፕሮጀክት ኩባንያው አንጻር ሲታይ ይህን ኃላፊነት በከፊል ካልሆነ በስተቀር ሊወጣው የማይችለው በመሆኑ የማስፈጸም አቅም ያለው አካል (የኃይል ግዢ ፈጻሚው) እንዲሆን ህጋዊ ጥያቄን የሚያቀርብ ይሆናል፡፡ ይህ ሁኔታ በይበልጥ እውን የሚሆነው ለሃይል ግዢ ፈፃሚውና የሃይል አስተላላፊው ኩባንያ መሰረት ያለው ግንኙነት ሲኖራቸው ይሆናል (ሁለቱም የመንግሥት አካላት ወይም የአንድ ተቋም ክፍሎች ናቸውና)፡፡ የፕሮጀክት ኩባንያው የሚያነሳው የመከራከሪያ ነጥብ ከሃይል አቅርቦቱ ተጠቃሚው መንግሥት እንደመሆኑ የሃይል ማመንጫው ከማሰራጫው ጋር በሚኖረው ግንኙነት ወይም በሃይል ስርጭት ረገድ የሚኖሩ ስጋቶችን ሃላፊነት መቀበል ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የሃይል ግዢ ስምምነቱ የተዘዋዋሪ ሃይል ስርጭት (unbundled power) ግብይት ሂደት በመሆኑ የሃይል ማስተላለፍ ስጋቶችን በከፊል ወይም በሙሉ ለሃይል ግዢ ክፍሉ ይሰጣል፡፡ በመሆኑም የሃይል ግዢ ክፍሉ ለሃይል አስተላላፊ ኩባንያው ግዴታዎች ዋስትና ሰጪ ይሆናል፡፡

# የውጭ ምንዛሪ

ከሃይል ግዢ ውሉ በተለየ የገንዘብ ክፍያ ሲፈፀም የፕሮጀክት ስፖንሰሮች ከምንዛሪ ጋር በተያያዘ ከገንዘብ ግሽበት ራሳቸውን ለመጠበቅ እርምጃዎች መውሰድ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ክፍያ በአገር ውስጥ በሚፈፀምበት ጊዜ የሚኖሩ የፕሮጀክት ስጋቶች ሁለት ናቸው፡-

- የአገር ውስጥ ገንዘብ በቀላሉ ሊመነዘር የማይችል ይሆናል (ይህም ማለት በዋናዋና ገንዘቦች

ሊመነዘር የማይችል ይሆናል)፤

- እንዲሁም ፕሮጀክቱ በሚንቀሳቀስበት አገር በስራ ዘመኑ የሚያስፈልገው የውጭ ምንዛሪ ክምችት ላይኖር ይችላል፡፡

ይህ ዓይነቱ ስጋት የሚኖር መሆኑ አስቀድ ሲታወቅ ሁለቱ ወገኖች የመንግሥት ዋስትናና የኢንሹራንስ አገልግሎትን በማቀናጀት ችግሩን ማስወገድ የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል፡፡

## የውጭ ምንዛሪ መለዋወጥ

በሃሳብ ደረጃ ሲታይ የፕሮጀክት ክፍያዎች ፕሮጀክቱ በሚንቀሳቀስበት አገር የገንዘብ ዓይነት መከፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት ከምንዛሪ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ስጋቶች ለመቀነስ ሲባል ነው፡፡ ይሁንና የዳበረ የባንክ ኢንደስትሪ በሌለበትና ውስን የብድር አገልግሎት ባለበት አካባቢ ይህን ለማድረግ አስቸጋሪ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ በሚንቀሳቀስበት አገር ደረጃ ለፕሮጀክት የሚሆን የአገር ውስጥ ገንዘብና በማንኛውም ምክንያት ምንዛሪ በእርዳታ ሰጪው አገር የገንዘብ ዓይነት ተፅኖ ስር በሚወድቅበት ጊዜ የፕሮጀክት ኩባንያው ሌላ የገንዘብ ድጋፍ በመፈለግ ለአጭር ጊዜ ከሚቆየው ግሽበት (እጅግ የከፋ ግሽበት የሚኖርበትን ሁኔታ አያካትትም) እራሱን ሊጠብቅ ይገባዋል፡፡

ለአጭር ጊዜ የሚቆይ የምንዛሪ መለዋወጥ በሚከሰትበት ጊዜ የምንዛሪ ስጋትን ለመከላከል ከሚያስችሉ ስልቶች ካከል ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፡

- ሁሉም የምንዛሪ መጠኖች የገንዘብ ድጋፍ በተገኘበት አገር የገንዘብ መጠን ተፅዕኖ ስር በሚሆኑበት ጊዜ የሃይል ግዢ ፈፃሚው አካል የኤሌክትሪክ አገልግሎት ክፍያዎችን በምንዛሪው አንፃር በአገር ውስጥ ገንዘብ እንዲከፍል ይደረጋል፤

- የተመሳሳይ ገንዘብ መጠን ስሌት ማስላትና ወደፊት የሚከሰቱ መሰል የገንዘብ ምንዛሪ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ስምምነትን አቅሙ ካላቸው ተቋማት ጋር መፈፀም ፣

- እንዲሁም በገንዘብ ምንዛሪ እጥረት የተከሰቱ ችግሮችን ለማካካስ የሚያስችል እርምጃ በመንግሥት ይወሰዳል (ይህ የግሽበት ክስተት አብዛኛውን ጊዜ የሚከሰት ባይሆንም)፡፡

ከላይ የተመለከቱት የአጭር ጊዜ የገንዘብ ምንዛሪ ግሽበትን ለመከላከል የሚያስችሉ ፍቱን መንገዶች መሆናቸው ቢታወቅም ከፍተኛ የገንዘብ ምንዛሪ መለዋወጥ ወይም ግሽበት በሚከሰትበት ጊዜ ኩባንያው በእነዚህ ስልቶች ራሱን መከላከል አይቻለውም፡፡ ይህ ዓይነቱ ከፍተኛ የግሽበት አደጋ የሚከሰትበት አገር መንግሥትም ሆነ የመጨረሻ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ክፍሎች እየጨመረ የሚሄደውን የምንዛሪ መጠን መቋቋምም ሆነ ለተራዘመ ጊዜ የሚፈለግበትን የገንዘብ መጠን መክፈል የሚያስችለው አቅም አይኖርም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ በከፍተኛ የገንዘብ ግሽበት ምክንያት የሚከሰት አደጋ የሚወገደው በኢንሹራንስ ኩባንያዎች የአከፋፈል ስሌት መሰረት ይሆናል፡፡

## ምንዛሪ ማግኘትና ማስተላለፍ መቻል

የአገር ውስጥ ገንዘብ በነፃነት ሊመነዘር በማይችልበትና የውጭ አገር ገንዘብ ለዕዳ መክፈያነት የሚውል ከሆነ የውጭ ገንዘብ ባለቤትና ኢንቨስትመንት ፈፃሚና አበዳሪ ከሆነው አገር ጋር የኢንቨስትመንት ግንኙነት ለማድረግ ለኩባንያው አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ ምንም እንኳን ኢንቨስትመንቱ ተፈፃሚ የሚሆንበት አገር በፕሮጀክቱ ዘመን በሙሉ የገንዘብ ምንዛሪ እጥረት የማይኖር መሆኑን የሚያረጋግጥ ስምምነት የሚፈጽም ቢሆንም ምንዛሪ የማግኘትና ማስተላለፍ የመቻል ስጋቶች በሚከተሉት ሁለት ምክንያቶች መከሰታቸው የማይቀር ይሆናል፡-

1. ፕሮጀክቱ በሚፈፀምበት ተዋዋይ አገር ምንግሥት የአገር ውስጥ ምንዛሪ ማጭበርበር፤ እና

2. የምንዛሪ ግዴታዎችን ለመወጣት የማያስችል የውጭ ገንዘብ ክምችት እጥረት ናቸው፡፡

እንዲህ ዓይነቶቹን ስጋቶች ማስወገድ የሚቻልባቸው በርካታ መንገዶች፡-

1. ለአጭር ጊዜ የሚቆይ የምንዛሪ እንቅፋቶችን ለማስወገድ የሚያስችል በሌላ አገር ተቀማጭ የሚሆን የብድር አቅርቦት አገልግሎት (offshore debt service) ማመቻቸት፣

2. በካሽ ምትክ ዋጋ በሚያወጡ ቁሳቁሶች ግብይት መፈጸም፤

3. የፖለቲካዊ ኢንሹራንስ ሽፋን በማግኘት የምንዛሪ አለመኖር ስጋትን መከላከል ናቸው፡፡

# ሌሎች ስጋቶች

## በህግ መሰረት መስራትና የህግ ለውጥ

መንግስትና ገዢው፣ የፕሮጀክት ኩባንያውን በኃይል ግዢ ስምምነቱ ውስጥ በሁሉም ተጨባጭ መስክ አግባብነት ባለው ሀገር ህግ እንደሚገዛ በውል ግዴታ እንዲገባ ሊጠይቁት ይችላሉ። በህግ ምክርና ቅድመ ጥንቃቄ ላይ በመመስረት፣ ቢያንስ ፕሮጀክቱ ሲጀምር ተፈጻሚ የነበሩ ህጎችን በመመልከት፣ የፕሮጀክት ኩባንያው በበኩሉ ከላይ የተባለውን ለመፈጸም ግዴታ መግባት መቻል አለበት። ይሁንና ህጎች በጊዜ ሂደት የሚለዋወጡ እንደሆነ የፕሮጀክት ኩባንያው(በተያያዥም አበዳሪዎቹ)፣ በህጎቹ መሰረት ለመስራት ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ግዴታ መግባት ያስቸግራቸዋል።

የህግ ለውጥ የሚባለው ጽንሰ ሀሳብ በጊዜ ሂደት የሚከተሉትን ሀሳቦች የሚያካትት ሆኗል፡- 1) የአዲስ ህግ መውጣት 2) የነባር ህጎች መሻሻል እና/ወይም 3) በፍርድ ቤቶች፣ በበሸንጎዎች፣ ፕሮጀክቱንም ሆነ የፕሮጀክት ኩባንያውን በተመለከተ ተግባራዊ ስልጣን ወይም የቁጥጥር ኃላፊነት ባለው መንግስታዊ ወይም ሌላ ባለስልጣን የተደረጉ የህግ ትርጉም ለውጦች። በዚህ ሁኔታ ውስጥ "ህግ" የሚለው ቃል ሲፈታ ህጎችን፣ አዋጆችንና ደንቦችን፣ ትእዛዞችን፣ መመሪያዎችን ወዘተ በሚሸፍን መልኩ መሆን አለበት።

**ጊዜ** - የህግ ለውጡ ከግምት ውስጥ የሚገባው ከምን ቀን ጀምሮ እንደሆነ በገዢውና በፕሮጀክት ኩባንያው መሀከል፣ ክርክር ሊነሳ ይችላል። ብዙውን ጊዜ የኃይል ግዢ ስምምነቱ ከተፈረመበት ቀን ጀምሮ ይሆናል። ይሁንና፣ በጨረታው ሂደት የፕሮጀክት ኩባንያው ግዴታ የገባበት የታሪፍ መጠን ያለ እንደሆነ፣ ቀኑ የፕሮጀክት ኩባንያው ፕሮፖዛሉን ካስገባበት ቀን(ለፕሮፖዛል ጥሪው ምላሽ በመስጠት) ጀምሮ ቢሆን ተገቢ ይሆናል። ይህ ጉዳይ አንዳንዴ፣ የፕሮጀክት ኩባንያው የወጪ አቋም/ዝርዝር/ሁኔታ ላይ ጫና የሚያሳድር የህግ ለውጥ ተደርጎ እንደሆን ለማጣራት በሚከናወነው ቅድመ ጥንቃቄ ወቅት መፍትሄ ሊያገኝ ይችላል። ሆኖም፣ ህጉ ተፈጻሚ በሚሆንበት ቦታ እንደሚገኘው የህግ አወጣጥ ግልጽነትና፣ የፕሮጀክት ኩባንያው ቅድመ ጥንቃቄ ለማከናወን እንደነበረው የጊዜ መጠን፣ ገዢው ይህን በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ስጋት፣ ብዙውን ጊዜ ሊወስዳቸው የሚስማማባቸው የኃይል ግዢ ስምምነቱ ከተፈጸመ በኋላ የሚነሱ የህግ ለውጥ ስጋቶች ላይ ደምሮ ቢያስበው የተሻለ ይሆናል።

የህግ ለውጥ በፕሮጀክት ኩባንያው ላይ በተለያየ አኳኋን ጫና ሊያሳድር ይችላል፡

- በኃይል ግዢ ስምምነቱ ውስጥ የሚገኝ አንድ ግዴታን አፈጻጸም በአሉታዊ መልኩ ሊነካ ወይም አፈጻጸሙን ጨርሶ የማይቻል ሊያደርገው ይችላል

- የፕሮጀክት ኩባንያውን የገቢ ምንጭ በአሉታዊ መልኩ ሊነካ ይችላል

- የፕሮጀክት ኩባንያውን የአንድ ጊዜ ክፍያ ካፒታል ወጪ እንዲከፍል ሊያስገድደው ወይም፣ በፕሮጀክት ኩባንያው የስራ ማስኬጃ ወጪ ላይ ቀጣይነት ያለው ጭማሪ ሊያስከትል ይችላል(የፕሮጀክት ኩባንያው በየጊዜው በህግ ለውጡ መሰረት ይፈጽም ዘንድ) ወይም

- በግልባጩ፣ በፕሮጀክት ኩባንያውን የስራ ማስኬጃ ወይም የተተነበየ/የሚጠበቅ ካፒታል ወጪን መቀነስ ሊያስከትል ይችላል።

ተገቢው የተጨባጭነት/የጉልህነት መጠን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ አግባብነት ያለው የህግ

ለውጥ ባይደረግ ኖሮ የፕሮጀክት ኩባንያው ሊገኝበት ከሚችልበት ሁኔታ ያልበለጠ ወይም ያላነሰ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ እንዲቆይ የፕሮጀክት ኩባንያውና ገዢው ጠቅላላ ስምምነት ይገባሉ። ስለዚህ በተደረገ የህግ ለውጥ አማካይነት፣ የፕሮጀክት ኩባንያው አንድን ግዴታ በጊዜያዊነት መወጣት እስካቃተው ድረስ፣ ይህ ሁኔታ የፕሮጀክት ኩባንያው የውል ግዴታውን እንደጣሰ አያስቆጥረውም፤ በፕሮጀክት ኩባንያው ላይ ተፈጻሚነት ያላቸው ማናቸውም የጊዜ ገደቦችም በዚሁ መሰረት ይራዘማሉ። በተጨማሪም የህግ ለውጡ የንግድ ትግበራ ቀን መዘግየትን እስካስከተለ ድረስ፣ የኃይል ማመንጫ ጣቢያው "እንደተጠናቀቀ የሚቆጠር" ሊሆን ይችላል፤ እንዲሁም የኃይል ማመንጫው ጥቅም ላይ ያልዋለው በተደረገው የህግ ለውጥ ምክንያት እስከሆነ ድረስ፣ የፕሮጀክት ኩባንያው፣ "ጥቅም ላይ እንደዋለ የሚቆጠር" እና "እንደመነጨ ኃይል የሚቆጠር" የሚባሉት ክፍያዎች ይገቡታል። ከዚህም በላይ፣ በህግ ለውጡ አማካይነት የፕሮጀክት ኩባንያው የወጪ መጨመር ወይም የገቢ መቀነስ እስከገጠመው ድረስ፣ ይህ ሁኔታ የፕሮጀክት ኩባንያው 1) የፕሮጀክት ኩባንያው ያወጣውን ወጪ ወይም የቀነሰበትን ገቢ የሚከፍል ወይም የሚተካ ቀጥተኛ የካሳ ክፍያ ወይም 2) ተገቢ የሆነ የታሪፍ ጭማሪ እንዲገባው/እንዲከፈለው ያደርጋል። በግልባጩ፣ የፕሮጀክት ኩባንያው ከተደረገው የህግ ለውጥ ያገኘው ጥቅም ካለ፣ ተገቢው የታሪፍ ቅናሽ ማስተካከያ እንደዛው ተግባራዊ ይደረጋል።

የህግ ለውጡ የኃይል ግዢ ስምምነቱን አፈጻጸም ጨርሶ የማይቻል እስካደረሰው ድረስ፣ መከፈል ያለበት የካሳ መጠን ልክ ስምምነቱ የተቋረጠው በፖለቲካዊ አስገዳጅ ሁኔታዎች ቢሆን ኖሮ እንደሚሰላው ተሰልቶለት፣ የፕሮጀክት ኩባንያው የኃይል ግዢ ስምምነቱን የማቋረጥ ጠቅላላ መብት ይኖረዋል።

# ስምምነት፣ ፈቃድና የፈቃድ ወረቀት፣ የስምምነት መቋረጥ

## የፕሮጀክት ኩባንያው ስምምነትን፣ ፈቃድንና የፈቃድ ወረቀትን የማግኘት ኃላፊነት

ለመረዳት በማይከብድ ሁኔታ፣ ገዢዎች የሚፈልጉት የኃይል ማመንጫ ጣቢያዎች ተፈጻሚነት ያለው ህግ በሚጠይቃቸው ስምምነቶች መሰረት እንዲገነቡና ወደ ስራ እንዲገቡ ነው።
የኃይል ማመንጫ ጣቢያውን ለመገንባት፣ በባለቤትነት ለመያዝና ወደ ስራ ለማስገባት የሚያስፈልጉትን ስምምነቶች ማግኘት የፕሮጀክት ኩባንያው አይነተኛ ኃላፊነት ነው። ስምምነቶቹም፣ ከሞላጎደል የሚከተሉትን ያካትታሉ፡ የግንባታ ፍቃድ ወረቀት፣ አካባቢያዊ ፈቃድ፣ የአርኪዎሎጂ ፈቃድ ወረቀት፣ የስራ ፈቃድ ወረቀት። **ስምምነቶች** የሚለው ቃል በአጠቃላይ፣ ማንኛውንም ምዝገባ፣ መግለጫ፣ ዶሴ መክፈት፣ ስምምነት፣ ፈቃድ፣ መብት፣ ማስጸደቅ፣ ስልጣን መስጠት ወይም የፈቃድ ወረቀትን እንደሚያካትት ተደርጎ ይታሰባል።

## ስምምነቶችን፣ የፈቃድ ወረቀቶችንና ፈቃድን በማስገኘት ረገድ የገዢው የመተባበር ግዴታ

ስምምነቶችን የተመለከቱ ሁሉም ግዴታዎች የፕሮጀክት ኩባንያው ብቻ አይደሉም። አብዛኛውን ጊዜ ገዢው ከመንግስት ጋር የተዛመደ በመሆኑ፣ መንግስት ከሌሎች የመንግስት መስሪያቤቶች ጋር ግንኙነት አለው፣ ወይም በእነሱ ላይ ጫና ማሳደር ይችላል ተብሎ ተስፋ ይደረጋል። ከዚህም በላይ፣ በሀገር ውስጥ ገበያ ውስጥ እንደተቋቋመ አካል፣ አብዛኛውን ጊዜ፣ ገበያው የሚሰራበትን መንገድና፣ ህግና ደንብ የሚጠይቋቸውን ነገሮች በተመለከተ ገዢው የበለጠ እውቀት አለው። በመሆኑም፣ የፕሮጀክት ኩባንያው ስምምነቶችን ያገኝ ዘንድ፣ ገዢው "ምክንያታዊ ትብብር" ማድረግ እንደሚኖርበት አብዛኛውን ግዜ ሁለቱም ወገኖች ይስማማሉ። ይህ ሁኔታም፣ የፕሮጀክት ኩባንያው አስፈላጊዎቹን ስምምነቶች ሁሉ ማግኘቱ እንዲረጋገጥለት የሚፈልገውን አበዳሪውን ጨምሮ መጨረሻ ላይ ሁሉም ወገኖች የሚጠቀሙበት ሁኔታ ነው።

## ለከፍተኛ ደረጃ የማስጸደቅ ስራዎች የሚደረግ የጋራ ትብብር

አንዳንድ ጊዜ፣ ከከፍተኛ የመንግስት አካላት የሚሰጡ አንዳንድ ስምምነቶችን የማግኘት ኃላፊነት፣ የጋራ ኃላፊነታቸው መሆኑን ሁለቱ ወገኖች ሊስማሙ ይችላሉ። እነዚህም የማስጸደቅ ስራዎች አግባብነት ያላቸውን (እንደ ካቢኔ፣ፓርላማ፣ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የኢነርጂ ሚኒስቴር፣ የግብር ሰብሳቢ ባለስልጣን፣ ተቆጣጣሪ አካላትና ማዕከላዊ ባንክ ያሉ) ባለስልጣናት ስምምነት ማግኘትን ሊያካትቱ ይችላሉ። እንደዚህ ያሉ ስምምነቶች ብዙውን ጊዜ ለኃይል ግዢ ስምምነቱ ውጤታማነት አስፈላጊ በመሆናቸው፣ ስምምነቶቹ በተገቢው ጊዜ መገኘታቸውን ለማረጋገጥ ሁለቱም ወገኖች አብረው መስራታቸው አጠቃላይ ተገቢነት አለው።

## የመሬት መብት

የኃይል ማመንጫ ጣቢያውና፣ ተገቢዎቹ የማስተላለፊያ መስመሮች የሚቆሙበትን ቦታ የይዞታ መብት የማስገኘት ኃላፊነት፣ ከስራ ስምምነት ወደ ስራ ስምምነት እንዲሁም ከቦታ ቦታ የሚለያይ ነው። የኃይል ማመንጫ ጣቢያው እንዲቆምበት የታሰበበት ስፍራ ላይ ሰፊ ቦታ የያዘው መሬት፣ ወይንም የሁሉም መሬት ባለቤት መንግስት በሆነባቸው ቦታዎች፣ አብዛኛውን ጊዜ ገዢው ለፕሮጀክት ኩባንያው አስፈላጊውን የመሬት መብት እንዲሰጥ ወይም ከሌላ የመንግስት አካል መብቱን እንዲያሰጥ ይጠበቅበታል። ይሁን እንጂ በሌሎች ቦታዎች፣ መሬትንም ሆነ መሬትን የመጠቀም መብትን እንዲያስፈቅድ ኃላፊነት የሚጣለው የፕሮጀክት ኩባንያው ላይ ነው። እንዲህ ባሉ ሁኔታዎች ውስጥ ገዢው አሁንም ቢሆን፣ የፕሮጀክት ኩባንያው እነዚያን መብቶች ያገኝ ዘንድ እንዲተባበረው ጥሪ ሊቀርብለት ይችላል፤ በተለይ፣ የግል ባለይዞታዎች መሬታቸውን መሸጥ ያልፈቀዱ እንደሆነና መንግስት መሬትን በህጉ መሰረትና ለልማት(የሉዓላዊ መንግስት ወይም በውስጡ የሚገኙ አካላት የግል ንብረትን ፍትሃዊ ካሳ በመስጠት ለሀገራዊ ጥቅም እንዲውል የመውረስ መብት) መውረስ የሚችል በሆነበት ጊዜ።
የመሬት መብቶች ሁኔታም ከቦታ ቦታ ይለያያል። የመሬት ስርዓቱ መሬትን በነጻ መያዝን የማይፈቅድ በሆነ ጊዜ፣ የመሬት ይዞታ ሁኔታዎቹ(ሊዝ) የፕሮጀክቱን ጊዜ ለመሸፈን በሚያስችሉበት መጠን በቂ መሆን አለባቸው።

## የስምምነት መቋረጥ

የፕሮጀክት ኩባንያው ተገቢውን ማመልከቻ ቢያቀርብም፣ አንድ የመንግስት አካል/ባለስልጣን፣ ስምምነትን መስጠት ወይም ማደስ ያልቻለ እንደሆነ፣ ይህ ከህግ ለውጥ ጋር በአንድ አይነት መልኩ የሚወሰድ ሁኔታ ይሆናል። ይህም አንዳንድ ጊዜ **የስምምነት መቋረጥ** ተብሎ ይጠራል። በህግ ለውጥ ምክንያት የፕሮጀክት ኩባንያው የሚያስፈልገውን ፎርማሊቲ አሟልቶ ስምምነትን ማግኘት ወይንም ማሳደስ ያልቻለ ቢሆንም፣ በህግ ለውጥ ጊዜ የሚደረጉለት ጥበቃዎች ግን አሁንም ተግባራዊ እንደሚደረጉለት ማስተዋል ይገባል። የስምምነት መቋረጥ ሀሳብ፣ በኃይል ግዢ ስምምነት ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ፖለቲካዊ አስገዳጅ ሁኔታ ተብሎ እንደሚጠራና፣ ተመሳሳይ የመጨረሻ ውጤት እንዳለውም ማስተዋል አስፈላጊ ነው።

# የግብር ለውጥ

የግብር ለውጥ የፕሮጀክት ገቢን በከፍተኛ መጠን ሊጎዳና ፕሮጀክቱንም መሰረታዊ በሆነ መልኩ የማያዋጣ ሊያደርገው ይችላል። ለውጡም በግብር መጠን ለውጥ፣ አዲስ የግብር አይነት በመፍጠር፣ ወይም አግባብነት ያላቸውን የግብር ጥቅማጥቅሞች በሚያስወግድና ፕሮጀክቱ ካፈሰሰው ሀብት ላይ ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ በሚቀንስ እና/ወይም እዳዎቹን የመክፈል አቅሙን በሚነካ መልኩ ሊደረግ ይችላል። የግብር ለውጥ ውጤቶችም፡

1. የፕሮጀክት ወጪዎችን ሊጨምሩ ወይም ሊቀንሱ
2. የጥገናና የስራ ማስኬጃ ወጪዎችን ሊጨምሩ ወይም ሊቀንሱ እና
3. የፕሮጀክት ኩባንያው የሚጠብቃቸውን ገቢዎች ሊጨምሩ ወይም ሊቀንሱ ይችላሉ።

ከግብር ለውጥ ጋር የሚገናኙ ስጋቶችን ከማስተዳደር ጋር በተያያዘ ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ጉልህ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው፡

## የግብር ለውጡ መሰላት የሚጀምርበት ማጣቀሻ ቀን

የግብር ሁኔታ/አቋም ላይ የሚደረግ ለውጥ፣ በማጣቀሻው ቀን ላይ ከነበረው የግብር ሁኔታ/አቋም ጋር በመነጻጸር መወሰን አለበት። የማጣቀሻው ቀን በተለምዶ በሁለቱ ወገኖች ስምምነት የሚደረግበት ሲሆን፣ የኃይል ግዢ ስምምነቱ የተፈረመበት ቀን ወይም ሂሳብ የሚዘጋበት ቀንም ሊሆን ይችላል።

## የለውጡ አድሏዊ መሆን ወይም አለመሆን

የግብር ለውጥ ስጋትን የሚሸከመውን ወገን ለመወሰን እንዲቻል፣ በመደበኛነት በሶስት አይነት ለውጦች መሀከል ልዩነት ይወጣል፡

1. በተለይ በፕሮጀክቱና በውስጡ ባሉ የገንዘብ ድጋፍ አድራጊዎች፣ ተቋራጮች እንዲሁም አበዳሪዎች ላይ ብቻ ተፈጻሚነት ያለው ለውጥ (**አድሏዊ የግብር ለውጥ**)
2. በአጠቃላይ በኢንዱስትሪው ወይም በተመሳሳይ የባለሀብቶች መደብ ላይ ተፈጻሚነት ያለው የግብር ለውጥ (**ልዩ/አይነተኛ የግብር ለውጥ**)
3. ከላይ በተቀመጡት ሁለት ክፍሎች ውስጥ የማይወድቁና በአጠቃላይ ማህበረሰቡ ላይ ተፈጻሚነት ያላቸው ለውጦች (**አድሏዊ ያልሆነ የግብር ለውጥ**)

አድሏዊ የግብር ለውጥን በተመለከተ፣ ብዙውን ጊዜ ገዢው ይህን ስጋት እንዲሸከም የሚጠበቅበት፣ በታሪፍ ውስጥ አጠቃሎ በማሳለፍ ነው። ይህም ማለት፣ ማንኛውም የጨመረ የግብር ክፍያ፣ በፕሮጀክቱ የወጪ ታሪፍ ስሌት ውስጥ ይጠቃለላል፤ በመሆኑም ደንበኛው የግብር ጭማሪ ክፍያውን የሚያንጸባርቅ ታሪፍ መክፈል ይኖርበታል። አድሏዊ ያልሆነ የግብር ለውጥን በተመለከተ፣ ብዙውን ጊዜ የፕሮጀክት ኩባንያው ይህንን ስጋት፣ በአስተናጋጁ ሀገር ውስጥ ስራ ከመስራት ጋር የሚያያዝ የስጋት አካል አድርጎ እንዲቀበል ይጠበቅበታል። አድሏዊ ካልሆነ ልዩ/አይነተኛ የግብር ለውጥ ጋር በተመለከተ፣ ብዙውን ጊዜ ይህ ጉዳይ ሁለቱ ወገኖች እንዲደራደሩበት ክፍት የተተወ ነው።

## የግብር ለውጥ ስጋትን መቀነስ

ብዙውን ጊዜ፣ የግብር ለውጥን በተመለከተ፣ የስጋት መቀነሻ እርምጃዎች፣ ተግባራዊ የሚደረጉት፣ ከሚከተሉት በአንዱ ወይም በሌሎች መንገዶች ነው፡

- የአስተናጋጁ መንግስት መተማመኛ/ማረጋገጫ እና የፖለቲካዊ ስጋት ዋስትና

በአስተናጋጁ ሀገር ውስጥ በሚገኝ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ግብርን የሚመለከት ለውጥ እንደማይኖር፣ አዲስ ግብር እንደማይጣል፣ ወይም የግብር ጠቅማጥቅሞች እንደማይነሱ/እንደማይሻሩ የተሰጠ መተማመኛ/ማረጋገጫ፣ ፕሮጀክቱ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ፣ በፕሮጀክት ኩባንያው፣ በገንዘብ ድጋፍ አድራጊዎቹ እና በተቋራጮቹ ላይ ሁሉ ተፈጻሚነት ይኖረዋል። የመተማመኛውን/ማረጋገጫውን በአስተናጋጅ መንግስቱ የመጣስ ሁኔታ ለመከላከል፣ የፖለቲካዊ ስጋት ዋስትና በመግባት የፕሮጀክት ኩባንያው፣ ስጋቱን በይበልጥ መቀነስ ይችላል።

- ታሪፍ ስሌት ውስጥ ማጠቃለል

ታሪፉ፣ ፕሮጀክቱ በሚተገበርበት ጊዜ፣ “አድሏዊ” ወይም “ልዩ/አይነተኛ” የሆኑ ማንኛቸውንም የግብር ጭማሪ፣ የአዲስ አይነት ግብር መጣል፣ ወይም የግብር ጥቅማጥቅምን መወገድ፣ በሙሉ በሙሉ እንዲያጠቃልል ተደርጎ ነው የሚዘጋጀው።

# የቁጥጥር/አመራር ለውጥ

አንድ ፕሮጀክትን በገንዘብ የመደገፍን ነገር ለመወሰን፣ የፕሮጀክት ኩባንያው የቀረጸውን ፕሮጀክት ተግባራዊነትና አዋጭነት መገምገም አስፈላጊ የሆነውን ያህል፣ አበዳሪዎችና ገዢው የፕሮጀክት ኩባንያውን ራሱንና፣ የፕሮጀክት ኩባንያውን የሚቆጣጠሩትን አካላት ይገመግማሉ። የነዚህ አካላት መልካም ስም፣ ልምዳቸውና ከዚህ በፊት ያስመዘገቡት የስራ ታሪክ በሙሉ፣ የፕሮጀክት ኩባንያው በኃይል ግዢ ስምምነቱ ውስጥ የገባቸውን ግዴታዎች የመፈጸም ችሎታ ይኖረዋል ወይስ አይኖረውም የሚለው የአበዳሪውና ገዢው ግምገማ ላይ አስተዋጽኦ አላቸው። በመሆኑም፣ የፕሮጀክት ኩባንያው ባለአክሲዮኖች የፕሮጀክት ኩባንያውን ቁጥጥር/አመራር በአንድ ወገን ውሳኔ በራሳቸው ከመቀየር የመገደባቸው/የመቆጠባቸው ጉዳይ አበዳሪዎችና ገዢው የሚፈልጉት ጉዳይ ነው።

ብዙውን ጊዜ የኃይል ግዢ ስምምነቶች፣ ቁጥጥር/አመራር ማለት ምን ማለት እንደሆነ፣ እንዲሁም የፕሮጀክት ኩባንያው ቁጥጥር/አመራር ለውጥ ምን ምንን እንደሚያካትት ግልጽ ድንጋጌዎች ይኖሯቸዋል። የኃይል ግዢ ስምምነቱ፣ የፕሮጀክት ኩባንያው ቁጥጥር/አመራር ለውጥ፣ የገዢው ፈቃድ ሳይገኝ እንዳይከናወን ሊደነግግ ይችላል። በተለምዶ፣ የኃይል ግዢ ስምምነቱ፣ ገዢው ያለበቂ ምክንያት ፈቃዱን ሊከለክል እንደማይችልም አብሮ ይገልጻል። እንደ አማራጭ፣ የፕሮጀክት ኩባንያው ቁጥጥር/አመራር ለውጥ፣ ተወስኖ ከተገለጸ የጊዜ ገደብ በኋላ (ለምሳሌ፣ የጊዜ ገደቡ ለመነሻው/ለመጀመሪያው የብድር ወቅት፣ ወይም በግንባታ ወቅት ላይ ለውጥ እንዳይኖር ማድረግ ላይ ያነጣጠረ ሊሆን ይችላል)ሊደረግ እንደሚችል ሊፈቀድ ይችላል። እንደ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታም፣ የፕሮጀክት ኩባንያው ቁጥጥር/አመራር ለውጥ የግድ መደረግ ያለበት ነገር ከሆነ፣ የሚደረገው ለውጥ ኩባንያው በሀገር ውስጥ ያለውን ተጨባጭ ደረጃ መስፈርት የሚቀንስ መሆን የለበትም፣ ወይም አዳዲሶቹ የቁጥጥር/አመራር አካላት ከቀድሞዎቹ ጋር ተመሳሳይ የመልካም ገጽታ አቋም ሊኖራቸው ይገባል የሚለው ቅድመ ሁኔታ ሊቀመጥ ይችላል። መጨረሻ ላይ የተጠቀሰው ሁኔታ እንደየሰዉ የሚለያይ የግምገማ መስፈርት ሊሆን ይችላል። እንዲህ አይነት ቅድመ ሁኔታዎችና ገደቦች ከፕሮጀክት ፕሮጀክትም ሊለያዩ ይችላሉ።

የፕሮጀክት ኩባንያውም እንደዚሁ በገዢው ድርጅት ውስጥ የሚደረግ የቁጥጥር/አመራር ለውጥ ይመለከተዋል፤ በተለይም የኤሌክትሪክ አቅርቦት ኢንዱስትሪው እየተፍታታ የሚገኝባቸው ሀገሮችና፣ አገልግሎቱን በሞኖፖል ይሰጥ የነበረ ገዢ ተቋም እንደገና እየተደራጀ በሚገኝባቸው ሀገሮች። በኃይል ግዢ ስምምነቱ ውስጥ የሚገኙት የገዢው ግዴታዎች መንግስታዊ ድጋፍ የሚደረግላቸው በሆነ ጊዜ፣ ይህ ጉዳይ ለፕሮጀክት ኩባንያው እምብዛም አስፈላጊ ላይሆን ይችላል። ይሁን እንጂ፣ ደንበኛው እንዲህ ያለው መንግስታዊ ድጋፍ የሌለው ሲሆንና የኢንቨስትመንት ደረጃው፣ መልካም ስሙና የእውቀቱ ጥልቀት፣ የፕሮጀክት ኩባንያውና አበዳሪዎች የኃይል ግዢ ስምምነቱን ሲፈርሙ ግምት ውስጥ ያስገቧቸው ቁልፍ ጉዳዮች ሲሆኑ፣ ገዢውም ቢሆን በተመሳሳይ መልኩ ያለ ፕሮጀክት ኩባንያው ፈቃድ የቁጥጥር/አመራር ለውጥ እንዳያደርግ ሊገደብ ይችላል። እንደዚሁም ገዢው ላይ ተጨማሪ ቅድመ ሁኔታዎች ሊደነገጉ ይችላሉ፤ ለምሳሌ፣ እንደገና የተደራጀው ገዢው ተቋም ከቀድሞው ጋር ተመሳሳይ የኢንቨስትመንት ደረጃ እንዲኖረው ወይም መንግስታዊ ድጋፍ እንዲደረግለት የሚሉ ቅድመ ሁኔታዎች ሊቀመጡ ይችላሉ።

# ፖለቲካዊ - መንግስታዊ ስጋት እና መውረስ /መወረስ

የኃይል ግዢ ስምምነት፣ በግል ባለሀብት/አልሚ ባለሀብት እና በመንግስት ባለቤትነት ስር የሚገኝ አካል/ድርጅት መሀከል፣ የኤሌክትሪክ አቅርቦትን እና ግዢን በሚመለከት የሚፈረም የንግድ ስምምነት ነው። የፕሮጀክት ኩባንያው ከዚህ ወዲያ የፕሮጀክት ገቢዎችን እንዳያገኝ በሚያደርግ

መልኩ፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኃይል ማመንጫ ጣቢያው ስራ ውስጥ መንግስት ጣልቃ ለመግባት ሊወስን የመቻሉ ስጋት አለ። ይህም የፕሮጀክት ኩባንያውን እዳውን እንዲሁም ባለአክሲዮኖች እንደድርሻቸው ማግኘት ያለባቸውን ትርፍ በየጊዜው እንዳይከፍል ያስተጓጉለዋል። ይህን አይነቱን ጣልቃ ገብነት በተመለከተ ብዙውን ጊዜ፣ ፖለቲካዊ አስገዳጅ ሁኔታዎች በሚለው ክፍል ውስጥ ይደነገጋል፣ ወይም ደግሞ መንግስታዊ የስጋት ሁኔታዎችን በሚመለከት የተለየ የስምምነቱ ክፍል ውስጥ ይደነገጋል።

በኃይል ግዢ ስምምነቱ ውስጥ የመወረስ ውጤቶችን የሚመለከት ነገር መገለጽ አለበት። መወረሱ የሚገናኘው ከኃይል ማመንጫ ጣቢያው ወይም ከፕሮጀክት ኩባንያው አክሲዮኖች ጋር ሊሆን ይችላል፤ ሁለቱንም ሁኔታዎች የኃይል ግዢ ስምምነቱ ሊሸፍናቸው/ሊመለከታቸው ይገባል። በመጀመሪያው ሁኔታ ውስጥ መንግስት የኃይል ማመንጫ ጣቢያውን በአካል ሄደው የሚቆጣጠሩ የጥበቃ ጓዶችን/ሰራተኞችን በቦታው ላይ ሊያሰፍር ይችላል፤ በኋለኛው ሁኔታ ውስጥ ደግሞ መንግስት በማስገደድ የኃይል ማመንጫ ጣቢያውን አክሲዮኖች ባለቤትነት በራሱ ቁጥጥር ስር ሊያደርግ ይችላል። እንደ ናሽናላይዜሽን፣ ኮንፊሲኬሽን፣ ሪክዊዚሽን እንዲሁም ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት የሚያካትቱ አጠቃላይ ተግባራትን የተመለከተ ግልጽ ብያኔ/ፍቺ ያስፈልጋል።

የእጃዙር መውረስንም በተመለከተ ድንጋጌዎችን ማስቀመጥ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል፤ ይህም አብዛኛውን ጊዜ መንግስት በቀጥታ የኃይል ማመንጫ ጣቢያውን የሚወርስበትን ሳይሆን፣ እጅግ አስቸጋሪ የደንብና ቁጥጥር ጫና በማድረግ እንዲሁም፣ የውጭ ምንዛሪ ግብይትን በመገደብ ወይም፣ የኃይል ግዢ ስምምነት ታሪፉ የሚቀናነሰው/የሚሰላው በሀገር ውስጥ ምንዛሪ በሆነ ጊዜ፣ ገንዘቡን ወደ ውጭ መላክን በመከልከል፣ የፕሮጀክት ኩባንያው የኃይል ማመንጫ ጣቢያውን ውጤታማ/ተጨባጭ በሆነ መልኩ መቆጣጠር እንዳይችል የሚያደርግበትን ሁኔታ ማለት ነው። እነዚህ እርምጃዎች፣ የሀገር ውስጥ ፖለቲካዊ አስገዳጅ ሁኔታን፣ ወይም የህግ ወይም የግብር ለውጥን በሚመለከቱት ድንጋጌዎች ውስጥ መሸፈን የሚችሉ ሲሆኑ፣ ገዢው ካሳ የማይከስባቸው ከሆነ ግን የፕሮጀክቱን ውድቀት ያስከትላሉ።

የኃይል ግዢ ስምምነቱ በመውረስ ውስጥ የማይካተቱ ጉዳዮችንም መደንገጉ አስፈላጊ ነው። አለበለዚያ፣ በአጠቃላይ አረዳድ እንደ መውረስ የማይቆጠሩ ህጋዊ ተግባራትንም ሲያከናውን፣ መንግስት ራሱን ከፍተኛ መቀጫዎችን ከመክፈል ጋር ተጋፍጦ ሊያገኘው ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ መንግስታት ሀገሪቱ ውስጥ ያለውን የጤናንና የአካባቢ ጥበቃ እርምጃዎችን እንዲሁም ከግብር ጋር የተገናኙ እርምጃዎችን የሚያካትተውን ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ፣ ለመቆጣጠርና ለማስተዳደር እርምጃዎችን መውሰድ ይችላሉ። ይሁንና፣ እነዚህ እርምጃዎች መወሰድ ያለባቸው በቅን ልቦና እንጂ፣ አድሏዊ በሆነ መልኩ ወይም በዋነኛነት የግል ንብረትን ለመውረስ በማሰብ አይደለም። በተጨማሪም፣ እንደ ኃይል ማስተላለፍና የነዳጅ ትራንስፖርት ያለ ተያያዥነት ያለውን መሰረተ ልማት በተመለከተ ኃላፊ ከሆኑ በመንግስት ባለቤትነት ስር ከሚገኙ ኩባንያዎች ጋር ፕሮጀክት ኩባንያው የውል ስምምነት ሲኖረው፣ በነዚህ የውል ስምምነቶች ውስጥ የተደነገጉ መፍትሄዎችን በመጠቀም የሚፈቱ ከንግድ ጋር የተገናኙ ክርክሮችንና በመሰረቱ ፖለቲካዊ እርምጃ የሆነውን መውረስን ለይቶ ማየት አስፈላጊ ነው። ብዙውን ጊዜ አልሚዎች፣ መወረስ፣ በኃይል ግዢ ስምምነቱ ውስጥ፣ እንደ ውል መቋረጥ መወሰድ እንዳለበትና፣ ለዚህም የፕሮጀክት ኩባንያው፣ በፕሮጀክቱ የትግበራ ዘመን ይጠብቀው ለነበረው የገቢ ምንጭ ካሳ ሊከፈለው እንደሚገባ ይከራከራሉ። የውል መቋረጥ ክፍያ ትክክለኛ አሰላል **ድህረ-ውል መቋረጥ ግዴታዎች** በሚለው ስር ተብራርቷል። ለማንኛውም፣ ገዢው ምን ያህል ከመንግስት ጥገኝነት ነጻ መሆኑ ላይ ተመስርቶ፣ በኃይል ግዢ ስምምነቱ ውስጥ የተቀመጠው የካሳ ክፍያ ተገቢ ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ገዢው ከመንግስት ጥገኝነት በጣም ነጻ የሆነ እንደሆነ፣ ከላይ የተባለው ሁኔታ በሚፈጠርበት ጊዜ፣ ገዢው ሙሉ በሙሉ ካሳ እንዲከፍላቸው ከመጠበቅ ይልቅ፣ የፕሮጀክት ኩባንያውና አበዳሪዎቹ፣ የመወረስ ስጋትን በሌላ መንገድ መሸፈን አለባቸው የሚለው ክርክር ይመረጣል።

ከዚህም በላይ፣ መውረስ በሚኖርበት ጊዜ፣ ገዢው ማናቸውንም የካሳ ክፍያ ለመፈጸም፣ የገንዘብ ምንጭ ይኖረው እንደሆን፣ ሁሉም ወገኖች ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው። ተመራጭ የሚሆነው፣ ይህ ግዴታ በመንግስታዊ ዋስትና/ማረጋገጫ ቢደገፍ ነው፤ ግን ደግሞ ይህንን ድጋፍ

ማግኘት የተከለከለ/የማይቻል ሊሆን ይችላል።

እንደ Put and Call Option Agreement ያለ፣ ከካሳ ጋር የተገናኙ ጉዳዮችን የሚመለከት የተለየ ስምምነት ሲኖር፣ አሻሚ ሁኔታን ለማስወገድ ሲባል፣ መወረስ በሚያጋጥምበት ጊዜ መከፈል የሚኖርበት የክፍያ መጠን በትክክል ምን ያህል እንደሆነ፣ በግልጽ መደንገግ አለበት።

አንድ አልሚ፣ የአለም ባንክ ቡድን አንድ ክፍል ከሆነ፣ እንደ መልቲላተራል ኢንቨስትመንት ጋራንቲ ኤጀንሲ(MIGA) ካለ ተቋም ዘንድ፣ የፖለቲካ ስጋት መድህን ዋስትና መግባትንም ሊያስብበት ይችላል። የMIGA መድህን ዋስትና ጠቀሜታ፣ መወረስ በሚያጋጥምበት ጊዜ ክፍያን ማረጋገጡ ብቻ ሳይሆን፣ በይበልጥም፣ በመንግስት ዘንድ መልካም ስምን/ገጽታን የማጣትን ስጋት የሚፈጥር በመሆኑ፣ እንዲሁም በሌሎች አለም አቀፍ የንግድ ግንኙነቶች ውስጥ መንግስት የሚታይበት ሁኔታ ላይ ከሚያስከትለው ተያያዥ አሉታዊ ውጤት የተነሳ፣ የመውረስ አዝማሚያን እጅጉን የሚቀንስ በመሆኑ ነው።

# አስገዳጅ ሁኔታዎች

በኃይል ግዢ ስምምነት ውስጥ የአስገዳጅ ሁኔታዎችን ትርጉም እና ውጤታቸውን በማስቀመጥ ስለ አስገዳጅ ሁኔታዎች የሚናገር ግልጽ ድንጋጌ ማስቀመጥ ያስፈልጋል። ድንጋጌው እንደ አስገዳጅ ሁኔታ ሊቆጠሩ የማይችሉ ጉዳዮችንም በተለይ ገልጦ በኃይል ግዢ ስምምነቱ ውስጥ ሊያስቀምጥ ይችላል።

## የአስገዳጅ ሁኔታዎች ቁልፍ ገጽታዎች/መገለጫዎች

በአጠቃላይ ስንመለከተው፣ አስገዳጅ ሁኔታ የሚከተሉት ገላጭ ገጽታዎች ይኖሩታል

- ሁኔታው በተዋዋይ ወገን የውል ግዴታዎችን የመፈጸም ችሎታ ላይ ተጨባጭ አሉታዊ ጫና አለው

- ጉዳዩ ፋታ የሚያስፈልገው ተዋዋይ ወገን ጥፋት ካለመሆኑም በላይ ከተዋዋዩ ምክንያታዊ ቁጥጥር ውጭ ነው

- ጉዳዩ ተዋዋይ ወገኑ በምክንያታዊ ህሊና ሊተነብየው የሚችለው አይነት ነገር አይደለም፣ እንዲሁም፣ አስገዳጅ ሁኔታውን ለመቀልበስ ወይም ጉዳቱን ለመቀነስ ማንም ትጉህ ተዋዋይ ወገን ሊወስዳቸው የሚችላቸው ምክንያታዊ እርምጃዎች በሙሉ ተግባራዊ ሊሆኑ የማይችሉበት ሁኔታ ነው።

አንዳንድ ጊዜ፣ የአስገዳጅ ሁኔታ ብያኔ/ትርጉም አንድ ጊዜ ከተፈጠረው ጉዳይ አልፎ ጉዳዩ በቀጣይነት ያስከተላቸው ጫናዎችንም ያካታትላል። ለምሳሌ፣ የኃይል ማመንጫ ጣቢያ ላይ ያልተጠበቀና ከፍተኛ የጎርፍ አደጋ ተከስቶ ጉዳት ቢያደርስና፣ እንዲሁም የጎርፉ ውሃ ተመጥጦ ወጥቶ አልቆ፣ የጉዳት መጠኑን የመገመት ስራው ከመጀመሩ በፊት አንድ ወር አካባቢ ቢወስድ፣ አስገዳጅ ሁኔታውን በመንተራስ የሚጠየቀው ፋታ፣ የጎርፍ አደጋው ከተከሰተበት የመጀመሪያ ቀን አልፎ፣ አደጋው በቀጣይነት እያስከተለ ያለውን ጉዳት ያጠቃልላል።

በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ የማይሸፈኑ ጉዳዮችንም በግልጽ ማብራራት አስፈላጊ ነው። አንድ የኃይል ማመንጫ ጣቢያ ከበቂ ጥገና እጦት ስራ ቢያቆም፣ ይህ በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ አይወድቅም። የኃይል ማመንጫ ጣቢያው ማመንጨት ይችላል የተባለውን ያህል እንዲያመነጭ፣ የሚያስችለውን የነዳጅ ፍጆታ፣ የፕሮጀክት ኩባንያው በበቂ መጠን ሳያቀርብ ከቀረም፣ በተመሳሳይ ሁኔታ በአስገዳጅ ሁኔታ ውስጥ አይሸፈንም።

## የአስገዳጅ ሁኔታ አይነቶች

በኃይል ግዢ ስምምነት ውስጥ የሚካተቱ የአስገዳጅ ሁኔታ አይነቶች፣ በበርካታ ክፍሎች ሊከፈሉ የሚችሉ ሲሆን፣ እንደ የሀገር ውስጥ ፖለቲካዊ አስገዳጅ ሁኔታ፣ የውጭ ፖለቲካዊ አስገዳጅ ሁኔታና ተፈጥሯዊ አስገዳጅ ሁኔታዎች ያሉት ቁልፍ የሆኑት ናቸው።

**የሀገር ውስጥ ፖለቲካዊ አስገዳጅ ሁኔታዎች** ወይ በአስተናጋጅ ሀገር መንግስት የሚፈጠሩ ወይም መንግስት ከሌላ አካል በተሻለ መልኩ ሊከላከላቸው፣ ሊቆጣጠራቸው ወይም ሊቀንሳቸው የሚችላቸውን ሁኔታዎች ያካትታሉ። እዚህ ክፍል ውስጥ የሚካተቱ ጉዳዮች፣ የተስፋፋ አመጽን፣ ህዝባዊ አለመረጋጋትን፣ የሽብርተኝነት ድርጊቶችን፣ እንዲሁም ሀገር አቀፍ ኢንዱስትሪያዊ አድማዎችን ያጠቃልላሉ። በተጨማሪም፣ በመንግስት ባለቤትነት ስር ከሚገኝ የኃይል ማመንጫ ጣቢያ ኃይልን ለማውጣት የሚያስፈልግ፣ የማስተላለፊያ መስመር አለመኖር፣ እንዲሁም፣ ባለቤትነቱ ወይም ቁጥጥሩ በመንግስት ስር ከሆነ የኃይል ማመንጫ ጣቢያ ጋር የተገናኘ የማንኛውም መሰረተ ልማት አለመኖርም በዚህ ክፍል ውስጥ ይሸፈናል። አስተናጋጁ መንግስት፣ ከሀገር ውጭ ባለድርሻዎችና ብድር አቅራቢዎች የሚደረጉ ክፍያዎችን በሚከለክል

መልኩ፣ ካፒታልን ከሀገር የማውጣት ተግባር ላይ ገደብ ሲያወጣ ለምሳሌ፣ እንዲህ አይነቱ የህግ መለወጥ ጉዳዮችም በሀገር ውስጥ ፖለቲካዊ አስገዳጅ ሁኔታዎች ስር ሊወድቁ ይችላሉ።

**የውጭ ፖለቲካዊ አስገዳጅ ሁኔታ** ከሀገር ውጪ ቢመነጩም፣ ተዋዋዩ ወገን በኃይል ግዢ ስምምነቱ ውስጥ የሚገኙ ግዴታዎቹን መወጣት የሚቀጥልበት ችሎታው ላይ ተጨባጭ አሉታዊ ተጽእኖን የሚፈጥሩ፣ ፖለቲካዊ ባህሪይ ያላቸውን ድርጊቶች የሚሸፍን ክፍል ነው። ለምሳሌ፣ እንደ ተለዋጭ ተርባይን/ተሽከርካሪ ሞተር/ የመሳሰለ ወሳኝ ለኃይል ማመንጫ ጣቢያው የሚያስፈልግ መሳሪያ በሚሰራበት አንድ የውጭ ሀገር ውስጥ፣ ኢንዱስትሪያዊ አድማ ተነሳ ማለት፣ የኃይል ማመንጫ ጣቢያው ወደሚገኝበት ሀገር መላክ አይችልም ማለት ነው። የንግድ ማእቀብም ቢሆን ተመሳሳይ ውጤት ይኖረዋል።

**ተፈጥሯዊ አስገዳጅ ሁኔታ** ደግሞ፣ በተዋዋዩ ወገን የውል ግዴታዎችን የመወጣት ችሎታ ላይ ተጨባጭ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩ እንደ ጎርፍ፣ አውሎ ንፋስ፣ የመሬት መንቀጥቀጥ፣ ከፍተኛ ማእበል/ጹናሚና ሌሎች ጎጂ የአየር ሁኔታ ወይም ተፈጥሯዊ ሁኔታዎችን ይሸፍናል።

## የአስገዳጅ ሁኔታ ተጨማሪ ሽፋን

ብዙውን ጊዜ የአስገዳጅ ሁኔታ ፋታው፣ ከኃይል ግዢ ስምምነቱ አልፎ፣ የኃይል ግዢ ስምምነቱ ተዋዋይ ወገኖች የፈረሟቸውን፣ የነዳጅ አቅርቦትና የትራንስፖርት ስምምነቶችን ጨምሮ፣ የምህንድስና፣ የግዢና የግንባታ ስምምነትን እንዲሁም የኃይል ማስተላለፍ ስምምነትን ሁሉ እንዲሸፍን አድርጎ፣ የኃይል ግዢ ስምምነቱ ይደነግጋል። በዚሁ መሰረት፣ የአስገዳጅ ሁኔታ መከሰት፣ ነዳጅ አቅራቢውን ወይም የትራንስፖርት አቅራቢውን፣ ለኃይል ማመንጫ ጣቢያው ነዳጅ ከማቅረብ ሲከለክለው፣ የፕሮጀክት ኩባንያው፣ ጣቢያውን በዝቅተኛ ደረጃም ቢሆን ለስራ ክፍት የማድረግ የኃይል ግዢ ስምምነት የውል ግዴታውን ከመወጣት፣ ፋታ ሊጠይቅ ይችላል። የኃይል ግዢ ስምምነቱ ሌላው ተዋዋይ ወገን፣ በሌሎቹ ስምምነቶች ውስጥ የተደነገጉ ጉዳዮች ሲከሰቱ፣ የአስገዳጅ ሁኔታ ፋታን ለመጠየቅ ሊፈልግ የሚችልበት ሁኔታ ስለሚኖር፣ የአስገዳጅ ሁኔታን ጽንሰ ሀሳብ በተሰናሰለ/በተስማማ አኳኋን፣ ሁሉንም ስምምነቶች በሚነካ/በሚያገናኝ መልኩ፣ ለማስቀመጥ መዘጋጀት አስፈላጊ ነው።

## በአስገዳጅ ሁኔታ አማካይነት የውል ግዴታን ለመፈጸም ያለመገደድ ፋታ

ከላይ እንደተብራራው፣ አስገዳጅ ሁኔታ አጋጠመኝ የሚል ተዋዋይ ወገን፣ ብዙውን ጊዜ፣ አስገዳጅ ሁኔታው ለሚቆይበት የጊዜ መጠን፣ የውል ግዴታውን ለመወጣት ከመገደድ፣ ፋታ እንዲያገኝ ሊጠይቅ ይችላል። አስገዳጅ ሁኔታው የሚቆይበት ጊዜ ከመጠን በላይ ከተራዘመ፣ በአስገዳጅ ሁኔታው ያልተነካው ተዋዋይ ወገን፣ የውል መቋረጥን ከመጠየቁ በፊት፣ የውል ግዴታን ለመወጣት ያለመገደድ ፋታው፣ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚፈቀድ፣ የኃይል ግዢ ስምምነቱ ብዙውን ጊዜ ይወስናል።

አብዛኛውን ጊዜ በኃይል ግዢ ስምምነት ውስጥ፣ ገዢውን በሚነካ አስገዳጅ ሁኔታና፣ የፕሮጀክት ኩባንያውን በሚነካ አስገዳጅ ሁኔታ መሀከል ያለውን ልዩነት፣ ተራ በተራ ገልጾ ማስቀመጥ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። በአስገዳጅ ሁኔታ የተነካው ገዢው ሲሆን፣ አስገዳጅ ሁኔታው ለሚቆይበት ጊዜ፣ የመፈጸም ችሎታ እንዲቀጥልና የኃይል ክፍያዎች ለፕሮጀክት ኩባንያው እንዲከፈሉ፣ የኃይል ግዢ ስምምነቱ አብዛኛውን ጊዜ ይደነግጋል። ገዢውን የነካው አስገዳጅ ሁኔታ ውጤት፣ የንግድ ትግበራ ቀንን ማዘግየት ሲሆን፣ የፕሮጀክት ኩባንያው፣ **ተግባሩን እንደጨረሰ እንዲቆጠርለት** መጠየቅ ሊገባው/ሊፈቀድለት ይችላል። ይህን ጊዜ፣ የፕሮጀክት ኩባንያው፣ በመጀመርያው የንግድ ትግበራ ቀን ላይ የጀመረ የእዳ ክፍያን፣ እንዲሁም በተፈጠረው መዘግየት ምክንያት በተጨማሪነት የመጡ የፕሮጀክት ወጪዎችን የሚሸፍን፣ የመፈጸም ችሎታ ውሳኔን ተከትሎ የሚከፈል ክፍያ ሊጠይቅ/ሊገባው ይችላል።

አስገዳጅ ሁኔታው የፕሮጀክት ኩባንያውን የሚነካ ሲሆን፣ በመፈጸም ችሎታ ወይም በኃይል ክፍያዎች ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ፣ እንደየ አስገዳጅ ሁኔታው አይነት ሊለያይ ይችላል። ብዙውን ጊዜ እንዲህ አይነት ክፍያዎች፣ በሀገር ውስጥ ፖለቲካዊ አስገዳጅ ሁኔታ ወቅት የሚቀጥሉ ሲሆኑ፣ በውጭ ፖለቲካዊ አስገዳጅ ሁኔታ ወይም በተፈጥሯዊ አስገዳጅ ሁኔታ ወቅት ግን ለጊዜው ሊቋረጡ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ በአስገዳጅ ሁኔታ የተጠቃው የፕሮጀክት ኩባንያ፣ በውሉ ከተጠቀሰው በታች ይሁን እንጂ፣ ጥቂትም ቢሆን ኃይል ማመንጨት ሊሳካለት ይችላል፤ ቢሆንም ይህ ኃይል፣ እንዲገዛና ክፍያም እንዲፈጸም የሚያደርግ ድንጋጌ፣ በኃይል ግዢ ስምምነቱ ውስጥ ሊቀመጥ ይገባል።

## አስገዳጅ ሁኔታ የሚያስከትላቸው አይነተኛ መፍትሄዎች

አስገዳጅ ሁኔታ በሚከሰትበት ወቅት የሚሰጠው ዋናው የፋታ አይነት፣ ምንም እንኳን የተወሰኑ የውል ግዴታዎች መቋረጥ ሊሆን ቢችልም፣ ለአስገዳጅ ሁኔታ የሚሆኑና በኃይል ግዢ ስምምነት ውስጥ ሊደነገጉ የሚችሉ፣ ሌሎችም ልዩ የፋታ አይነቶች አሉ። የስራ መቋረጡን የፈጠረው ሁነት ያስከተለውን መዘግየት ለማጣጣት፣ በውሉ ውስጥ የሚገኙ የተወሰኑ የጊዜ ገደቦችን ማራዘም፣ አንዱ የተለመደ ምሳሌ ነው። በአስገዳጅ ሁኔታ ምክንያት የመጣው መዘግየት የተከሰተው፣ በግንባታ ወቅት ከሆነ፣ የፕሮጀክት ኩባንያው፣ የንግድ ትግበራ ቀኑን እንዲጠብቅ የሚያስችለው፣

የጊዜ ገደብ መራዘም ሊደረግለት ይገባል። በአስገዳጅ ሁኔታ ምክንያት የመጣው መዘግየት የተፈጠረው፣ ከንግድ ትግበራ ቀኑ በፊት ከሆነ፣ መዘግየቱን ለማጣጣት፣ የአጠቃላይ ውሉ የመፈጸሚያ ጊዜ መራዘም አለበት። ሌሎች የፕሮጀክት ስምምነቶችም፣ ይህንኑ አኳኋን የተከተሉ መሆን አለባቸው።

# ዋስትና

ከፕሮጀክቱ እቅድ፣ እስከ ግንባታና ትግበራ ደረጃዎች፣ የመድን ዋስትናን በመጠቀም በተሻለ ሁኔታ ሊቀንሱ የሚችሉ፣ ብዙ አይነት ስጋቶች አሉ።

## የግንባታ ደረጃ

በግንባታ ደረጃ ወቅት፣ በንብረት ላይ ለሚደርስ አደጋና በሰራተኞች ላይ ለሚደርስ ጉዳት፣ የመድን ዋስትና ለመግባት፣ የምህንድስና፣ የግዢና የግንባታ ውሉ ተቋራጭ፣ በዋነኝነት ኃላፊ ይሆናል። የዋስትና ሽፋን አይነቶች፣

- የሁሉም አይነት ስጋት(ንብረት ላይ የሚደርስ አደጋ) የመድን ዋስትና - ይህ አይነቱ የመድን ዋስትና፣ ብዙውን ጊዜ የሚሸፍነው፣ የፕሮጀክቱን የኃይል ማመንጫ ጣቢያ የመለወጫ ወጪን ነው።

- የአሰሪ ኃላፊነት መድን ዋስትና - እንዲህ አይነቱ የመድን ዋስትና፣ ብዙውን ጊዜ የሚሸፍነው፣ ከአሰራር ወይም ከስራ ቦታ ሁኔታዎች የሚመነጭ፣ ህመምን፣ ሞትን ወይም በሰራተኞች ላይ የሚደርስ ጉዳትን በተመለከተ፣ አሰሪው ያለበትን ኃላፊነት ነው። እንዲሁም

- የሁሉም አይነት የባህር ላይ/የመርከብ ጭነት የመድን ዋስትና - ይህ አይነቱ የመድን ዋስትና ብዙውን ጊዜ የሚሸፍነው፣ የኃይል ማመንጫ ጣቢያውን ወይም፣ ለጣቢያው አካል እንዲሆን ታስቦ በመርከብ የተጫነን መሳሪያ፣ የመለወጫ ወጪን ነው።

## የንግድ ትግበራ ደረጃ

በኃይል ማመንጫ ጣቢያው የንግድ ስራ ትግበራ መጀመሪያ ላይ፣ የሁሉም አይነት ስጋት (ንብረት ላይ የሚደርስ አደጋ) የመድን ዋስትናና የአሰሪ ኃላፊነት የመድን ዋስትና የመግባትንና የማስቀጠልን ኃላፊነት፣ የፕሮጀክት ኩባንያው መሸከም አለበት።

በተጨማሪም፣ አስተናጋጁ መንግስት፣ የሰጠውን መተማመኛ ወይም ማረጋገጫ በተመለከተ ቃሉን ያፈረሰ እንደሆን፣ የፕሮጀክት ኩባንያው፣ በሚከተሉት ላይ (ምናልባት ካጋጠሙ)፣ የፖለቲካ ስጋት ዋስትናን ጨምሮ መግባት ሊያስፈልገው ይችላል፡

- ገንዘብን በነጻነት መቀየር ስለመቻሉና በቂ የውጭ ምንዛሬ ተቀማጭ ስለመኖሩ መተማመኛ

- በህግ ወይም በግብር ላይ ለውጥ እንደማይኖር፣ ወይም የግብር ጥቅማጥቅሞች ፕሮጀክቱን በአሉታዊ አኳኋን በሚነካ መልኩ እንደማይሰረዙ መተማመኛ

- የፍቃድ ወረቀቶችና መሬትንና ንብረትን የመጠቀም ስምምነቶች መሰረዝ፣ እና/ወይም

- መወረስ

በሁሉም አይነት ሁኔታዎች ውስጥ፣ ለአንድ የኃይል ፕሮጀክት አይነት የሚያስፈልገው ትክክለኛ የመድን ዋስትና ሽፋን፣ በመድን ዋስትና ላይ ካተኮረ አማካሪ ጋር በመመካከር፣ እንደየሁኔታው እየታየ ይወሰናል። አበዳሪዎች ብዙውን ጊዜ፣ የኃይል ፕሮጀክቱ የመድን ዋስትና ፕሮግራም በቂ ስለመሆኑ የሚያማክራቸው፣ የመድን ዋስትና አማካሪ እንዲቀጠር ይጠይቃሉ።

# የዋና ነጥቦች ማጠቃለያ

## የስጋት አስተዳደር

- የስጋት ክፍፍል፡ ከኃይል ግዢ ስምምነቱ ባህሪይ የሚፈልቁ ስጋቶች፣ እነዚያን ስጋቶች ለመቀነስ በተሻለ አቋም ላይ ለሚገኙ ተዋዋይ ወገኖች መመደብ አለባቸው።

- የሻጭ ስጋት፡ ብዙውን ጊዜ ሻጭ፣ በኃይል ግዢ ስምምነት ውስጥ ከሚገኙ የግንባታና የትግበራ ግዴታዎች ጋር የተያያዙ ስጋቶችን ይሸከማል። ይህም፣ ግንባታን መጀመር ያለመቻልን፣ በውሉ የተጠቀሰውን የንግድ ትግበራ ቀን ያለመድረስን ወይም፣ የመፈጸም ችሎታ መስፈርትን የሚያሟላ የኃይል ማመንጫ ጣቢያ መገንባት ያለመቻልን ስጋት ሊያካትት ይችላል።

- የሻጭ ስጋት ልዩ ሁኔታ፡ መዘግየት የተፈጠረው፣ ገዢው አንድን ድርጊት በማድረጉ(ወይም ባለማድረጉ) እንደሆነ፣ ሻጩ ግዴታዎቹን መወጣት እንዳልቻለ ተደርጎ ሳይቆጠርበት ይታለፋል። ይህን ጊዜ ሻጩ፣ የተፈጠረውን መዘግየት መፍትሄ ለመስጠት ላወጣው ማንኛውም ተጨማሪ ወጪ፣ ተጨማሪ ጊዜ ወይም ካሳ ሊፈቀድለት ይችላል።

- የገዢ ስጋት፡ የሚጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ሲሆኑ በመፈጸም ችሎታ ክፍያ መልክ ወይም፣ የማይጠናቀቁ የታዳሽ ኃይል ፕሮጀክቶች ሲሆኑ ኃይል እንደመነጨ ተቆጥሮ በሚከፈል ክፍያ መልክ፣ የኃይል ፍላጎት በኃይል ገበያ ውስጥ ከተጠበቀው በታች የመሆኑ ስጋት፣ ብዙውን ጊዜ የሚመደበው ለገዢው ነው። ገዢው በአንድ የተወሰነ ጊዜ የሚደርስ ጉዳትን የሚመለከቱ ስምምነቶችን በመጠቀም፣ የነዳጅ አቅርቦት ስጋትንም ሊሸከም ይችላል።

# አጠቃላይ ስጋቶች

- አስገዳጅ ሁኔታ፡ ሻጩ ወይም ደንበኛው፣ ከቁጥጥራቸው ውጭ የሆኑ እንዲሁም በምክንያታዊ ህሊና ሊተነብዩአቸው የማይችሏቸው ሁነቶች ሲከሰቱ፣ በኃይል ግዢ ስምምነቱ ውስጥ ከሚገኙ ግዴታዎቻቸው ነጻ ሊወጡ ይችላሉ። የተወሰኑ አስገዳጅ ሁኔታዎች ከተከሰቱ፣ ሻጮች፣ ከግዴታቸው ነጻ ከመውጣት በተጨማሪ፣ የመፈጸም ችሎታ ክፍያዎችን ሊቀበሉ ይችላሉ።

- የማረጋጊያ ድንጋጌዎች፡ የመነሻውን/የመጀመሪያውን ስምምነት ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ከመሰረቱ ሊቀይሩ ስለሚችሉ፣ በህግ ወይም በግብር ላይ የሚደረጉ ለውጦች፣ ለሻጮች ስጋትን ሊፈጥሩ ይችላሉ። ብዙውን ጊዜ፣ ተጨባጭ ለውጥ ሲከሰት፣ የኃይል ግዢ ስምምነቱ፣ ሻጭ የኢኮኖሚ ሁኔታው ሳይጎደል ምሉእ ሆኖ እንዲቆም፣ የሚፈቅዱ ሁኔታዎችን ያካትታል።

- የቁጥጥር ለውጥ፡ ገዢዎች የኃይል ግዢ ስምምነቱን የመፈራረም ሀሳብ ያቀረቡት፣ በፕሮጀክት ኩባንያው ውስጥ አብዛኛውን የአክሲዮን መጠን በተቆጣጠረው ሰው፣ ጠንካራ የገንዘብ አቅም ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፣ የኃይል ግዢ ስምምነቶች፣ የሻጮችን ባለ ብዙ ድምጽ የአክሲዮን ባለቤቶችን የመቀየር ችሎታ፣ ለመገደብ ሊፈልጉ ይችላሉ። አበዳሪዎችም ተመሳሳይ ሀሳብ/አሳሳቢ ጉዳይ ሊኖራቸው ይችላል።

# ሌሎች የኃይል ግዢ ስምምነት ድንጋጌዎች

መግቢያ

ክርክሮችን ማስታረቅ

የኃይል ግዢ ስምምነት ማብቃት

አካባቢያዊ/የሀገር ውስጥ ሁኔታ

ሚስጥር መጠበቅ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

የዋና ነጥቦች ማጠቃለያ

# መግቢያ

ይህ ምእራፍ፣ ብዙውን ጊዜ በኃይል ግዢ ስምምነት ውስጥ የሚብራሩ፣ ነገር ግን ሁልጊዜ ግልጽ ሆነው፣ በሌሎቹ የዚህ ሰነድ ምእራፎች ውስጥ የማይገቡ አስፈላጊ ጉዳዮችን፣ በአጭሩ ይገልጻል። ለምሳሌ - ተዋዋይ ወገኖች፣ ማንኛውንም ክርክሮች እንዴት ነው የሚፈቱት? የኃይል ግዢ ስምምነቱ የሚፈጸምበት ጊዜ ሲያበቃ ምን ይፈጠራል? የአከባቢያዊ/የሀገር ውስጥ ሁኔታ መስፈርቶች፣ በኃይል ግዢ ስምምነቱ ላይ ምን አይነት ተጽእኖ ያሳድራሉ? የምስጢር መጠበቅ ጉዳዮች እንዴት ነው የሚያዙት? በመጨረሻም፣ በአንጻራዊነት ለድርድር የማይቀርቡ ወይም፣ ጠበቆች ብቻ ሊጨነቁባቸው የሚገባቸው፣ በውሉ ውስጥ መካተት ያለባቸው የውል ድንጋጌዎች የትኞቹ ናቸው? ይህ ምእራፍ እነዚህንና ሌሎችንም ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል።

# ክርክሮችን ማስታረቅ

## ክርክሮችን የማስታረቅ ግቦች

ግጭቶች ይፈጠራሉ። ይህ የመመሪያ ሰነድ ከተነበበና፣ ቀና አስተሳሰብ እያለ፣ አግባብነት ያላቸው አማካሪዎች ሁሉ በተገኙበት፣ በጣም ጥሩ የኃይል ግዢ ስምምነት ለድርድር ከቀረበ በኋላ እንኳን፣ ነገሮች ይበላሻሉ፤ ሁኔታዎችም ይቀየራሉ። ምንም ቢደረግ፣ የኃይል ግዢ ስምምነት የረጅም ጊዜ ውል ነው፤ ተዋዋይ ወገኖችም፣ አንዳንዴ እስከ 30 አመት ሊረዝም በሚችል ግዜ ውስጥ ምን እንደሚፈጠር፣ ሁልጊዜ በእርግጠኝነት ሊያውቁ አይችሉም!

ክርክር በእርግጥም ሲፈጠር፣ እነዚህን ክርክሮች፣ በተቻለው ፍጥነትና በውጤታማነት መፍታት፣ የሁሉም ተዋዋይ ወገኖች ፍላጎት ነው። የክርክር ማስታረቂያ ዘዴዎች አላማ፣ ምንም አይነት ክርክር ቢነሳ፣ በፍጥነት እንዲፈታና፣ ተዋዋይ ወገኖች፣ በኃይል ግዢ ስምምነት ውስጥ ያለውን፣ የየራሳቸውን ግዴታ ወደመወጣት በፍጥነት መዞር መቻላቸውን ማረጋገጥ ነው። ክርክር ለረጅም ጊዜ ሲራዘም ማንም አይጠቀምም።

ክርክሮች በተለያዩ ምክንያቶች መነሻነት ይፈጠራሉ። እነኚህ ክርክሮች፣ የቴክኒክ እና የገንዘብ ጉዳዮችን ጨምሮ፣ ከብዙ አይነት ጉዳዮች ጋር ሊገናኙ ይችላሉ፤ ለምሳሌ፣ በክፍያ ጥያቄ ወቅት የሚነሳ ክርክር፣ ኃይል በሚለካበት መንገድ ላይ የሚነሳ ክርክር፣ ወይም የኢንዱስትሪ ቃል ትርጓሜ ላይ የሚነሳ ክርክር። ክርክሮች፣ በተለይ የእያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን ግዴታ፣ ከሚፈጸምበት ጊዜና ሁኔታ ጋር በተገናኙ ጉዳዮች ዙሪያ፣ ከውል አተረጓጎም ጋርም ሊገናኙ ይችላሉ።

## ኢ - መደበኛ የክርክር ማስታረቂያ ዘዴዎች

አንድ ክርክርሲፈጠር፣ ተዋዋይ ወገኖች ሊያደርጉት የሚችሉት መልካሙ ነገር፣ እርስ በእርስ መነጋገር ነው። የኃይል ግዢ ስምምነት ከተጠናቀቀ በኋላ፣ በተዋዋይ ወገኖች መሀከል፣ ቀጣይነት ያለው ውይይት ማካሄድ፣ አብዛኞቹን ክርክሮች በፍጥነት ለመፍታት ይረዳል። የቴክኒክ ሰራተኞች፣ አንድን ጉዳይ መፍታት ካልተቻላቸው፣ በደንበኛውና በፕሮጀክት ኩባንያው፣ ከፍተኛ አመራሮች መሀከል፣ የሚደረግ ውይይትን መጨመር ሊረዳ ይችላል።

ብዙውን ጊዜ፣ ወደ መደበኛ የክርክር ማስታረቂያ ሂደት ከመገባቱ በፊት፣ የእርስ በእርስ ንግግር የማድረጉ አስፈላጊነት፣ በኃይል ግዢ ስምምነቱ ውስጥ ይቀመጣል። በተለምዶ፣ ወደ ማንኛውም መደበኛ የክርክር ማስታረቂያ መንገድ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት፣ ተዋዋይ ወገኖች በቅን ልቦና እንዲደራደሩ፣ የኃይል ግዢ ስምምነቱ ይጠይቃል። ተዋዋይ ወገኖች፣ ክርክሩን በስምምነት ለመፍታት እንደሞከሩ ሳይታይ፣ ሌሎች መደበኛ የክርክር ማስታረቂያ መንገዶች ላይገኙ ይችላሉ።

# መደበኛ የክርክር ማስታረቂያ ዘዴዎች

ኢ- መደበኛ ዘዴዎች ክርክሩን ማስታረቅ ካቃታቸው፣ የኃይል ግዢ ስምምነቱ፣ የተለያዩ መደበኛ የክርክር ማስታረቂያ ዘዴዎችን ይደነግጋል።

## ፈጣን የክርክር ማስታረቂያ መንገድ

ሌሎች አማራጭ ፈጣን የክርክር መፍቻ መንገዶች ግምት ውስጥ መግባት ይችላሉ። እነዚህም ብዙውን ጊዜ፣ ከቴክኒክ ወይም ከክፍያ ጥያቄ ጉዳዮች ጋር ከተገናኙ፣ ለአንዳንድ “ተመሳሳይ”ክርክሮች፣ የተሰጡ አፋጣኝ ውሳኔዎችን፣ የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ያካትታሉ።

በዚህ ስር የሚሸፈኑ የክርክር አይነቶች፣ አስቀድመው ሊወሰኑ ይችላሉ። ተዋዋይ ወገኖችም፣ የፈጣን መንገድ ውሳኔዎቹ፣ የአስገዳጅነት ባህሪይ ይኑራቸው ወይም አይኑራቸው በሚለው መካከል መምረጥ ይችላሉ።

## የገለልተኛ መሃንዲስ ሚና

እንደ የንግድ ትግበራ ቀን መጠበቅ፣ ልኬት፣ ምዘና ወይም የመፈጸም ችሎታ ላሉት የቴክኒክ ጉዳዮች፣ ክርክሩ ለገለልተኛ መሃንዲስ መቅረብ ይችላል። ገለልተኛው መሃንዲስ፣ ክርክሩን ለመፍታት የሚረዳ አስተያየት መስጠት ይችላል። የገለልተኛው መሃንዲስ ውሳኔ፣ በተዋዋይ ወገኖች ላይ አስገዳጅ የሚሆንባቸው፣ አይነተኛ የተለዩ ጉዳዮችም ሊኖሩ ይችላሉ።

ለገለልተኛ መሃንዲስ ሊቀርቡ የሚችሉ ጉዳዮች ዝርዝርም፣ በድርድሩ ወቅት ስምምነት ሊደረግበት ይችላል። ይህም በኃይል ግዢ ስምምነቱ ውስጥ ሊካተት ይችላል። አብዛኛውን ጊዜም፣ የገለልተኛው መሃንዲስ ስልጣን፣ በኃይል ግዢ ስምምነቱ ተዋዋይ ወገኖችና፣ በገለልተኛው መሃንዲስ መሀከል በሚፈረም የተለየ ስምምነት ውስጥ ይመዘገባል። የኃይል ግዢ ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች፣ ገለልተኛውን መሃንዲስ፣ የኃይል ግዢ ስምምነቱን ከሚፈርሙበት ወቅት አስቀድመው ለመቅጠር ይፈልጉ እንደሆነ፣ አብረው ሊወስኑ፣ ወይም በኋላ ላይ እንደሚወስኑ ሊስማሙ ይችላሉ።

## ሽምግልና

በተዋዋይ ወገኖች ላይ አስገዳጅነት የሌለው፣ የሽምግልና ሂደትን የሚመለከት ድንጋጌም ሊቀመጥ ይችላል። ይህም ሂደት ገዢውና በፕሮጀክት ኩባንያው መሀከል ውይይትን የሚያመቻች ገለልተኛ ወገንን ይጠቀማል። የሂደቱ ውጤትም፣ ክርክሩን በፍጥነት ለመፍታት የሚረዳ የመፍትሄ ሃሳብን ማቅረብ ሊሆን ይችላል።

## ግልግል/እርቅ

ግልግል፣ በኢ-መደበኛ ወይም በፈጣን የክርክር ማስታረቂያ መንገዶች፣ ሊፈቱ የማይችሉ፣ ክርክሮችን ለመፍታት፣ በኃይል ግዢ ስምምነት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውል ሂደት ነው። የኃይል ግዢ ስምምነቱ፣ ተዋዋይ ወገኖች ግልግልን እንዲጠቀሙ የሚጠይቅ ድንጋጌን ካላካተተ በስተቀር፣ ክርክሩ፣ በተዋዋይ ወገኖችና በጭብጦቹ ላይ ስልጣን ላላቸው ፍርድ ቤቶች ይቀርባል። የአለም ባንኩን፣ ዓለም አቀፍ የኢንዱስትሪ ክርክሮች ማስታረቂያ ማዕከልን፣ የዓለም አቀፍ ንግድ ማኅበርን፣ የተባበሩት መንግስታት ዓለም አቀፍ የንግድ ህግ ኮሚሽንን፣ ወይም፣ የለንደን ዓለም አቀፍ የግልግል ፍርድ ቤትን ጨምሮ፣ ግልግልን በተመለከተ በርካታ እስካሁን ስራ ላይ የቆዩ የአካሄድ ህግጋት አማራጮች አሉ።

እነዚህ የአካሄድ ህግጋት እያንዳንዳቸው፣ የገላጋይ ዳኞችን የብቃት መስፈርት፣ የገላጋይ ዳኞችን ቁጥር፣ ገላጋይ ዳኞች የሚሾሙበትን መንገድ፣ የቃለጉባኤዎችን/የውይቶችን ሚስጥራዊነት፣ የገላጋይ ዳኞችን ስልጣን፣ የገላጋይ ዳኞችን ክፍያና ወጪ፣ እንዲሁም የውሳኔያቸውን የተፈጻሚነት ኃይል የተመለከቱ ድንጋጌዎችን ያካትታሉ። ከግልግል መድረክ ጠቀሚታዎች አንዱ፣ የተከራከሩት ወገኖች፣ ክርክሩን ለፈጠረው ጉዳይ በሚስማማ መልኩ፣ መድረኩን በፈቀዱበት ሁኔታ በነጻነት ማካሄድን ማስቻሉ ነው።

## የግልግል/እርቅ መድረኩ መቀመጫ

የኃይል ግዢ ስምምነቱ፣ የማንኛውም የክርክር ማስታረቂያ መድረክ መቀመጫ ገልጾ ማስቀመጥ አለበት። መቀመጫ የሚባለው የግልግል መድረኩ የሚካሄድበትን ቦታ ይመስላል፤ ነገር ግን መቀመጫው ሲባል፣ የግልግል መድረኩ የሚካሄድበት፣ ስፍራ/ህንጻ/አዳራሽ ለማለት ታስቦ አይደለም። የግልግል ደንቦች የማይሸፍኗቸውን ክፍተቶች፣ በሚጠቅም ወይም በሚጎዳ መልኩ ስለሚሞላ፣ ከገላጋዮች ነጻነት ጋር ተያይዞ የፍርድ ቤቶችን ሚና ስለሚነካ፣ እንዲሁም አንዳንድ የግልግል ህግጋትን ከነጭራሹ ሊሰርዛቸው ስለሚችል፣ መቀመጫው ያለበት ቦታ/ሀገር ህግ፣ አስፈላጊ ነገር ነው። አልፎ ተርፎም መቀመጫው ያለበት ሀገር ህግ፣ የግልግል/እርቅ ውሳኔው ተፈጻሚነት ላይ ሳይቀር ተጽእኖ አለው። ብልህ የሆኑ ተዋዋይ ወገኖች፣ የመረጡትን መቀመጫ የሚመለከት፣ ሁለንተናዊ ቅድመ ጥንቃቄ ያካሂዳሉ። አስተናጋጅ ሀገሮች አብዛኛውን ጊዜ የራሳቸው ሀገር በግልግል መድረክ መቀመጫነት እንዲመረጥ ይፈልጋሉ፤ ዓለም አቀፍ ባለሀብቶች ደግሞ ብዙውን ጊዜ፣ የግልግል መድረክ መቀመጫ፣ ከገዛ ሀገራቸው ጋር ቢገናኝ ወይም፣ ለሌሎች ዓለም አቀፍ የገንዘብ ማዕከል የሆኑ ሁሉም የሚጠቀምባቸው ሀገራት ቢሆኑላቸው ይመርጣሉ።

## የህግ ምርጫ

የኃይል ግዢ ስምምነቱ አተረጓጎም፣ አተረጓጎሙን በሚገዛው ሀገር ህግ ላይ ተመስርቶ፣ እጅግ በጣም ሊለያይ ይችላል።

በጣም የተሻለ የሚሆነው፣ ሁሉንም የፕሮጀክት ሰነዶች የሚገዛ አንድ ህግ ቢመረጥ ነው። ነገር

ግን ይህ በሃሳብ ደረጃ ተመራጭ የሆነው ነገር ነው፤ በኃይል ፕሮጀክቶች ውስጥ በርካታ ፕሮጀክት ሰነዶች ከመኖራቸው የተነሳ፣ አብዛኛውን ጊዜ በተግባር የሚፈጸም ነገር አይደለም። ገዢውን ህግ ለመምረጥ ሲታሰብ፣ በተለያዩ ስምምነቶች ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ህግ እንደዛው የተለያየ ስለሚሆን፣ በተለያዩ የፕሮጀክት ስምምነቶች ውስጥ ሊነሱ የሚችሉ ግጭቶችን በሙሉ፣ ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው። ክርክሮችን የማጣመርና የማጠናቀር ጉዳይም፣ በጥንቃቄ ሊታይና ሊታሰብበት ይገባል።

## የግልግል ውሳኔ ተፈጻሚነት

ተዋዋይ ወገኖች ብዙውን ጊዜ ከፍርድ ቤት ሙግት ይልቅ ግልግልን የሚመርጡት፣ በግልግል ውሳኔ ተፈጻሚነት የተነሳ ነው። የግልግል ውሳኔ፣ የኒዮርክን ስምምነት(የውጪ ሀገር የግልግል ውሳኔዎች እውቅና እና ተፈጻሚነት ስምምነት) በፈረመ የትኛውም ሀገር ውስጥ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

# ከህግ ባሻገር-የፈሰሰሀብት ስምምነቶች (investment treaties) ሚና

ብዙ አስተናጋጅ ሀገሮች፣ የተለያዩ የፈሰሰሀብት ስምምነቶችን የፈረሙ መሆናቸውን ማስተዋል ያስፈልጋል። የፈሰሰሀብት ስምምነቶች፣ እያንዳንዱ ተስማሚ ሀገር፣ ከሌላው ተስማሚ ሀገር የሚመጡ ባለሀብቶችን፣ በተወሰነ አይነት መንገድ ለመያዝ ቃል የሚገባባቸው፣ በሀገሮች መካከል የሚፈረሙ ስምምነቶች ናቸው። ሀገሮች የውጪ ድርጅቶችን በ“ፍትሀዊና በትክክለኛ” መንገድ ለመያዝ ግዴታ ይገባሉ፤ እንዲሁም ለፈሰሰው መዋዕለ ንዋይ ደህንነትና ጥበቃ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

የሀገር ውስጥ ህግጋትን ማክበር፣ የፈሰሰሀብት ስምምነቶችን ለመጣስ፣ መከላከያ እንደማይሆን ማስተዋል ያስፈልጋል። የመንግስት ድርጊት፣ ከራሱ ህግ አንጻር ትክክል ቢሆንም፣ ከፈሰሰሀብት ስምምነቱ ጋር ግን የሚጣረስ ሊሆን ይችላል። አስተናጋጅ ሀገሮችም ሆኑ ባለሀብቶች፣ ግጭት ከተፈጠረ፣ ለመፍታት ተፈጻሚ የሚሆኑት ስምምነቶች የትኞቹ እንደሆኑ መረዳታቸው አስፈላጊ ነው።

# የኃይል ግዢ ስምምነት ማብቃት

የተጨመሩ የጊዜ ማራዘሚያዎችም አልቀው፣ የኃይል ግዢ ስምምነቱ የሚፈጸምበት ጊዜ ሲያበቃ፣ የኃይል ማመንጫ ጣቢያው፣ ወይ ወደ መንግስት ይተላለፋል/ይዛወራል፣ ወይ ለሶስተኛ ወገን ይሸጣል፣ ወይ መጀመሪያውኑ በገነባው አካል ባለቤትነት ስር ይቀጥላል፣ ወይም ስራውን እንዲያቆም ይደረጋል/ይዘጋል።

## ማስተላለፍ/መተላለፍ ወይም በባለቤትነት መቀጠል

የኃይል ግዢ ስምምነቱ ተግባራዊ የሚደረግበት ጊዜ ሲያበቃ፣ የስምምነቱን መዋቅር በመንተራስ፣ የኃይል ማመንጫ ጣቢያው፣ ወደ አስተናጋጁ መንግስት ሊተላለፍ ይችላል። በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ፣ ተዋዋይ ወገኑ የኃይል ማመንጫ ጣቢያውን፣ ለሶስተኛ ወገን የመሸጥ ችሎታም ሊኖረው ይችላል። ከኃይል ግዢ ስምምነቱ የተፈጻሚነት ዘመን ማብቃት ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎችም፣ በዚህ ጊዜ የሚፈጠሩትን ሁኔታዎች ያስቀምጣሉ። በየትኛውም ሁኔታ ቢሆን፣ በኃይል ግዢ ስምምነቱ ላይ ድርድር ሲደረግ፣ በስምምነቱ ማብቂያ ጊዜ ላይ፣ የኃይል ማመንጫ ጣቢያው ቀሪ ዋጋ/ዕሴት ይዞ የመቀጠሉ ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል መታወቅ አለበት።

በስምምነቱ ተፈጻሚነት ማብቂያ ላይ፣ የኃይል ማመንጫ ጣቢያውን የገነባው አካል፣ የጣቢያውን ባለቤትነት ሲይዝና፣ ጣቢያውን ለገዢው ወይም ለአስተናጋጁ መንግስት ሳያስተላልፍ ሲቀር፣ ሌላ አዲስ የኃይል ግዢ ስምምነትን ሊፈራረም ወይም ጣቢያውን እዚያው ስራውን እያሰራ፣ የሚመነጨውን ኃይል እዚያው እየሸጠ መቀጠልን ሊመርጥ ይችላል።

## የኃይል ማመንጫ ጣቢያው ስራውን ማቆም/መዘጋት

የኃይል ማመንጫ ጣቢያው፣ ኃይል ለማመንጨት ምንም ጥቅም የማይሰጥ ሆኖ የሚገኝባቸው አጋጣሚዎች ሲፈጠሩ፣ የፕሮጀክት ኩባንያው፣ የህግን እና የአካባቢ ጥበቃን መስፈርቶች በሚያሟላ ሁኔታ፣ ጣቢያውን ስራ የማስቆም/የመዝጋት፣ የውል ግዴታ ሊኖርበት ይችላል። ይህ ሁኔታም እንደየቴክኖሎጂውና እንደ ህግና ደንቡ መዋቅር ይለያያል።

የኃይል ማመንጫ ጣቢያውን ስራ የማስቆም/የመዝጋት ግዴታዎች፣ የማመንጫ ጣቢያውን መሳሪያዎች ፈትቶ ማወላለቅንና ከፕሮጀክት ቦታው ላይ ማንሳትን፣ እንዲሁም መንግስት በሚፈልገው መልኩ፣ የፕሮጀክት ቦታውን ማጽዳትንና ማደስን ያጠቃልላል። የማጽዳት ስራውም፣ የፕሮጀክት ቦታው ከዚህ በኋላ፣ ለሌላ ስራ ይፈለግ እንደሆነ፣ ቦታውን ሞልቶ መደልደልን ያካትታል። የአካባቢ ጥበቃን የሚመለከቱ ግዴታዎችም፣ የኃይል ግዢ ስምምነቱ ካበቃ በኋላ፣ ለበርካታ አመታት ሊቀጥሉ ይችላሉ።

# አከባቢያዊ/የሀገር ውስጥ ሁኔታ

በርካታ ሀገሮች፣ የሀገር ውስጥ ሁኔታ መስፈርትን የሚጠይቁ ህግጋትንና ፖሊሲዎችን ቀርጸዋል። እነዚህ ህግጋትና ፖሊሲዎች፣ እራሳቸውን የቻሉ ሰነዶች ወይም፣ አንድን ዘርፍ ብቻ የሚመለከቱ ሰነዶች ሆነው ሊገኙ ወይም በሀገራዊ የግዢ ህግጋት ውስጥ ተካተው ሊገኙ ይችላሉ። አንዳንድ ጊዜ፣ እንደ ህግና ደንብ ሆነው ወይም በሀገሪቱ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይልን በሚያስተዳድረው አካል የፈቃድ መስፈርት ሆነው ሊገኙ ይችላሉ። የነዚህ ህግጋትና አጠቃላይ ፖሊሲዎች ግብ/አላማ፣ በውጭ ባለሀብቶችና በሀገር ውስጥ ገበያው መካከል፣ የኢኮኖሚ ግንኙነቶችን ማጎልበት ነው።

የሀገር ውስጥ ሁኔታ በርካታ ገጽታዎች ሊኖረው ይችላል። ከሀገር ውስጥ ሁኔታ መስፈርቶች መካከል እንደ፣ ባለቤትነት፣ ሀገር ውስጥ ማምረት፣ የሀገር ውስጥ ሰራተኞች፣ አገልግሎቶች፣ ጥሬ እቃዎችና መሳሪያ፣ የቴክኖሎጂ መተላለፍ፣ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ዜጎች ስልጠና፣ ያሉት ጥቂቶቹ ምሳሌዎች ናቸው።

የሀገር ውስጥ ሁኔታ ድንጋጌዎች፣ በአጠቃላይ በኃይል ግዢ ስምምነት ውስጥ መካተት የሚያስፈልጋቸው ባለመሆናቸው፣ ብዙውን ጊዜ አይካተቱም (በተለይ በጉዳዩ ላይ ህግ ወይም ፖሊሲ ባላቸው ሀገሮች)። የሀገር ውስጥ ሁኔታ ድንጋጌዎች፣በይበልጥ ሊገኙ የሚችሉት፣ በፕሮፖዛል ጥሪው ላይ፣ በስምምነቱ ወይም በፕሮጀክት ኩባንያውና በአስተናጋጁ መንግስት መካከል በሚፈረመው የትግበራ ውል ላይ ነው። የሀገር ውስጥ ሁኔታ ድንጋጌዎችም፣ የማትጊያና የፍላጎት/የውጥን መግለጫዎች ቢሆኑ ነው እንጂ፣ ሁልጊዜ የግድ መፈጸም ያለባቸው ጉዳዮች አይደሉም።

የሀገር ውስጥ ሁኔታ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት በሚኖራቸው ጊዜ፣ በፕሮጀክታቸው ላይ ምን አይነት ተጽእኖ እንደሚፈጥሩ፣ ተዋዋይ ወገኖች መረዳት ያስፈልጋቸዋል። ይህም የሚሆንበት ምክንያት የሀገር ውስጥ ሁኔታ ድንጋጌዎች፣ በታሪፍና በገንዘብ አቅርቦት አማራጮች ላይ ተጽእኖ ሊኖራቸው ስለሚችልና፣ አስተናጋጁ መንግስት ከፈረማቸው፣ ዓለም አቀፍ የፈሰሰሀብት ስምምነቶች ጋር የሚጋጩ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው።

# ሚስጥር መጠበቅ

ብዙዎቹ የኃይል ግዢ ስምምነቶች፣ ጥንቃቄ የሚሹ የንግድና የቴክኒክ መረጃዎችን በተመለከተ፣ ሁለቱንም ተዋዋይ ወገኖች ሚስጥር እንደጠብቁ የሚጠይቁ ድንጋጌዎችን ያካትታሉ። ህግ፣ ፍርድ ቤቶች ወይም ደንብ አስከባሪ አካላት በሚጠይቁበት ጊዜ ብቻ፣ በልዩ ሁኔታ፣ መገለጽ የሚኖርባቸው ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ።

የምስጢር መጠበቅ ድንጋጌዎች፣ በአጠቃላይ የኃይል ገበያው ውስጥ በሚገኙ፣ ከፖሊሲ ጋር በተያያዙ አሳሳቢ ጉዳዮች ምክንያት ሊወሳሰቡ ይችላሉ። መንግስት እና ገዢው፣ መጀመሪያ ላይ ፕሮጀክቱ ላይ መዋዕለ ንዋይ የሚያፈሱ አካላትን ለመሳብ የተደረጉ፣ ማንኛውንም የገንዘብ ማትጊያና ሌሎች ድርጊቶችን/እርምጃዎችን፣ በሚስጥር ሊይዙ ይፈልጉ ይሆናል። መንግስንም፣ በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ላይ፣ ተትረፍርፈው የተሰጡ የውል ሁኔታዎች፣ ወደፊት በሚጀምራቸው ፕሮጀክቶች ላይ ዝቅተኛ የታሪፍ መጠንን ለመደራደር ያለውን ችሎታ ሊቀንሱ የመቻላቸው ጉዳይ፣ ሊያሳስበው ይችላል። ምስጢርን የመጠበቅ ፍላጎትም፣ ከግልጽነትና ከተጠያቂነት ጉዳዮች አንጻር የተመዛዘነ መሆን ይገባዋል። የኃይል ማመንጫት ፕሮጀክቱን ወጪ፣ ዞሮ ዞሮ የሚሸከመው ተጠቃሚው ህዝብ እንደመሆኑ መጠን፣ በተለይ፣ ከህዝቡ ጋር የመነጋገርና/አብሮ የመስራትና መተማመንን የመገንባት ጉዳይ እጅግ አስፈላጊ ነው።

# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

በኃይል ግዢ ስምምነት ውስጥ የሚገኙት፣ ከላይ ከተጠቀሱት ግዴታዎች በተጨማሪ፣ እምብዛም የማይወደዱትን የጠቅላላ ድንጋጌዎች መኖር፣ በትንሹም ቢሆን ማስታወስ ይገባል። እነኚህ ባይተዋር ድንጋጌዎች፣ የብዙዎቹን የኃይል ግዢ ስምምነቶች፣ ራቅ ያለውን ጥግ ይዘው ይገኛሉ፤ አርእስቶቻቸው በወፍ በረር ሲቃኙ እንኳን፣ እጅግ በጣም አብጠርጥሮ አንባቢ የተባለ ሰውን አይኖች ራሱ የማፍዘዝ አስደናቂ ችሎታ አላቸው። እነዚህ ድንጋጌዎች፣ የተሻለ በሚወደዱትና የዋና ዋናው ቁምነገር ብልት በተቀመጠባቸው የኃይል ግዢ ስምምነቱ ድንጋጌዎች ውስጥ፣ ገዥና ሻጭ የተስማሙበትን ነገር ተፈጻሚነት ማረጋገጥን ጨምሮ፣ ለሌሎችም የተለያዩ ምክንያቶች ሲባል በስምምነቱ ውስጥ ይኖራሉ ማለት በቂ ነው። ጠቅላላ ድንጋጌዎች፣ የኃይል ግዢ ስምምነቱ አስፈላጊ አካላት ከመሆናቸውም በላይ፣ ብዙውን ጊዜ አጨቃጫቂ ድንጋጌዎች አይደሉም።

ይህ ክፍል፣ ከአንድ የኃይል ግዢ ስምምነት በስተጀርባ ላይ ልታዩአቸው የምትችሏቸውን ጠቅላላ ድንጋጌዎች፣ በመጠኑ ያሳያል።

# ተጠያቂነትንና የካሳ ኃላፊነትን መገደብ

የኃይል ግዢ ስምምነቱ ሁልጊዜ፣ አንዱ ወገን ለሌላው ወገን የሚኖርበትን ተጠያቂነት፣ የሚገድቡ ድንጋጌዎችን ይይዛል። እነዚህም ድንጋጌዎች፣ ሩቅ ወይም አሁን ላይ ሊተነበዩ የማይችሉ ኪሳራዎችን(ከባድ ኪሳራ ወይም ትርፍን ማጣት) በተመለከተ፣ አንዱ ተዋዋይ ወገን ለሌላው ተጠያቂ የሚሆንበትን ሁኔታ ያስቀራሉ። እንደ አጠቃላይ መርህ፣ በኃይል ግዢ ስምምነት ውስጥ፣ በገዢውም ሆነ በሻጭ ይከፈላል ተብሎ፣ የተቀመጠ የካሳ ወይም የኪሳራ ክፍያ፣ በውሉ ውስጥ ስምምነት የተደረገበትና በግልጽ ተለይቶ የተጠቀሰ (የተወሰነ ኪሳራ)መሆን አለበት።

በተጨማሪም፣ ካሳ መካስን እና ዋና/ብቸኛ መፍትሄን በማገናኘት የሚመለከት ድንጋጌም አለ። የመጀመሪያው ክፍል፣ አንዱ ወገን በቸልተኝነት፣ በግትርነት ወይም ያለኃላፊነት ስሜት የፈጸመው ወይም ያልፈጸመው ድርጊት ሲኖርና፣ በዚሁም ምክንያት ሌላው ወገን የደረሰበት ኪሳራ ወይም የከፈለው ክፍያ ሲኖር፣ አንዱ ወገን ሌላውን ወገን ካሳ እንደሚከፍል ሊደነግግ ይችላል። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ፣ ተዋዋይ ወገኖች ማግኘት የሚችሏቸው ዋናዎቹ መፍትሄዎች፣ በኃይል ግዢ ስምምነቱ ውስጥ መካተታቸውን ሊያስቀምጥ ይችላል።

አንዳንድ ጊዜም፣ አመታዊ ዝቅተኛ ገደብ በስምምነት ይወሰንና፣ ከዚያ ገደብ በላይ የሆነ ኪሳራ ሲያጋጥም፣ ካሳ የሚከፈልበት ይሆናል። የዚህ አሰራር አጠቃላይ አላማም፣ ለትናንሽ መጠን ክፍያዎች ሲባል፣ በየጊዜው የካሳ ክፍያ መጠየቅ የሚፈጥረውን ተደራራቢ የስራ ጫና መቀነስ ነው።

በሶስተኛ ወገን ላይ ለደረሰ ሞት ወይም ጉዳት የሚከፈለው የካሳ መጠን ብዙውን ጊዜ ሳይወሰን የሚተው ነው።

# ገዢው ህግ

የኃይል ግዢ ስምምነቱ፣ በስምምነቱ ላይ ተፈጻሚነት ያለውን ገዢ ህግ ገልጾ ያስቀምጣል። በቀጥታ ተፈጻሚነት ያላቸው ወይም በሌላ በኩል፣ ተዋዋይ ወገንን ውሉ ላይ መሻሻል እንዲደረግ(የገንዘብ እጥረትን የሚመለከቱ አንቀጾች በተመለከተ)፣ ለፍርድ ቤት እንዲያመለክት የሚፈቅዱለት፣ ጠቅላላ የህግ ድንጋጌዎች፣ ህግ በሚፈቅደው መጠን፣ ከስምምነቱ ውጭ መሆን አለባቸው/በስምምነቱ መካተት የለባቸውም። ይህም የሚደረገው፣ ተዋዋይ ወገኖች በጋራ ተደራድረው ባዘጋጁት ውል፣

# የኃይል ግዢ ስምምነቱን ማሻሻል/ስምምነቱ መሻሻል

እንደማንኛውም ውል፣ የኃይል ግዢ ስምምነቱ፣ ብዙውን ጊዜ፣ ስምምነቱ ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎችን የሚመለከት ድንጋጌ ይኖረዋል። አንዳንድ ጊዜ፣ የኃይልግዢ ስምምነቱን መተግበር ተከትሎ፣ የፕሮጀክት ኩባንያው ገንዘብ ለማሰባሰብ የሚያደርገው ጥረት ሲጨምር፣ ለኃይል ማመንጫው ግንባታ የተለያዩ ብድር ሊያቀርቡ የሚችሉ፣ የኃይል ግዢ ስምምነቱንና ሌሎችንም የፕሮጀክት ሰነዶች እየመረመሩ ያሉ አካላት የተለያዩ ስጋቶች፣ የፕሮጀክቱን እዳዎች ለመክፈል የሚያስፈልገውን የፕሮጀክቱን የገቢ ምንጭ፣ እንዴት አደጋ ውስጥ ሊጥሉት እንደሚችሉ፣ ያላቸውን አስተያየት/አረዳድ ተመስርቶ፣ አንዳንድ የስምምነቱ ድንጋጌዎች እንዲሻሻሉ ሊጠይቁ ይችላሉ።

ብዙውን ጊዜ፣ ስምምነቱ ላይ የሚደረጉ ማሻሻያዎችን፣ ሁለቱም የኃይል ግዢ ስምምነቱ ተዋዋይ ወገኖች በጽሁፍ አድርገው ሊስማሙባቸው ያስፈልጋል። ስምምነቱ እንደሚተገበርበት ሀገር/ቦታ፣ ማሻሻያው ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት፣ በደንብ አስከባሪው/በተቆጣጣሪው አካል ወይም በፓርላማ፣ መጽደቅ ሊያስፈልገው ይችላል።

# የዋና ነጥቦች ማጠቃለያ

- **ክርክርን ማስታረቅ፡** የውሎችን መቋረጥ ለመከላከል የተፈጠሩ በርካታ ዘዴዎች አሉ። እነዚህም በተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን ለማስታረቅ የሚደረጉ የሽምግልና ወይም የግልግል/እርቅ ተግባራትን ያካትታሉ። አንዳንዴ ግን፣ ተዋዋይ ወገኖች ጉዳያቸውን ወደ ፍርድ ቤት መውሰድ ሊያስፈልጋቸው ይችላል።

- **የኃይል ግዢ ስምምነቱ ማብቃት፡** የኃይል ግዢ ስምምነቱ የሚተገበርበት ጊዜ ሲያበቃ፣ ተዋዋይ ወገኖች፣ የኃይል ማመንጫ ጣቢያውን ለሌላ ለማስተላለፍ፣ ለመሸጥ፣ ወይም ተግባሩን መወጣቱን እንዲያበቃ ለማድረግ፣ ሊስማሙ ይችላሉ። እንደ አማራጭም፣ የፕሮጀክት ኩባንያው፣ የኃይል ማመንጫ ጣቢያውን ይዞ ስራውን ሊያስቀጥለውም ይችላል።

- **አከባቢያዊ/የሀገር ውስጥ ሁኔታ፡** መንግስታት፣ በውጭ ባለሀብቶችና በሀገር ውስጥ ገበያው መሀከል፣ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶችን የሚጨምሩ ህግጋትንና ፖሊሲዎችን ወደ መቅረጽ ሊያዘነብሉ ይችላሉ። ይሁን እንጂ፣ ይህ ሁኔታ ከዓለም አቀፍ የፈሰሰሀብት ስምምነቶች ጋር በሚኖረው ግጭት የተነሳ፣ የገንዘብ አቅርቦት አማራጮችን፣ ሊገድባቸው ይችላል።

- **ምስጢር መጠበቅ፡** ለተወሰኑ አካላት ብቻ መገለጥ የሚገባውን መረጃ ምስጢራዊነት ለመጠበቅ ሲባል፣ በኃይል ግዢ ስምምነቱ ውስጥ፣ ልዩ ግዴታዎች ሊደነገጉ ይችላሉ።

- **ጠቅላላ ድንጋጌዎች፡** በመደበኛ ሁኔታ የኃይል ግዢ ስምምነቱ፣ በስተመጨረሻው ላይ፣ ተጠያቂነትን የሚወስኑ፣ ካሳን የሚመለከቱ፣ ገዢ ህግን የሚመለከቱና ሌሎችንም በርካታ ድንጋጌዎች ያካትታል።

# ውልን አለማክበር/እንደውሉ

# አለመፈጸምና የውል መቋረጥ

## መግቢያ

## የገዢው ውልን አለማክበር/እንደውሉ አለመፈጸም

## የሻጭ ውልን አለማክበር/እንደውሉ አለመፈጸም

## ውል ከተቋረጠ/ከቀረ በኋላ የሚኖሩ ግዴታዎች

## ውል እንዳለማክበር የማይቆጠሩ ሁኔታዎች

## የአበዳሪ መብቶች

## የዋና ነጥቦች ማጠቃለያ

# ምህጻረ ቃላት

| | |
|---|---|
| **ኤኤፍዲቢ** | የአፍሪካ ልማት ባንክ |
| **ቢኦኦ** | ቢልድ አውን ኦፐሬት |
| **ቢኦኦቲ** | ቢልድ አውን ኦፐሬት ትራንስፈር |
| **ቢኦት** | ቢልድ ኦፐሬት ትራንስፈር |
| **ሲኦዴ** | ኮመርሺያል ኦፐሬሽንስ ዴት |
| **ሲፒ** | ኮንዲሺንስ ፕሬሲደንት |
| **ሲኤስኤ** | ክሬዲት ሰፖርት አገሪመንት |
| **ሲኤስፒ** | ኮንሴንትሬትድ ሶላር ፓወር |
| **ዲቢአ** | ዲዛይን ቢልድ አግሪመንት |
| **ዲኤፍአይ** | ዲቨሎፕመንት ፋይናንስ ኢንስቲቱሽንስ |
| **ዲኤስሲአር** | ዴት ሰርቪስ ካቨሬጅ ሬሺዮ |
| **ዲኤስአርኤ** | ዴት ሰርቪስዴት ሰርቪስ ሪዘርቭ አካውንት |
| **ኢቢአርዲ** | ኢውሮፐያን ባንክ ፎር ሪኮንስትረክሽን ኤንድ ዲቬሎፕመንት |
| **ኢሲኤ** | ኤክስፖርት ክሬዲት ኤጀንሲ |
| **ኤአይኤ** | ኤንቫዮርሜንታል ኢምፓክት አሴስመንት |
| **ኢአይኤስ** | ኤንቫዮርሜንታል ኢምፓክት ስቴትመንት |
| **ኢኤስአይኤ** | ኤንቫዮርሜንታል ኤንድ ሶሻል ኢምፓክት አሴስመንት |
| **ኢፒሲ** | ኤንጂኒየሪንግ፣ ፕሮኩርመንት እና ኮንስትረክሽን (ኮንትራት) |
| **ኢፒሲኤም** | ኤንጂኒየሪንግ፣ ፕሮኩርመንት፣ ኮንስትረክሽን፣ ማኔጅመንት |
| **ኢዩአርአይቢኦአር** | ኢውሮ ኢንተርባንክ ኦፈርድ ሬት |
| **ኤፍኤም** | ከአቅም በላይ የሆነ ኃይል |

| | |
|---|---|
| **ኤፍኤምኢ** | ከአቅም በላይ የሆነ ክስተት |
| **ኤፍኤምቪ** | ፌር ማርኬት ቫሊው |
| **ኤፍኤስኤ** | ፊውል ሰፕላይ አግሪመንት |
| **ጂጄ** | ጂጋጁል |
| **አይኤ** | የትግበራ ስምምነት |
| **አይሲኤ** | የአፍሪካ መሠረተ ልማት ኮንሶርቲየም |
| **አይሲሲ** | ዓለም አቀፍ ንግድ ምክር ቤት |
| **አይሲኤስአይዲ** | የኢንቨስትመንት ልዩነቶችን የሚፈታ ዓለም አቀፍ ማዕከል |
| **አይዲሲ** | በግንባታ ሂደት የሚታይ ዝንባሌ |
| **አይኢ** | ገለልተኛ መሐንዲስ |
| **አይኤፍሲ** | ዓለም አቀፍ ፋይናንስ ኮረፖሬሽን |
| **አይፒፒ** | ራሱን የቻለ የኃይል አመንጪ/ፕሮጀክት |
| **ኬደብልዩ** | ኪሎዋት |
| **ኬደብልዩኤች** | ኪሎዋት በሰዓት |
| **ኤልዲ** | **የጉዳት ካሳ** |
| **ኤልኤችቪ** | ዝቅተኛ የሙቀት መጠን |
| **ኤልአይቢኦአር** | ለንደን ኢንተርባንክ ኦፈርድ ሬት |
| **ኤልሲ** | ሌተር ኦፍ ክሬዲት |
| **ኤልሲአይኤ** | ለንደን ኮርት ኦፍ ኢንተርናሺናል አረቢትሬሽን |
| **ኤልቲኤስኤ** | የረጅም ጊዜ አገልግሎት ስምምነት |
| **ኤምኤኢ** | ማቴሪያል አድቨርስ ኢፌክት |
| **ኤምዲቢ** | መልቲላተራል የልማት ባንክ |
| **ኤምአይጂኤ** | መልቲላተራል ኢንቨስትመንት ጋራንቲ ኤጀንሲ |
| **ኤምኤምብሩ** | ሚሊየን ብሪቲሽ ተርማል ዩኒትስ |
| **ኤምደብሊዩ** | ሜጋዋት |

| | |
|---|---|
| **ኤምደብሊዩኤች** | ሜጋዋት በሰዓት |
| **ኦኤንድኤም** | እንቅስቃሴና ጥገና |
| **ኦፒክ** | ኦቨርሲስ የግል ኢንቨስትመንት ኮርፖሬሽን |
| **ፒሲኦኤ** | ፑት ኤንድ ኮል ኦፕሺን አግሪመንት |
| **ፒኦዲ** | ፖይንት ኦፍ ዴሊቨሪ |
| **ፒፒኤ** | የኃይል ግዢ ስምምነት |
| **ፒፒፒ** | ፐብሊክ ፕራይቬት ፓርትነርሺፕ |
| **ፒአርጂ** | ፓረሺያል ሪስክ ጋራንቲ |
| **ፒአርአይ** | ፖለቲካል ሪስክ ኢንሹራንስ |
| **ፒቪ** | ፎቶቮልታይክ |
| **ፒኪው** | ፕሪኳሊፊኬሽን |
| **አረኤፍፒ** | ሪክዌስት ፎር ፕሮፖሳዛል |
| **ኤስኦኢ** | ስቴት ኦውንድ ኤንቲቲ |
| **ኤስቪፒ** | ስፔሻል ፐርፐዝ ቬሂክል |
| **ቲ-ላይን** | ትራንስሚሽን ላይን |
| **ዩኤንሲትራል** | ዓለምአቀፍ ሕግን በተመለከተ የተባበሩት መንግሥታት ኮሚሽን |
| **ቪኤቲ** | ቫሊው አድድ ታክስ |
| **ደብሊውሲኤልሲ** | ዎርኪንግ ካፒታል ሌተርስ ኦፍ ክሬዲት |

# ሌሎች ምንጮች

ከዚህ በታች የሚገኙት ያልተሟሉ ተጨማሪ ድረ-ገጽ ምንጮች ናቸው፡፡

የአገር የጉዳት ስጋት ደረጃ መለየት

ስታንዳርድ ኤንድ ፑር ካንትሪ ሪስክ ሬቲንግስ፡- http://goo.gl/E8Ha4

### አካባቢና ማህበረሰባዊ ነክ ምንጮች

African Development Bank's Integrated Safeguard System: http://goo.gl/hWTO5p

Equator Principles: http://www.equator-principles.com

IFC Environmental and Social Performance Standards: http://goo.gl/pNaCOv

### ለልማት የሚውል የገንዘብ ምንጭ ተቋማት

Africa Finance Corporation: http://www.africafc.org

African Development Bank Group: http://www.afdb.org

Asian Development Bank: http://www.adb.org

DEG German Investment Company: http://www.deginvest.de

Development Bank of Southern Africa: http://www.dbsa.org

European Bank for Reconstruction and Development: http://www.ebrd.com

European Investment Bank: http://www.eib.org

FMO Netherlands Development Finance Company: http://www.fmo.nl

International Finance Corporation: http://www.ifc.org

Islamic Development Bank: http://www.isdb.org

Proparco Investment and Promotions Company for Economic

Cooperation: http://www.proparco.fr

Overseas Private Investment Corporation: http://www.opic.gov

World Bank Group: http://www.worldbank.org

### የድርድር ድጋፍ

African Legal Support Facility: http://goo.gl/hux9Va

Host Government Negotiation Support

Portal: http://www.negotiationsupport.org

### የኃይል ዘርፍ መመሪያዎች

Africa Power Guide: http://www.africapowerguide.com

Geothermal Handbook: Planning and Financing Power Generation by World Bank: http://goo.gl/Ftms70

IEA Wind Power Technology Roadmap: http://goo.gl/5uaStk

Important Features of Bankable Power Purchase Agreements by OPIC: http://goo.gl/fBRXys

Power Africa: http://www.usaid.gov/powerafrica

World Energy Outook 2014: http://www.worldenergyoutlook.org

Eberhard, A. and Gratwick, K. N, Demise of the Standard Model for Power Sector Reform and the Emergence of Hybrid Power Markets, Energy Policy Volume 36, Issue 10. 2008. http://goo.gl/7y4076

### ግዥ

EIB Procurement

Guidelines: http://www.eib.org/infocentre/publications/all/guide-toprocurement.htm

South Africa's Renewable Energy IPP Procurement Program: Success Factors and Lessons: http://goo.gl/1YnSGy

World Bank Procurement Guidelines: http://www.worldbank.org/procurement

### የፕሮጀክት ፋይናንስ

World Bank: Project Finance and Guarantee Notes: http://goo.gl/rdCkTH

World Bank: Partial Risk Guarantees: http://goo.gl/7z6ZQo

### የፕሮጀክት ዝግጅት

ICA Assessment of Project Preparation Facilities for Africa: http://goo.gl/MfLS92

### የመንግስትና የግሉ ዘርፍ አጋርነት

Infrastructure Consortium for Africa: http://www.icafrica.org

Unsolicited Proposals - An Exception to Public Initiation of Infrastructure PPPs: http://goo.gl/hXJgFZ

World Bank Public Private Partnership in Infrastructure Resource Center: http://www.worldbank.org/pppirc

-

# ምስጋና

ምንም እንኳን የሚከተሉት ሰዎች የዚህን የመመሪያ መጽሐፍ ረቂቅ በምናዘጋጅበት ወቅት መሣተፍ ባይችሉም የመመሪያ መጽሐፉ ረቂቅ ከመዘጋጀቱ እና ከመታተሙ በፊት በነበረው የምክክር ሂደት ወቅት ላበረከቱት ከፍተኛ አስተዋጽኦና  ዕውቀት ልናመሰግናችው እንወዳለን።

Andrew Alli, President & CEO, Africa Finance Corporation (AFC)

Yesufu Alonge, Head, Power Procurement & Power

Contracts, Nigerian Bulk Electricity Trading Plc (NBET)

Sam Amadi, Chairman/CEO, Nigerian Electricity

Regulatory Commission (NERC)

Justin Antonipillai, Deputy General Counsel, US Department of Commerce

John J. Beardsworth, Jr. , Partner, Hunton & Williams LLP

Joseph C. Brandt, President & CEO, ContourGlobal

Michael Boyd, Senior Energy Advisor, Economic Growth Office, US Agency for International Development (USAID), Tanzania

Rosanne Casey, Policy Coordinator - Power Africa, Africa Bureau, US Agency for International Development (USAID)

Brian Christaldi, Associate General Counsel, Project Finance, Overseas Private Investment Corporation (OPIC)

Carl Fleming, Associate, Akin Gump Strauss Hauer & Feld LLP

Cephas Galley, Division Manager, Contracts (Legal Counsel), Electric Company of Ghana, Ltd

John. L. Garrison, Energy Advisor, Africa Bureau, US Agency for International Development (USAID)

Andrew Gray, Senior Legal Consultant, Trinity LLP

Kenneth Hansen, Partner, Chadbourne & Parke LLP

Andrew M. Herscowitz, Coordinator for Power Africa and Trade Africa, US Agency for International Development (USAID)

Paul Hinks, CEO, Symbion Power LLC

William H Holmes, Partner, K&L Gates LLP

David Hunt, Principal Consultant, Legal and Project Finance, Nexant, Inc.

Robert F. Ichord, Jr., Deputy Assistant Secretary, Bureau of Energy Resources,US Department of State

James Kamau, Managing Partner, Iseme Kamau & Maema Advocates

Zahra Omar, Partner, Iseme Kamau & Maema Advocates

Astri Kimball, Senior Advisor to the President & CEO for Policy and Operations, Overseas Private Investment Corporation (OPIC)

Mohamed Loraoui, Intl. Program Specialist, Commercial Law Development Program (CLDP)

Rwabangi Luteganya, Investment Manager, Tanzania Electric Supply Company (TANESCO)

Stephen Mallowah, Partner, MMC Africa Advocates

Patrick Mbengwalu, Director and Head, Debt and Infrastructure Financing, FBN Capital

Alex McClain, US Agency for International Development (USAID)

Elise McDonald, Senior International Program Specialist, Commercial Law Development Program, US Department of Commerce

Decklan Mhaiki, Deputy Managing Director, Tanzania Electric Supply Company (TANESCO)

Robert Mosbacher, Jr., Chairman of the Board, Initiative for Global Development (IGD)

Amyn Mussa, Partner, Anjarwalla & Khanna Advocates

Professor Chinedu Nebo, Honourable Minister of Power, Federal Republic of Nigeria

Dr. Mima S. Nedelcovych., President & CEO, Initiative for Global Development (IGD)

Lisa O'Brien, Partner, Freshfields Bruckhaus Deringer LLP

Crispine Odhiambo, Partner, Kiptiness and Odhiambo Associates

Nicholas Okafor, Partner, Udo Udoma & Belo-Osagie

Imeh Okon, Power Africa, USAID Nigeria

Dozie Okpalaobieri, Special Advisor to the Coordinating Minister for the Economy and Honourable Minister of Finance

Kwame Parker, Executive & Head, Power and Infrastructure, East Africa, Stanbic Bank

Sharon Pauling, Director - Economic Growth and Environment, US Agency for International Development (USAID)

David Powers, Partner, Baker Botts LLP

Jeremy Schwer, Partner, Akin Gump LLP

Adeola Sunmola, Senior Associate, Udo Udoma & Belo-Osagie

Nils Tcheyan, Director, Government Affairs and Policy, Africa, General

Electric Company (GE)

Aniekan Ukpanah, Partner, Udo Udoma

Sheryl Weisflog, Attorney Advisor, Commercial Law Development Program, US Department of Commerce

Kelly R. Welsh, General Counsel, US Department of Commerce

Julie Wenah, Special Advisor to the General Counsel, US Department of Commerce

Rumundaka Wonodi, Managing Director & CEO, Nigerian Bulk Electricity Trading Plc (NBET)

ከልባዊ ምስጋና ጋር፤



Stephen Karangizi
Director
African Legal Support Facility



Nnamdi Ezera
Senior Counsel
U.S. Department of Commerce
Commercial Law Development Program